

ያልታተሙ የሰበር ውሳኔዎች በአንድ ተሰብስበው የተዘጋጁ

ቅፅ – 7

በዳንኤል ፍቃዱ (ጠበቃና የህግ አማካሪ)

የሰበር መ/ቁ/215321

ግንቦት 2 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ መ/ር ሙሴ አሳየኸኝ --ቀረቡ

ተጠሪ፡ የአ/አ ከተማ አስተዳደር ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ -አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ በአስተዳደር አካል የወጣ መመሪያ አግባብነት በፌደራል አስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2013 መሠረት እንዲከለስ የቀረበ አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበዉ አቤቱታ ተጠሪ ነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ያወጣው የትምህርት አመራሮች ድልድል መመሪያ ህግን ባልተከተለ መልኩ ስለወጣ መመሪያው ተፈፃሚ እንዳይሆን እና እንዲከለስ የሚል ነዉ፡፡የአቤቱታ ይዘትም አመልካች የአለም ብርሃን የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰ-መምህር በመሆን ታህሳስ 12 ቀን 2012 ዓ.ም በፌደራል ደረጃ በወጣው የመምህራን እና ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘር የስራ መደብ የድልድል አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 2/2012 መሰረት አድርጎ ጂ.ጂ.ኤ ጥናት አንቀጽ 9 መሰረት ያለውድድር ከነበረበት ርዕሰ መምህር ኬሪየር በደረጃ 18 ተመድቦ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ይሁን እንጂ ተጠሪ ነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ባወጣው የት/ቤት አመራሮች የድልድል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አፈፃፀም መመሪያ በተመደብኩበት ት/ቤት 1 ርዕሰ መምህር እና 3 ም/ር/መምህር መመደቡ እና የኬርየር ድረጃ ወደ አዲስ ስታንዳርድ የስራ መደብ መቀየሩን ያሳያል፡፡ቀደም ሲል በህዳር ወር የወጣው መመሪያ በታህሳስ በወጣው የፌዴራል የድልድል መመሪያ ተሽሯል፡፡የፌዴራል መመሪያ በሀገር አቀፍ ደረጃ በጂ.ኢ.ጂ ደረጃ የተመደቡ ር/መምህራን ከምደባቸው ላይ ለማንሳት የተደረገ ጥናት ይሁን የወጣ አዲስ መመሪያ በሌለበትና ባልተሻረበት ሁኔታ አመልካች የያዙትን ቦታ/መደብ በተመሳሳይ መደብ መመደብ ሲገባው ቦታውን በነሀሴ ወር 2012 ዓ.ም ባወጣው መመሪያ መሰረት ክፊት ማድረጉ መመሪያን የጣሰ ነው፡፡በዚህ ነሀሴ ወር 2012 ዓ.ም በወጣው መመሪያ መሰረት በክ/ከተማ እና በወረዳው የሚገኙ ር/መምህራን መደቦች ለውድድር እንዲቀርቡ ተደርጎ አመልካች የያዘው ቦታ ለውድድር ክፍት ሆኗል፡፡በመሆኑም ይህ ነሀሴ 2012 የወጣዉ መመሪያ በፌዴራል አስተዳደር አዋጅ ቁ.1183/2011 መሰረት በተጠሪ ድህረ-ገጽ ላይ ያልተጫነ እና ያልተመዘገበ በመሆኑ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ተፈፃሚነት በሌለው መመሪያ መሰረት አመልካች ከተመደብኩበት መደብ እንዲነሳ ሊደረግ አይገባም፡፡ስለዚህ አመልካች የያዝኩት ቦታ ለውድድር ክፍት መደረጉ ተቀባይነት የለውም እንዲባልልኝ፤ተጠሪ ነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ያወጣው መመሪያ ስነ-ስርዓት ህግን ሳይከተል የወጣ ነው ተብሎ እንዲወሰን፤የተደረገው ውድድር እንዳልተደረገ ተቆጥረው ቀደም ሲል የያዝኩት ደረጃ 18 ላይ እንዲመለስ ተገቢው ካሳም እንዲከፈል እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ ያቀረበው መልስ ነሀሴ 2012 ዓ.ም የወጣው መመሪያ ሀምሌ 28/2012 ዓ.ም ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ተልኮ ዐቃቤ ህግም ህዳር 11/2013 ዓ.ም መመሪያ ቁጥር 20/2012 ሆኖ መመዝገቡን አሳውቋል፤በመሆኑም መመሪያ ህግን ተከትሎ የወጣ ስለሆነ አመልካች በቀጥታ ክስ ማቅረብ የሚችሉት ለከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች እንጂ ለዚህ ፍ/ቤት ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፡፡ተጠሪ በአዋጅ ቁ.64/2010 መሰረት መመሪያ የማውጣት ስልጣን አለው፣ መመሪያው ለሁሉም መምህራን እኩል የመወዳደር መብት ያላቸው መሆኑን ይደነግጋል፣ስለሆነም አመልካች ቀድሞ የያዝኩት ቦታ ይሰጠኝ ያሉት ተገቢ አይደለም፣ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ተገቢ ባለመሆኑ ውድቅ እንዲደረግ በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር ከቀረበው ማስረጃ ጋር መርምሮ ተጠሪ መመሪያ የማውጣት ስልጣን አለው፤ ይሁን እንጂ ይህ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 ዓ.ም ከአንቀጽ 6-11 መሰረት መመሪያው ከመውጣቱ በፊት ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም ድህረ-ገጽ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ስለማውጣቱ አልተረጋገጠም፤ረቂቅ መመሪያው ላይም ከሚመለከተው አካል ጋር ውይይት አልተደረገም፣ግብዓት ስለመሰበሰቡ በኋላም ከነማብራሪያው ለፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ስለመላኩ፣ዐቃቤ ህግም ወዲያውኑ መመሪያውን ስለመመዝገቡ ማሳወቅ እንዳለበት አዋጅ 1183/2012 አንቀጽ 16 ያሳያል፣ይሁን እንጂ ተጠሪ ያወጣው መመሪያ በዚሁ መሰረት ስለመወጣቱ አልተረጋገጠም፤ስለዚህ ነሀሴ ወር 2012 ዓ.ም የወጣው መመሪያ እንዲሰረዝ፣ መመሪያው በህጉ መሰረት ተከልሶ እንዲወጣ፣በመመሪያው መሰረት የተደረገው የድልድልም ሆነ ውድድር እንዲሰረዝ፣ተጠሪ ለአመልካች ብር 4000 ኪሳራ እንዲከፍል ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት መዝገቡን መርምሮ አንድ መመሪያ ህጋዊ ስርዓትን ተከትሎ ከወጣ በኋላ መመሪያው ህጋዊ ስርዓትን ሳይከተል ወጥቷል በሚል ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ በህጉ መሰረት ቀርቦ መመሪያው ተፈፃሚ እንዳይሆን ሲደረግ ቀደም ሲል በመመሪያው መሰረት ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች እንደፀኑ የሚቆዩ እንጂ መመሪያው ከመሻሩ በፊት ያለ የአስተዳደር ውሳኔዎች ሊሰረዙ እንደማይገባ የአዋጅ ቁ/ 1183/2013 አንቀጽ 57/4/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መመሪያው ህግን ተከትሎ መውጣት አለመውጣቱን አረጋግጦ ውሳኔ ከመስጠት ባለፈ መመሪያውን መሰረት አድርጎ የተሰጡ ውሳኔዎችም ላይ ገብቶ የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ ሊሽሩ የሚችለብት አግባብ የለም፤ስለዚህ የስር ፍ/ቤት መመሪያውን ተፈፃሚ እንዳይሆን ውሳኔ ከሰጠበት ቀን በፊት በተጠሪ የተፈፀሙ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እንዲሰረዙ የሰጠው ውሳኔ የአዋጁን አንቀጽ 57(4)ን ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በከፊል በመሻር መመሪያው ተከልሶ እንደገና እንዲወጣ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡የአቤቱታ ይዘት ባጭሩ፡- አመልካች ለከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበው የአስተዳደር ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ፍ/ቤቱም የፍሬ ነገርና የህግ ጉዳይ መርምሮ የአስተዳደር ውሳኔ ህጋዊ አይደለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፤የአስተዳደር መመሪያ ወይም ውሳኔ እንዲከለስ አቤቱታ የሚቀርበው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል በማለት ይደነግጋል፣በአንቀጽ 49(2) መሰረት የአስተዳደር መመሪያን በተመለከተ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል፣ ስለዚህ ጠቅላይ ፍ/ቤት የመመሪያን ይግባኝ እንጂ የአስተዳደር ውሳኔን ይግባኝ ተቀብሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም፣ ይህንን አልፈው የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ በስር ፍ/ቤት መመሪያው ከመሻሩ በፊት

የተፈፀመውን አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እንዲሻር መወሰኑ ስህተት ነው እንዲያርምልን በማለት በስር ፍ/ቤት ያልቀረበውና ክርክር ያልቀረበበት አዲስ ነገር ተቀብሎ የስር ፍ/ቤት መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል፡፡በነህሴ ወር 2012 ዓ.ም በረቂቅ መመሪያ እንደ ህግና የፀደቀ መመሪያ ቆጥሮ የወሰዳቸው አስተዳደራዊ ተግባራትን ማፅደቅ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡የአስተዳደር ውሳኔዎች ይፀድቃሉ የሚባለው በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መመሪያ ሆኖ ከተመዘገበ በኋላ እንጂ መመሪያው ወደ ኋላ መልሰው መመሪያው ሳይወጣ የተፈፀሙ ተግባራትን ሁሉ እንዲጸኑ ማድረጉ ከአዋጁ መንፈስ እና አላማ ውጪ በመሆኑ ውሳኔው እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ የመጨረሻ ነው ሲል ያቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉን አግባብ ከአዋጅ ቁ.1183/2012 አንቀጽ 49 አንፃር ለማጣራት መዝገቡ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡ለተጠሪ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሶት መልስ ያላቀረበ በመሆኑ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበት ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘበነዉ አመልካቾች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ መመሪያዉ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 ላይ በተመለከተዉ አግባብ ሥነ ሥርዓቱን ጠብቆ ያልወጣ እንዲሁም ከሌሎች አዋጆች እና በፌዴራል ደረጃ የወጣዉን መመሪያ የሚቃረን ሌላ መመሪያ ስራ ላይ በማዋል ቀደም ሲል በነበረዉ መመሪያ መሰረት ያለዉድድር ተመድበንበት የነበረዉን ቦታ አስለቅቆን ሌሎች ሠራተኞችን የመደበ መሆኑን ሲሆን፣የጠየቁት ዳኝነትም ሥርዓቱን ሳይጠብቅ ተግባራዊ የተደረገዉ መመሪያ እንዲከለስ እና መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የተደረገዉ ምደባም እንዲሰረዝ የሚል ነዉ፡፡

የፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት እና ተጠሪነታቸዉ ለፌዴራል መንግስት የሆነዉ አስፈፃሚ አካላት የሚያወጧቸዉ መመሪያዎች መከተል ያለባቸዉን መርሆዎች እና ሥርዓቶች፣ አንድ መመሪያ ተግቢዉን ሥርዓት ተከትሎ አልወጣም የሚል ማንኛዉም ጉዳዩ የሚመለከተዉ ሰዉ መመሪያዉ እንዲከለስ ዳኝነት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል እና የዳኝነት ጥያቄዉ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሚሰጠዉ ዉሳኔ ወሰኑ

እስከምን ድረስ አንደሆነ ይደነግጋል፡፡አዋጁ እነዚህንና መሰል ድንጋጌዎችን እንዲያካትት የተደረገበት ምክንያትም የሚመለከተዉ የአስፈፃሚ አካል የሚያወጣዉ መመሪያ ግልጽ የሆኑ ሥነ ሥርዓቶችን ተከትሎ እንዲወጣ እና ይህን ሥርዓት ተከትሎ ያልወጣ ከሆነ ከነግድፈቱ ተፈፃሚ ሆኖ እንዳይቀጥል በማድረግ መንግስታዊ አሠራር ለህዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲከናወን እና በመመሪያዎች አወጣጥ መርሆዎች እና ሥነ ስርዓት ላይ ቅሬታ ያለዉ ሰዉ የመመሪያዎቹን ህጋዊነት በፍርድ ቤት የሚያስመረምርበት ሥርዓትን በመደንገግ አስተዳደራዊ ፍትሕ ማስፈን ነዉ የሚለዉን የአዋጁን አንዱ ዓላማ ገቢራዊ ለማድረግ እንዲቻል ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡አመልካች መመሪያዉ እንዲከለስ ዳኝነት የጠየቁትም በዚሁ መነሻነት ሲሆን፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ ጉዳዩ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ሥርዓቱን ሳይጠብቅ የወጣ ነዉ የሚሉት መመሪያ እንዲከለስ የወሰነ ሲሆን መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የተደረገ ምደባ በሚመለከት ይግባኝ ሰሚዉ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊሰረዝ አይገባም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

በበኩላችንም እንደተመለከትነዉ ስለ ክለሳ ዉሳኔ አሰጣጥ እና አፈፃፀም የሚደነግገዉ የአዋጁ ክፍል አራት ንዑስ ክፍል አራት የዉሳኔ አሰጣጥ በሚለዉ አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ላይ የክለሳ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል ያወጣዉን መመሪያ ሊያጸና ወይም በሙሉ ወይም በከፊል መሻር እንደሚችል እና መመሪያዉን በሙሉ ወይም በከፊል የሻረ እንደሆነ የሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል መመሪያዉን እንደገና እንዲያወጣ ወይም እንዲያሻሽል ማዘዝ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ስለ ክለሳ ዉሳኔ አፈፃፀም በሚያወራዉ አንቀጽ 57 ንዑስ አንቀጽ 3 ስር የክለሳ አቤቱታ የቀረበበት መመሪያ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሻር ከተደረገ በዚያዉ ልክ መመሪያዉ ህጋዊ ኃይል እንደማይኖረዉ በመርህ ደረጃ የሚደነግግ ሲሆን፣የመመሪያዉ በከፊል ወይም በሙሉ መሻር የአስተዳደር ተቋሙ መመሪያዉ ከመሻሩ በፊት በተሻረዉ መመሪያ መሰረት የሰጣቸዉ አስተዳደራዊ ዉሳኔዎቹ እንደጸኑ እንደሚቀሩ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ በአዋጁ ላይ የተመለከተዉን የመመሪያ አወጣጥ ሥርዓትን ተከትሎ አልወጣም በሚል መብት ባለዉ ሰዉ የቀረበለትን የክለሳ አቤቱታ በመቀበል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መመሪያዉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሻር በሚል የሚሰጠዉ ዉሳኔ ዉጤቱ ዉሳኔዉ ከተሰጠ በኋላ የተሻረዉን መመሪያ መሠረት በማድረግ የአስተዳደር አካሉ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ዋጋ እንዳይኖረዉ የሚያደርግ ሲሆን፣መመሪያዉ ከመሻሩ በፊት በሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል በተሻረዉ መመሪያ መሰረት የተሰጠዉን አስተዳደራዊ ዉሳኔ

ዋጋ እንዲያጣ ወይም ተፈፃሚነት እንዳይኖረዉ የማድረግ ዉጤት የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ማንኛዉም ሰዉ ተገቢዉን ሥርዓት ተከትሎ አልወጣም የሚለዉ መመሪያ በፍርድ ቤት እንዲከለስ ዳኝነት ለመጠየቅ መብት ያለዉ ቢሆንም (የአዋጁ አንቀጽ 46/1/ ይመለከቷል)፣ ይህ መብቱ አቤቱታ በቀረበበት መመሪያ መሠረት በአስተዳደር አካሉ የተሰጠ ዉሳኔ እንዲሻር ጭምር መጠየቅን የማያካትት መሆኑን ነዉ፡፡ይልቁንም የአስተዳደር አካሉ መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ይነካል የሚል ሰዉ መብቱን የሚያስከብረዉ እንደየጉዳዩ ዓይነት ለጉዳዩ አግባብነት ባለዉ ህግ መሠረት የተዘረጋዉን የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት መሠረት በማድረግ ቅሬታዉን ስልጣን ላለዉ አካል በማቅረብ ሊሆን ይገባል፡፡ አዋጁ የመመሪያዉ መሻር ቀደም ሲል በመመሪያዉ መሰረት የተሰጠዉን አስተዳደራዊ ዉሳኔ የመሻር ዉጤት እንደሌለዉ ከላይ በተመለከተዉ አንቀጽ 57(4) ላይ የደነገገበት አንዱ ምክንያት ሊሆን የሚችለዉም እንደየጉዳዩ ባህርይ አንድ የአስተዳደር አካል በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ የሚቀርብበት አካል እና የአቀራረብ ሥርዓቱን በተመለከተ በሌሎች ህጎች ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲከበሩ እና የአንድ አስተዳደር አካል ዉሳኔ ህጋዊነት በሁለት የተለያዩ አካላት ሊታዩ የሚችልበትን ሁኔታ እንዳይኖር ለማድረግም ጭምር እንደሆነ ይታመናል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በዚህ ችሎት ባቀረቡት ቅሬታ አጥብቀዉ የሚከራከሩት መመሪያዉ ከተሻረ መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የተደረገ ምደባም መብቴን የሚጎዳ በመሆኑ ተሰርዞ ቀደም ሲል ያለዉድድር ተመድቤበት ወደ ነበረዉ ቦታ ልመለስ ይገባል በማለት ነዉ፡፡ በመሠረቱ ከስራ ምደባና ደረጃ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያለዉ የመንግስት ሠራተኛ ቅሬታዉን የሚያቀርብበትን ሥርዓት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 56/2010 ይደነግጋል፡፡ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓቱ በልዩ ሁኔታ እንዲደነግግ የተፈለገበት ምክንያትም ለቅሬታዎች አፋጣኝ መፍትሔ ለመስጠት፣ ለቅሬታዎች መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ስህተቶችንና ድክመቶችን የማረም እና ሁሉንም የመንግስት ሠራተኞች በእኩልነት ለማስተናገድ የሚያስችል እና ፍትሐዊ የሆነ አሠራር በማስፈን የሰመረ የስራ ግንኙነት እንዲኖር በማሰብ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 75 ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በዚህም መሠረት ከስራ ምደባ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያለዉ ሠራተኛ ቅሬታዉን በቅድሚያ ለመስሪያ ቤቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታዉን ማቅረብ እንዳለበት፣ቅሬታ ሰሚዉ ኮሚቴ በሰጠዉ ፍርድ ቤት ላይ ቅሬታ ካለዉ ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል እና የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ የህግ ስህተት አለዉ የሚል ከሆነም ቅሬታዉን

ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በማቅረብ መብቱን ማስከበር የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 77(4)፣ 77፣ 81(1/ሠ) እና 81(5) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌች መገነዝብ ይቻላል፡፡ ቅሬታዉ በዚህ መልኩ የሚቀርብለት ፍርድ ቤት ህግን የመተርጎም ስልጣን ያለዉ በመሆኑ የምደባዉን አግባብነት ሲመረምር ቅሬታ የቀረበበት ምደባ ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉን ህግ መሠረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑን ብቻ ሳይሆን ለምደባዉ መሠረት የሆነዉ መመሪያ ስልጣን ባለዉ አካል ተገቢዉን ሥርዓት ጠብቆ የወጣ እና ከሌሎች የበላይ ህጎች (superior laws) ጋር የሚጋጭ መሆን ያለመሆኑን እና ተያያዥ ጉዳዮችን በመመርመር እና ትርጉም በመስጠት የመመሪያዉን ህጋዊ ዉጤት ቍምር በማየት የምደባዉን ህጋዊነት መወሰን ይችላሉ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይም አመልካች ምደባዉ መብታችን ይነካል የሚሉ ከሆነ ከፍ ሲል በተመለከተዉ አግባብ ለሲቪል ሰርቪስ ፍርድ ቤት ብሎም ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡ ኖሮ ፍርድ ቤቶቹ የምደባዉን ህጋዊነት ሲመረምሩ ለምደባዉ መሰረት የሆነዉ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 6 እና ተከታዮቹ ላይ የተመለከቱትን የመመሪያ አወጣጥ ሥርዓቶችን ተከትሎ የወጣ መሆን ያለመሆኑን ቍምር መርምረዉ የመመሪያዉን ህጋዊ ዉጤት ወስነዉ ይህን መሰረት በማድረግም በምደባዉ ህጋዊነት ላይ ተገቢዉን መወሰን ይችሉ ነበር፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ከምደባ ጋር በተያያዘ በህግ የተዘረጋዉን ሥርዓት ተከትሎ ቅሬታቸዉን አቅርበዉ መብታቸዉን ማስከበር እየቻሉ፣ በመመሪያ ክለሳ ዳኝነት ሰበብ አስቀድሞ በመመሪያ መሠረት በተጠሪ የተሰጠዉ ምደባ እንዲሰረዝ የሚያቀርቡት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለዉ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መመሪያ በአዋጁ የተመለከተዉን ሥርዓት የተከተለ አለመሆኑን አረጋግጦ መመሪያዉ እንዲሻር በማለት፣ በሌላ በኩል መመሪያዉን መሰረት በማድረግ በተጠሪ የተደረገዉ ምደባ ሊሰረዝ አይገባም በማለት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በአዋጁ አንቀጽ 57(4) ላይ የተመለከተዉን ግልጽ ድንጋጌ ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማሻሻል በመ/ቁጥር 208855 ላይ ሐምሌ 27 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

አ/መ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

የሰ/መ/ቁጥር 215268

ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡ አቶ ኤልያስ ግደይ፡- ቀረቡ

ተጠሪ ፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ በአስተዳደር አካል የወጣ መመሪያ አግባብነት በፌደራል አስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2013 መሠረት እንዲከለስ የቀረበ አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበዉ አቤቱታ ተጠሪ ነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ያወጣው የትምህርት አመራሮች ድልድል መመሪያ ህግን ባልተከተለ መልኩ ስለወጣ መመሪያው ተፈፃሚ እንዳይሆን እና እንዲከለስ የሚል ነዉ፡፡የአቤቱታ ይዘትም አመልካች በወ/ሮ

ቀለመወርቅ መሰናዶ ትምህር ቤት ርዕሰ-መምህር በመሆን ታህሳስ 12 ቀን 2012 ዓ.ም በፌደራል ደረጃ በወጣው የመምህራን እና ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘር የስራ መደብ የድልድል አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 2/2012 መሰረት አድርጎ ጄ.ጂ.ኤ ጥናት አንቀጽ 9 መሰረት ያለውድድር ከነበረበት ርዕሰ መምህር ኬሪየር በደረጃ 18 ተመድቦ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ይሁን እንጂ ተጠሪ ነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ባወጣው የትምህር ቤት አመራሮች የድልድል አፈፃፀም መመሪያ በተመደብኩበት ትምህርት ቤት 1 ርዕሰ መምህር እና 3 ምክትል ርዕሰ መምህራን መመደቡ እና የኬርየር ደረጃ ወደ አዲስ ስታንዳርድ የስራ መደብ መቀየሩን ያሳያል፡፡ቀደም ሲል በህዳር ወር የወጣው መመሪያ በታህሳስ በወጣው የፌዴራል የድልድል መመሪያ ተሽሯል፡፡የፌዴራል መመሪያ በሀገር አቀፍ ደረጃ በጄ.ኢ.ጂ ደረጃ የተመደቡ ርዕሰ መምህራን ከምደባቸው ላይ ለማንሳት የተደረገ ጥናት ይሁን የወጣ አዲስ መመሪያ በሌለበትና ባልተሻረበት ሁኔታ አመልካች የያዙትን ቦታ/መደብ በተመሳሳይ መደብ መመደብ ሲገባው ቦታውን በነሀሴ ወር 2012 ዓ.ም ባወጣው መመሪያ መሰረት ክፍት ማድረጉ መመሪያን የጣሰ ነው፡፡በዚህ ነሀሴ ወር 2012 ዓ.ም በወጣው መመሪያ መሰረት በክፍለ ከተማ እና በወረዳው የሚገኙ ርዕሰ መምህራን መደቦች ለውድድር እንዲቀርቡ ተደርጎ አመልካች የያዘው ቦታ ለውድድር ክፍት ሆኗል፡፡ በመሆኑም ይህ ነሀሴ 2012 ዓ.ም የወጣዉ መመሪያ በፌዴራል አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1183/2011 መሰረት በተጠሪ ድህረ-ገጽ ላይ ያልተጫነ እና ያልተመዘገበ በመሆኑ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ተፈፃሚነት በሌለው መመሪያ አመልካች ከተመደብኩበት መደብ እንድነሳ ሊደረግ አይገባም፡፡ስለዚህ አመልካች የያዝኩት ቦታ ለውድድር ክፍት መደረጉ ተቀባይነት የለውም እንዲባልልኝ፣ ተጠሪ ነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ያወጣው መመሪያ ስነ-ስርዓት ህግን ሳይከተል የወጣ ነው ተብሎ እንዲወሰኝ፣ የተደረገው ውድድር እንዳልተደረገ ተቆጥሮ ቀደም ሲል የያዝኩት ደረጃ 18 ላይ እንዲመለስ ተገቢው ካሳም እንዲከፈል እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ ያቀረበው መልስ ነሀሴ 2012 ዓ.ም የወጣው መመሪያ ሀምሌ 28/2012 ዓ.ም ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ተልኮ ዐቃቤ ህግም ህዳር 11/2013 ዓ.ም መመሪያ ቁጥር 20/2012 ሆኖ መመዝገቡን አሳውቋል፡፡ በመሆኑም መመሪያ ህግን ተከትሎ የወጣ ስለሆነ አመልካች በቀጥታ ክስ ማቅረብ የሚችሉት ለከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች እንጂ ለዚህ ፍርድ ቤት ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፡፡ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 64/2010 መሰረት መመሪያ የማውጣት ስልጣን አለው፡፡ መመሪያው ለሁሉም መምህራን እኩል የመወዳደር መብት ያላቸው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም አመልካች ቀድሞ የያዝኩት ቦታ ይሰጠኝ ያሉት ተገቢ አይደለም፣ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ተገቢ ባለመሆኑ ውድቅ እንዲደረግ በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር ከቀረበው ማስረጃ ጋር መርምሮ ተጠሪ መመሪያ የማውጣት ስልጣን አለው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 ዓ.ም ከአንቀጽ 6-11 መሰረት መመሪያው ከመውጣቱ በፊት ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም ድህረ-ገጽ ስለመውጣቱ አልተረጋገጠም፡፡ ረቂቅ መመሪያው ላይም ከሚመለከተው አካል ጋር ውይይት አልተደረገም፡፡ ግብዓት

ስለመሰበሰቡ በኋላም ከነማብራሪያው ለፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ስለመላኩ፤ ዐቃቤ ህግም ወዲያውኑ መመሪያውን ስለመመዝገቡ ማሳወቅ እንዳለበት አዋጅ 1183/2012 አንቀጽ 16 ያሳያል፡፡ይሁን እንጂ ተጠሪ ያወጣው መመሪያ በዚሁ መሰረት ስለመወጣቱ አልተረጋገጠም፡፡ ስለዚህ ነሀሴ ወር 2012 ዓ.ም የወጣው መመሪያ እንዲሰረዝ፤ መመሪያው በህጉ መሰረት ተከልሶ እንዲወጣ፤ በመመሪያው መሰረት የተደረገው ድልድልም ሆነ ውድድር እንዲሰረዝ እና ተጠሪ ለአመልካች ብር 4000 ኪሳራ ይክፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት መዝገቡን መርምሮ አንድ መመሪያ ህጋዊ ስርዓትን ተከትሎ ከወጣ በኋላ መመሪያው ህጋዊ ስርዓትን ሳይከተል ወጥቷል በሚል ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ አቤቱታ በህጉ መሰረት ቀርቦ መመሪያው ተፈፃሚ እንዳይሆን ሲደረግ ቀደም ሲል በመመሪያው መሰረት ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች እንደፀኑ የሚቆዩ እንጂ መመሪያው ከመሻሩ በፊት ያሉ የአስተዳደር ውሳኔዎች ሊሰረዙ እንደማይገባ የአዋጅ ቁጥር 1183/2013 አንቀጽ 57/4/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መመሪያው ህግን ተከትሎ መውጣት አለመውጣቱን አረጋግጦ ውሳኔ ከመስጠት ባለፈ መመሪያውን መሰረት አድርጎ የተሰጡ ውሳኔዎችም ላይ ገብቶ የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ ሊሽር የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ስለዚህ የስር ፍርድ ቤት መመሪያውን ተፈፃሚ እንዳይሆን ውሳኔ ከሰጠበት ቀን በፊት በተጠሪ የተፈፀሙ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እንዲሰረዙ የሰጠው ውሳኔ የአዋጁን አንቀጽ 57(4)ን ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በከፊል በመሻር መመሪያው ተከልሶ እንደገና እንዲወጣ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ውሳኔ ላይ ነዉ፡፡ የአቤቱታ ይዘት ባጭሩ፡- አመልካች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበው በአስተዳደር ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ፍርድ ቤቱም የፍሬ ነገርና የህግ ጉዳይ መርምሮ የአስተዳደሩ ውሳኔ ህጋዊ አይደለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአስተዳደር መመሪያ ወይም ውሳኔ እንዲከለስ አቤቱታ የሚቀርበው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል በማለት ይደነግጋል፡፡ በአንቀጽ 49(2) መሰረት የአስተዳደር መመሪያን በተመለከተ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል፣ ስለዚህ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመመሪያን ይግባኝ እንጂ የአስተዳደር ውሳኔን ይግባኝ ተቀብሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም፡፡ ይህንን አልፎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ በስር ፍርድ ቤት መመሪያው ከመሻሩ በፊት የተፈፀመውን አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እንዲሻር መወሰኑ ስህተት ነው እንዲያርምልን በማለት በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ እና ክርክር ያልቀረበበት አዲስ ነገር ተቀብሎ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በነሀሴ ወር 2012 ዓ.ም የወጣ ረቂቅ መመሪያ እንደ ህግና የፀደቀ መመሪያ ተቆጥሮ የወሰዳቸው አስተዳደራዊ ተግባራትን ማፅደቅ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ የአስተዳደር ውሳኔዎች ይፀድቃሉ የሚባለው በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መመሪያ ሆኖ ከተመዘገበ በኋላ እንጂ መመሪያው

ወደ ኋላ ተመልሶ መመሪያው ሳይወጣ የተፈፀሙ ተግባራትን ሁሉ እንዲጸኑ ማድረጉ ከአዋጁ መንፈስ እና አላማ ውጪ በመሆኑ ውሳኔው እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የመጨረሻ ነው ሲል ያቀረበው ክርክር ውድቅ የመደረጉን አግባብ ከአዋጅ ቁ.1183/2012 አንቀጽ 49 አንፃር ለማጣራት መዝገቡ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡ለተጠሪ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሶት መልስ ያላቀረበ በመሆኑ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበትን ሞጉጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ አመልካቾች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ መመሪያዉ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 ላይ በተመለከተዉ አግባብ ሥነ-ሥርዓቱን ጠብቆ ያልወጣ እንዲሁም ከሌሎች አዋጆች እና በፌዴራል ደረጃ የወጣዉን መመሪያ የሚቃረን ሌላ መመሪያ ስራ ላይ በማዋል ቀደም ሲል በነበረዉ መመሪያ መሰረት ያለዉድድር ተመድበንበት የነበረዉን ቦታ አስለቅቆን ሌሎች ሠራተኞችን የመደበ በመሆኑ ሥርዓቱን ሳይጠብቅ ተግባራዊ የተደረገዉ መመሪያ እንዲከለስ እና መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የተደረገዉ ምደባም እንዲሰረዝ የሚል ነዉ፡፡

የፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት እና ተጠሪነታቸዉ ለፌዴራል መንግስት የሆነዉ አስፈፃሚ አካላት የሚያወጧቸዉ መመሪያዎች መከተል ያለባቸዉን መርሆዎች እና ሥርዓቶች፣ አንድ መመሪያ ተግቢዉን ሥርዓት ተከትሎ አልወጣም የሚል ማንኛዉም ጉዳዩ የሚመለከተዉ ሰዉ መመሪያዉ እንዲከለስ ዳኝነት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል እና የዳኝነት ጥያቄዉ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሚሰጠዉ ዉሳኔ ወሰኑ እስከምን ድረስ አንደሆነ ይደነግጋል፡፡አዋጁ እነዚህንና መሰል ድንጋጌዎችን እንዲያካትት የተደረገበት ምክንያትም የሚመለከተዉ የአስፈፃሚ አካል የሚያወጣዉ መመሪያ ግልጽ የሆኑ ሥነ-ሥርዓቶችን ተከትሎ እንዲወጣ እና ይህን ሥርዓት ተከትሎ ያልወጣ ከሆነ ከነግድፈቱ ተፈፃሚ ሆኖ እንዳይቀጥል በማድረግ መንግስታዊ አሠራር ለህዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲከናወን እና በመመሪያዎች አወጣጥ መርሆዎች እና ሥነ-ስርዓት ላይ ቅሬታ ያለዉ ሰዉ የመመሪያዎቹን ህጋዊነት በፍርድ ቤት የሚያስመረምርበት ሥርዓትን በመደንገግ አስተዳደራዊ ፍትሕ ማስፈን ነዉ የሚለዉን የአዋጁን አንዱ ዓላማ ገቢራዊ ለማድረግ እንዲቻል ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች መመሪያዉ እንዲከለስ ዳኝነት የጠየቁትም በዚሁ መነሻነት ሲሆን ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ ጉዳዩ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ሥርዓቱን ሳይጠብቅ የወጣ ነዉ የሚሉት መመሪያ እንዲከለስ የወሰነ ሲሆን መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የተደረገ ምደባ

በሚመለከት ይግባኝ ሰሚዉ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊሰረዝ አይገባም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

በበኩላችንም እንደተመለከትነዉ ስለ ክለሳ ዉሳኔ አሰጣጥ እና አፈፃፀም የሚደነግገዉ የአዋጁ ክፍል አራት ንዑስ ክፍል አራት የዉሳኔ አሰጣጥ በሚለዉ አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ላይ የክለሳ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል ያወጣዉን መመሪያ ሊያጸና ወይም በሙሉ ወይም በከፊል መሻር እንደሚችል እና መመሪያዉን በሙሉ ወይም በከፊል የሻረ እንደሆነ የሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል መመሪያዉን እንደገና እንዲያወጣ ወይም እንዲያሻሽል ማዘዝ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ስለ ክለሳ ዉሳኔ አፈፃፀም በሚያወራዉ አንቀጽ 57 ንዑስ አንቀጽ 3 ስር የክለሳ አቤቱታ የቀረበበት መመሪያ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሻር ከተደረገ በዚያዉ ልክ መመሪያዉ ህጋዊ ኃይል እንደማይኖረዉ በመርህ ደረጃ ተደንግጓል፡፡ የመመሪያዉ በከፊል ወይም በሙሉ መሻር የአስተዳደር ተቋሙ መመሪያዉ ከመሻሩ በፊት በተሻረዉ መመሪያ መሰረት የሰጣቸዉ አስተዳደራዊ ዉሳኔዎቹ እንደጸኑ እንደሚቀሩ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ በአዋጁ ላይ የተመለከተዉን የመመሪያ አወጣጥ ሥርዓትን ተከትሎ አልወጣም በሚል መብት ባለዉ ሰዉ የቀረበለትን የክለሳ አቤቱታ በመቀበል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መመሪያዉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሻር በሚል የሚሰጠዉ ዉሳኔ ዉጤቱ ዉሳኔዉ ከተሰጠ በኋላ የተሻረዉን መመሪያ መሠረት በማድረግ የአስተዳደር አካሉ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ዋጋ እንዳይኖረዉ የሚያደርግ ሲሆን፣መመሪያዉ ከመሻሩ በፊት በሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል በተሻረዉ መመሪያ መሰረት የተሰጠዉን አስተዳደራዊ ዉሳኔ ዋጋ እንዲያጣ ወይም ተፈፃሚነት እንዳይኖረዉ የማድረግ ዉጤት የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ማንኛዉም ሰዉ ተገቢዉን ሥርዓት ተከትሎ አልወጣም የሚለዉ መመሪያ በፍርድ ቤት እንዲከለስ ዳኝነት ለመጠየቅ መብት ያለዉ ቢሆንም (የአዋጁ አንቀጽ 46/1/ ይመለከቷል)፣ ይህ መብቱ አቤቱታ በቀረበበት መመሪያ መሠረት በአስተዳደር አካሉ የተሰጠ ዉሳኔ እንዲሻር ጭምር መጠየቅን የማያካትት መሆኑን ነዉ፡፡ ይልቁንም የአስተዳደር አካሉ መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ መብቱን ይነካል የሚል ሰዉ መብቱን የሚያስከብረዉ እንደየጉዳዩ ዓይነት ለጉዳዩ አግባብነት ባለዉ ህግ መሠረት የተዘረጋዉን የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት መሠረት በማድረግ ቅሬታዉን ስልጣን ላለዉ አካል በማቅረብ ሊሆን ይገባል፡፡ አዋጁ የመመሪያዉ መሻር ቀደም ሲል በመመሪያዉ መሰረት የተሰጠዉን አስተዳደራዊ ዉሳኔ የመሻር ዉጤት እንደሌለዉ ከላይ በተመለከተዉ አንቀጽ 57(4) ላይ የደነገገበት አንዱ ምክንያት ሊሆን የሚችለዉም እንደየጉዳዩ ባህርይ አንድ የአስተዳደር አካል በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ የሚቀርብበት አካል እና የአቀራረብ ሥርዓቱን በተመለከተ በሌሎች ህጎች ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲከበሩ እና የአንድ አስተዳደር አካል ዉሳኔ ህጋዊነት በሁለት የተለያዩ አካላት ሊታዩ የሚችልበትን ሁኔታ እንዳይኖር ለማድረግም ጭምር እንደሆነ ይታመናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በዚህ ችሎት ባቀረቡት ቅሬታ አጥብቀዉ የሚከራከሩት መመሪያዉ ከተሻረ መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የተደረገ ምደባም መብቴን የሚጎዳ በመሆኑ ተሰርዞ ቀደም ሲል ያለዉድድር ተመድቤበት ወደ ነበረዉ ቦታ ልመለስ ይገባል በማለት ነዉ፡፡ በመሠረቱ ከስራ ምደባና ደረጃ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያለዉ የመንግስት ሠራተኛ ቅሬታዉን የሚያቀርብበትን ሥርዓት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 56/2010 ይደነግጋል፡፡ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓቱ በልዩ ሁኔታ እንዲደነግግ የተፈለገበት ምክንያትም ለቅሬታዎች አፋጣኝ መፍትሔ ለመስጠት፣ ለቅሬታዎች መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ስህተቶችንና ድክመቶችን የማረም እና ሁሉንም የመንግስት ሠራተኞች በእኩልነት ለማስተናገድ የሚያስችል ፍትሐዊ የሆነ አሠራር በማስፈን የሰመረ የስራ ግንኙነት እንዲኖር በማሰብ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 75 ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በዚህም መሠረት ከስራ ምደባ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያለዉ ሠራተኛ ቅሬታዉን በቅድሚያ ለመስሪያ ቤቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታዉን ማቅረብ እንዳለበት፤ ቅሬታ ሰሚዉ ኮሚቴ በሰጠዉ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለዉ ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል እና የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ የህግ ስህተት አለዉ የሚል ከሆነም ቅሬታዉን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በማቅረብ መብቱን ማስከበር የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 77(4)፣ 77፣ 81(1/ሠ) እና 81(5) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ቅሬታዉ በዚህ መልኩ የሚቀርብለት ፍርድ ቤት ህግን የመተርጎም ስልጣን ያለዉ በመሆኑ የምደባዉን አግባብነት ሲመረምር ቅሬታ የቀረበበት ምደባ ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉን ህግ መሠረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑን ብቻ ሳይሆን ለምደባዉ መሠረት የሆነዉ መመሪያ ስልጣን ባለዉ አካል ተገቢዉን ሥርዓት ጠብቆ የወጣ እና ከሌሎች የበላይ ህጎች (superior laws) ጋር የሚጋጭ መሆን ያለመሆኑን እና ተያያዥ ጉዳዮችን በመመርመር እና ትርጉም በመስጠት የመመሪያዉን ህጋዊ ዉጤት ጭምር በማየት የምደባዉን ህጋዊነት መወሰን ይችላል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይም አመልካች ምደባዉ መብቴን ይነካል የሚሉ ከሆነ ከፍ ሲል በተመለከተዉ አግባብ ለሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት ብሎም ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡ ኖሮ ፍርድ ቤቶቹ የምደባዉን ህጋዊነት ሲመረምሩ ለምደባዉ መሰረት የሆነዉ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 6 እና ተከታዮቹ ላይ የተመለከቱትን የመመሪያ አወጣጥ ሥርዓቶችን ተከትሎ የወጣ መሆን ያለመሆኑን ጭምር መርምረዉ የመመሪያዉን ህጋዊ ዉጤት ወስነዉ ይህን መሰረት በማድረግም በምደባዉ ህጋዊነት ላይ ተገቢዉን መወሰን ይችሉ ነበር፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ከምደባ ጋር በተያያዘ በህግ የተዘረጋዉን ሥርዓት ተከትሎ ቅሬታቸዉን አቅርበዉ መብታቸዉን ማስከበር እየቻሉ በመመሪያ ክለሳ ዳኝነት ሰበብ አስቀድሞ በመመሪያ መሠረት በተጠሪ የተሰጠዉ ምደባ እንዲሰረዝ የሚያቀርቡት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለዉ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መመሪያ በአዋጁ የተመለከተዉን ሥርዓት የተከተለ አለመሆኑን አረጋግጦ መመሪያዉ እንዲሻር በሌላ በኩል መመሪያዉን መሰረት በማድረግ በተጠሪ የተደረገዉ ምደባ ሊሰረዝ አይገባም በማለት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በአዋጁ አንቀጽ

57(4) ላይ የተመለከተዉን ግልጽ ድንጋጌ ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማሻሻል በመዝገብ ቁጥር 208859 ላይ ሐምሌ 27 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ.መ.ቁ 215250
ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. ጋሊ አባሳንቢ
2. ቲጃኒ አባሳንቢ } አልቀረቡም

ተጠሪ፡- በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓቃቤሕግ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ጥቅምት 02 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 35449 ሐምሌ 22 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኮንታ ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካቾች እና በስር 1ኛ ተከሳሽ ላይ በስር ፍ/ቤት አሻሽሎ ያቀረባቸው ክሶች ሰባት ሲሆኑ ይዘታቸውም፡-

1ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና አንቀጽ 323 ድንጋጌን በመተላለፍ በኮንታ ልዩ ወረዳ በቂራሪ ቀበሌ ውስጥ በቀን 11/07/2011 ዓ.ም ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት አካባቢ በጋራ በመሆን ቆጭበሬ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በሚባል መንደር የነበረውን የአካባቢውን ጸጥታ ለመቆጣጠር የሄዱትን የፖሊስ አባላት ለግዜው ካልተያዙ ግብረአበሮቻቸው ጋር በመሆን በድንጋይ በመደብደብ ስራ እንዳይሰሩ ያደረጉና የስራ ግዴታን በማይገባ ሁኔታ እንዲጣስ ማስገደድ ወንጀል ፈጽመዋል፡፡

2ኛ.ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና 324 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በተገለፀው ልዩ ቦታ፣ቀንና ሰዓት ስራቸውን በማከናወን ላይ ባሉ የፖሊስ አባለት ላይ ጥቃት ፈጽመዋል፡፡

3ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና 333(2) ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛው ክስ በተገለፀው ልዩ ቦታ፣ቀንና ሰዓት ወታደራዊ ትዕዛዞች እንዲጣሱ በማድረግ ሌላውን ሰው የማነሳሳት ወንጀል ፈጽመዋል፡፡

4ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1(ሀ) እና አንቀጽ 337 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በተገለፀው ልዩ ቦታ፣ ቀንና ሰዓት በፖሊስ አባላት የሀሰት ወይም የሚያደናግር መረጃ ማሰራጨት ወንጀል ፈጽመዋል፡፡ 5ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና 485 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛው ክስ በተገለፀው ልዩ ቦታ፣ቀንና ሰዓት በወሬ ህዘብን የማሸበር ወንጀል ፈጽመዋል፡፡

6ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና 486 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛው ክስ በተገለፀው ልዩ ቦታ፣ቀንና ሰዓት የሀሰት ወሬዎችን በማውራት ሕዝብን ማነሳሳት ወንጀል ፈጽመዋል፡፡ 7ኛ ክስ፡- የስር 1ኛ ተከሳሽና 2ኛ አመልከች ብቻ የንግድ ፈቃድና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2/ ድንጋጌን በመተላለፍ ከ2002 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ የጸና የንግድ ፈቃድ ሳይኖራቸው ንግድ መነገድ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

አመልካች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ክሱን እንደማይቃወሙ ገልጸው የእምነት ክሕደት ቃላቸውንም ሲጠየቁ ድርጊቱን አልፈጸምንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱ የዓቃቤሕግን ማስረጃ ከሰማ በኋላ ዓቃቤሕግ እንደክሱ አስረድቷል በማለት አመልካቾች በተከሰሱበት የወንጀል ድንጋጌ እንዲከላከሉ ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካቾችም መከላከያ ምስክሮቻቸውን አስቀርበው አሰምተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካቾች ያቀረቧቸው ምስክሮች ከሌሊቱ 9፡00 ሰዓት ስለተፈጸመ ወንጀል እንጅ ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት ስለተፈጸመው ወንጀል የማያውቁ መሆኑን፣ የስር 1ኛ ተከሳሽና የአሁን 2ኛ አመልካች ሀገ-ወጥ ንግድ ስለመነገዳቸው በዓ/ህግ ምስክር የተረጋገጠባቸውን አመልካቾች ያላስተባበሉ መሆኑን ገልጾ የስር 1ኛ ተከሳሽን በ1ኛ፣3ኛ፣4ኛ፣6ኛና 7ኛ ክስ ጥፋተኛ በማድረግ በ 9 ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 10000 / አስር ሽህ / 1ኛ አመልካችን በ1ኛ፣ 3ኛ፣ 4ኛ እና 6ኛ ክስ ጥፋተኛ ባማድረግ በ5 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት፣

2ኛ አመልካችን ደግሞ በ2ኛ፣ 3ኛ፣ 4ኛ፣ 6ኛና 7ኛ ክስ ጥፋተኛ በማድረግ በ15 ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 20000 / ሃያ ሽህ / መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

በአመልካቾች ይግባኝ አቅራቢነት ይግባኙን የተመለከተው የኮንታ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ተመልክቶ የአመልካቾችን የቅጣት ውሳኔ ብቻ በማሻሻል የስር 1ኛ ተከሳሽ በ5 ዓመት ጽኑ እስራትና በብር 10000 / አስር ሽህ / የገንዘብ መቀጮ፣ 1ኛ አመልካችን በ4 ዓመት ጽኑ እስራት፤ 2ኛ አመልካችን ደግሞ በ11 ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 20000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካቾች በድጋሜ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ከክስ 1-6 የተጠቀሱት ክሶች በአንድ በዛ ቢባል በሁለት ተጠቃለው መቅረብ የሚገባቸው መሆኑን፣ 7ኛ ክስም ቢሆን አመልካቾች ይህን ያህል ረዥም ዓመት ንግድ ፍቃድ ሳይኖራቸው ሲነግዱ መንግስት ያልተቆጣጠረበት ምክንያት ግልጽ አለመሆኑንና የክሱ አቀራረብ የህጉን ዓላማ ያልተከተለ መሆኑን፣ ቅጣቱን በተመለከተ ደግሞ የስር ፍ/ቤት እንደ ማክበጃ ተብለው የተያዙ ነጥቦች በአብዛኛው አመልካቾች ተከሰው ጥፋተኛ የሆኑበትን የህግ አንቀጾች ማቋቋሚያ ሆነው እያለ ዳግመኛ ማክበጃ መያዙ የወንጀል ህግ አንቀጽ 84/2/ ዓላማ ያልተከተለ መሆኑን፣ የአመልካቾችን ቅጣት ማቅለያ በአግባቡ ያልያዘላቸው መሆኑን በመግለጽ አመልካቾች እያንዳንዳቸው በ1 ዓመት ከ6 ወር እስራት እና የስር 1ኛ ተከሳሽና 2ኛ አመልካች ደግሞ እያንዳንዳቸው በብር 500 / አምስት መቶ / መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት የጥፋተኝነት ውሳኔውን በተመለከተ በከፍተኛ ፍ/ቤት የፀና በመሆኑ አልመለከትም ካለ በኋላ እገረ መንገዱን በማለት ተችቶ ቅጣትን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት የወንጀል ህጉን 88/2/ እና 179/ሐ/ በመጥቀስ ቅጣቱን አሻሽሎ በዘፈቀደ የስር ፍ/ቤትን የቅጣት ውሳኔ አግባብነት ሳይመዝንና ሳይተች ቅጣቱ ፍትሀዊ አይደለም ብሎ ማቅለሉ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያን እና አጠቃላይ የወንጀል ቅጣት ዓላማ እና ግብ ያልተከተለና አስተማሪ ያልሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው በማለት የስር የኮንታ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤትን የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ጥቅምት 02 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም የስር 1 ተከሰሽና 1ኛ አመልካች ከዚህ ክስ በፊት በኮንታ ልዩ ወረዳ ዓ/ህግ በቁጥር 3403 በቀን 08/09/2011 ዓ.ም በተጻፈ ክስ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና 438 ን ተላለፋችሃል ተብለው የጦር መሳሪያ በመያዝ የብርበራ ተዕዛዝ የያዙትን ፖሊሶች ስራቸውን እንዳይሰሩ ሀሰተኛ ወሬ በመንዛት የአካባቢው ሰው ገጀራና ጦር ይዞ እንዲወጣ በመንገር

ብርበራው እንዳይካሄድና በፖሊሶችና በመኪናቸው ላይ ጉዳት በማድረስ ወንጀል ተከሰው በመ/ቁ 17999 በቀን 22/11/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጥፋተኛ በማድረግ በ7 ዓመት ጽኑ እስራት የተወሰነባቸው መሆኑን፣ 1ኛ አመልካችና የስር 1ኛ ተከሳሽ በውሳኔው መሰረት ቅጣቱን እየፈጸሙ እያለ በድጋሜ 2ኛ አመልካችን ጨምረው በቀረበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ ላይ ተጠቅሶ አልቀረበም በሚል ምክንያት የስር ፍ/ቤት ከ1-6 በጠቀሳቸው ክሶች ላይ በድጋሜ ተከሰው የተወሰነባቸው መሆኑንና፣ 2ኛ አመልካች ከ1-6 በተጠቀሱት ክሶች ላይ ጥፋተኛ መባሉ ከጥርጣሬ በላይ ባልተረጋገጠ ማስረጃ መሆኑን፣ 7ኛ ክስን በተመለከተ አመልካቾች ሱቅ እንደሌላቸው እና መኪኖች ሲያልፉ ህጻናት ሶፍትና ውሃ ሲሸጡ በማየት ነጋዴ ናቸው ማለቱ አግባብ አለመሆኑን ገልጸው የስር የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾች ፈጽመዋል በሚል በተለያዩ ወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ስር የተከሰሱበትን ክስ መሰረት በማድረግ የተሰጠው የትፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አግባብነት ከወንጀል ህግ አንቀጽ 61 እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ነጥቦች አንጻር ለመመርመር ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን የካቲት 25/2014 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልስ አመልካቾች የተከሰሱባቸው የወንጀል ድንጋጌዎች በአንድ ድርጊት ከሁለት በላይ የሆኑ ወንጀል ድንጋጌዎች በመጣስ ልዩልዩ ግዙፋዊ ውጤት የሚያስከትሉ ወንጀሎችን በአደገኛ ሁኔታ የጦር መሳሪያ ገጀራ፣ ጦር እና ድንጋይ በመያዝ የተፈጸሙ መሆናቸው በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ ይህን መሠረት በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት፡፡

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 61/1 ድንጋጌ በሕግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚደረጉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የወንጀል ድርጊቶች የተደረጉት በአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኝነት ሲሆን እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈኑ ሲሆን አድራጊው ተመሣሣይ ባሕርይ ባላቸው በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች አይቀጣም በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 2 ድንጋጌም በሕግ በተጠበቀ በዚያው በአንድ መብት ላይ ተደጋግመው ወይም ተከታትለው የተደረጉ የወንጀል ተግባሮች በአንድ የወንጀል ማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኝነት እንደ አንድ ወንጀል የሚቆጠሩ መሆኑ፤ ወንጀል አድራጊው ለዚሁ እንደ አንድ ወንጀል

ለተቆጠረው እንጂ ተደጋግሞ ወይም ተከታትሎ ለተፈጸመው ለእያንዳንዱ ድርጊት የማይቀጣ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች ከ1ኛ እስከ 6ኛ ባሉት ክሶች ፈጸሙበት የተባለው የወንጀል ተግባር የአካባቢውን ጸጥታ ለመቆጣጠር የሄዱትን የፖሊስ አባላት በመደብደብ ስራ እንዳይሰሩ አድርገዋል፤ የፖሊስ አባለት ላይ ጥቃት ፈጽመዋል፤ ወታደራዊ ትዕዛዞች እንዲጣሱ አድርገዋል፤ ሌላውን ሰው አነሳስተዋል፤ በፖሊስ አባላት የሀሰት መረጃ አሰራጭተዋል፤ በወሬ ሕዝብን አሸብረዋል፤ የሀሰት ወሬ በማውራት ሕዝብን አነሳስተዋል የሚል ነው፤ ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 61(1)(2) ላይ እንደተገለጸው በአንድ የወንጀል ማድረግ ሐሳብ የተፈጸመ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል ማንም ሰው የጸና የንግድ ፈቃድ ሳይኖረው ንግድ ሲነግድ በተገኘ ጊዜ ተጠያቂ እንዲሚሆን አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2/ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ዓቃቤሕግ ይህንኑ መሠረት በማድረግ በ2ኛ አመልካች ላይ ክስ ያቀረበ ቢሆንም 2ኛ አመልካች ባቀረበው መከላከየ ማስረጃ ሱቅ እንደሌለው እና ባለቤቱ ድንች፣ ቅመማቅመምና በርበሬ ገበያ እየወሰደች የምትሸጥ መሆኑን አስረድቷል፡፡ ይህም የእለት ጉርስ ለማግኘት የሚፈጸም ተግባር መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዘሁ አግባብ 2ኛ አመልካች የቀረበበትን 7ኛ ክስ አስተባብሏል ማለት ሲገባው በፍርድ ትችቱ ላይ አመልካቾች ይህን ያህል ረዥም ዓመት ንግድ ፍቃድ ሳይኖራቸው ሲነግዱ መንግስት ያልተቆጣጠረበት ምክንያት ግልጽ አይደለም በማለት ያስቀመጠው ሀሳብ የሕጉን አላማ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ መሠረት በማድረግ በሥር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ማጽናት ሲገባው አመልካቾች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በተከሰሱበት እያንዳንዱ አንቀጽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 34496 የካቲት 11 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

ትዕዛዝ

- አመልካቾች የቅጣት ውሳኔ ከተላለፈባቸው ከነሐሴ 22 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ያለው ጊዜ ሲሰላ በዚህ ችሎት የጸናው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እያንዳንዳቸው በ1 ዓመት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከ6 ወር እስራት እንዲቀጡ በማለት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ የፈጸሙ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አመልካቾችን በሌላ ጉዳይ የማይፈልጋቸው ከሆነ በዛሬው ዕለት ከእስር እንዲለቃቸው ታዟል። በትዕዛዙ መሠረት ማስፈጸም ይቻለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ይድረሰው።

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት

ሠ/ን

የሰበር መዝገብ ቁጥር 215158

ግንቦት 22 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ፌዳ ብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር

ተጠሪ፡- አቶ ፋሲካ መርሻ } የቀረበ የለም

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የአመልካች ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ የማኅበሩ ሥራ አሲኪያጅ ከ3ኛ ወገኖች ጋር ውል መዋዋል የሚችል መሆኑን በግልጽ ደንግጎ እያለና ይህ የሚያደርገው ውልም የብደር ስምምነትን የሚጨምር በመሆኑና ይህን ሥልጣኑን መሠረት በማድረግ የማኅበሩ ሥራ አሲኪያጅ በ11/09/2008 ፣ በ22/10/2008 ፣ በ09/06/2009 ፣ 01/07/2009 እና 06/09/2009 ያደረገው የብድር ውል ስምምነት በተጠሪ አልተረጋገጠም በማለት ሂሳብ አጣሪው ውድቅ በማድረግ ሂሳቡ ውስጥ ገብቶ የማኅበሩ ዕዳ ተብሎ አለመያዙ የሕግ ፣ የመተደደሪ ደንብም ሆነ የውል መሠረት የሌለው ፣ የፍርድ ቤት ሥልጣን የሆነውን የብርድ ውል ማስረጃ ተገቢነትና ተቀባይነት የመመዘን ሥልጣን ለሂሳብ አጣሪ ተላልፎ መሰጠቱ ፣ ለብድሩ መነሻ የሆነውን ቃለ ጉባኤ ተጠሪ መውሰዱን ማመኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በፍርድ ቤት ተዕዛዝ እንዲቀርብለት አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ላይ ተገቢው ትዕዛዝ ሳይሰጥ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ ቀርቦ ሂሳቡ መጣራት ሲገባው ታልፎ ውሳኔ መሰጠቱ እና ይህ ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም መጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሰሚው ችሎት ሊታረም ይግባል በማለት አመልካች ጥቅምት 9 ቀን 2014 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት መዝገቡ ለችሎት ሊቀርብ ችሏል፡፡

ጉዳዩ ተጠሪ ከአመልካች ማኅበር ለመውጣት ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ በዚሁ አግባብ ተውስኖ ከማህበሩ ሲወጡ የሚከፈላቸውን ድርሻ ለማጣራ የሂሳብ አጣሪ ተሹሞ ሐምሌ 28 ቀን 2012 ዓ/ም የቀረበው ሪፖርት ስህተት አለበት ተብሎ እንደገና ተስተካክሎ በቀረበው ሪፖርት ላይ ግራቀኙ አስተያየታቸውን የሰጡ ሲሆን አመልካች በአስተያየታቸው ተከፈለ የተባው የማኅበሩ ዕዳ በተጠሪ የተከፈለውን እንጅ በአመልካች የተወሰደው የብድር ገንዘብ በሪፖርቱ አለመካተቱንና ብድሩን ለመውሰድ የተያዘውን ቃለ ጉባኤ ተጠሪ ወስድው ያልመለሱ ሲሆን መውሰዳቸውን ያመኑበት ቃለ ጉባኤ ቀርቦ ሳይጣራ ሂሳቡ መሰራቱ ፍትሐዊ አይደለም በማለት ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡ የሂሳብ አጣሪው በቀረበው ቅሬታ ላይ በሰጠው ማብራሪያ በአመልካች የቀረበው ሰነድ በአመልካች ብቻ የተፈረመ ፣ ተጠሪ ያልፈረሙበት የተሟላ ሕጋዊ ሰነድ ባለመሆኑ በሂሳብ ማጣራቱ አለመካተቱን አስረድተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በአመልካች ለሂሳብ አጣሪው የቀረበው ሰነድ በግራቀኙ ያልተረጋገጡ በመሆኑ ሂሳቡን ለመሥራት እንደህጋዊ ሰነድ ሊያቀርቡ የማይችሉ በሂሳብ አሰራር ደንብ ተቀባይነት የሌላቸው ሰነዶች በመሆናቸው በሂሳብ አጣሪው ተቀባይነት ማጣቱ አግባብ ነው በማለት የአመልካችን ቅሬታ ውድቅ በማድረግ የቀረበው የሂሳብ ማጣራት ሪፖርት በማጽደቅ ተጣርቶ በቀረበው ሪፖርት መሠረት የተጠሪ ድርሻ ብር 42,788.5(አርባ ሁለት ሺ ሰባት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከ5/100) እንዲከፈላቸው የወሰነ ሲሆን ፣ አመልካች በውሳኔው ባለመስማማት ያቀረቡት ይግባኝ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረዙ በፍርዱ መግቢያ ላይ የተመለከተውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአመልካችን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ አመልካች ማኅበር የወሰደው ብድር ተጠሪ ያልፈረመበት ነው በሚል በዕዳነት አይያዝም ተብሎ ውድቅ የመሆኑን አግባብነት ከመሠረታዊ ማስረጃ ሚዘና መርህ አንፃር ተገቢነቱን ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- የአመልካች ማኅበር ሥራ አስኪያጅ ማኅበሩን ወኪሎ ብድር የመዋዋል ሥልጣን በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍም ሆነ መተዳደሪያ ደንብ ያልተሰጠው በመሆኑ ሥራ አስኪያጁ የወሰደው ብድር በሁሉም ማኅበርተኞች ካልተረጋገጠ ለማኅበሩ ዓላማ የተደረገ ሕጋዊ ውል ባለመሆኑ የማህበሩ ሂሳብ ሲጣራ በወጪነት ሊያዝ የሚገባው በሕጋዊ ሁኔታ ሥልጣን ባለው አካል የወጡ ወጪዎች ብቻ በመሆናቸው አመልካች ያቀረባቸው የብድር ውሎች ሥልጣን በሌለው የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ የተደረጉ መሆኑን አረጋግጦ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ፀንቶ ለክርክሩ ያወጡትና ወጪና ኪሳራ አመልካች እንዲተኩላቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ የማኅበሩ ሂሳብ ተጣርቶ ተጠሪ ድርሻቸውን አግኝተው ከማኅበሩ እንዲሰናበቱ በተወሰነው መሠረት የሥር ፍርድ ቤት የማኅበሩን ሂሳብ እንዲጣራ አድርጓል፡፡ ግራቀኙ ብድር መኖሩን ገልፀው

የተከራከሩ ሲሆን በተጠሪ በኩል የቀረበው ዕዳ መወሰዱ በግራቀኙ ፊርማ ተረጋግጦ በወጪነት የተያዘ ሲሆን ፤ አመልካች በዕዳነት እንዲያዝ ያቀረቧቸው ብደሮች በአመልካችና ተጠሪ ያልተፈረመ ነው በሚል ውድቅ ሆኗል፡፡ በዕዳነት እንድያዝ ተቀባይነት ያገኘው ማስረጃ በግራቀኙ ፊርማ የተረጋገጠው ሲሆን፣ አመልካች በዕዳነት እንዲያዝለት ያቀረብው የብድር ውል በግራቀኙ አለመፈረሙ ያላከራከረ ሆኖ አመልካች ብድሮቹ በአመልካች ሥራ አስኪያጅ የተወሰዱ ናቸው ቢልም የአመልካች ማኅበር ሥራ አስኪያጅ ማኅበሩን ወኪሎ ብድር የመዋዋል ሥልጣን በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍም ሆነ መተዳደሪያ ደንብ ያልተሰጠው በመሆኑ ሥራ አስኪያጁ የወሰደው ብድር በሁሉም ማኅበርተኞች ካልተረጋገጠ ለማኅበሩ ዓላማ የተደረገ ሕጋዊ ውል ባለመሆኑ የማህበሩ ሂሳብ ሲጣራ በወጪነት ሊያዝ የሚገባው በሕጋዊ ሁኔታ ሥልጣን ባለው አካል የወጡ ወጪዎች ብቻ በመሆናቸውን ተጠሪ ተከራክረዋል፡፡ የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ከማኅበሩ ንግድ ጋር የሚያያዝ የንግድ ልውውጥን በተመለከተ ከ3ኛ ወገኖች ጋር ከመዋዋል ባለፈ ማኅበሩን ወኪሎ ገንዘብ የሚበደር መሆኑን የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍም ሆነ መተዳደሪያ ደንብ የማያመለክት መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት በችሎቱ ትዕዛዝ ከመጣው መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡ ብድሩን ለመውሰድ የተያዘውን ቃለ ጉባኤ ተጠሪ ወስድው ያልመለሱ መሆኑን ተጠሪ ያመኑ መሆኑን የሚያመለክተው ቃለ ጉባኤ ቀርቦ ሳይጣራ ውሳኔ መሰጠቱን አመልካች የታቀወሙ ቢሆንም ቃለ ጉባኤው ቀርቦ ቢሆንኖሮ ብድር ለመውድ ውሳኔ መተላለፉን ከሚያመለክት በቀር አመልካች በዕዳነት አልተያዙልኝም የሚላቸውን ብድሮች በማኅበሩ አሰራር መሠረት በግራቀኙ ተፈርሞ መወሰዳቸውን የማያስረዳ በመሆኑ አመልካች እንዲቀርብለት የጠየቀው ማስረጃ ሳይቀርብ ውሳኔ ተሰጥቷል በማለት የሚያቀርበው ቅሬታ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ቁጥር 145 ድንጋጌን ዓላማ መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ ሲጠቃለል አመልካች ያቀረበው ቅሬታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን የማያመለክት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 261534 ሐምሌ 9 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 276706 ታህሳስ 14 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ***ፀንቷል።***
2. በዚህ መዝገብ ላይ ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ዕገዳ ተነስቷል፡፡
3. ከሥር ፍርድ ቤት የመጣው መዝገብ በመጣበት አካን እንዲመለስ ታዟል፡፡
4. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔው ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተነቧል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰበር መዝገብ ቁጥር 215158

ግንቦት 22 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ፌዳ ብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር

ተጠሪ፡- አቶ ፋሲካ መርሻ } የቀረበ የለም

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የአመልካች ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ የማኅበሩ ሥራ አሲኪያጅ ከ3ኛ ወገኖች ጋር ውል መዋዋል የሚችል መሆኑን በግልጽ ደንግጎ እያለና ይህ የሚያደርገው ውልም የብደር ስምምነትን የሚጨምር በመሆኑና ይህን ሥልጣኑን መሠረት በማድረግ የማኅበሩ ሥራ አሲኪያጅ በ11/09/2008 ፣ በ22/10/2008 ፣ በ09/06/2009 ፣ 01/07/2009 እና 06/09/2009 ያደረገው የብድር ውል ስምምነት በተጠሪ አልተረጋገጠም በማለት ሂሳብ አጣሪው ውድቅ በማድረግ ሂሳቡ ውስጥ ገብቶ የማኅበሩ ዕዳ ተብሎ አለመያዙ የሕግ ፣ የመተደደሪ ደንብም ሆነ የውል መሠረት የሌለው ፣ የፍርድ ቤት ሥልጣን የሆነውን የብርድ ውል ማስረጃ ተገቢነትና ተቀባይነት የመመዘን ሥልጣን ለሂሳብ አጣሪ ተላልፎ መሰጠቱ ፣ ለብድሩ መነሻ የሆነውን ቃለ ጉባኤ ተጠሪ መውሰዱን ማመኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በፍርድ ቤት ተዕዛዝ እንዲቀርብለት አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ላይ ተገቢው ትዕዛዝ ሳይሰጥ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ ቀርቦ ሂሳቡ መጣራት ሲገባው ታልፎ ውሳኔ መሰጠቱ እና ይህ ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም መጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሰሚው ችሎት ሊታረም ይግባል በማለት አመልካች ጥቅምት 9 ቀን 2014 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት መዝገቡ ለችሎት ሊቀርብ ችሏል፡፡

ጉዳዩ ተጠሪ ከአመልካች ማኅበር ለመውጣት ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ በዚሁ አግባብ ተውስኖ ከማህበሩ ሲወጡ የሚከፈላቸውን ድርሻ ለማጣራ የሂሳብ አጣሪ ተሹሞ ሐምሌ 28 ቀን 2012 ዓ/ም የቀረበው ሪፖርት ስህተት አለበት ተብሎ እንደገና ተስተካክሎ በቀረበው ሪፖርት ላይ ግራቀኙ አስተያየታቸውን የሰጡ ሲሆን አመልካች በአስተያየታቸው ተከፈለ የተባው የማኅበሩ ዕዳ በተጠሪ የተከፈለውን እንጅ በአመልካች የተወሰደው የብድር ገንዘብ በሪፖርቱ አለመካተቱንና ብድሩን ለመውሰድ የተያዘውን ቃለ ጉባኤ ተጠሪ ወስድው ያልመለሱ ሲሆን መውሰዳቸውን ያመኑበት ቃለ ጉባኤ ቀርቦ ሳይጣራ ሂሳቡ መሰራቱ ፍትሐዊ አይደለም በማለት ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡ የሂሳብ አጣሪው በቀረበው ቅሬታ ላይ በሰጠው ማብራሪያ በአመልካች የቀረበው ሰነድ በአመልካች ብቻ የተፈረመ ፣ ተጠሪ ያልፈረሙበት የተሟላ ሕጋዊ ሰነድ ባለመሆኑ በሂሳብ ማጣራቱ አለመካተቱን አስረድተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በአመልካች ለሂሳብ አጣሪው የቀረበው ሰነድ በግራቀኙ ያልተረጋገጡ በመሆኑ ሂሳቡን ለመሥራት እንደህጋዊ ሰነድ ሊያቀርቡ የማይችሉ በሂሳብ አሰራር ደንብ ተቀባይነት የሌላቸው ሰነዶች በመሆናቸው በሂሳብ አጣሪው ተቀባይነት ማጣቱ አግባብ ነው በማለት የአመልካችን ቅሬታ ውድቅ በማድረግ የቀረበው የሂሳብ ማጣራት ሪፖርት በማጽደቅ ተጣርቶ በቀረበው ሪፖርት መሠረት የተጠሪ ድርሻ ብር 42,788.5(አርባ ሁለት ሺ ሰባት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከ5/100) እንዲከፈላቸው የወሰነ ሲሆን ፣ አመልካች በውሳኔው ባለመስማማት ያቀረቡት ይግባኝ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረዙ በፍርዱ መግቢያ ላይ የተመለከተውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአመልካችን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ አመልካች ማኅበር የወሰደው ብድር ተጠሪ ያልፈረመበት ነው በሚል በዕዳነት አይያዝም ተብሎ ውድቅ የመሆኑን አግባብነት ከመሠረታዊ ማስረጃ ሚዘና መርህ አንፃር ተገቢነቱን ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- የአመልካች ማኅበር ሥራ አስኪያጅ ማኅበሩን ወኪሎ ብድር የመዋዋል ሥልጣን በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍም ሆነ መተዳደሪያ ደንብ ያልተሰጠው በመሆኑ ሥራ አስኪያጁ የወሰደው ብድር በሁሉም ማኅበርተኞች ካልተረጋገጠ ለማኅበሩ ዓላማ የተደረገ ሕጋዊ ውል ባለመሆኑ የማህበሩ ሂሳብ ሲጣራ በወጪነት ሊያዝ የሚገባው በሕጋዊ ሁኔታ ሥልጣን ባለው አካል የወጡ ወጪዎች ብቻ በመሆናቸው አመልካች ያቀረባቸው የብድር ውሎች ሥልጣን በሌለው የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ የተደረጉ መሆኑን አረጋግጦ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ፀንቶ ለክርክሩ ያወጡትና ወጪና ኪሳራ አመልካች እንዲተኩላቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ የማኅበሩ ሂሳብ ተጣርቶ ተጠሪ ድርሻቸውን አግኝተው ከማኅበሩ እንዲሰናበቱ በተወሰነው መሠረት የሥር ፍርድ ቤት የማኅበሩን ሂሳብ እንዲጣራ አድርጓል፡፡ ግራቀኙ ብድር መኖሩን ገልፀው

የተከራከሩ ሲሆን በተጠሪ በኩል የቀረበው ዕዳ መወሰዱ በግራቀኙ ፊርማ ተረጋግጦ በወጪነት የተያዘ ሲሆን ፤ አመልካች በዕዳነት እንዲያዝ ያቀረቧቸው ብደሮች በአመልካችና ተጠሪ ያልተፈረመ ነው በሚል ውድቅ ሆኗል፡፡ በዕዳነት እንድያዝ ተቀባይነት ያገኘው ማስረጃ በግራቀኙ ፊርማ የተረጋገጠው ሲሆን፣ አመልካች በዕዳነት እንዲያዝለት ያቀረብው የብድር ውል በግራቀኙ አለመፈረሙ ያላከራከረ ሆኖ አመልካች ብድሮቹ በአመልካች ሥራ አስኪያጅ የተወሰዱ ናቸው ቢልም የአመልካች ማኅበር ሥራ አስኪያጅ ማኅበሩን ወኪሎ ብድር የመዋዋል ሥልጣን በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍም ሆነ መተዳደሪያ ደንብ ያልተሰጠው በመሆኑ ሥራ አስኪያጁ የወሰደው ብድር በሁሉም ማኅበርተኞች ካልተረጋገጠ ለማኅበሩ ዓላማ የተደረገ ሕጋዊ ውል ባለመሆኑ የማህበሩ ሂሳብ ሲጣራ በወጪነት ሊያዝ የሚገባው በሕጋዊ ሁኔታ ሥልጣን ባለው አካል የወጡ ወጪዎች ብቻ በመሆናቸውን ተጠሪ ተከራክረዋል፡፡ የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ከማኅበሩ ንግድ ጋር የሚያያዝ የንግድ ልውውጥን በተመለከተ ከ3ኛ ወገኖች ጋር ከመዋዋል ባለፈ ማኅበሩን ወኪሎ ገንዘብ የሚበደር መሆኑን የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍም ሆነ መተዳደሪያ ደንብ የማያመለክት መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት በችሎቱ ትዕዛዝ ከመጣው መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡ ብድሩን ለመውሰድ የተያዘውን ቃለ ጉባኤ ተጠሪ ወስድው ያልመለሱ መሆኑን ተጠሪ ያመኑ መሆኑን የሚያመለክተው ቃለ ጉባኤ ቀርቦ ሳይጣራ ውሳኔ መሰጠቱን አመልካች የታቀወሙ ቢሆንም ቃለ ጉባኤው ቀርቦ ቢሆንኖሮ ብድር ለመውድ ውሳኔ መተላለፉን ከሚያመለክት በቀር አመልካች በዕዳነት አልተያዙልኝም የሚላቸውን ብድሮች በማኅበሩ አሰራር መሠረት በግራቀኙ ተፈርሞ መወሰዳቸውን የማያስረዳ በመሆኑ አመልካች እንዲቀርብለት የጠየቀው ማስረጃ ሳይቀርብ ውሳኔ ተሰጥቷል በማለት የሚያቀርበው ቅሬታ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ቁጥር 145 ድንጋጌን ዓላማ መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ ሲጠቃለል አመልካች ያቀረበው ቅሬታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን የማያመለክት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 261534 ሐምሌ 9 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 276706 ታህሳስ 14 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ***ፀንቷል።***
2. በዚህ መዝገብ ላይ ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ዕገዳ ተነስቷል፡፡
3. ከሥር ፍርድ ቤት የመጣው መዝገብ በመጣበት አካን እንዲመለስ ታዟል፡፡
4. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔው ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተነቧል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

??/? /??? 215115
?? 25/9/2014 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን፡- ነ/ፊጅ ክፍለ ሀይለይ ቀረበ

ተጠሪ - አቶ ሄኖክ ዘረማሪየም፡- ጠበቃ ሀይማኖት ሞላ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ጥቅምት 9 ቀን 2014 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 279571 ጥቅምት 4 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 99967 ሐምሌ 1 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዬን በቂ ባልሆነ ምክንያት መታለፋቸው ተገቢ አይደለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 እና በመመሪያ ቁጥር 118/2006 አንቀጽ 5 መሰረት ተጠሪ በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ለአቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት ቀረቦ ከታየ በኋላ በይግባኝ ለከፍተኛ ፍ/ቤት የሚቀርብ ሆኖ እያለ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 153 እና 155(1) ታልፎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ የአሁን ተጠሪ የውጪ ሀገር ገንዘብ የተወረሰው ህጉን ተከትሎ ሲሆን በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር 49/2017 አንቀጽ 4(1) እና በአዋጅ ቁጥር 859/2006 እና በመመሪያ ቁጥር 118/2006 አንቀጽ 15 መሰረት የአንድ ጊዜ ማስፈቀጃ ላይ ተመዝግቦ የገባ በተለያዩ ጉዞዎች መጠቀም ከሀገር ይዞ መውጣት እንዲችል በማድረግ የተዘጋጀበትን ዓላማ በመጣስ ገንዘቡን ለ3ኛ ጊዜ ሲወጣ መያዙ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተገቢ ነው፡፡ የተሰሙት የሰው ምስክሮች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የተሰሙትን ቃል ለፍሬ ነገር ክርክር መጠቀሙ እየተቃወምን መታለፉ ተገቢ አይደለም፡፡ ለአንድ ጉዞ ብቻ የሚያገለግል ማስፈቀጃ ከሀገር ወጥቶ ሲመለስ ያላስመዘገበ ሆኖ እየለ ይዞ የወጣ ገንዘብ ስመለስ ደግሞ ያላስመዘገበ መሆኑ የሚያስረዳና ግምት የሚወሰድበት ሆኖ እያለ ታልፎ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ከሳሽ የአሜሪካ ዜግነት ያለኝና በአሜሪካ አገር ነዋሪ ነኝ፡፡ ጥቅምት 27 ቀን 2011 ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ በመጣሁ ጊዜ 6350 ዩሮ፣ 9250 ድርሃም፣ 390 ዶላር፣ 1020 ራንድ በተከሳሽ የአሁን አመልካች አዲስ አበባ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በውጪ ምንዛሪ መመዝገቢያ ቅጽ አስመዝግቤ የገንዘብ ዲክላራሲዮን ተሰጥቶኛል፡፡ ሀገር ውስጥ ቆይቼ የቀረኝ ገንዘብ 9250 ድርሃም፣ 1020 ራንድ፣ 2890 ዮሮ ሲሆን፣ ይህም በወቅቱ ምንዛሪ 167,837 የሚሆን ነው፡፡ ይሁንና ተከሳሽ በ19/3/2011 ዓ/ም ከሀገር ልወጣ ሲል የቀረኝን ገንዘብ ይዞብኛል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቁጥር- በውማሮ/ውምስጥ/472/09 በ25/9/2001 ዓ/ም ባወጣው መመሪያ መሰረት ከ3000 ዶላር በላይ ወይም ሌላ ተመጣጣኝ ገንዘብ ይዤ ከሀገር መውጣት እንደምችል እየታወቀ ተከሳሽ ገንዘቤን የያዘብኝ ብሔራዊ ባንክን ለማቋቋም ከወጣው አዋጅ ቁጥር 591/2000 እና ከመመሪያው ውጪ በመሆኑ ካለአግባብ የያዘብኝን ገንዘብ እንዲለቅልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ተከሳሽም የአሁን አመልካች ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም፡፡ ከሳሽ በ19/3/2011 ዓ/ም ይዞ ከሀገር ሊወጣ የነበረን የውጪ ምንዛሪ በፍተሻ መያዙ ተገቢ ነው፡፡ ገንዘቡም ለመንግስት ካዝና ገቢ ሆኗል፡፡ አንድ የውጪ ሀገር ዜጋ ይዞ የሚገባውን የውጪ ምንዛሪ በ30 ቀን ውስጥ በአንድ ጉዞ ብቻ ይዞ መውጣት እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ከሳሽ ባያያዘው የውጪ ምንዛሪ መመዝገቢያው ቅፅ ሴሪ ቁጥር 55539 ተ/ቁጥር 02 ላይ የሚጠበቅበት ግዴታ ተገልጾ እያለ በሁለት ጉዞ ምንዛሪውን በድጋሚ ከሀገር ይዞ ለመውጣት ሲሞክር የተያዘና ለመንግስት ገቢ የተደረገ በመሆኑ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር 49/2017 አንቀጽ 4(1ለ) ከ3000 ዶላር በላይ ይዞ የሚገባ ሰው በጉምሩክ ማሳወቅ ወይም ድክሌር ማደርግ አለበት፡፡ይህ ግዴታ አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸም ሳይሆን ከሀገር ወጥቶ በገባ ጊዜ ሁሉ ነው፡፡ ዲክላራሲዮኑ የሚያገለግለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ከሳሽ መጀመሪያ ለጉምሩክ አሳውቆ ወደ ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ ከሀገር ወጥቶ እንደገና ሲመለስ የያዘውን የገንዘብ መጠን ማስመዝገብ አለበት፡፡ ነገር ግን ከሳሽ አላስመዘገበም፡፡ፈታሽና ቡድን አስተባባሪውም ከሳሽ መጀመሪያ ይዞ የገባውን የውጪ ምንዛሪ ከሀገር ይዞ ወጥቷል፡፡ የሁለተኛ ጊዜው አልተመዘገበም፡፡ ይሄውም ፓስፖርቱ የሚያረጋግጥ ሲሆን አሁን የተያዘው የውጪ ምንዛሪ መጀመሪያ ያስመዘገበውም አይደለም፡፡ በህጉ እና በመመሪያ ቁጥር 49/2017 መሰረት የተወረሰ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 99967 ሐምሌ 1 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ከሳሽ በ27/2/2011 ዓ/ም ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ የያዘውን የውጪ ምንዛሪ ያስመዘገበ (ድክሌር ያደረገ) ሲሆን በመሀል ዩጋንዳ ወጥቶ የተመለሰ ሲሆን ከሳሽ ዩጋንዳ ወጥቶ ሲመለስ የውጪ ምንዛሪውን ይዞ ያልወጣ መሆኑ ተመስክሯል፡፡ ተከሳሽ ወደ ዩጋንዳ ይዞ የወጣ ስለመሆኑ ማስረዳት አልቻለም፡፡ ዲክላራሲዮን ለአንድ ጊዜ የቪዛ ቆይታ ብቻ እንደሚያገለግል በዲክላራሲዮኑ ተራ ቁጥር 2 ላይ ተገልጿል፡፡ ከሳሽ በ19/3/2011 ዓ/ም ከሀገር ሲወጣ የተያዘበት ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ ያስመዘገበው (ድክሌር ያደረገው) እና ተጠቅሞበት የቀረውን ገንዘብ በመሆኑ የውጪ ምንዛሪ ከህግ ውጪ ይዞ ሲወጣ ተይዟል የሚባል አይደለም፡፡ ቀድሞ ካስመዘገበው ገንዘብ ማነሱም ተጠቅሞበት የቀረው በመሆኑ የተለየ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ ካለአግባብ የያዘበትን የውጪ ምንዛሪ በኢትዮጵያ ብር 167,837 ለከሳሽ እንዲከፍለው ሲል ወሰኗል፡፡ ተከሳሽ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ

በመ/ቁጥር 279571 ጥቅምት 4 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት በአሁን አመልካች የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የታለፈበት አግባብ ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 153 እና 155 አንጻር እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች በተመለከተ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ህዳር 24 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የስር ፍ/ቤት መዝገብ በማስመጣት ጭምር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በነበረው ክርክር የአሁን ተጠሪ የውጪ ምንዛር 6350 ዩሮ፣ 9250 ድርሃም፣ 390 ዶላር፣ 1020 ራንድ መጀመሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ በተከሳሽ የአሁን አመልካች አዲስ አበባ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በውጪ ምንዛሪ መመዝገቢያ ቅጽ ያስመዘገበ መሆኑ የተረጋገጠ እና ያላከራከረ ጉዳይም ነው፡፡ የአሁን አመልካች ክርክር የአሁን ተጠሪ ምንዛሪው እጁ ላይ እንዲቆይ በተፈቀደለት ጊዜ ውስጥ በመሀል ወደ ዩጋንዳ ሀገር ወጥቶ የተመለሰ በመሆኑ እና ወደ ዩጋንዳ ሀገር ወጥቶ ሲመለስ የውጪ ሀገር ምንዛሪ ያላስመዘገበ በመሆኑ አሁን ለሁለተኛ ጊዜ ተመልሶ ሲወጣ የያዘው ገንዘብ ያልተመዘገበ በመሆኑ ሊወረስ ይገባል የሚል ነው፡፡ የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር ኤፍኤክዲ49/2017 ቀጥር 4(1ለ) ማናቸውም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ እና ከ3000 ዩኤስ ዲ ወይም ተመጣጣኝ ሌሎች መመንዘር የሚችሉ የውጭ አገር ገንዘብ በላይ ይዞ የሚገባ ሰው የያዘውን ገንዘብ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው የጉምሩክ የውጭ ገንዘብ ማሳወቂያ ቅጽ ወደ አገሪቱ በሚገባበት ጊዜ በአየር ማረፊያ ወይም በማንኛውም መግቢያ በር ማሳወቅ ይኖርበታል ሲል ይገልጻል እንዲሁም የዚሁ መመሪያ አንቀጽ 4(2ሐ) ማንኛውም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ቪዛው አገልግሎት እስኪያበቃ ድረስ የውጭ ሀገር ገንዘብ ይዞ መቆየት እንደሚችል ይገልጻል፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪ በመሀል ወደ ዩጋንዳ ሀገር ወጥቶ ተመልሷል የሚል ክርክር እንጂ ተጠሪ ወደ ዩጋንዳ ሀገር ወጥቶ ሲመለስ ቀደም ብሎ አስመዝግቦ ይዞ የገባውን የውጪ ሀገረ ምንዛሪ ዩጋንዳ ሀገር ይዞ የወጣ ስለመሆኑ ማስረዳት አልቻለም፡፡ አንድ ሰው በህጋዊ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ እና ከሀገር ውስጥ ሲወጣ ካለ አሁን አመልካች እውቅና ውጪ የውጪ ምንዛሪ ይዞ ሊወጣ የሚችል አይደለም፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪ ወደ ዩጋንዳ ሀገር ሲወጣ ይዞ የገባውን የውጪ ሀገር ምንዛሪ ይዞ ወጥቷል የሚል ከሆነ ተቋም ነው በህጋዊ መንገድ ወደ ውጪ ሀገር የሚወጣ ሰው በቁጥጥሩ ስር የሚያልፍ ነው፡፡ የወጪ ምንዛሪ ይዞ ወጥቶ ከሆነ በማስረጃ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ ይሁንና ወደ ወጪ ሀገር የሚወጣ ሰው የወጪ ምንዛር ይዞ ሊወጣ ይችላል በሚል ግምት መሰረት ተደርጎ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችል አይደለም፡፡ በዚሁ ምክንያት የስር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካችን ክርክር ሳይቀበሉት መቅረታቸው ካለአግባብ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

የፍ/ቤት ሥልጣን በተመለከተ የስር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ ያለፉት የአሁን ተጠሪ ከኤየርፖርት ጀምሮ እስከ ዋናው መ/ቤት ድረስ ማመልከቻ የሚቀበለው አጥቶ እንዲያውም ጉዳይህ ለፍ/ቤት የሚቀርብ ነው የተባለ መሆኑ በማስረጃ በማረገገጡ እና አንድ ሰው ፍትህ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብቱን ለማስገበር ጉዳዩ ለፍ/ቤት ክስ ማቅረቡ የፍ/ቤት ሥልጣን አይደለም ሊባል አይችለም በሚል ነው፡፡ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር

859/2006 አንቀጽ 153 እና 155 ከጉምሩክ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ተዘርዝረው፣ ከነዚህ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ለአቤቱታ አጣሪ ቀርቦ በሂደት በይግባኝ ለፍ/ቤት አንደሚቀርብ ይደነግጋል፡፡ ይህ ሆኖ የአሁን ተጠሪ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 153 እና 155 ድንጋጌ መሰረት መብቱን እንዳይጠይቅ አቤቱታውን የሚቀበለው ያላገኘ መሆኑን በስር ማስረጃ በሚሰማውና በሚመዝነው ፍ/ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የኢፌዴሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 37(1) ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችልት በመ/ቁጥር 72420 አንድን ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን የተሰጠው አካል ጉዳዩን ተቀብሎ ለመዳኘት ፍቃደኛ ካልሆነ በፍ/ቤት የሚታይ ጉዳይ የዜጎችን ፍትህ የማግኘት መብት ለማስከበር መደበኛ ፍ/ቤቶች ተቀብሎ ማስተናገድ የሚገባው ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት ይገናል፡፡ በመሆኑም ከዚሁ አንጻር የስር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሳይቀበሉት መቅረታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 279571 ጥቅምት 4 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 99967 ሐምሌ 1 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. ጥቅምት 12 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር130415 ላይ የሰጠው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. ከስር ፍ/ቤት የመጣው መዝገብ በመጣበት ሁኔታ ይመለስ ብለናል፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡
6. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 215098

ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1ኛ. አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 05 አስተዳደር ጽ/ቤት

2ኛ. አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 05 የምግብ ዋስትና ልማት } አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ በለው አድማሱ

2ኛ. ወ/ሮ ቆንጂት ሀብቴ ማህደር

3ኛ. ወ/ሪት ምህረት ፍቃዱ ሁንዴሳ

4ኛ. ተማሪ ሲመሌ ፍቃዱ ሞግዚት ምህረት ፍቃዱ } ጠበቃ ጀማል ሁሴን ቀረቡ

5ኛ. ወ/ሮ ሶስና ፍቃዱ

6ኛ. ሲዲሴ ፍቃዱ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች በቀን 27/01/2014 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ፍርድ በማፅናት በመ/ቁ 275191 በቀን 22/11/2013 ዓ.ም የሰጠው ብይን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልፀው በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ ያደረገ ሲሆን አመልካቾች በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከሳሾች የነበሩ ሲሆን ተጠሪዎች ከሳሾች ነበሩ፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት በአሁን አመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 05 ክልል ውስጥ የቤት ቁጥር 223 እና 233(ለ) የሆኑት የግል ቤቶች ከሌሎች የመንግስት ቤቶች ጋር በአንድ ግቢ ውስጥ ያሉ ሲሆን የአሁን አመልካቾች እኛን ሳያስፈቅዱ ለሚያስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች የጋራ የመጸዳጃ ቤት እሰራለሁ ብሎ የሁከት ተግባር እየፈጠረብን ስለሆነ የተፈጠረው የሁከት እና የኃይል ተግባር እንዲወገድልን ይወሰንልን በማለት አመልክተዋል፡፡የአሁን አመልካቾችም በሰጡት መልስም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ የመንግስት ክፍት ይዞታ ሲሆን መፀዳጃ ቤቱ መገንባቱ ለተጠሪዎች የጤና ጠንቅ የሚፈጥር ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ አይደለም፤የሚገነባው መፀዳጃ ቤት ለቤት ቁጥር 233(ለ) መግቢያና መውጫ የማይከልክል እንዲሁም ለአደጋ ጊዜ ማንኛውንም ተሽከርካሪ ማሳለፍ የሚችል በመሆኑ፤አመልካች በራሱ ይዞታ ላይ የጋራ መፀዳጃ ቤት መገንባቱ የሁከት ተግባር ሊባል ስለማይችል የፈጠርነው የሁከት ተግባር የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በሰጠው ውሳኔም ተጠሪዎች ይዘውት የሚገኙት ይዞታና አመልካቾች የጋራ መፀዳጃ ቤት እየገነቡላቸው ያሉት ግለሰቦች የሚኖሩበት የመንግስት ቤት በአጠቃላይ በፕሮፖርሽን ካርታ ጠቅላላ ይዞታ 570.40 ካሜ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን ማረጋጡን፤በፕሮፖርሽን ካርታ ውስጥ ተካትተው የሚገኙ ይዞታዎች ውስጥ የሚገነቡ አጥርም ሆነ ሌላ ግንባታ ሊከናወን የሚችለው የግንባታ ፈቃድ ተጋሪ የሆኑ ግለሰቦች ለግንባታው ፈቃዳቸውን ሲሰጡ መሆኑን፤ የአሁን ተጠሪዎች መፀዳጃ ቤቱ እንዲገነባ ፈቃዳቸውን የሰጡ ስለመሆኑ የሚያመለክት ግልጽ ማስረጃ ወይንም የፈቃድ መስጫ ሰነድ ሆኖ ተረጋግጦ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ የአሁን አመልካቾች በአሁን ተጠሪዎች ላይ የፈፀሙት የሁከት ተግባር ሊወገድ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በማፅናት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም ለስር ፍርድ ቤት በተጨማሪነት ጉዳዩን ያስረዱልናል ብለን ያሰብናቸውን ሞያዊ ማብራሪያ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.136 መሰረት ከሚመለከታቸው አካለት ማስረጃ እንዲያቀርቡልን ትዕዛዝ እንዲሰጥ የጠየቅነውን የማስረጃ ማስቀረብ የመብት ጥያቄዎች ወደጎን በመተው እንዲሁም ክርክር በተነሳበት ግቢ ውስጥ ያሉትን የመንግስት ቤት

ተከራይተው የሚኖሩ ማህበረሰቦች ለጤናማ ሕይወት አስፈላጊ የሆነ እና አንገብጋቢ የሆነውን የመፀዳጃ ቤት ይገንባልን ጥያቄ ወደጎን በመተው በግቢው ውስጥ የጋራ መፀዳጃ ቤት ሊገነባ አይገባም ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ጉዳዬን ለማስረዳት ይችላሉ ብሎ የቆጠራቸውን ምስክሮች ፍርድ ቤቱ ሳይሰማ የሚገነባው የጋራ መፀዳጃ ቤት በተጠሪዎች ይዞታ ላይ ነው ወይስ በመንግስት የሚለውን ሳያጣራ በደፈናው መፀዳጃ ቤት ግንባታው ሕገ ወጥ ነው ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤አመልካች የሚገነባው መፀዳጃ ቤት በተጠሪዎች ይዞታ ሳይሆን በመንግስት ቦታ ላይ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት አከራካሪው መፀዳጃ ቤት በመንግስት ይዞታ ነው ወይስ በተጠሪዎች ይዞታ፣ ለጤና ችግር ይፈጥራል ወይስ አይፈጥርም መግቢያና መውጫ ይዘጋል ወይስ አይዘጋም የሚለውን ከሚመለከተው አካል ሞያዊ ማብራሪያ ሳይጠይቅ በምትክ ዳኛ ወርዶ ሳያጣራ ግንባታው ሕገ ወጥ ነው ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ያለበት ነው፤ የስር ፍርድ ቤቱ ያቀረብናቸውን ማስረጃ ማለትም ተጠሪዎች ግንባታው እንዲገነባ ነፃ ፈቃድ መስጠታቸውን የሚያስረዳ የቃለ-ጉባኤ ማስረጃ መንፈስ ባለመረዳት እንዲሁም ክርክር በተነሳበት ግቢ ውስጥ የሚገኙ የመንግስት ተከራዮች እንዲሁም ተጠሪዎችንም ጨምሮ ጤናማ ሕይወት እንዲኖራቸው በግቢው ውስጥ የጋራ መፀዳጃ ቤት ግንባታ አስፈላጊ መሆኑ እየታወቀ መፀዳጃ ቤት ሊገነባ አይገባም ሲሉ የፌደራል መጀመሪያ ደረጀ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ እንዲሻርልን በማለት አመልክተዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤት ምንም ዓይነት ማስረጃ እና የባለሙያ ማስረጃ ሳይሰማ አመልካች የሁከት ተግባር ፈጽሟል ሲል የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪዎች በሰጡት መልስም የስር ፍርድ ቤት በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.136 መሰረት ልዩ አዋቂ/ኤክስፐርት/ የመሾም ስልጣን ያለው ቢሆንም የሚሾመው ግን ጉዳዩን ይበልጥ ለማብራራት ወይም ለክርክሩ ውሳኔ አሰጣጥ ጠቃሚ መስሎ በታየው ጊዜ ነው፡፡በአከራካሪው ጉዳይ ላይ የቀረበው መልስና ማስረጃ በቂ ነው ብሎ ካረጋገጠ ተጨማሪ ማጣራት እንዲደረግ ልዩ አዋቂ ወይም ኤክስፐርት ወይም ምትክ ዳኛ መሾም ወይም ተጨማሪ ምስክሮች መጥራት እና መስማት እንዳለበት የሚያስገድድ የሕግ ድንጋጌ አይደለም፡፡ከዚህ አንፃር በስር ፍርድ ቤት ያቀረብነው የሁከት ይወገድልን ክስ በመሆኑ እና አመልካቾችም መልስና ማስረጃዎቻቸውን ያቀረቡ በመሆኑ የቃል ክርክርም ስለተሰማ ከዚህም በላይ ተጨማሪ ማጣራት እና ማስረጃ መስማት አስፈላጊ ሆኖ ስላልተገኘ ውሳኔ መስጠቱ ይህም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መጽናቱ ተገቢ በመሆኑ የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ስለሆነም ውሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች የመልስ መልሳቸውን አላቀረቡም፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡በመሰረቱ

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10(1) እንደተመለከተው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ውስጥ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ በሰበር አይቶ የማረም ነው፡፡በዚህ አግባብም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ሰሚነት ስልጣኑን ተግባራዊ ሲያደርግ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በዋነኝነት መነሻ የሚያደርገው ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ነው፡፡አሁን በያዝነው ጉዳይ ማስረጃን የመስማት፣የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶች በዋነኝነትም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ይዘውት የሚገኙት ይዞታና አመልካቾች የጋራ መፀዳጃ ቤት እየገነቡላቸው ያሉት ግለሰቦች የሚኖሩበት የመንግስት ቤት በአጠቃላይ በፕሮፖርሽን ካርታ ጠቅላላ ይዞታ 570.40 ካሜ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ በግልፅ አመልክቷል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች መሬቱ ተከፍሎ መስጠት ካልተቻለ የተነፃፃሪ የመሬት ድርሻ ይዞታ ካርታ የሚሰጥ መሆኑ በይዞታ አስተዳደር አግልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 12/2004 አንቀፅ 13.1 የተመለከተ ሲሆን አሁን በተያዘው ጉዳይም ከላይ እንደተመለከተው ተጠሪዎችና አመልካቾች የመፀዳጃ ቤት የሚገነቡላቸው ግለሰቦች ለይዞታቸው ያላቸው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ በተነፃፃሪ የተሰጠ ሲሆን በዚህ አግባብ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰጠ ደግሞ በጋራ በግቢው ውስጥ የሚኖሩ ባለይዞታዎች በጋራ ተስማምተው ካልመጡ በተናጠል ለማልማት የማይፈቅድላቸው መሆኑን ከአንቀፅ 13.6 እና ከተነፃፃሪ ካርታ አሰጣጥ አጠቃላይ ግብና አላማ ለመረዳት የሚቻል ሲሆን አሁን በያዝነው ጉዳይም የአሁን ተጠሪዎች መፀዳጃ ቤቱ እንዲገነባ ፈቃዳቸውን የሰጡ ስለመሆኑ የሚያመለክት ግልጽ ማስረጃ ወይንም የፈቃድ መስጫ ሰነድ ሆኖ ተረጋግጦ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩ፣ ቃለጉባኤውም በዚህ አግባብ የሚያረጋግጥ አለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ከመሆኑ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች የተነፃፃሪ ካርታው ተጋሪዎች ፍቃድ ሳይገኝ በአመልካቾች በኩል መፀዳጃ ቤቱን ለመገንባት መንቀሳቀሳቸውን የሁከት ተግባር ነው ማለታቸው የሚነቀፍ ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 291319 ቀን 03/09/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን አመልካቾች በአሁን ተጠሪዎች ላይ የፈፀሙት የሁከት ተግባር ሊወገድ ይገባል በማለት የሰጠው ፍርድ እና ይህንን ፍርድ በማፅናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 275191 በቀን 22/11/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 214803

ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡-

1. አቶ ሁሴን አሊ እንድሪስ
2. አቶ አማን አሊ እንድሪስ
3. ወ/ሮ ፋጡማ አሊ እንድሪስ
4. ወ/ሮ ሳዲያ አሊ እንድሪስ
5. አቶ ኑሩ አሊ እንድሪስ

ጠበቃ ታረቀኝ አለማየሁ ቀርቧል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዘሀራ ዱሌቦ- ከጠበቃ ተስፋዬ ታደሰ ጋር ቀርቧል፡፡

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪ ክርክር የነበረው ንብረቶቹን ከሚቹ ሀጂ አሊ እንድሪስ ጋር አፍርቻለሁ የሚል ሆኖ ንብረቶቹ ከአመልካቾች እናት ጋር የተፈሩ መሆኑ ተረጋግጦ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርቡ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የነበረውን የክርክር ጭብጥ በመለወጥ ንብረቶቹን ሚች ከመጀመሪያ ሚስታቸው ጋር ያፈሯቸው መሆኑ ከተረጋገጠ ቢያንስ ከባል ድርሻ እኩል መካፈል አለብኝ በማለት ያቀረቡትን አዲስ መከራከሪያ ጭብጥ በይግባኝ ደረጃ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት አግኝቶ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሻሉ ሥነ ሥርዓታዊ አለመሆኑን በመቃወም ያቀረቡትን ይግባኝ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ያለበቂ ምክንያት መሰረዙ ስህተት በመሆኑ ጋራዥ ቤቱ ተሸጦ ከተገኘው ገንዘብ ተጠሪ ¼ ድርሻ አላቸው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተሸሮ ለክርክሩ ካወጡት ወጪ እና ኪሳራን ጨምሮ እንዲወሰንላቸው አመልካቾች ጥቅምት 1 ቀን 2014 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት መዝገቡ ለችሎት ሊቀርብ ችሏል።

ጉዳዩ ተጠሪ የሚቹ ሚስት መሆናቸውን እንዲሁም በሰበር ክርክሩ የሌሉት ሌሎች አራት ሰዎች ደግሞ የሚቹ ልጆች ስለሆኑ የሚች ሐጂ አሊ እንድሪስ ሙሳ ውርስ እንዲጣራ ውርስ አጣሪ እንዲሾምላቸው 1ኛ አመልካችን ተጠሪ በማድረግ አቤቱታ አቅርበው 1ኛ አመልካችም ውርሱ ቢጣራ እንዳማይቃወሙ መልስ የሰጡ ሲሆን ፤ ቀሪዎቹ አመልካቾችም የሚቹ ልጆች መሆናቸውን በመግለጽ ጣልቃ ገብተው የውርስ ማጣራት ክርክሩ ተካፋይ ለመሆን ጠይቀው ፍርድ ቤቱም ውርሱ ተጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ ውርሱ ተጣርቶ ሪፖርቱ ቀርቧል። አመልካቾች በሚቹ ስም በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ቁጥሩ 1588 የሆነው ቤት እና በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ቁጥሩ 1577 የሆነው ጋራዥ ቤት ተሸጦ የተገኘው ገንዘብ ሚች አባታቸው ሐጂ አሊ እንድሪስ ከሚቿ እናታቸው ወ/ሮ ዘውድነሽ ጋር በጋራ ያፈሩት ነው በማለት አስተያየታቸውን ስያቀርቡ ተጠሪ ሚች ንብረቱን ያፈሩት ከእሳቸው ጋር መሆኑንና ከሚቹ ጋር በጋብቻ ውስጥ እያሉ በቤት ቁጥር 1588 ላይ ከሁለት ሚልዮን ብር በላይ በማውጣታቸውንና ጋራዥ ቤት ተሸጦ በ1ኛ አመልካች እጅ የሚገኘው የሽያጭ ገንዘብ ግማሹ እንዲሰጣቸው ተከራክረዋል።

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ሚቹ ንብረቶቹን ያፈሩት ከተጠሪ ጋር ነው ወይስ ከአመልካቾች እናት የሚለውን በጭብጥነት ይዞ የግራቀኙን ማስረጃ ሰምቶ መዝገቡን እንደመረመረው በተሰሙት የግራቀኙ የሰው ምስክሮች እና ከቀረበው የሰነድ ማስረጃ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች ሚች ተጠሪን ከማግባታቸው በፊት የተፈሩ መሆኑና ከተጠሪ ጋር ከተጋቡ በኋላ ለውጥ አለመደረጉን ስላስረዱ ሚች አከራካሪዎቹን ንብረቶች ያፈሩት ከአመልካቾቹ እናት ከወ/ሮ ዘውድነሽ ሸዋዬ ጋር እንጅ ከተጠሪ ጋር ባለመሆኑ ተጠሪ ከንብረቱ ድርሻ የላቸውም በማለት የውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ያፀደቀ ሲሆን ፤ ተጠሪ ከሚች ጋር ከ35 ዓመት በለይ ሲኖሩ በንብረቱ ላይ ምንም አስተዋጽኦ እንዳላደረጉ ተቆጥሮ ከንብረቱ ላይ ድርሻ የለሽም መባላቸው ፤ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ የላቸውም ቢባል እንኳን ከሚች ባለቤታቸው ድርሻ ላይ እኩል የመካፈል መብት እያላቸው የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አለመሆኑንና ለ1ኛ አመልካች በሰጡት ውክልና የተሸጠው ንብረት ዋጋ እንዲከፈላቸው አለመደረጉ አግባብነት የለውም በማለት ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ ግራቀኙን አከራክሮ መዝገቡን የመረመረው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤት ቁጥር 1588 ሚች ከቀድሞ ባለቤታቸው ጋር ያፈሩት መሆኑና ከተጠሪ ጋር ከተጋቡ በኋላ የተደረገ ለውጥ አለመኖሩ በተጠሪ ምስክሮች ጭምር ተረጋግጦ የተደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ ነው በማለት ያፀና ሲሆን ፤ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ቁጥሩ 1577 ሆነውን ጋረዥ ሚች በህወት እያሉ 1ኛ አመልካች በውክልና ሽጦ አክስዮንና ቤት ገዝቶ አክስዮኑን 1,450,000.00 (አንድ ሚልዮን አራት መቶ ሃምሳ ሺ) ፤ እንዲሁም የገዙት ቤት 1,800,000.00 (አንድ ሚልዮን ስምት መቶ ሺ) ብር መልሰው መሸጣቸው ስለተረጋገጠ ሚች ሀጂ አሊ እንድሪስ ከቀድ ሚስታቸው ጋር ያፈሩትን ንብረት በውክልና ሲሸጡ ድርሻቸውን የግል ባለማስባላቸው ከአክስዮንና ቤት ሽያጭ የተገኘው ገንዘብ ¼ ወይንም ከሚች ሀጂ አሊ እንድሪስ ግማሽ ድርሻ ላይ 25%

ድርሻ አላቸው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች በውሳኔው ባለመስማማት ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመሰረዙ በፍርዱ መግቢያ ላይ የተመለከተውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር ቅሬታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሥር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልተነሳን ክርክር መሠረት አድርጎ ውሳኔ መስጠቱና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ውሳኔውን የማጽናቱ ሥነ ሥርዓታዊነት መጣራት አለበት በማለቱ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- በውርስ ይጣራልኝ ክርክር ተጠሪ እና ሟች ከ35 ዓመት በላይ አብሮ ሲኖሩ ሟች በህይወት እያሉ የተሸጠው ቤት ገንዘብ ግማሹ ይገባኛል ክርክር አቅርበው ተጠሪዎችም አይገባቸው በማለት ተከራክረው ማስረጃ ተስምቶ ቤቱ መሸጡና በሽያጭ ገንዘቡም ሌላ ንብረት መገዛቱ ተረጋግጦ ለጉዳዩ ተገቢ የሆነው ሕግ እና አስገዳጅነት ያለው የሰበር ውሳኔ ተጠቅሶ ውሳኔ ላይ የተደረሰ እንጅ በይግባኝ ደረጃ የቀረበ አዲስ የክርክር ጭብጥ አለመኖሩን ፤ ተጠሪ ገንዘቡ ይገባኛል ያሉበትን የሕግ አንቀጽ መጥቀስ የግድ ባለመሆኑና የፍርድ ቤት ሥራ ሕግ መተርጎም በመሆኑ የቀረበውን ክርክር መሠረት አድርጎ የሚገባቸው በምን አግባብ እንደሆነና የድርሻቸው መጠን ምንያህል እንደሆነ በጭብጥነት ታይቶ የሚገባቸው ሽያጭ የተገኘው ገንዘብ ¼ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በሥር ፍርድ ቤት የቀረበን ክርክር መሠረት ያደረገ በመሆኑ የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ ሆኖ ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ ተጠሪ ከሟቹ ሀጂ አሊ እንድሪስ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 75(ሀ) መሠረት በሀጂ አሊ እንድሪስ ሞት ምክንያት ስለፈረሰ በአንቀጽ 85 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት የባልና ሚስት ንብረት እንዲጣራ ጠይቀው አመልካቾቹም ቢጣራ እንደማይቃወሙ ገልፀው ንብረቱ ተጣርቶ ሪፖርቱ ቀርቧል፡፡ ተጣርቶ በቀረበው ሪፖርትም ሟች በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ቁጥሩ 1588 የሆነው ቤት እና በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ቁጥሩ 1577 የሆነው ጋራዥ ቤት ከሟች የአመልካቾች እናት ጋር ያፈሩ መሆኑና ሟቹ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ እያሉ በንብረቱ ላይ የተደረገ ማሻሻያ አለመኖሩንና ከሟቹ ህልፈተ ሕይወት በፊት ከተጠሪ ጋር በትዳር ውስጥ እያሉ ጋራዥ ቤቱ ተሸጦ የተገዙት ንብረቶች በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 68 መሠረት ሟች የግል ንብረታቸው መሆኑን ለፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው ሳያስገልሉ በግብይት የተገኙት አክስዮኖችና ቤት ሟችና ተጠሪ ለ1ኛ አመልካች በሰጡት ውክልና ተሸጦ የተገኘው ገንዘብ በ1ኛ አመልካች እጅ መኖሩ መረጋገጡን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ግላዊ ግንኙነት እና ንብረት በኩል ሕጋዊ ውጤትን የሚያስከትል በመሆኑ ሕጋዊ ውጤቱም በተጋቢዎች ስምምነት ወይንም በፍርድ ቤት ውሳኔ እንደምቋጭ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 83 ያመለክታል፡፡ ጋብቻ በንብረት በኩል የሚኖረው ውጤት በቤተሰብ ሕጉ ቁጥር 57 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ሥር ተመላክቷል፡፡ ጋብቻ በሕጉ አግባብ ከፈረሰ በኋላ የጋብቻው መፍረስ በንብረት በኩል

ስለሚኖረው ሕጋዊ ውጤት አስመልክቶ ጋብቻ ሲፈፀም ወይንም በፍቺ ወቅት የተደረገ በሕጉ ተቀባይነት ያለው ውል ካለ በውሉ መሰረት ንብረቱ የሚጣራ ሲሆን ፤ በሕግ ፊት የፀና ውል በሌለ ጊዜ የባልና ሚስት ንብረት በሕጉ አግባብ ተጣርቶ የግል የሆነውን ባለንብረቱ ሲወስድ ፤ የጋራ የሆነው ንብረት በሕጉ አግባብ ከፍፍል የሚደረግ መሆኑን አንቀጽ 86 እና 90 ያመለክታሉ፡፡

የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ የባልና ሚስት የጋራ ከሆነው ንብረት ድርሻቸው እንዲሰጣቸው ሲሆን ተጠሪ ከሚቹ ጋር የጋራ ንብረት ያላቸው መሆኑን ማጣራት እና ድርሻቸውን ለይቶ መወሰን የፍርድ ቤት ድርሻ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ የጋራ ንብረት እንዲጣራ ተጠሪ ጠይቀው ንብረቱ ተጣርቶ ከቀረበ በኋላ በሚቹ ስም በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ቁጥሩ 1588 የሆነው ቤት እና በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ቁጥሩ 1577 የሆነው ጋራዥ ቤት ተሸጦ በ1ኛ አመልካች እጅ የሚገኘው የሽያጭ ገንዘብ ግማሹ እንዲሰጣቸው ከባልና ሚስት የጋራ ንብረት እኩል ለመካፈል ያቀረቡት ዳኝነት ሙሉ በሙሉ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውድቅ ስለሆነ ከሚች ጋር ከ35 ዓመት በለይ ሲኖሩ በንብረቱ ላይ ምንም አስተዋጽኦ እንዳላደረጉ ተቆጥሮ ከንብረቱ ላይ ድርሻ የለሽም መባላቸው እንዲሁም ቀጥተኛ አስተዋጽኦ የላቸውም ቢባል እንኳን ከሚች ባለቤታቸው ድርሻ ላይ እኩል የመካፈል መብት መነፈጋቸውን በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ቅሬታ በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ነው የሚሰኝ ባለመሆኑ ሚች ሀጂ አሊ እንድሪስ ከቀድሞ ሚስታቸው ጋር ያፈሩትን ንብረት በውክልና ሲሸጥ ድርሻቸውን የግል ባለማስባላቸው ከአክስዮንና ቤት ሽያጭ የተገኘው ገንዘብ ¼ ወይንም ከሚች ሀጂ አሊ እንድሪስ ግማሽ ድርሻ ላይ 25% ለአመልካች መወሰኑ በሕጉ አግባብ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ባመሆነሙ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 207281 ሐምሌ 23 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 259328 መጋቢት 27 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፤ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ***ፀንቷል***፡፡
2. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 214796

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመካው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች ፡ የወ/ሮ ሮማን ሙሉጌታ በቀለ ወራሾች፡-

1ኛ. አቶ አብይ ጎሹ

2ኛ. ወ/ሮ ሰብለወንጌል ጎሹ

3ኛ. ወ/ሮ ሙሉመቤት ጎሹ

4ኛ. አቶ እንዳልካቸው ጎሹ

5ኛ. ወ/ሪት ፀደንያ ጎሹ

6ኛ. አቶ ዳንኤል ጎሹ

ተጠሪ ፡ አቶ ማረን ወንደ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ፍርድ

ጉዳዩ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በነሐሴ 10 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ የአመልካቾች እናት በውርስ ባገኙት በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/18 የቤት ቁጥር 649 ላይ ያላቸውን መብት ተከራክሬ እንዳስወስንላቸው በመስከረም 14 ቀን 2002 ዓ.ም የጥብቅና አገልግሎት ስምምነት ከእናታቸው ጋር አድርገናል፡፡ በስምምነታችን መሰረት ተከራክሬ ግምቱ 10,000,000 የሆነ ቤት በአፈጻጸም ተረክበዋል፡፡ ነገር ግን የሚች ወራሾች የሆኑት አመልካቾች የአገልግሎት ክፍያ ለመክፈል ፍቃደኛ ስላልሆኑ ብር 2,000,000 እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች በመጋቢት 10 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ በጠበቆች የሥነ-ምግባር ደንብ ላይ የአገልግሎት ክፍያ ከ10% ሊበልጥ እንደማይገባ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ ያደረጉት ውል ግን 25% የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል የሚል በመሆኑ ውሉ ህገ ወጥ ነው፡፡ ለተጠሪ የጥብቅና አገልግሎት ሊከፈል ይገባል ቢባል እንኳን በጠበቆች ደንብ ላይ ከተቀመጠው የአገልግሎት ክፍያ በላይ መጠየቅ አይችሉም፡፡ ቤቱ አሮጌ በመሆኑ በተጠሪ የተጠቀሰውን ግምት ያክል አያወጣም፡፡ በመሆኑም የቤቱ ትክክለኛ ዋጋ ተገምቶ ተመጣጣኝ ክፍያ እንድንከፍል ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች ተጠሪ የጥብቅና አገልግሎት መስጠታቸውን አልካዱም፡፡ ተጠሪ የቤቱን ግምት 10,000,000 በሚል ያቀረቡ ቢሆንም ግምቱ ይህንን ያክል እንደሚሆን ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ ተጠሪ የጠየቁት ክፍያም በተለምዶ ከሚጠየቀው አንጻር በጣም የተጋነነ ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ ከወሰደው ጊዜ እና ከክርክሩ ውስብስብነት አንጻር 1% ብር 100,000 የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ በቂ ስለሆነ ከ9% ወለድ ጋር አመልካቾች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ ክርክሩ ከአምስት አመት በላይ መውሰዱን እና ውስብስብነት የነበረው መሆኑን የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ አስፍሮ እያለ የጠበቃ አበል የቤቱን ግምት 1% ብቻ መወሰኑ ተጠሪ ለሰጡት አገልግሎት ተመጣጣኝ ሆኖ ስላልተገኘ የቤቱን ግምት 7% ብር 700,000 ከ9% ወለድ ጋር አመልካቾች ሊከፍሉ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሏል፡፡

አመልካቾች በጥቅምት 01 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረቡት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሎ መወሰኑን በመቃወም ለማሳረም ሲሆን የቅሬታው ይዘት፡- በጥብቅና አገልግሎት ውሉ ላይ የአገልግሎት ክፍያ 25% በሚል የተገለጸ በመሆኑ ውሉ ህገ-ወጥ ነው የሚል ክርክር አቅርበን እያለ ውሉ ህገ-ወጥ አይደለም መባሉ፤ የአገልግሎት ክፍያ ውሉ ቤቱ ተሸጦ ከሚገኘው ገንዘብ ላይ ይከፈላል በማለት በግልጽ አስቀምጦ እያለ ከውሉ ውጪ ተጠሪ ባቀረቡት የቤት

ግምት 7% እንድንከፍል የአመልካቾች ማስረጃ ሳይሰማ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ቤቱ በህጋዊ ባለሙያ ተገምቶ ተገቢውን የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ እንድንከፍል ይወሰንልን የሚል ነው።

የአመልካቾች የሰበር ቅሬታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ለክርክር መነሻ የሆነውን ቤት ግምት በገለልተኛ ባለሙያ ሳይገመት ተጠሪ 10,000,000 በሚል ባቀረቡት ግምት የጠበቃ አበል የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጥቷል።

ተጠሪ በጥር 04 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ የጥብቅና አገልግሎት የክፍያ መጠን በስምምነት የሚወሰን በመሆኑ 25% ክፍያ መስማማታችን ውሉን ህገ-ወጥ አያደርገውም። ቤቱ ካርታ የሌለው በመሆኑ ቤቱ ከሚገኝበት ክፍለ ከተማ የቤቱን ግምት ማግኘት ስለማይቻል ቤቱ የሚገኝበትን አከባቢ፣ የቤቱን እና ቦታውን ስፋት እንዲሁም የቤቱን ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ግምት ውስጥ በማስገባት ክሱ የቀረበ በመሆኑ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክርክሩ ከወሰደው ጊዜ እና ተጠሪ ከሰጠሁት አገልግሎት አንጻር 7% አመልካቾች እንዲከፍሉ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ ህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል።

አመልካቾችም በጥር 17 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታቸውን አጠናክረዋል።

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ፤ በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነው ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ለአመልካቾች እናት ለሰጡት የጥብቅና አገልግሎት ከእናታቸው ጋር በተደረገ የጥብቅና አገልግሎት ውል ላይ የተመለከተው የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈላቸው ነው። አመልካቾች ለሟች እናታቸው ተጠሪ ጥብቅና አገልግሎት መስጠታቸውን ሳይክዱ በውሉ ላይ የክፍያ መጠን 25% በሚል ስምምነት መደረጉ ውሉን ህገ-ወጥ ያደርገዋል። እንዲሁም ተጠሪ ተከራክረው ያስወሰኑት ቤት ግምት ተጋኖ የቀረበ በመሆኑ የቤቱ ግምት ከታወቀ በኋላ ተመጣጣኝ ክፍያ እንድንከፍል ይወሰንልን የሚል ነው። በመሆኑም በመጀመሪያ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ የጥብቅና ውሉ ላይ የክፍያ መጠን 25% መባሉ ውሉን ሕገ-ወጥ ያደርገዋል ወይስ አያደርገውም? የሚለው ይሆናል።

እንደሚታወቀው ውል ማለት ተዋዋይ ወገኖች በሚኖራቸው ግንኙነት አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ግዴታ የሚገቡበት መሆኑን የፍ/ሕ/ቁጥር 1675 ያመለክታል። ተዋዋይ ወገኖች አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ግዴታ ሲገቡ ሊሟሉ የሚገባቸው ነገሮች በፍ/ሕ/ቁጥር 1678 ላይ የተመለከቱ ሲሆን እነዚህም የተዋዋይ ወገኖች ችሎታ መኖር፤ የውሉ ጉዳይ ህጋዊ መሆን እና ውሉ በህግ የተመለከተውን የአጻጻፍ ስርአት/ፎርም የተከተለ መሆን ናቸው። አንድ ውል እነዚህን መስፈርቶች አሟልቶ ካልተገኘ ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም። በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ውሉ ህጋዊ አይደለም በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም በተጠሪ እና በአመልካቾች መካከል የተደረገው የጥብቅና አገልግሎት ውል የፈቃድ

ጉድለት ያለበት ስለመሆኑ በማስረጃ አስደግፈው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ የውሉን ጉዳይም በፍ/ሕ/ቁጥር 1711 መሰረት በህግ የተከለከለ እስካልሆነ ድረስ ተዋዋዮች የመወሰን ነጻነት አላቸው፡፡ በዚህም መሰረት የጥብቅና አገልግሎት ውል መዋዋል በህግ ያልተከለከለ እና ክፍያ መጠን ጣሪያ በልምድ ከሚሰራበት ውጪ በህግ ያልተገደበ በመሆኑ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ 25% በሚል ውሉ ላይ መገለጹ ውሉን ህገ-ወጥ ሊያደርገው አይችልም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ጥብቅና አገልግሎት ውሉ ህገ-ወጥ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ መደረጉን ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመቀጠል በክፍያ መጠን ላይ የተነሳውን ክርክር ስንመለከት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል ሙያዊ አገልግሎትን ወይም የእውቀት ስራን የሚመለከት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት የሚኖራቸው በፍትሐ ብሔር ህጉ አምስተኛ መጽሐፍ አራተኛ ምእራፍ ስር ከአንቀጽ 2632 ጀምሮ ስለ እውቀት ስራ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ ተዋዋይ ወገኖች በነጻ ፈቃድ የመዋዋል መስፈርትን አሟልተው የእውቀት ስራ ውልን ቢዋዋሉም እንኳን ከውሉ ልዩ ባህሪ አንጻር የክፍያው መጠን ወይም የስራው ዋጋ የተጋነነ መሆኑ ግልጽ ከሆነ እና ለሙያው ክብር ተቃራኒ ሆኖ ከተገኘ ስምምነት የተደረገበትን የክፍያ መጠን ዳኞች ሊቀንሱ እንደሚችሉ በፍ/ሕ/ቁጥር 2635 ላይ ተመልክቷል፡፡ የዚህ ድንጋጌ አላማ ባለሙያው የሙያውን ተፈላጊነት እና የሙያ ስራው ተጠቃሚ ሌላ አማራጭ የለውም በሚል እምነት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ከሚያገኘው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነን ክፍያን እንዳያስከፍል ለመከላከል እና የሙያ ክብርን ለመጠበቅ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 17191 (በቅጽ 1 የታተመ) የህግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ለሚሰጡት የጥብቅና አገልግሎት ለክርክሩ መሰረት የሆነውን ቤት ዋጋ 25% እንዲከፈላቸው መስማማታቸው በግራ ቀኙ የታመነ ነው፡፡ የአመልካቾች እናት እና ተጠሪ ባላቸው የመዋዋል ነጻነት በክፍያ መጠኑ ላይ ተስማምተው ውሉን ያደረጉ ቢሆንም እንኳን ከላይ እንደተገለጸው ክፍያው የተጋነነ ሆኖ ከተገኘ መቀነስ የፍርድ ቤቶች ስልጣን ነው፡፡ በልማድ የዳበረው የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ጣሪያው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት ወይም ገንዘብ 10% እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ክርክሩ የወሰደውን ጊዜ እና የጉዳዩን ውስብስብነት ከግምት በማስገባት በጥብቅና አገልግሎት የተመለከተውን 25% ወደ 7% ዝቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ይሁን እንጂ ለተጠሪ የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት ምክንያት በሆነው ቤት ግምት ላይ ግራ ቀኙ ተካክደዋል፡፡ ተጠሪ የቤቱ ግምት 10,000,000 በሚል ያቀረቡትን አመልካቾች በመቃወም ቤቱ በባለሙያ እንዲገመትላቸው ጠይቀዋል፡፡ ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥ/ሥ/ሕጉ አላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነት መፈለግ፤ ስነስርአታዊ ፍትህ፤ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጪ እና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ በመሆኑም በቤቱ ግምት ላይ ክርክር እስከቀረበ ድረስ የስር ፍርድ ቤቶች በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ አንቀጽ 246 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት ጭብጥ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ይዘው ግምቱን በማስረጃ ሊያጣሩ ሲገባ ግምቱን በማስረጃ ሳያጣሩ በተጠሪ በቀረበው ግምት ተመስርተው ውሳኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የክርክር አመራር ግድፈት ነው፡፡

ሲጠቃለል ለተጠየቀው የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ለክርክሩ መሰረት የሆነውን ቤት ተጠሪ የአመልካቾችን እናት ወክለው የውርስ ክርክር ባደረጉበት መዝገብ ላይ ተገምቶ ከሆነ ያንን ግምት መሰረት በማድረግ በመዝገቡ ላይ ያልተገመተ ከሆነ ደግሞ የጥብቅና አገልግሎት ውሉ በተደረገበት 2002 ዓ.ም የነበረው የቤቱ የገበያ ዋጋ በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ ማድረግ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ሆኖ እያለ በማስረጃ የተደገፈ የቤቱ ግምት ሳይታወቅ ተጠሪ ባቀረቡት ግምት መወሰኑ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1ኛ. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 241852 በጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 200411 በሐምሌ 20 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ. የፌደራል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጠሪ የቀረበውን የቤት ግምት መሰረት በማድረግ የወሰኑት የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ተሽሯል፡፡

3ኛ. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ አንቀሳቅሶ ተጠሪ የውርስ ንብረት ክርክር ባደረጉበት መዝገብ ላይ ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት ተገምቶ ከነበረ ከመዝገቡ ላይ ግምቱን በማጣራት በመዝገቡ ላይ የቤቱ ግምት ከሌለ ግን የጥብቅና አገልግሎት ውሉ በተደረገበት 2002 ዓ.ም በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/18 የቤት ቁጥር 649 የሆነውን ቤት የገበያ ዋጋ በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ በማድረግ በሚቀርበው ግምት መሰረት ተገቢውን የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 343/1 መሰረት ተመልሶለታል፡፡

4ኛ በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ትእዛዝ

በዚህ መዝገብ ታህሳስ 08 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መዝገቡ ተዘግቷልᎁ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ን

የሰ/መ/ቁጥር 214756

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች የኢትዮጵያ ኤርፖርት ጎንደር አዬ ቱወድሮስ ኤርፖርት አስተዳደርነ/ፈግደይ አስገዶምቀረቡ

ተጠሪ ፡ አዘዞ ጠዳ ክፍለ ከተማ የገቢዎች ጽህፈት ቤት ዐ/ሕግ መላኩ ጥላሁን ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የቦታ አገልግሎት ግብርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በጎንደር ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በሚያዝያ 19 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ክስ ከ2000-2012 ዓ.ም አመልካች ለአውሮፕላን ማረፊያነት እና ለቢሮ አገልግሎት ለተጠቀመው ስፋቱ 2,343,162 ካሬ ሜትር ለሆነ ቦታ ግብር ብር 97,584,125.76 እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡ አመልካችም በግንቦት 15 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ በተጠሪ የተጠየቀውን ግብር የምከፍልበት የህግ አግባብ ስለሌለ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም በመመሪያ ቁጥር 7/2006 መሰረት አመልካች ግብር እንዲከፍል በተጠሪ መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ አመልካች ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ

ውሳኔ ላይ አመልካች ለይግባኝ ሰሚ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ምንም እንኳን አመልካች የፌደራል መንግስት የልማት ድርጅት ቢሆንም ቦታው የሚገኝበት አከባቢ የሚገኘው የግብር ሰብሳቢ አካል ግብር የመሰብሰብ ስልጣን ስላለው፤ በጉዳዩ አከባቢያዊ ባህሪ ምክንያት እና በተመሳሳይ ጉዳይ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 196996 ላይ በሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት የከተማ ነክ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው፡፡ አመልካች የ10 ዓመት የቦታ ግብር ተወስኖ የተነገረው በ2012 ዓ.ም በመሆኑ ቅጣት እና ወለድ ሊከፍል አይገባም፡፡ አመልካች ሊከፍል የሚገባው ዋናውን የግብር እዳ ብር 48,533,326.26 ብቻ ሊሆን ይገባል በማለት የስር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች በመስከረም 28 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረበው ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ሲሆን የቅሬታው ይዘት አመልካች የፌደራል መንግስት አካል የሆነ የልማት ድርጅት በመሆኑ ጉዳዩን የፌደራል ጉዳይ ስለሚያደርገው የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ስልጣን ላቸውም፡፡ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 196996 የሰጠው የህግ ትርጉም በሰባት ዳኛ ሊቀየር ይገባል፡፡ በአየር ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 111/69 መሰረት አመልካች መሬት በነጻ የመጠቀም መብት አለው፡፡ ይህ የአመልካች መሬት በነጻ የመጠቀም መብት በመንግሰት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/84 ላይም የተጠበቀ ነው፡፡ አመልካች ግብር የመክፈል ኃላፊነት አለበት ቢባል እንኳን ለደህንነት መጠበቂያ በሚል ነጻ ለሚደረጉ አከባቢዎች ግብር የመክፈል ግዴታ የለብኝም የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር ቅሬታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች የቦታ አገልግሎት ኪራይ እንዲከፍል የተወሰነበትን አግባብነት ከአየር ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 111/1969 እና የመንግስት ልማት ድርጅት አዋጅ ቁጥር 25/84 እንደዚሁም ከሌሌች አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በጥቅምት 02 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ በኢ.ፌ.ድ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 52 ክልሎች የከተማ ቦታ ኪራይ እና የአገልግሎት ክፍያ ወስኖ የመሰብሰብ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች በመመሪያ ቁጥር 7/2006 አግባብ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል መጠየቁ ተገቢ ነው፡፡ የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶችም ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለቸው ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 196996 የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ይህ ትርጉም በሰባት ዳኛ የሚቀየርበትም ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካችም በህዳር 27 ቀን የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታውን አጠናክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የስር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው ወይስ የለውም? አመልካች በተጠሪ የተጠየቀውን የቦታ አገልግሎት ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት አለበት

ወይስ የለበትም? የሚሉትን ነጥቦች ከግራ ቀኙ ክርክር፤ በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች የፌደራል መንግስት ልማት ድርጅት አካል ስለሆንኩ ጉዳዩን የከተማ ነክ ፍርድ ቤት የማየት ስልጣን የለውም፤ የቦታ ግብርም/የአገልግሎት ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከር ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ጉዳዩን የከተማ ነክ ፍርድ ቤት የማየት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ በፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ አመልካች ለተጠቀመበት ቦታ ግብር የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ተከራክሯል፡፡

በመጀመሪያ ጉዳዩ የተጀመረበት ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ስንመለከት ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው አመልካች በጎንደር ከተማ ውስጥ ለተገለገለበት የቦታ ኪራይ እና የከተማ አገልግሎት ክፍያ ለማስከፈል ነው፡፡አመልካች ደግሞ የፌዴራል መንግስት አካል የሆነ የልማት ድርጅት እንደሆነ በግልጽ የሚታወቅ ነው፡፡ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/1 ስር እንደተደነገገው የፌዴራል መንግስቱ አካል ተከራካሪ በሆነበት ጉዳይ ላይ የመዳኘት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 50/4 ስር እንደተደነገገው ክልሎች አስፈላጊ ሆነው የሚያገኙአቸውን የአስተዳደር እርከኖች የማዋቀር ስልጣን አላቸው፡፡ እንዲሁም በክልል ደረጃ የሕግ አውጪነት፣የሕግ አስፈጻሚነትና የዳኝነት ሥልጣን ኖሯቸው በክልል ጉዳዮቻቸው ላይ ሕግ በማውጣት፣በማስፈጸምና የክልል ጉዳዮችን በክልል የዳኝነት አካል እንዲታይ የማድረግ ሥልጣን እንዳላቸውና የፌዴራል መንግስት ይህንን የክልሎችን ሥልጣን ማክበር እንዳለበት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(2፣5-8) ስር ከተደነገገው መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት ክልሎች ሕግ ከሚያወጡበት፣ ከሚያስፈጽሙበትና በዳኝነት እንዲታይ ሊያደርጉ ከሚችሉበት ጉዳዮች መካከል አንዱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 52(1 እና 2/ሠ) መሰረት ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ ክልል ውስጥ ሆኖ ግብር እና ታክስ እንዲሁም የከተማ ቦታ ኪራይ እና አገልግሎት ክፍያ በሕግ መጣልና መሰብሰብ የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ክልላዊ ጉዳዮች ስለሆኑ በክልል ደረጃ በሚቋቋሙ መደበኛም ሆነ የከተማ ነክ ጉዳዮችን ብቻ እንዲዳኙ በተቋቋሙ ፍርድ ቤቶች እንዲዳኙ ለማድረግ የሚችሉ የፍርድ ቤቶችን አደረጃጀት፣ ስልጣን እና ተግባራቸውን ከፋፍሎ በክልል ሕግ የመወሰን ጉዳይ በተጠቃሾቹ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች ለክልል መንግስታት የተፈቀደና የተተው ሥልጣንና ተግባራት ናቸው፡፡

ከላይ ከተመለከተው አንጻር የያዝነውን ጉዳይ ስንመለከት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት የክልሉን ከተሞች እንደገና ማቋቋሚያ፣ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 91/1996 አንቀጽ 54 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች(በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 245/2009 አንቀጽ 76 እና ተከታዮቹ ላይ ሁለት እርከኖች ያሉትን የከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚ ከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤት አቋቁሟል፤ ሥልጣናቸውንም ወስኗል፡፡ በዚህ መሰረት ለተቋቋሙ ፍርድ ቤቶች ከተሰጡ

ሥልጣኖች ዉስጥ አንዱ በአዋጅ ቁጥር 91/1996 አንቀጽ 57/3 እና በተሻሻለዉ አዋጅ ቁጥር 245/2009 አንቀጽ 79(1/ረ) ስር እንደተደነገገዉ የማዘጋጃ ቤት ግብር፣ቀረጥና የአገልግሎት ክፍያዎችን አወሳሰንና አሰባሰብ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የአካባቢና የሥረ ነገር ዳኝነት ስልጣን እንዳላቸዉ የተመለከተዉ ነዉ።በዚህ መልኩ የተቋቋሙት የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤቶች መደበኛ ፍርድ ቤቶች ስላልሆኑ በተጠቃሾቹ ሕጎች ተዘርዝረዉ በተሰጣቸዉ ከተማ ነክ ጉዳዮች ላይ የተከራካሪ ወገኖች ማንነት ከግምት ሳይገባ የመዳኘት ስልጣን እንዳላቸዉ ከተቋቋሙበት ዓላማ አንጻር በማየት መገንዘብ ይቻላል።በያዝነዉ ጉዳይም በክሱ አመልካች እንዲከፍል የተጠየቀዉ የቦታ ኪራይና የከተማ ነክ(የማዘጋጃ ቤት) አገልግሎት ክፍያዎች ጉዳይ የከተማ ነክ ጉዳይን የሚመለከት በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ ፀንቶ ባለዉ የአማራ ክልል አዋጅ ቁጥር 245/2009 አንቀጽ 79(1/ረ) መሰረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን የመዳኘት ሥልጣን ያለዉ የጎንደር ከተማ አስተዳደር ከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንጂ የክልል መደበኛ ፍርድ ቤት አይደለም።

በኢ.ፌ.ደ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 ላይ የፌዴራል ጉዳዮችን የክልል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በዉክልና ሥልጣን ማየት ስለሚችሉበት ሁኔታ ተደንግጓል። ይህም የሚመለከተዉ የክልል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች(መደበኛ ፍርድ ቤቶች) እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ጣምራ ሥልጣን እንጂ ከዚህ ዉጭ ያሉ በልዩ ሁኔታ በክልል መንግስታት የሚደራጁ ከተማ ነክ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ፍርድ ቤቶችን አይደለም። ምንም እንኳን አመልካች የፌዴራል መንግስት አካል የሆነ የልማት ድርጅት መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ክስ የቀረበበት ጉዳይ በክልሉ ሕግ በተወሰነዉ መሰረት ከተማ ነክ ጉዳይ በመሆኑ በክልሉ መደበኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን የሚታይ ባለመሆኑና የጉዳዩም ስረ ነገር የክልል ጉዳይን የሚመለከት ስለሆነ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/1 እና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ስር የተደነገገዉን የፍርድ ቤቶች የጣምራነት ሥልጣን መሰረት በማድረግ ጉዳዩ መታየት ያለበት በፌዴራል ፍርድ ቤት ሊሆን ይገባል ሲል ያቀረበዉ መከራከሪያ ተቀባይነት በማጣቱ የተፈጸመ ስህተት የለም።

የክልል ከተማ ነክ ፍርድ ቤት በዚህ መዝገብ የተያዘውን አይነት ጉዳይ አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው መሆኑን ቀደም ሲል በሰበር መዝገብ ቁጥር 196996 ላይ የህግ ትርጉም የተሰጠበት ሲሆን አመልካች ይህ ትርጉም በሰባት ዳኛ ሊቀየር ይገባል በሚል የሰበር ቅሬታው ላይ ጠቅሷል። በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26 ቀድሞ የተሰጠ የሰበር ውሳኔ በሰባት ዳኛ ሊቀየር የሚችልበትን ሁኔታ የሚያመለክት ሲሆን ለመቀየር ወይም ለማሻሻል በቂ ምክንያት ሊኖር እንደሚገባም ተመልክቷል። ይህ ችሎት ከላይ እንደተገለጸው ጉዳዩን የከተማ ነክ ችሎት የማየት ስልጣን አለው የሚል እምነት ስላለው ውሳኔው በሰባት ዳኛ የሚቀየርበት ምክንያት አላገኘንም። በመሆኑም ጉዳዩ የአመልካች ማንነት ከግምት ሳይገባ በጎንደር ከተማ አስተዳደር ከተማ ነክ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መታየቱ ተገቢ ነዉ ብለናል።

በመቀጠል አመልካች የቦታ አገልግሎት ክፍያ ወይም የቦታ ኪራይ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? የሚለውን ስንመለከት አመልካች ከስር የከተማ ነክ ፍርድ ቤት ጀምሮ የቦታ ኪራይ ወይም የአገልግሎት ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በሚል የተከራከረ መሆኑን የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ነገር ግን አመልካች ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ ጭብጥ ተይዞ የተሰጠ ውሳኔ የለም፡፡ ከስር ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ የተጠየቀውን ክፍያ ወስኖ ማስከፈል ይችላላል ወይስ አይችልም ከሚለው አንጻር ብቻ ጉዳዩ መታየቱን ነው፡፡ ተጠሪ እንደ አጠቃላይ ግብር እና የአገልግሎት ክፍያዎችን የመወሰን ስልጣን የተሰጠው መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ነገር ግን ተጠሪ የመወሰን ስልጣን ቢኖረውም አግባብነት ባለው ህግ ይህንን ግብር ወይም የአገልግሎት ክፍያ ከመክፈል ነጻ የሆኑ አካላት ካሉ እና ክርክር ከተነሳ ተጠሪ ወስኖ የመሰብሰብ ስልጣን ቢኖረውም የተወሰነባቸው አካላትም የመክፈል ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ ሊጣራ ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት የስር ፍርድ ቤቶች እንደ አመልካች የክርክር አቀራረብ አመልካች የተጠየቀውን ግብር ከመክፈል በህግ ከኃላፊነት ነጻ ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የሰጡት ውሳኔ የለም፡፡ እንደሚታወቀው የፍትሐ ብሔር ክርክሮች የሚመሩት የፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ የዘረጋውን ስርአት በመከተል ነው፡፡ ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥ/ሥ/ሕጉ አላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነት መፈለግ፤ ስነስርአታዊ ፍትህ፤ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጪ እና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠየቀው የግብር እዳ ኃላፊ አለመሆኑን ክርክር እስካቀረበ ድረስ የስር ፍርድ ቤቶች በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ አንቀጽ 246 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት ጭብጥ ይዘው የአመልካችን ኃላፊነት ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ ውሳኔ ሊሰጡ ሲገባ ከአመልካች ኃላፊነት አንጻር ጭበጥ ይዘው ሳይመረምሩ እንዲከፍል ውሳኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የክርክር አመራር ግድፈት ስለሆነ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1ኛ. የጎንደር ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12485 በሐምሌ 10 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የጎንደር ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01277 በሐምሌ 2012 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 97925 በሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ. የጎንደር ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ አንቀሳቅሶ አመልካች በተጠሪ የተወሰነበትን ግብር የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? ማለትም አመልካች የተወሰነውን የቦታ መጠቀሚያ ኪራይ/ግብር እንዳይከፍል በህግ ነጻ ተደርጓል ወይስ አልተደረገም? የሚለውን ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምሮ አመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለበት የሚል ከሆነ በክፍያው መጠን ላይ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1 መሰረት ተመልሶለታል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

3ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገው ክርክር ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።

<u>ትእዛዝ</u>

በዚህ መዝገብ በጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል። ይጻፍ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

አ/መ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት**

የሰ/መ/ቁጥር 214738

ሚያዝያ 26 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ኑርሁሴን ሙደሲር

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ባህሩ አራርሶ

2. ወ/ሮ አስቴር አራርሶ

3. የአቶ ወርቁ ነገዎ ወራሾች

1.ወ/ሪት ራሂል ወርቁ

2.ወ/ሪት መዓዛ ወርቁ

3.አቶ ሮቤል ወርቁ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻው አመልካች መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.198456 በ30/10/2013 ዓም በዋለው ችሎት የፌደራል ከፍተኛ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ፍርድ ቤት በመ/ቁ.154391 የሰጠውን ትዕዛዝ በማሻሻል የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይኸው ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡

በግራ ቀኙ መሃል ያለው የሰበር ክርክር የአፈፃፀም ጉዳይን መሰረት ያደረገ ሲሆን የጉዳዩን አመጣጥ ስንመለከተውም በኮ/ቀ/ክ/ከ/ወረዳ 05 የሚገኘው የቤት ቁጥር 359 የሆነው በሟች ወ/ሮ ብርሌ መስቀሌ ስም ያለ ቤት ላይ የተሰጠውን የውርስ ሀብት ክፍፍል ለማስፈፀም አከራካሪው ቤት በጨረታ ሲሸጥ አመልካች ጨረታውን አሸንፈው የገዙ ሲሆን፤በጨረታ ማስታወቂያው ላይ የተመለከተው የቤቱ ስፋት 360 ካሜ የነበረ ቢሆንም ቤቱን ለአመልካች ለማስረከብ ሲለካ 642 ካሜ ሆኖ በመገኘቱ የአፈፃፀም ዳይሬክቶሬቱ ርክክቡ የሚፈፀምበትን አግባብ አስመልክቶ ማብራሪያ ፍርድ ቤቱን የጠየቀ ሲሆን ፍርድ ቤቱም አመልካች ቤቱን ሲገዙ በአካል አይተው መግዛታቸውን፤ዋናው ነጥብ ውሳኔው የተሰጠው በቤት ቁጥር 359 ላይ በመሆኑን፤ይዞታው ሰነድ አልባ በመሆኑ ሊፈፀም የሚገባው በሁሉም የቤቱ ይዞታ እንጂ በጂአይኤስ ግምታዊ ልኬት ሊሆን አይገባም በማለት በልኬት በተገኘው ሙሉ ይዞታ ላይ ርክክቡ ሊፈፀም ይገባል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በዚህ ትዕዛዝ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ፍርድም በጨረታ ማስታወቂያው ላይ በጂአይኤስ ልኬት 360 ካሜ ላይ ያረፈ ቤት እንደሚሸጥ ተጠቅሶ የሀራጅ ማስታወቂያው የወጣ መሆኑን፤አመልካች ተወዳድረው ሊገዙ የሚመጡትም በጨረታ ሰነዱ የተመለከተውን ይዞታ መሆኑን፤በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.423 አመልካች ስለ ንብረቱ ጉብኝት የሚያደርጉት በጨረታ ማስተወቂያው ላይ የተመለከቱትን ነጥቦች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንጂ በጨረታ ማስታወቂያው ላይ ያልተካተቱትን ነገሮች ለማካተት አለመሆኑን በመጥቀስ ሊረከቡ የሚገባው በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለፀው አግባብ ሊሆን ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤትን ትዕዛዝ በማሻሻል ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከቤት ቁጥር 359 ውጪ ያለው የቤት ቁጥር 360 የእነሱ መሆኑን ጠቅሰው በስር ፍርድ ቤት ቢከራከሩም በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በኮሚቴ ተጣርቶ በቀረበው ምላሽ የቤት ቁጥር 359 በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እጅ የሚገኝ የቤት ቁጥር 360 ደግሞ የዕርዳታ ማስተባበሪያ መሆኑ የተረጋጠ ሲሆን፤ተጠሪዎች ሲከራከሩበት የነበረው የቤት ቁጥር 359 በወ/ሮ ብርሌ መስቀሌ ስም የተመዘገበ ሆኖ ዋና ቤትና ሰርቪስ ቤቶች የያዘ የውርስ ሀብት ሆኖ እያለ የይዞታው ስፋት 360 ካሜ መሆኑ በክፍለ ከተማው ባልተረጋገጠበት፤ከክፍለ ከተማው የተሰጠው ምላሽ ቦታው ካርታ ያልወጣለት የሰነድ አልባ ይዞታ በመሆኑ የይዞታውን ስፋት መግለፅ የማይቻል መሆኑን የሚያመለክት ቢሆንም ካድስተር ቢል ቅፅ 008 የሚያሳየው የቦታው ስፋት ልኬት 642 ካሜ ሆኖ እያለ፤1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት በነበራቸው ክርክር 322 ካሜ የሆነው ይዞታ በወ/ሮ ጅፋር ነገሎ እና አቶ አሰፋ ነገሎ ይዞታ ስር የነበረ መሆኑንና ወላጅ እናታቸው በሰነድ አልባ ይዞታነት ከ1987 ዓም በፊት ይዘውት እንደነበረ

ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃ በሌለበት ለ642 ካሜ ይዞታው ወ/ሮ ብርሌ መስቀሌ ግብር ሲከፍሉበት የነበረ ለመሆኑ የግብር ደረሰኞቹ እያረጋገጡ፣የመኖሪያ ቤቱ ሙሉ ግቢ ዋና ቤትና ሰርቪስ ቤት ያለው መሆኑ፣ሰርቪስ ቤት 1ኛ ተጠሪ የሰሩት ወጪው ከውርስ ሀብት ሽያጭ ላይ ተመላሽ እንዲሆን ተደርጎ እያለ በሃራጅ ሂደቱ ሙሉ ግቢው ዋናው ቤት እና ሰርቪስ ቤቶቹ በአመልካች ሲገበኙ ተጠሪዎች ሳይቃወሙ ሂደቱ ተፈፅሞ እያለ እነዚህ አጠቃላይ ሁኔታዎች በሽያጭ የተላለፈው አጠቃላዩ 642 ካሜ መሆኑን እያሳየ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ አመልካች ሊረከቡ የሚገባው በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለፀው አግባብ ሊሆን ይገባል በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው ሊሻር ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡

አከራካሪው ቤት ያረፈበት ይዞታ ሰነድ አልባ ሆኖ አመልካች ቤቱን በጨረታ ከገዙ በኋላ አጠቃላይ ይዞታው ተለክቶ 680 ካሜ የሆነውን አመልካች ሊረከቡ አይገባም ሊረከቡ የሚገባው በጂአይኤስ ላይ ያለውን 360 ካሜ ሊሆን ይገባል በማለት የተወሰነበትን አግባብ ከዋናው ውሳኔ ይዘትና መሰረታዊ የክርክር አመራር መርሆዎች አንፃር በማገናዘብ ለመመርመር የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ለተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው መልሳቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የካቲት 14 ቀን 2014 ዓም በተፃፈ መልሳቸውም ለሽያጩ የጋዜጣ ማስታወቂያ ሲወጣ የቦታው ስፋት በአግባቡ ተገልፆ ማስታወቂያው የወጣ ሲሆን አመልካችም ይህንኑ አይተው ቦታው ድረስ በመሄድ የመስክ ጉብኝት አድርገው አጠቃላይ ስፋቱ 360 ካሜ የሆነውን ይዞታ የገዙ ስለሆነ፣በጉብኝቱ ወቅት አመልካች አሁን ካልወሰድኩት የሚሉት 320 ካሜ ቦታ ለብቻው በአጥር ተለይቶ የተቀመጠ በመሆኑ ይህ ይዞታ በተጠሪዎች ወላጅ እናት ወይዘሮ ጅፋሬ ነገዎ ስም የተመዘገበ የቤት ቁጥር 359 እንደ ካደስተር ቢል፣የመብራትና የውሀ ቢሎች ያሉት ሲሆን የወ/ሮ ብርሌ መስቀሌ ይዞታ ደግሞ የተመዘገበ ይዞታም ሆነ ሰነድ እንደሌለው በክፍለ ከተማው ተረጋግጦ እያለ ፣በርክክቡ ሂደት ሲጣራም በቅፅ 008 በካደስተር ቢል ተመዝግቦ የሚገኘው በወ/ሮ ጅፋሬ ነገዎ እና አሰፋ ነገዎ ስም መሆኑ በምላሹ የተረጋገጠ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የ3ኛ ተጠሪ ወራሾች ባቀረቡት መልስም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችና በአፈፃፀም ክርክሩ ያልተካተትን ጨምሮ በድምሩ 12 ሰዎች ከውርስ ሃብቱ ያላቸው ድርሻ 1/3ኛ ብቻ ቢሆንም የውርስ ድርሻውን በመያዝ እየተጠቀሙ ያሉት እነሱ ስለሆነ በተለያየ ጊዜ አዲስ ክርክር በማቅረብ ጉዳዩን በማወሳሰብ ቀጠሮ የማራዘም ስራ ሲሰሩ የቆዩ ሲሆን መሃንዲስ ሊለካ ሲመጣ በመከልከል፣ሌላ ጊዜ ደግሞ የተወሰነውን ቤት ለይተው በማጠር መሃንዲሶችን ግራ እያጋቡ የይዞታው ትክክለኛ ልኬት እንዳይገኝ ጥረት ሲያደርጉ የቆዩ ሲሆን በውሳኔው ላይ የይዞታው ልክ ስላልተመለከተ ለሀራጅ ሽያጩ እንዲረዳ ልኬት ሲደረግ ክፍለ ከተማው ባለሙያዎችን ልኮ ከተደጋጋሚ ጥረት በኋላ ስፋቱ 360 ካሜ መሆኑን የገለፀ ሰሆን ጨረታው በወጣበት ወቅት ተጫራቾች የቤት ቁጥር 360 ሙሉ ግቢና ቤቶችን የጎበኙ ሲሆን ይህ የተጎበኘው ቦታም ስፋቱ 360 ካሜ ሳይሆን 680 ካሜ በመሆኑ በልኬት የተረጋገጠ

በመሆኑ፣ተጠሪዎች ይዞታው የጁፋሬ ነገዎ እና አሰፋ ነገዎ ለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ ስለሌለ የተሸጠው አጠቃላይ ግቢው በመሆኑ አመልካች ተረክበው የሽያጭ ገንዘቡን ድርሻችንን እንድንወስድ ይወሰንልን፣አመልካች ሊረከቡ የሚገባው 360 ካሜ ይዞታ ብቻ ነው የሚባል ከሆነም ቀሪ 320 ካሜ ይዞታ ድርሻችንን ከሁሉም የፍርድ ባለዕዳዎች የመጠየቅ መብታችንን ጠብቆ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ያፅናልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በመጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን አጣሪው በማሰቀረቢያነት ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡በመሰረቱ በፍርድ አፈፃፀም ጉዳይ አንድ ንብረት በሀራጅ እንዲሸጥ ሲወሰን የሀራጁ ሽያጭ የሚከናወነው በቅድሚያ የሐራጁን ስርዓት አፈፃፀም ለህዝብ በማስታወቅ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.423(1) የተመለከተ ሲሆን የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያውም የሚሸጠውን ንብረትናአይነት፣ንብረቱ የሚሸጥበትን ሁኔታና ገደቡን፣የግምቱን ልክ፣በንብረቱ ላይ የተቋቋመ መብት ካለ መብቱንና ልኩን፣የሽያጩ ገንዘብ የሚከፈልበትን ጊዜና ሌሎች ገዢው ከመግዛቱ በፊት ማወቅ ይገባዋል ብሎ ፍርድ ቤቱ የሚያምነውን ዝርዝር መያዝ ያለበት መሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.423(2) መመልከቱና ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.239 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የማይንቀሳቀስ ንብረት ስለሚሸጥበት ሁኔታ ከሚደነግጉት ጥብቅ መስፈርቶች አንፃር በጋራ ሲመረመር ፍርድ ቤቱ ከማይንቀሳቀስ ንብረቶች የሀራጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ የሸጠውን ንብረት በአግባቡ ለይቶ ሊያስረክብ ስለሚገባ በቅድሚያ የሚሸጠውን ንብረት ስፋትና አይነት በንብረቱ ላይ የተቋቋመ መብትም ካለ ይህንኑ በሀራጅ ማስታወቂያው ላይ በግልፅ በማመልከት በጥንቃቄ ሽያጩን ሊያከናውን የሚገባ መሆኑን ያሳያል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የሀራጅ ሽያጭ አስመልክቶ የቤቱ ይዞታ መጠን 360 ካሜ መሆኑ ተገልፆ ለህዝብ የማስታወቅ ሂደቱ የተፈፀመ መሆኑ ግራ ቀኙ ያልተካካዱበት ነጥብ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት መዝገብም ይህንኑ ያሳያል፡፡አመልካች ይህንኑ ማስታወቂያ አይተው በሀራጅ ሽያጩ የተሳተፉ ከሆነ ደግሞ ሽያጩን ያከናወነው የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሀራጁን ላሸነፉት አመልካች ለማስረከብ የሚገደደው፣አመልካችምመብታቸውን ሊያረጋግጡ የሚገባው በዚሁ ስፋቱ በአግባቡ ተገልፆ በተሸጠው መጠን ሊሆን ከሚገባ በስተቀር አመልካች በጉብኝቱ ወቅት ተመለከትኩት ባሉት መጠን ልክ ወይም በተጠሪዎች መሃል በነበረው ክርክር መፍትሄ ያልተሰጣቸው ናቸው በማለት አመልካች በገለጿቸው የክርክር ነጥቦች መነሻነት በሀራጅ ማስታወቂያው ላይ በግልፅ ከተመለከተው ስፋት በማለፍ አመልካች እንዲረከቡ የሚወሰንበት አግባብ ስለሌለ፣በዚህ አግባብም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር በመመርመር የደረሰበት መደምደሚያ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቃቂ ቃሊቲ ምድብ ችሎት በመ/ቁ.198456 በ30/10/2013 ዓም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላልተገኘ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት

ሠ/ን

??/? /?? ? 214389
?? 22/9/2014 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - አቶ ገዛሄኝ ጉታ ፡ የቀረበ የለም

ተጠሪ - አቶ ማርቆስ ባልቻ ፡ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች መስከረም 15 ቀን 2014 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 376464 ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 343284 ሚያዝያ 19 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 34778 መጋቢት 3 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የደንዲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 65240 የካቲት 8 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የውርስ ንብረት በፍ/ቤት በውርስ አጣር ሳይጣራ እና ክፍፍል ሳናደርግበት ተከፋፍላችኋል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከደንዲ ወረደ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን አመልካች ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ጣልቃ ገብ ደግም አሁን ክርክር ውስጥ የሌለው አቶ አበራ ጉታ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ከሳሽ ባቀረበው ክስ እናቴ ወ/ሮ ጡሬ ሚጀና በ1986 ዓ/ም ሞታለች፡፡ እኔና ተከሳሽ በእናት ወንድም ስንሆን የእናታችን ንብረት በደንዲ ወረዳ ጊንጪ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ

ያለው የመኖሪያ ቤት በ288 ካ/ሜ ላይ ያረፈ 3 ቤቶች እስከ 2004 ዓ/ም በእናታችን ስም ስንገብርበት የነበረና ከ2004 ዓ/ም በኋላ በሶስታችን ስም አበራ ጉታ ጨምሮ ስንገብርበት ቆይተናል፡፡ ይሁንና ተከሳሽ ሳናውቅ በስሙ ያስመዘገበ በመሆኑ ድርሻችንን ያካፍለን ሲል ጠይቋል፡፡ ተከሳሽም የአሁን ተጠሪ ክስ ያቀረበበት የመሬት ይዞታ 200 ካ/ሜ ብቻ ነው፡፡ እናታችን በ1986 ዓ/ም የሞተች ሲሆን፣ እናታችን በህይወት እያለች በ288 ካ/ሜ ቦታ ላይ የተሰራ ቤት ነበራት፡፡ ያ ቤት አሁን የለም፡፡ የእናታችን የመሬት ይዞታ የድሮ ይዞታ ስለሆነ 500 ካ/ሜ የነበረና እናታችን ከሞተች በኋላ በስማችን አስመዝግበን ተከፋፍለን በ200 ካ/ሜ ላይ ካርታ ተሰጥቶኛል፡፡ በዚሁ መሰረተ የእናታችን አሮጌ ቤት አፍርሼ ሰርቻለሁ፡፡ አቶ አበራ ጉታም 150 ካ/ሜ ደርሶት ቤት ሰርቶበት ይገኛል፡፡ ይህ ሆኖ እያለና ድርሻውን ወስዶ እያለ የኔን ድርሻ እንዳካፍለው መጠየቁ ተገቢ ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ጣልቃ ገብ አሁን በክርክር ውስጥ የሌለው አቶ አበራ ጉታ በጣልቃ ገብነት ባቀረበው ክርክር እናታችን ጥላ የሞተችው የመሬት ይዞታ 500 ካ/ሜ ነው፡፡ ከተማ አስተዳደሩ የድሮ ይዞታ ስመዘግብ ስትገብርበት የነበረው በ288 ካ/ሜ ቢሆንም ይዞታው 500 ካ/ሜ በመሆኑ በ500 ካ/ሜ ገብረንበት የነበረና ተከፋፍለን እኔና ከሳሽ 150 ካ/ሜ ተከሳሽ ደግሞ 200 ካ/ሜ ደርሶን የእናታችን ቤት ተከሳሽ በደረሰው ድርሻ ላይ ያረፈና አርጅቶ በመፍረሱ ተከሳሽ ሌላ ቤት ሰርቶበት እኛም በደረሰን ቦታ ላይ ቤት ሰርተንበት አስመዝግበን ይዘን የምንገኝ ሲሆን ይህ ሆኖ እያለ ከሳሽ ክስ ማቅርቡ ተገቢ ባለመሆኑ ውድቅ ይሁንልን ብሏል፡፡ የደንዲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 65240 የካቲት 8 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የተሰሙት ምስክሮችና የቀረበው የሰነድ ማስረጃ እናታቸው ጥላ የሞተችው ይዞታ 500 ካ/ሜ ሲሆን ስትገብርበት የነበረው በ288 ካ/ሜ የነበረና ከተማ አስተዳደሩ ሲለካ 500 ካ/ሜ በመሆኑ በ500 ካ/ሜ መዝግቦላቸው ተከፋፍለው ይዘው እንደሚገኙና ተከሳሽ የእናታቸው ቤት ደርሶት ቤቱን አሳድሶ ኩሽናና ሽንት ቤት ሰርቶበት በስሙ አስመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ በመረጋገጡ ወራሾች ተስማምተው ተከፋፍለው ይዘው የሚገኙትን የተከሳሽ ድርሻ ላይ ከሳሽ ክስ ማቅረቡ ተገቢ ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ከሳሽ ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 34778 መጋቢት 3 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የደንዲ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከሳሽ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 343284 ሚያዝያ 19 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ እና የወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከሳሽ የአሁን አመልካች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 376464 ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ እና የወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ አያስቀርብም ሲል አቤቱታውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ አከራካሪ የሆነው ቤት አመልካች ከተጠሪ ጋር የይዞታ ማረጋገጫ ያወጡ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሮ ባለበትና ይህ ስለመሆኑ ተጠሪ ባልካደበት የስር ፍ/ቤት በምን ሁኔታ የቤቱ ሰም ወደ ተጠሪ ሊዞር የቻለበትን ሁኔታ ሳያጣራ መወሰኑ ሥነ ሥረዓት ህጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ የካቲት 8 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም መጋቢት 1 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረተው ክርክር ማስረጃ የሚሰማውና የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው ፍ/ቤቶች የደንዲ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በቀረቡት የሰው ምስክሮችና እና የሰነድ ማስረጃ እናታቸው ወ/ሮ ጡሬ ሚጀና በ288 ካ/ሜ ቦታ ላይ ስትገብር የነበረ መሆኑን ይሄው የመሬት ይዞታ ሲለካ 500 ካ/ሜ መሆኑን በዚሁ መሰረት የከተማ አስተዳደሩ የእናታቸው የውርስ ንብረት የከተማ የመሬት ይዞታ ሲለካ 500 ካ/ሜ በመሆኑ ለወራሾቹ 500 ካ/ሜ መዝግቦላቸው እንዲገብሩበት ያደረገ መሆኑን በኋላም በስምምነት ተከፋፍለው ይዘው እንደሚገኙና ተከሳሽ የእናታቸው ቤት ያረፈበት ቦታ ደርሶት ቤቱን አሳድሶ ኩሽናና ሽንት ቤት ጨምሮ ሰርቶበት በስሙ አስመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ አረጋግጠ ወራሾች የእናታቸውን የውርስ ንብረት ተስማምተው ተከፋፍለው ድርሻቸውን ይዘው የሚገኙ መሆኑ በመረጋገጡ የአሁን አመልካችን ክስ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ተለይቶ የሚታወቅ ወራሽና የውርስ ንብረት፣ ወራሾች በስምምነት ቢካፈሉ እና በስምምነት መከፋፈላቸው ከተረጋገጠ የግድ በፍርድ ቤት የውርስ አጣሪ ተሹሞ በፍ/ቤት ክፍፍሉ ያልተፈጸመ ባለመሆኑ በስምምነት የተደረገው የውርስ ሀብት ክፍፍል ህገ ወጥ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1079 ይህንኑ ደንግጎ ይገኛል፡፡ የአሁን አመልካች፣ በስር ፍ/ቤት ጣልቃ ገብ የነበረው አቶ አበራ ጉታ እና የአሁን ተጠሪ የእናታቸውን የውርስ ንብረት ቤት በስምምነት ተከፋፍለው ድርሻቸውን ይዘው የሚገኙ መሆኑ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች የእናቱን የውርስ ንብረት በስምምነት ተካፍሎ ድርሻውን ይዞ እያለ ለአሁን ተጠሪ የደረሰውን የውርስ ድርሻ እንዲያካፍለው መጠየቁ ካለአግባብ በመሆኑ ክሱ ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 376464 ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 343284 ሚያዝያ 19 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 34778 መጋቢት 3 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የደንዲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 65240 የካቲት 8 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

3. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ 214325

ግንቦት 2 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ ለምለም ቅጣው- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዘቢባ የሱፍ-ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በቀን 14/01/2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0332243 በቀን 21/11/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ የጀመረው በስር የደዋ ጨፋ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ነበሩ።

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የአሁን ተጠሪ በቀን 09/06/2012 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ሟች አባቴ የሱፍ ኢብራሂም በቀን 05/05/1987 ዓ.ም በሞት ተለይቷል። የአባቴን ወራሽነት በደዋ ጨፋ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0302372 አረጋግጫለሁ። አባቴ በህይወት ሲኖር ተከሳሽን አግብቶ 6 ልጅ

ያላቸው ሲሆን እኔ ደግሞ ከበፊት ሚስቱ ወ/ሮ ሀሊማ ኡስማን የወለደኝ ስሆን አባቴ በህይወት እያለ በከሚሴ ከተማ ውስጥ 528 ካ.ሜ በሆነ ቦታ ላይ የሚገኝ 1 ትልቅ ቆርቆሮ ቤት በውስጡ 2 ክፍል ያለው፣ 1 ትልቅ ቆርቆሮ ቤት 6 ክፍል ያለው እንዲሁም 6 ክፍል ሰርቪስ ቤት ያለው ሁሉንም በጋራ አፍርተዋል። አባቴ ሲሞት ህጻን ስለነበርኩ ካደኩኝ በኋላ በተከሳሽ ስር እንደ ወላጅ እናት በማየት በፍርሀትና በማክበር ክስ ሳላቀርብ ቆይቼ ንብረት እንድታካፍለኝ በሽማግሌ ብጠይቅም ለማካፈል እንቢ ስላለች የውርስ ንብረት ድርሻዬን እንድታካፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

ተከሳሽ በሰጡት መልስ የቀረበው ክስ በ15 አመት ይርጋ ይታገዳል፤ የከሳሽ አባት የሞተው በ1987 ዓ.ም ሲሆን የከሳሽ እድሜ በግዜው 15 አመት ነበር፤ 18 አመት የሚሞላት በ1991 ዓ.ም ነው። ከዚህ አመት ጀምሮ እስከ 2006 ዓ.ም መጠየቅ ነበረባት። ስለሆነም ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል። በሌላም በኩል ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ከሳሽን እንደ ልጄ ሳሳድጋት እንደነበርና በራሴ ወጪ የዳርኪት መሆኑን እሷም አትክድም፤ የምታገኘው የውርስ ድርሻ በግዜው የቤቱን ዋጋ በሽማግሌ ተገምቶ እና ከእኔ የሚወለዱ 7 ልጆች ስላሉ የእሷ ድርሻ ብር 3000.00 (ሶስት ሺህ) ከተወሰነላት በኋላ እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ከእኛ ጋር ኖራለች በዚህ አመት ውስጥ የድርሻ ገንዘቡን ጨምረን 15,000.00 (አስራ አምስት ሺህ) ስንሰጥ ከሳሽ እንዴት ከወንድሞቼ እለያለሁ ወንድሞቼ ይበልጡብኛል በማለት አልወሰደችም። ስለሆነም ፍርድ ቤቱ እኔው ጋር መኖሯን ተረድቶልኝ እንዲሁም ስራ እሰራለሁ በማለት ገንዘብ መውሰዷ ታይቶ ከክሱ በነፃ እንድሰናበት በማለት ተከራክረዋል።

የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የከሳሽ አባት የሞተ በ1987 ዓ.ም መሆኑና ክርክር ያስነሳው ንብረት በተከሳሽ እጅ መኖሩ ግራ ቀኙ አልተካካዱበትም። ከሳሽ በ1995 ዓ.ም እድዋ 18 ዓመት ስለሚሆን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክሱ መቅረብ ያለበት በ15 አመት ውስጥ ነበር፤ ይሁን እንጂ ክስ ያቀረበችው እድሜዋ ለአቅመ ሄዋን ከደረሰች በኋላ 18 አመት ቆይታ በካቲት 9 ቀን 2012 ዓ.ም ነው። ስለሆነም የቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ከሳሽ ይግባኝ ለኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ችሎት ክርክራቸውን ሰምቶ የከሳሽ የውርስ መብት በይርጋ የታገደ ነው በማለት ውሳኔውን አጽንቷል።

በመጨረሻ ከሳሽ ቅሬታቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል። አጣሪ ችሎቱ ቅሬታውን መርምሮ ተከሳሽ ከሰጡት መልስ አንጻር የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ነው የሚለውን ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል። ሰበር ችሎቱም የግራቀኙን ክርክር ተመልክቶ ከሳሽ በሚያከራክረው ቤት ላይ እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ የምትጠቀምበት እንደነበር እንዲሁም በየግዜው ተከሳሽ ገንዘብ ትሰጣት እንደነበር በመልስዋ ላይ መግለጽዋ ሲታይ እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ያለውን ጊዜ ይርጋ ማቋረጫ ምክንያት እንደሚሆን ከፍ/ብ/ሕ/ሀ/ቁ 1851፣ 1852 መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉትን ውሳኔ ሽሮ የወረዳው ፍ/ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ በፍሬ ነገሩ ላይ ተገቢውን እንዲወስን በማለት ጉዳዩን ወደ ስር ፍርድ ቤት መልሷል።

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች በቀን 14/01/2014 ዓ/ም ያቀረቡት ማመልከቻ በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረቡትን ክርክር የስር ፍርድ ቤቶች ተቀብለው ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የወሰኑትን የክልሉ ሰበር ችሎት በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት ወደስር ፍርድ ቤት በመመለስ የወሰነበትን አግባብ ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል። በዚህ መሰረት ግራቀኙ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተለዋውጠዋል።

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል።

እንደሚታወቀው አንድን ክስ ለማቅረብ በህጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ ክስ ለማቅረብ የማይቻል ቢሆንም ህጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ምክንያቶች የይርጋው ጊዜ ሊቋረጥ የሚችል እና አዲስ የይርጋ ጊዜ መቆጠር እንደሚጀምር በፍ/ብ/ህ/ቁ 1852(1) ሥር ተመልክቷል። በተለይ

በውርስ ንብረት በጋራ ሲገለገሉ መኖር እንዲሁም ከውርስ ንብረት ዕዳን አምኖ ክፍያ ለመፈፀም ፈቅዶ በዚሁ አግባብ ሲከፈል መኖር ይርጋ ከሚቋረጥባቸው ምክንያቶች መካከል የሚጠቀስ ነው።

በተያዘው ጉዳይ ከፍሲል እንደተገለፀው ተጠሪ የሟች ልጅ እና ወራሽ መሆኗ፤ ከልጅነቷ ጀምሮ ከአመልካች ጋር በአከራካሪው ቤት እስከ 2004 ዓ.ም እና ከዚያም በኃላ እየተጠቀሙች መኖሯ ግራቀኙን አላከራከረም። አመልካችም በስር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ ይህንኑ አረጋግጠዋል። ከዚህም ሌላ አመልካች የውርስ ሀብት ድርሻዋን እንድትወስድ በአመልካች ስትጠየቅ የነበረ መሆኑ እና በሽማግሌ ድርሻዋ ከተወሰነላት በኋላ አልወስድም ስላለች ለስራ መጀመሪያ በሚል የውርስ ድርሻን ታሳቢ በማድረግ ገንዘብ ይሰጧት እንደነበርም አመልካች በስር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ አረጋግጠዋል። ስለሆነም ተጠሪ በውርስ ንብረቱ መገልገል ያቋረጠችበት ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ (ወደ ሳውዲ አረቢያ ሄደች ከተባለችበት) ነው ቢባል እንኳ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አዲስ የይርጋ ጊዜ መቆጠር እንደሚጀምር የክልሉ ሰበር ችሎት የደረሰበት መደምደሚያ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም። ክርክሩ ወራሽ በሆነችው ተጠሪ እና ወራሽ ባልሆኑት አመልካች መካከል በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000 መሰረት የይርጋ ጊዜው 10 (አስር) አመት ነው። አዲስ የይርጋ ጊዜ መቆጠር ከጀመረበት ክስ እስከቀረበበት በካቲት 9 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ ሲሰላ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበችው ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም።

ስለሆነም የክልሉ ሰበር ችሎት ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉትን ውሳኔ ሽሮ የወረዳው ፍ/ቤት ፍሬ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን እንዲወስን መመለሱ ከፍሲል የተገለፁትን የህጉን ድንጋጌዎች እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም። ተከታዩንም ወስነናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0332243 በቀን 21/11/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት በውጤቱ ፀንቷል።

2. የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ የታገደ አይደለም ተብሎ የፍሬ ነገር ክርክሩ ታይቶ እንዲወሰን ጉዳዩ ለስር ፍርድ ቤት በመመለስ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል።

3. ዕግድ ካለ ተነስቷል። ይጻፍ።

4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፈርማ አለበት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 214291
ግንቦት 26 ቀን 2014ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ሰድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ዳቫል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሐይማኖት መራ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 104335 በሆነው ሰኔ 17ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሣኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ሲል የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምለት አመልካች በመጠየቁ ነው፡፡

ጉዳዩ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩ በተጀመረበት አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ይልማና ዴንሣ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ አመልካች የካቲት 24ቀን 2012ዓ/ም በተፃፈ ክሱ በእጁ አድርጎ በሚጠቀምበት ስምንት ቃዳ ይዞታው ውስጥ ተጠሪዋ ከ2003ዓ/ም ጀምሮ የግንባታ ፈቃድና የይዞታ ማረጋጫ ሣይኖራት በ75 ካሬ ሜትር ላይ በ12ዚንጎ ቆርቆሮ የተሰራ ቤት ስርታ የአልኮል መጠጦችን፣ ምግቦችንና ልዩ ልዩ ሸቀጣቀጦችን እየሸጠች የመማር ማስተማሩን ስራው ላይ ችግር እየፈጠረችበት ለትምህርት ቤቱ ገቢ የሚያስኝ ይዞታውንም የያዘችበት መሆኑን በመዘርዘር ይዞታው በአንድ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመት የሚያስገኘውን የሳር ግምት በአመት መቶ ብር ሆኖ የዘጠኝ ዓመት በድምሩ 900 ብር ክፍላ ቤቱን አፍርሣ እንድትለቅ እንዲወሰንባት ጠይቋል።

ተጠሪ በበኩሏ በግምቱ የማትስማማ መሆኑን ገልፃ ሌላ ለእርሻም ሆነ መጠለያ ለመስራት የምትጠቀምበት ይዞታ የሌላት መሆኑ ተረጋግጦ ከአመልካች ይዞታ ውጪ ከሆነ መሬት ላይ በ1989ዓ/ም ተሰጥቷት ለ24ዓመታት በይዞታዋ አድርጋ የምትጠቀምበት መሆኑን፣ የሰብል ግምት የዘጠኝ ዓመት መጠየቁ ተገቢ አለመሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ እንዲደረግላት ተከራክራለች።

የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ልትለቅ ይባል ወይስ አይገባም የሣር ግምትስ ልትከፍል ይገባታልን የሚለውን ጭብጥ ይዞ የግራ ቀኙን ማስረጃ መርምሯል፤ የወረዳው መሬት አስተዳደርም ማስረጃ እንዲሰጠው ትዕዛዝ ሰጥቶ በቀረበለት ማስረጃ ተጠሪ ከ1991ዓ/ም እስከ 2003ዓ/ም ድረስ በይዞታው ላይ ሸራ ዝርግታ ሻይና ዳቦ ስትሸጥ መቆየቷን በ2003ዓ/ም በ12ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት መስርቷን፣ ለወጣቶች መሬት ሲሰጥ በአመራሩ ፈቃድ የተሰጣት ስለመሆኑ በምስክሮች ተረጋግጧል ካለ በኋላ ተጠሪዋ ከ1991ዓ/ም ጀምሮ ይዛ የምትጠቀምበትን መሬት ትክ ሣይሰጣት ልትለቅ አይገባም ሲል የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጓል። በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘው አመልካች ይግባኝና የሰበር አቤቱታውን በየደረጃው ለሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች አቀርቦ ስለፀናና ስለተሰረዘበት ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል።

አመልካች መስከረም 10ቀን 2014ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት መሬት በመሆኑ ተጠሪዋ ባለይዞታ መሆንዋን እንዲሁም ግብር የምትከፍል መሆኑን የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ማስረጃ ሣጣቀርብ ከ1991ዓ/ም ጀምራ በህገወጥ መንገድ መያዟን ብቻ መሰረት በማድረግ ትክ ሣይሰጣት ልትለቅ አይገባም ሲል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምለት ጠይቋል።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የሰበር ተጠሪ ሕጋዊ ይዞታ ማረጋገጫ የሌላት መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከመረጋጡም አንፃር አከራካሪውን ይዞታና ቤት ያለትክ ልትለቅ አይገባም ተብሎ የመወሰኑ ሕጋዊነት ለመመርመር ሲባል ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

ተጠሪ በበኩሏ መጋቢት 1ቀን 2014ዓ/ም በተፃፈ መልሷ በጥቅሉ አመልካች ሳቃወማት ከት/ቤቱ ይዞታ ውጪ ቤት መገንባቷን፣ የስር ፍርድ ቤትም መሬቱን ልትለቅ አይገባም ሲል ውሣኔ የሰጠው ከ1989ዓ/ም የተሰጣት መሆኑን በሕዝብ አጣርቶ በማስረጃ አረጋግጦ መሆኑን በመዘርዘር ስር ፍርድ ቤቱ ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ስትል ተከራክራለች። የግራ ቀኙ ክርክር በዚሁ ተጠናቋል።

ከፍ በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥና በዚህ ችሎት የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክር ነበር። የስር ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ለያዘችው መሬት ትክ ሣይሰታት ልትለቅ አይገባም ሲል በሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጭብጥነት ተይዞ ተመርምሯል።

እንደተመረመረው አመልካች ክስ ያቀረበው የይዞታው አካል የሆነውን መሬት ስምንት ቃዳ ከሆነው የአመልካች ይዞታ ውስጥ ተጠሪዋ የግንባታ ፈቃድና የይዞታ ማረጋገጫ ሣኖራት በሕገወጥ መንገድ 75 ካሬ

ሜትር ላይ ቤት በመስራት የተለያዩ ሽቀጣ ሽቀጦችንና አልኮሆል መጠጥ በመሸጥ በትምህርት ስራው ላይ ችግር መፍጠሯን በመዘርዘር የገነባችውን ቤት አፍርሣ ይዞታውን እንድትለቅለት የተቋረጠ ጥቅም የዘጠኝ ዓመት እንድትከፍለው ጠይቋል።

ተጠሪ በበኩሏ ለመጠለያም ሆነ ለሌላ አገልግሎት የምትጠቀምበት ሌላ መሬት ስላልነበራት መጠለያ እንድትሰራ

በት አት/ቤቱ ይዞታ ውጪ ከወል መሬት ላይ በ1989ዓ/ም በቀበሌ አስተዳደደሩ ተሰጥታት በዚሁ መሬት ላይ ቤት ሰርታ ላለፉት 24 ዓመታት ሻይና ዳቦ በመሸጥ የምትተዳደር መሆኑን ዘርዝራ የአመልካችን ይዞታ በሕገወጥ መንገድ አለመያዟንገለፃ ተከራካራለች።

የስር ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ አዳምጦ እንዲሁም የወረዳው መሬት አስተዳደር አጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል። በአመልካች በኩል የቀረቡት ምስክሮች ለክሱ መነሻ በሆነው ቦታ ላይ ተጠሪዋ ከ1991ዓ/ም ጀምሮ ይዛ መቆየቷን አሁን ላይ ት/ቤቱ ሲታጠር ወደ ት/ቤቱ ግቢ መግባቱን አረጋግጠዋል። አመልካች ባቀረበው ክስ ተጠሪዋ ከ2003ዓ/ም ጀምሮ ይዞታውን እንደያዘችበት የገለፀ ቢሆንም የራሱ ምስክሮች ከ1991ዓ/ም ጀምሮ ለክርክሩ መንስዔ የሆነው ይዞታ በተጠሪ እጅ መሆኑንና ይህ ይዞታ ወደ ት/ቤቱ የገባው ተጠሪ ከመያዟ በፊት ሳይሆን የት/ቤቱ ይዞታ ሲታጠር መሆኑን አረጋግጠዋል። በአንፃሩ ተጠሪ ባቀረበቻቸው ምስክሮች በ1991ዓ/ም በቀበሌው የሚገኙ ወጣቶች መሬት ሲደለደሉ ተጠሪም ሻይ ሸጣ እንድትደደርበት አሁን የያዘችውን መሬት የተሰጣት መሆኑን አረጋግጠዋል። መሬት አስተዳደደሩ በበኩሉ ተጠሪዋ አሁን በያዘችው ይዞታ ላይ ከ1991ዓ/ም ጀምሮ ላለፉት 23 ዓመታት በመጀመሪያ ሸራ ዘርግታ ከ2003ዓ/ም ጀምሮ ደግሞ አሁን ያለውን ቤት በቆርቆሮ ስርታ ሻይና ዳቦ በመሸጥ ላይ መሆኗን ማረጋገጡን የሚገልፅ ማስረጃ ሰጥቷል።

እንደሚታወቀው ሕግ ከሚፈቅደው ውጪ መብቱ የተጣሰበት ወይም ጥቅሙ የተነካበት ወይም የተወሰደበት ሰው ሕገወጥ ድርጊቱ ተወግዶ የተወሰደበት ንብረት እንዲመለስለት የደረሰበት ጉዳትም እንዲካካስለት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ዳኝነት ጠይቆ ፍትህ የማግኘት መብቱ በሀገሪቱ ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37 እውቅና የተሰጠው መብት ነው። ይሁን እንጅ መብቱ በመጣሡ ወይም ጥቅሙ በመነካቱ የፍ/ብሔር ክርክር ያቀረበ ወይም መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ይኖርበታል። በማስረጃ ረገድም ግዴታው ወይም መብቱ መኖሩን ለማስረዳት ህጉ የተለየ ማስረጃ እንዲቀርብ ካላዘዘ በስተቀር ግዴታው መኖሩን በጽሁፍ፣ በምስክር፣ በሀሊና ግምት በተከራካሪው ወገን እምነት ወይም በመሃላ ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 2002 ይደነግጋል።

በዚህም መሰረት የተካደ ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማጣራት የዳኝነት ስልጣን በተሰጠው የስር ፍርድ ቤት ያቀረበውን ክስ በቅድሚያ የማስረዳት ሸክም ያለበት አመልካች ለክርክሩ መንስዔ የሆነውን ይዞታ ተጠሪዋ ከመያዟ በፊት ይዞታው የእርሱ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ሲኖርበት ይህን ግዴታውን በአግባቡ ስለመጣቱ የጉዳዩ አመጣጥ አያስገነዝብም። በሌላ በኩል አመልካች የመንግስት ተቋም በመሆኑ በክልሉ የገጠር መሬት

አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 2(23) መሰረት የአመልካች ይዞታ የመንግስት ይዞታ በመሆኑ ይዞታውን መጠንና ጠሪዋም በእርሱ ይዞታ ላይ ቤት የሰራች ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስለማቅረቡ የውሣኔው ቅጅ አያስገነዝብም።

በመሆኑም ማስረጃን የመመዘን የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ክስ የተጠሪን የግል

ይዞታ ለመውሰድ በማሰብ የቀረ እንጅ ይዞታው ስለተወሰደበት የቀረበ ስለመሆኑ በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል ትክ ተሰጥቷት ካሣ ሣይከፈላት ይዞታዋን ለአመልካች የምትለቅበት መንገድ የለም ሲል የሰጠው ውሣኔና በየደረጃው የሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማጽናታቸው ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት ምክንያት ስላልተገኘ ተከታዩ ተወስኗል።

ውሣኔ

1) የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 104335 ሰኔ 17ቀን 2013ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0325368 የካቲት 26ቀን 2013ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ፣ የይልማና ዴንሳ ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥሩ ባልተጠቀሰ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን ክርክር መርምሮ ታሕሳስ 23ቀን 2013 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል።
2) ይህ የሰበር ክርክር ያስከተውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ እልባት ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 214192

ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች- 1. አቶ ግርማ አንቂቶ- ቀርበዋል

2. አቶ ዳንኤል ባልካቸው- ቀርበዋል

3. አቶ ኃይሉ ታደሰ- ቀርበዋል

4. አቶ እንዳካቸው መኮንን- ቀርበዋል

ተጠሪ- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ- ፅጌ ካሳ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአስተዳደር አካል የወጣ መመሪያ አግባብነት በፌደራል አስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2013 መሠረት እንዲከለስ የቀረበ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የአመልካቾች ክስ ይዘትም በአጭሩ በታህሳስ 12 ቀን 2012 ዓ.ም በፌደራል ደረጃ ባወጣው የመምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ስፐርቫይዘሮች የስራ መደብ ድልድል አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 2/2012 መሠረት በተደረገ ጂ.ኤ.ጂ ጥናት አንቀጽ 9 መሠረት ከነበርንበት ደረጃ ያለ ውድድር ከሐምሌ 1 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተመድበን በመስራት ላይ እያለን የመመሪያውን አንቀጽ 17 ድንጋጌ በሚቃረን መልኩ በነሐሴ 2012 ዓ.ም በወጣ አዲስ መመሪያ በተመደብንበት የስራ መደብ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ላይ አዲስ ውድድር ተደርጎ ሌሎች ሰዎች እንዲመደቡ ተደርጓል። በጂ.ኤ.ጂ ምደባ የተሰጣቸው ርዕሰ መምህራንን ከምደባቸው ላይ ለማንሳት የሚያስችል የተደረገ ጥናት በሌለበት የተሰጠው አዲስ ምደባ የህግ መሠረት የለውም። ህግ ወይም መመሪያ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም የሚለው መርህ እንዳለ ሆኖ በጂ.ኤ.ጂ የተሰጠው ምደባ በአዋጅ ቁጥር 56/2010 ዓ.ም መሠረት ተሠርዟል እንኳን ቢባል አመልካቾች በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ተመሳሳይ ደረጃ ወዳለው የስራ መደብ ልንመደብ ሲገባ ለምደባው ውድድር እንዲኖር መደረጉ የመመሪያ ጥሰት ነው፤ መስሪያ ቤቱ ያወጣው መመሪያም በፌደራል አስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ላይ የተመለከቱትን የስነ-ስርዓት ድንጋጌዎች ያልተከተለና ከበላዩ ካሉ ሌሎች ህጎች ጋር የሚቃረን ሲሆን በድልድል ስም የተደረገው ውድድርም የኮሚሽኑን መመሪያ የሚጥስ በመሆኑ መመሪያ እና ውድድሩ ተሽሮ ከሐምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ተመደብንበት የስራ መደብ እንድንመለስ እንዲሁም ካሳ በቁርጥ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ ፍርድ ቤቱ ክሱን ለማየት ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በፍሬ ነገሩ ላይ በሰጠው መልስ ነሐሴ 2012 ዓ.ም ባወጣነው መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 19 መሠረት የወጣ ስለሆነ ተገቢነት ያለው ነው፤ የአመልካቾች ቅሬታ ሊፈታ የሚችለው በመመሪያው ውስጥ ባሉ የቅሬታ መፍቻ መንገዶች እንጂ መመሪያውን በማሻሻል አይደለም፤ ድልድሉ የተካሄደው የከተማው ትምህርት ቢሮ የትምህርት ቤት ተቋማዊ አደረጃጀት ጥናት በተጠሪ ሙያዊ ድጋፍ ሲካሔድ ቆይቶ ቢሮው ጥናቱ እንዲፀድቅለት በቀን 22/03/2012 ዓ.ም ለተጠሪ ጥያቄ አቅርቦ የጥናቱ ሰነድ በቀን 25/03/2012 ዓ.ም ከፀደቀ በኋላ በመሆኑ መመሪያን የተከተለ ነው፤ መመሪያውም ሆነ ምደባው የህግ ጥሰት የሌለባቸው ሲሆን አለባቸው እንኳን ቢባል የአመልካቾች ቅሬታ በቀን 08/12/2012 ዓ.ም በወጣው መመሪያ ላይ የተመለከቱትን የቅሬታ አፈታት ስርዓቶች ተከትለው ሊያቀርቡ ይገባል እንጂ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካቾች ነሀሴ 2012 ዓ.ም የወጣው መመሪያ የበላይ ከሆኑ ህጎች ጋር ይቃረናል የሚሉት የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያወጣውን መመሪያ ሲሆን ይህ መመሪያ በራሱ መመሪያ ከመሆኑ አንፃር ነሐሴ 2012 ዓ.ም የወጣው መመሪያ በእርከን ከመመሪያ በላይ ከሆኑ ሌሎች ህጎች ጋር አይቃረንም፤ ይህ መመሪያ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ያልተመዘገበ እና በተጠሪ ተቋም ድህረ-ገጽ ላይ ያልተጫነ በመሆኑ በፌደራል አስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/12 አንቀጽ 18 መሰረት ተፈፃሚነት የሌለዉ አዲስ የመመሪያ አወጣጥ ስነ-ስርዓትን ተከትሎ ተጠሪ መመሪያዉን እንደ አዲስ ሊያወጣ ይገባል ካለ በኋላ፣ አመልካቾች ያቀረቡትን የካሳ እና የምደባ ይስተካከልልን ጥያቄን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል። አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ውድቅ ተደርጎባቸዋል።

አመልካቾች በቀን 11/01/2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል። የአቤቱታቸዉ ይዘትም በአጭሩ በታህሳስ ወር 2012 ዓ.ም የወጣው የመምህራን፣ ርዕሰ መምህራን እና ሱፐርቫይዘሮች የስራ መደብ ድልድል አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 2/2012 መሠረት በተደረገ የጂ.ኤ.ጂ ጥናት ያለውድድር ከሐምሌ 01 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ብንመደብም ተጠሪ መስሪያ ቤት በነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ያወጣው የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመሠረታዊ የስራ ሂደት ለዉጥ ትግበራ የትምህርት ቤቶች አመራሮች የድልድል አፈፃፀም መመሪያ ያወጣ ሰሲሆነ ይህም መመሪያ የከተማ አስተዳደሩን ቻርተር፣ የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 25 እና 37 'ን' የሚቃረን እና በፌደራል አስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጅ 1183/2012 ከአንቀጽ 12 እስከ 19 ላይ የተቀመጠውን ስነ-ስርዓት ሳይከተል የወጣ ነው፤ የስር ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ ግንዛቤ በመውሰድ መመሪያ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው ቢያደርጉም ውጤቱን በሚመለከት መመሪያውን መሠረት አድርጎ የተፈፀመው ውድድር እና ምደባ አንዲቀርና ወደ ቀደመው መደባችን እንድንመለስ ያቀረብነውን ጥያቄ በዝምታ ማለፉቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው።

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ህጋዊ ተፈፃሚነት የለውም በተባለ መመሪያ የተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቀሪ ሊሆን አይገባም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል። በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ በቀን 06/03/2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ በፌደራል አስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 57(1) መሠረት ፍርድ ቤት አንድን የአስተዳደር መመሪያ ከመሻሩ በፊት በተሻረው መመሪያ መሰረት የተሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እንደፀኑ እንደሚቆዩ የሚደነግግ በመሆኑ አመልካቾች ውሳኔው ተሽሮ ወደ ስራችን እንድንመለስ ይወሰንልን በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢነት የለውም፤ አመልካቾች በመመሪያው ይዘት ላይ ያላቸውን ቅሬታ በሚመለከት በመመሪያው ከአንቀጽ 16 እስከ 21 ድረስ በተቀመጠው ስርዓት ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ከሚችሉ በስተቀር ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ አይችሉም፤ የህገ-መንግስቱን አንቀጽ 25 በመጥቀስ የእኩልነት ጥያቄን ያነሱበት መከራከሪያ በስር ፍርድ ቤቶች ያልቀረበ በመሆኑ በዚህ ደረጃ ሊቀርብና ሊስተናገድ አይችልም በማለት ተከራክሯል። አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ከተያዘው ጭብጥ፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረዉም አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 ላይ በተመለከተዉ አግባብ ሥነ ሥርዓቱን ጠብቆ ያልወጣ እንዲሁም ከሌሎች አዋጆች እና በፌዴራል ደረጃ የወጣዉን መመሪያ የሚቃረን ሌላ መመሪያ ስራ ላይ በማዋል ቀደም ሲል በነበረዉ መመሪያ መሰረት ያለዉድድር ተመድበንበት የነበረዉን ቦታ አስለቅቆን ሌሎች ሠራተኞችን የመደበ መሆኑን

ሲሆን፣ የጠየቁት ዳኝነትም ሥርዓቱን ሳይጠብቅ ተግባራዊ የተደረገዉ መመሪያ እንዲከለስ እና መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የተደረገዉ ምደባም እንዲሰረዝ የሚል ነዉ።

የፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት እና ተጠሪነታቸዉ ለፌዴራል መንግስት የሆነዉ አስፈፃሚ አካላት የሚያወጧቸዉ መመሪያዎች መከተል ያለባቸዉን መርሆዎች እና ሥርዓቶች፣ አንድ መመሪያ ተገቢዉን ሥርዓት ተከትሎ አልወጣም የሚል ማንኛዉም ጉዳዩ የሚመለከተዉ ሰዉ መመሪያዉ እንዲከለስ ዳኝነት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል እና የዳኝነት ጥያቄዉ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሚሰጠዉ ዉሳኔ ወሰኑ እስከምን ድረስ እንደሆነ ይደነግጋል። አዋጁ እነዚህንና መሰል ድንጋጌዎችን እንዲያካትት የተደረገበት ምክንያትም የሚመለከተዉ የአስፈፃሚ አካል የሚያወጣዉ መመሪያ ግልጽ የሆኑ ሥነ ሥርዓቶችን ተከትሎ እንዲወጣ እና ይህን ሥርዓት ተከትሎ ያልወጣ ከሆነ ከነግድፈቱ ተፈፃሚ ሆኖ እንዳይቀጥል በማድረግ መንግስታዊ አሠራር ለህዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲከናወን እና በመመሪያዎች አወጣጥ መርሆዎች እና ሥነ ስርዓት ላይ ቅሬታ ያለዉ ሰዉ የመመሪያዎቹን ህጋዊነት በፍርድ ቤት የሚያስመረምርበት ሥርዓትን በመደንገግ አስተዳደራዊ ፍትሕ ማስፈን ነዉ የሚለዉን የአዋጁን አንዱ ዓላማ ገቢራዊ ለማድረግ እንዲቻል ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል። አመልካቾች መመሪያዉ እንዲከለስ ዳኝነት የጠየቁትም በዚሁ መነሻነት ሲሆን፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ ጉዳዩ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ሥርዓቱን ሳይጠብቅ የወጣ ነዉ የሚሉት መመሪያ እንዲከለስ የወሰነ ሲሆን መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የተደረገ ምደባ ግን ሊሰረዝ አይገባም በሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል።

በበኩላችንም እንደተመለከትነዉ ስለ ክለሳ ዉሳኔ አሰጣጥ እና አፈፃፀም የሚደነግገዉ የአዋጁ ክፍል አራት ንዑስ ክፍል አራት የዉሳኔ አሰጣጥ በሚለዉ አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ላይ የክለሳ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል ያወጣዉን መመሪያ ሊያጸና ወይም በሙሉ ወይም በከፊል መሻር እንደሚችል እና መመሪያዉን በሙሉ ወይም በከፊል የሻረ እንደሆነ የሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል መመሪያዉን እንደገና እንዲያወጣ ወይም እንዲያሻሽል ማዘዝ እንደሚችል ይደነግጋል። ስለ ክለሳ ዉሳኔ አፈፃፀም በሚያወራዉ አንቀጽ 57 ንዑስ አንቀጽ 3 ስር የክለሳ አቤቱታ የቀረበበት መመሪያ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሻር ከተደረገ በዚያዉ ልክ መመሪያዉ ህጋዊ ኃይል እንደማይኖረዉ በመርህ ደረጃ የሚደነግግ ሲሆን፣ የመመሪያዉ በከፊል ወይም በሙሉ መሻር የአስተዳደር ተቋሙ መመሪያዉ ከመሻሩ በፊት በተሻረዉ መመሪያ መሰረት የሰጣቸዉ አስተዳደራዊ ዉሳኔዎቹ እንደጸኑ እንደሚቀሩ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በግልጽ ተመልክቷል። ከዚህም የምንረዳዉ በአዋጁ ላይ የተመለከተዉን የመመሪያ አወጣጥ ሥርዓትን ተከትሎ አልወጣም በሚል መብት ባለዉ ሰዉ የቀረበለትን የክለሳ አቤቱታ በመቀበል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መመሪያዉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሻር በሚል የሚሰጠዉ ዉሳኔ ዉጤቱ ዉሳኔዉ ከተሰጠ በኋላ የተሻረዉን መመሪያ መሠረት በማድረግ የአስተዳደር አካሉ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ዋጋ እንዳይኖረዉ የሚያደርግ ሲሆን፣ መመሪያዉ ከመሻሩ በፊት በሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል በተሻረዉ መመሪያ መሰረት የተሰጠዉን አስተዳደራዊ ዉሳኔ ዋጋ እንዲያጣ ወይም

ተፈፃሚነት እንዳይኖረዉ የማድረግ ዉጤት የሌለዉ መሆኑን ነዉ። ይህም የሚያሳየዉ ማንኛዉም ሰዉ ተገቢዉን ሥርዓት ተከትሎ አልወጣም የሚለዉ መመሪያ በፍርድ ቤት እንዲከለስ ዳኝነት ለመጠየቅ መብት ያለዉ ቢሆንም (የአዋጁ አንቀጽ 46/1/ ይመለከቷል)፣ ይህ መብቱ አቤቱታ በቀረበበት መመሪያ መሠረት በአስተዳደር አካሉ የተሰጠ ዉሳኔ እንዲሻር ጭምር መጠየቅን የማያካትት መሆኑን ነዉ። ይልቁንም የአስተዳደር አካሉ መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ይነካል የሚል ሰዉ መብቱን የሚያስከብረዉ እንደየጉዳዩ ዓይነት ለጉዳዩ አግባብነት ባለዉ ህግ መሠረት የተዘረጋዉን የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት መሠረት በማድረግ ቅሬታዉን ስልጣን ላለዉ አካል በማቅረብ ሊሆን ይገባል። አዋጁ የመመሪያዉ መሻር ቀደም ሲል በመመሪያዉ መሰረት የተሰጠዉን አስተዳደራዊ ዉሳኔ የመሻር ዉጤት እንደሌለዉ ከላይ በተመለከተዉ አንቀጽ 57(4) ላይ የደነገገበት አንዱ ምክንያት ሊሆን የሚችለዉም እንደየጉዳዩ ባህርይ አንድ የአስተዳደር አካል በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ የሚቀርብበት አካል እና የአቀራረብ ሥርዓቱን በተመለከተ በሌሎች ህጎች ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲከበሩ እና የአንድ አስተዳደር አካል ዉሳኔ ህጋዊነት በሁለት የተለያዩ አካላት ሊታዩ የሚችሉበትን ሁኔታ እንዳይኖር ለማድረግም ጭምር እንደሆነ ይታመናል።

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካቾች በዚህ ችሎት ባቀረቡት ቅሬታ አጥብቀዉ የሚከራከሩት መመሪያዉ ከተሻረ መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የተደረገ ምደባም መብቴን የሚጎዳ በመሆኑ ተሰርዞ ቀደም ሲል ያለዉድድር ተመድቤበት ወደ ነበረዉ ቦታ ልመለስ ይገባል በማለት ነዉ። በመሠረቱ ከስራ ምደባና ደረጃ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያለዉ የመንግስት ሠራተኛ ቅሬታዉን የሚያቀርብበትን ሥርዓት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 56/2010 ይደነግጋል። የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓቱ በልዩ ሁኔታ እንዲደነግግ የተፈለገበት ምክንያትም ለቅሬታዎች አፋጣን መፍትሔ ለመስጠት፣ ለቅሬታዎች መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ስህተቶችንና ድክመቶችን የማረም እና ሁሉንም የመንግስት ሠራተኞች በእኩልነት ለማስተናገድ የሚያስችል እና ፍትሐዊ የሆነ አሠራር በማስፈን የሰመረ የስራ ግንኙነት እንዲኖር በማሰብ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 75 ይዘት ያስገነዝባል። በዚህም መሠረት ከስራ ምደባ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያለዉ ሠራተኛ ቅሬታዉን በቅድሚያ ለመስሪያ ቤቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታዉን ማቅረብ እንዳለበት፣ ቅሬታ ሰሚዉ ኮሚቴ በሰጠዉ ፍርድ ቤት ላይ ቅሬታ ካለዉ ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል እና የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ የህግ ስህተት አለዉ የሚል ከሆነም ቅሬታዉን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በማቅረብ መብቱን ማስከበር የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 77(4)፣ 77፣ 81(1/ሠ) እና 81(5) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። ቅሬታዉ በዚህ መልኩ የሚቀርብለት ፍርድ ቤት ህግን የመተርጎም ስልጣን ያለዉ በመሆኑ የምደባዉን አግባብነት ሲመረምር ቅሬታ የቀረበበት ምደባ ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉን ህግ መሠረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑን ብቻ ሳይሆን ለምደባዉ መሠረት የሆነዉ መመሪያ ስልጣን ባለዉ አካል ተገቢዉን ሥርዓት ጠብቆ የወጣ እና ከሌሎች የበላይ ህጎች (superior laws) ጋር የሚጋጭ መሆን ያለመሆኑን እና ተያያዥ ጉዳዮችን በመመርመር እና ትርጉም በመስጠት የመመሪያዉን ህጋዊ ዉጤት ጭምር በማየት የምደባዉን ህጋዊነት መወሰን ይችላሉ። በተያዘዉ

ጉዳይም አመልካቾች ምደባዉ መብታችን ይነካል የሚሉ ከሆነ ከፍ ሲል በተመለከተዉ አግባብ ለሲቪል ሰርቪስ ፍርድ ቤት ብሎም ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡ ኖሮ ፍርድ ቤቶቹ የምደባዉን ህጋዊነት ሲመረምሩ ለምደባዉ መሰረት የሆነዉ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 6 እና ተከታዮቹ ላይ የተመለከቱትን የመመሪያ አወጣጥ ሥርዓቶችን ተከትሎ የወጣ መሆን ያለመሆኑን ጭምር መርምረዉ የመመሪያዉን ህጋዊ ዉጤት ወስነዉ ይህን መሰረት በማድረግም በምደባዉ ህጋዊነት ላይ ተገቢዉን መወሰን ይችሉ ነበር፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ከምደባ ጋር በተያያዘ በህግ የተዘረጋዉን ሥርዓት ተከትሎ ቅሬታቸዉን አቅርበዉ መብታቸዉን ማስከበር እየቻሉ፣ በመመሪያ ክለሳ ዳኝነት ሰበብ አስቀድሞ በመመሪያ መሠረት በተጠሪ የተሰጠዉ ምደባ እንዲሰረዝ የሚያቀርቡት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለዉ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መመሪያ በአዋጁ የተመለከተዉን ሥርዓት የተከተለ አለመሆኑን አረጋግጦ መመሪያዉ እንዲሻር በማለት፣ በሌላ በኩል መመሪያዉን መሰረት በማድረግ በተጠሪ የተደረገዉ ምደባ ሊሰረዝ አይገባም በማለት በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ በአዋጁ አንቀጽ 57(4) ላይ የተመለከተዉን ግልጽ ድንጋጌ ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 261985 ሚያዝያ 19 ቀን 2013 ዓ.ም በወለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 209483 ሐምሌ 06 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

ማ/አ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 214184
ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1ኛ. መ/ር ገመቹ ቹዋታ
2ኛ. ተማሪ ከድር አለሙ
3ኛ. ተማሪ ጃፓን ኡጁሉ
4ኛ. ተማሪ ኡቦንግ ኡጊድ
5ኛ. ተማሪ ዌካ ኡጁሉ
ተ/ጠ ፊርአን ማስረሻ- ቀረቡ

ተጠሪ፡- የጋምቤላ ብ/ክ/መ/ ጠ/ዓ/ህግ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ ከባድ የሰው ግድያ ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በጋምቤላ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 01056 በቀን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሐምሌ 29/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በቀን ታህሳስ 15/2013 ዓ.ም በጻፈው የወንጀል ክስ በአሁን አመልካቾች እና በሌሎች 6ኛ፣7ኛ እና 8ኛ የስር ተከሳሽች ላይ በጋምቤላ ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ የመጀመሪያ ክስ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ድ.ሪ ወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/፣ 37/1/ሀ እና 539/1/ ን በመተላለፍ አመልካቾች በክሱ በተገለፀው ልዩ ቦታ፣ቀንና ሰዓት 1ኛና 2ኛ አመልካቾች ከስር ተከሳሾችና ከሌሎች አመልካቾች ጋር በመገናኘት 2ኛ አመልካች ለግል ተበዳይ ተማሪ ቤር አጆክ ስልክ በመደወል ቴድባሌ ወደሚባል ሰፈር በመውሰድ አንገቷን ቆርጠው ህይወቷ ካለፈ በኋላ ሞተር ሳይክል እንዲመጣ ለ3ኛ አመልካች ደውለው ሬሳውን በሞተር ሳይክል ጫካ ውስጥ የጣሉ መሆኑንና አባሪ ተባባሪ በመሆን የግድያ ወንጀል የፈጸሙ መሆኑን በመጥቀስ የከሰሰ ሲሆን፣ ሁለተኛው ክስ በ2ኛ፣ 3ኛ 4ኛና 5ኛ አመልካቾች ላይ የቀረበ ሲሆን በ1996 ዓ.ም በወጣውን የኢፌድሪ ወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና አንቀጽ 841/1//1 ን በመተላለፍ ከላይ በተገለፀው ልዩ ቦታ፣ቀንና ሰዓት በፈጸሙት ሬሳ የማንገላታት ወንጀል ክስ ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

አመልካቾች ቀርበው የእምነት ክህደት ቃል የሰጡ ሲሆን ክሱን እንደማይቃወሙና ወንጀሉን ያልፈጸሙና ጥፈተኛ አለመሆናቸውን ገልጸው ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪም እንደ ክሱ ያስረዱልኛል በሚል 3 ምስክሮችን ያቀረበ ሲሆን ምስክሮችም 1ኛ ምስክር የማረሚያ ቤት ፖሊስ መሆናቸውን ገልጸው 1ኛ፣2ኛ፣4ኛና 5ኛ አመልካቾች ሬሳ ሲሸከሙ ያዩ መሆኑን፣ 4ኛ አመልካች ለ3ኛ አመልካች ስልክ ደውሎ ሞተር ሳይክል እንዲያመጣ እንዳዘዘውና 3ኛ አመልካች ከመጣ በኋላ ሬሳ ሲያይ የደነገጠ መሆኑን፣ 1ኛ አመልካች በቢላዋ ያሥፈራራው መሆኑን፣ 2ኛ እና 4ኛ አመልካቾች በሌላ ሞተር ሲከተሉ 5ኛ የስር ተከሳሽ ከሬሳ ኋላ ተጭኖ በ3ኛ አመልካች አሽከርካሪነት ሬሳ ይዘው የሄዱ መሆኑን፣ 1ኛ አመልካች ወደ መጣበት ግቢ መሄዱን ተደብቀው የተከታተሉት መሆኑን አስረድተዋል፣ 2ኛ ምስክር በበኩሏ ሟች ጓደኞቿ ጋር ወደ ቀበሌ ስትሄድ እንዳየቻትና በኋላ የሟች ጓደኞች ደውለው አልመጣችም ወይ እንዳሏትና ካልመጣች ቅድም መድሃኒት ቤት መድሃኒት ልግዛ ብላ ነው የሄደችው እርጉዝ በመሆኗ መድሀኒት ገዝታ ወደጫካ ሳትሄድ አትቀርም ጫካ ፈልጓት ያሏት መሆኑን አስረድታለች፣ 3ኛ ምስክር ደግሞ 2ኛ አመልካች የራሱ ሰልክ ሳንቲም የሌለውና ስልክ እንዲያስደውለው ጠይቆት ስልኩን ከሰጠው በኋላ አይነሳም ብሎ መጨረሻው 47 ቁጥር ነው ከደወለ በኋላ የመለሰለት መሆኑን ከተደወለ መልስልኝ ስላለውና ስልኩ ስለተደወለ መልሶ የሰጠውና ራቅ ብሎ ማውራት የጀመረ መሆኑን ገልጸ መስክሯል፡፡ እንዲሁም የህክምና ማስረጃ ሟች ተኝታ የታረደችና በቢላዋ መሞቷን የሚገልጽ በፎቶ የተደገፈ ማስረጃ የቀረበ መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

ክሱን የያዘው ፍ/ቤትም አመልካቾች ክስ የቀረበበትን የወንጀል አንቀጽ መስፈርት በሚያሟላ መልኩ ወንጀሉን መፈጸማቸውን በቀረቡት ምስክሮች እና ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል በሚል በተከሰሱበት

የወንጀል ድንጋጌ ተከላከሉ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡በዚሁ አግባብ የተሰሙት የመከላከያ ምስክሮች የተሰሙ ሲሆን የአመልካቾች የመ/ ምስክሮች የተጠሪን ማስረጃ ሙሉ በሙሉ ሊያስተባብሉ ያልቻሉ መሆናቸውን ፍ/ቤቱ ገልጾ አመልካቾችን በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ ብሎ 1ኛና 2ኛ አመልካቾች ዋና ወንጀል አድራጊ በመሆናቸው እያንዳንዳቸው በ25 ዓመት ጽኑ አስራት፣ 3ኛና 4ኛና 5ኛ አመልካቾች ደግሞ ሬሳ በማንገላታት ወንጀል እያንዳንዳቸው በ18 ዓመት ጽኑ እስራት፣ እንዲሁም አመልካቾች እያንዳንዳቸው በብር 10,000.00 (አስር ሽህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡ ይህ ውሳኔ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት ፀንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ነሐሴ 20/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም በስር ፍ/በት በሰው ምስክር በተገለጸውና በህክምና ማስረጃ በተገለጸው መሰረት ማንነቱ ባልታወቀ ግለሰብ ተገድላ የተገኘችውን የግል ተበዳይ በተመለከተ ምስክሮች የሚያስረዱትና ወንጀሉ የተፈጸመው ቀን የሁለት ቀን ልዩነት ያለው መሆኑን፣ የተጠሪ ክስ አቤቱታ የወንጀል ህግ ቁጥር 539/1/ ን የማያሟላና አገዳደሉ መሳሪያ ያልተጠቀመ፣ ከሀዲነት ወስላታነት እና ወንጀልን ሞያው ባደረገ ሰው ወንጀሉ ያልተፈጸመ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የስር ፍ/ቤት ይህን ሳያረጋግጥ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን፣ በስር ፍ/ቤት ከተዘረዘሩት ሙሉ ተሳትፎ ካላቸው ተከሳሾች ሶስቱን ነጥሎ በማውጣት የህግ አንቀጽ ሳይጠቅስ በገንዘብ መቀጮ መወሰኑ ህጉን ያላገናዘበ መሆኑን፣ የተጠሪ 1ኛ ምስክር የጋምቤላ ክልል ማረሚያ ቤት ፖሊስ ስትሆን ወንጅል ሲፈጸም አይቻለው ካለች እንዴት እጅ ከፍንጅ ለመያዝ አልሞከረችም ወይም ስልክ ደውላ ለማስያዝ አልሞከረችም የሚለውን የስር ፍ/ቤት በዝምታ ያለፈው መሆኑን፣ 2ኛ አመልካች ስልክ ለሟች ስለመደወሉ ሳይመሰከርበት የተወሰነበት መሆኑን፣ የዓ/ህግ ምስክር እርስበርሱ የተቃረነና የሟችን አስከሬን ሲወስዱ አንዱ በ1 ሳይክል ሌላው በሶስት ሳይክል በማለትና የተለያየ ሰዓት የገለጹ ሲሆን ፍ/ቤቱ ይህን ሳያገናዝብ ውሳኔ ያሰተላለፈ መሆኑን፣ ወንጀሉ ህጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን የሚያሟላ አለመሆኑን ገልጸው የስር ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ማስተላለፋቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት መሆኑ ጠቅሰው እንዲሻርላቸው በማመልከታቸው ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾች የወንጀል ህግ ቁጥር 32/1/ሀ/፣ 37/1/ እና 539/1/ ን በመተላለፍ ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ፈጽመዋል በሚል የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የተረጋገጠበት አግባብነት ከመሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር ለመመርመር ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን የካቲት 21/2014 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ አመልካቾች ወንጀሉን ስለመፈጸማቸው በስር ፍ/ቤት ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ መልኩ ያስረዱ መሆኑን፣ የሥር 6-8 የተጠቀሱ ተከሳሾች በገንዘብ ብቻ ተቀጡ ለሚለው የወንጀል አፈጻጸሙን አይቶ ፍ/ቤቱ የሕጉን ዓላማ በማሳካት በቅጣት

ማቅለያና ማክበጃ ምክንያት ለይቶ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ይህም ቢሆን በይግባኝ ተሸሮ በ6 ዓመት ጽኑ እስራት የተቀጡ መሆኑን፣ የተጠሪ 1ኛ ምስክር አመልካቾችን እጅ ከፍንጅ መያዝ ይችሉ ነበር ለተባለው ወንጀሉ በረቀቀ መንገድ የተፈጸመ በመሆኑ አስቸጋሪ መሆኑን፣ በክስ ቻርጁ ላይ አንድ ሞተር ሳይክል ተብሎ በማስረጃ ከዛ በላይ መሆኑ የወንጀሉን ከባድነት ከሚገልጽ በቀር የህግ ስህተት የሌለ መሆኑን፣ በተጠሪ የቀረቡት ምስክሮች ተዓማኒና በሚገባ እንደ ክሱ ያስረዱ መሆኑን ገልጸው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸናላቸው መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች በተጠሪ በቀረበባቸው መልስ ላይ በቀን መጋቢት 15/2014 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ ሚች በአመልካቾች ስለመገደሏ የሚያስረዳ ቀጥተኛ ምስክር የሌለና የተጠሪ 1ኛ ምስክር ፖሊስ ሆና እያለ ሲገደል እያየች ለህግ ማቅረብ ሲገባት ከባለሙያ የማይጠበቅ ጉዳይ ሆኖ አስከሬኑ ከቀናት በኋላ ጫካ ሲገኝ እንዲሁም ምስክሯ የሚች ቤተ ዘመድ መሆኗና ሚች በእርሷ ቤት እየኖረች የነበር መሆኑ ሲታይ እምነት የማይጣልበት ምስክርነት መሆኑን፣ ጫካ ውስጥ ተገኘ የተባለው ቢላዋ በፎረንሲክ ያልተመረመረና ሚች ተገድላ ተወሰደች ከሚለው ጋር የሚቃረን መሆኑን፣ ቅጣትን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ምን ያሕል የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ እንደተጠቀመ ሳይገልጽ በደፈናው ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስጀህተት መሆኑን ገልጸው ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ከሰበር ቅሬታው አኳያ እና ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ይዘት አንፃር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል፡፡በመሰረቱ በኢፌዲሪ ህግ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10(1) እንደተመለከተው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ውስጥ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ በሰበር አይቶ የማረም ነው፡፡በዚህ አግባብም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ሰሚነት ስልጣኑን ተግባራዊ ሲያደርግ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በዋነኝነት መነሻ የሚያደርገው ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ማስረጃን የመስማት፣የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶች በዋነኝነትም የጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ1ኛ፣2ኛ፣4ኛ እና 5ኛ አመልካቾች ላይ በክሱ ተጠቅሶ በቀረበው ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጡት 2ኛ ምስክር ሚች ከመሞቷ አንድ ቀን በፊት ሞታ ወደ ተገኘችበት ቦታ ከ4ኛ አመልካችና ከስር 6ኛ ተከሳሽ ጋር ሲሄዱ የተመለከቱ መሆኑን ስላስረዱ፣3ኛ ምስክር ደግሞ 2ኛ አመልካች ድርጊቱ በተፈፀመበት እለት ከቀኑ 10፡00 ስልኬ ገንዘብ የለውም በሚል ምክንያት ስልካቸውን ተውሰው ቁጥሩን ወደማያስታውሱት ስልክ መደወላቸውን ስላስረዱ እና ለጉዳዩ ቀጥተኛ ማስረጃ የሆኑት 1ኛ ምስክር 1ኛ፣2ኛ፣4ኛ እና 5ኛ አመልካቾች በቢላዋ ታርዳ የተገኘችውን የግል ተበዳይን ሬሳ ተሸክመው ሲወጡ የተመለከቱ መሆኑን፣ሬሳውን ለመጣል እንዲረዳቸው ሞተር ሳይክል እንዲጥሉ 3ኛ አመልካችን በስልክ የጠሩት 4ኛ አመልካች ቢሆንም 3ኛ

አመልካች ሬሳ ለመጫን የተጠራ መሆኑን አውቆ ቅሬታ ሲያሰማ 1ኛ አመልካች ቢላዋ በማውጣት አስፈራርቶ ያስጫነው መሆኑን ከሬሳው ጋርም 5ኛ አመልካች በሞተሩ ላይ ከኋላ 5ኛ አመልካች ሲጫን 2ኛ እና 4ኛ አመልካቾች በሌላ ሞተር አስከሬኑን እየተከተሉ የሄዱ መሆኑን ስላስረዱ፣1ኛ፣2ኛ፣4ኛ እና 5ኛ አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ እንዲከላከሉ ብይን ከተሰጠ በኋላ ያቀረቧቸው የመከላከያ ምስክሮች አመልካቾች በቦታው አለመኖራቸውን በሚያሳምን ሁኔታ አለማስረዳታቸውን በመጥቀስ ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን የመስማት፣የመመርመርና የመመዘን ስልጣናቸውን ተጠቅመው የደረሱበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ሊለወጥ የሚችለው የስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ምዘና ረገድ የፊፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት ከተገኘ ብቻ ሲሆን ይህ ችሎት ባደረገው ምርመራም በስር ፍርድ ቤቶች የተፈፀመ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት ያልተገኘ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች 1ኛ፣2ኛ፣4ኛ እና 5ኛ አመልካቾችን አስመልክቶ በቀረበባቸው ክስ አግባብ የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠታቸው የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፣

3ኛ አመልካችን በተመለከተ ሟችን ወደ ግድያው ስፍራው ከማምጣት ጀምሮ በግፍ እስከመግደሉ ድረስ ያልተሳተፉ መሆኑን፣ከዚህ ይልቅ በስልክ ተጠርተው የመጡ መሆኑን፣በስፍራው በደረሱበትም ወቅት አስከሬኑን ለማጓጓዝ ፍቃደኛ ያልነበሩ ቢሆንም ከ1ኛ አመልካች በደረሳባቸው ማስፈራሪያ ምክንያት በድርጊቱ የተሳተፉ መሆኑን የዐቃቤ ህግ ምስክሮች በግልፅ እያስረዱ ይህም አመልካች በግፍ ግድያው አለመሳተፋቸው በግልፅ እያታየ የሥር ፍርድ ቤት አመልካችን በወ/ህ/አ.539(1) ስር ጥፋተኛ በማለት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው በ3ኛ አመልካች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል 3ኛ አመልካች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወ/ህ/አ.443(1)(ሀ) ስር በሞት ወይም በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ቅጣት የሚያስቀጣ የወንጀል ድርጊትን ባለማስታወቅ የወንጀል ድርጊት ሊሆን ይገባል በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1.የጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.20820 በ17/07/2013 ዓም 1ኛ፣2ኛ፣4ኛ እና 5ኛ አመልካቾችን አስመልክቶ የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔና ይህንን የውሳኔ ክፍል በማፅናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.02925/2013 በ29/10/2013 ዓም የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.01056/13 በ29/11/2013 ዓም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.195(2)(ለ)(2) መሰረት ፀንቷል፡፡3ኛ አመልካች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወ/ህ/አ.443(1)(ሀ) ስር በሞት ወይም በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ቅጣት የሚያስቀጣ የወንጀል ድርጊትን ባለማስታወቅ የወንጀል ድርጊት ሊሆን ስለሚገባ 3ኛ አመልካች ሳያስታውቁ የቀሩትን የወንጀል ድርጊት አሰቃቂነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በህጉ የተመለከተውን ጣሪያ ቅጣት በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ጊዜ ካለ ታስቦ በስድስት ወር

ቀላል እስራት ሊቀጡ ይገባል በማለት በ3ኛ አመልካች ላይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በማሻሻል ወስነናል፡፡

2. 1ኛ፣2ኛ፣4ኛ እና 5ኛ አመልካቾችን አስመልክቶ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መፅናቱን እንዲያውቀው፣ እንዲሁም በ3ኛ አመልካች ላይ ተሻሽሎ በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ አንፃር እንዲያስፈፅም ለማረሚያ ቤቱ የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡

<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁጥር 214179

ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ አብዲ አህመድ ጃማ -- ጠበቃ አጥሉ ሀብታሙ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አምባሳደር ፒተር ገብርኤል
2ኛ. አቶ ዮሴፍ ገብርኤል ጠበቃ አድማሱ መአዛ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካች መስከረም 11 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ.05-1-328/2013 ዓ.ም መጋቢት 30 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልፀው በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ ያደረገ ሲሆን አመልካች በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪዎች ከሳሾች ነበሩ፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ ስንመለከተው ተጠሪዎችና የስር ከሳሾች በአመልካች ላይ በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ በጅጅጋ ከተማ ቀበሌ 05 የሚገኘውን 13838 ካሜ ይዞታ አላግባብ

የያዘባቸው መሆኑን ገልፀው ይዞታውንና ቤቱን ለቆ እንዲያስረክባቸው ላቀረቡት ክስ አመልካች ባቀረቡት መልስ የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ጠቅሶ ያቀረበውን መቃወሚያ ተቀብሎ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት በብይን የዘጋውና ይህ ብይን በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የፀና ቢሆንም ይህንን ብይን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.162536 መስከረም 28 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ፍርድ በመሻር የፋፊን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክር ያስነሳውን መሬት በተመለከተ በአሁን አመልካች እጅ ያለው ምን ያህል ነው? መሬቱ በአሁን አመልካች እጅ ሊገባ የቻለው በምን ሁኔታ ነው? የአሁን አመልካች የገዙት ቤት ነው? ወይስ ባዶ መሬት ነው? ሽያጩ በባዶ ቦታ ከሆነ በይርጋ ክርክር ላይ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት የሚለውንና መሬቱ ወደ አሁን አመልካች ያስተላለፉት ግለሰቦችም ወደ ክርክሩ በማስገባት መሬቱን እንዴት ሊያገኙ እንደቻሉ እንደዚሁም ይዞታው የሚገኝበት የጅጅጋ ከተማ ቀበሌ 05 አስተዳደር በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰራ በማድረግና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችንም ጭምር በማጣራት እንዲወስን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.341(1) መሰረት መዝገቡን ወደ ስር ፍርድ ቤት መልሶታል።

በዚሁ መሰረት የፋፊን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተገቢውን ማጣራት አድርጎ በሰጠው ውሳኔም በመ/ቁ.550/1985 በቀን 18/01/1986 ዓ.ም ለአሁን ተጠሪዎች በተሰጠው የወራሽነት ማረጋገጫ ውሳኔ መሰረት የአሁን ተጠሪዎች የተወለዱበት የክርክሩ መነሻ የሆነውን 13938 ካ.ሜ መሬት የአሁን ተጠሪዎች ነው ሲል በአብላጫ ድምጽ ፍርድ የሰጠ ሲሆን የአሁን አመልካች 500 ካ.ሜ የሆነውን 3 ክፍል ቤቶች የተሰራበት መሬት በሕጋዊ መንገድ በሽያጭ ያገኘው ስለሆነ ይዞታው የአሁን አመልካች ነው በማለት ወስኗል።ይህ ውሳኔ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ፀንቷል።

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም የፋፊን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይዞታው የሚገኝበት ቀበሌ ይዞታው የማን እንደሆነ እንዲያጣራ በጠየቀው መሰረት በቁ.QX05/483/2013 በቀን 2/4/2013 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ከተሰጠው መልስም ሆነ ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ላይ ከገለጸው ሐተታ ወይም ፍሬ ነገር ላይ መረዳት የሚቻለው አከራካሪው ይዞታ ከ3 ክፍል ቤቶች ጋር በሕጋዊ መንገድ አራዶም ሀጎስ ከተባለ ግለሰብ ላይ እንደገዛው እና በአሁን ሰዓትም በአመልካች ይዞታ ስር እንደሚገኝ በውሳኔው ላይ በገለፀበት ሁኔታ ተጣርቶ እና ተረጋግጦ የቀረበውንም የመንግስት የሰነድ ማስረጃ ያለ በቂ ምክንያት እና በሌላ የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ ተጠሪዎች አቅርበው ባላስተባበሉበት ሁኔታ ውድቅ አድርጎ የሰጠው እና በተዋረድ ያፀናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ስለሆነ እንዲታረምልኝ።

የፋፊን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጅጅጋ አስተዳደር ጽ/ቤትን የመሬቱን ስፋት ለክቶ እንዲያቀርብ እና ባለይዞታውንም አረጋግጦ እንዲያቀርብ የጠየቀው ሲሆን ጽ/ቤቱም በቁጥር A2/2116/390/13 b16/4/2013 ዓ.ም በተፃፈው ከሰጠው መልስ እና ፍርድ ቤቱም በውሳኔው ላይ ካሰፈረው ፍሬ ነገር ላይ መረዳት የሚቻለው አከራካሪው ይዞታ የአመልካች መሆኑን እና ስፋቱ 13983 ካ.ሜ ነው የሚል

ነው ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱ ይህንን አግባብነት እና ተቀባይነት ያለውን የመንግስት ሰነድ እና ማስረጃ አጣርቶ ያገኘውን ውጤት አለግባብ ውድቅ አድርጎ 13983 ካ.ሜ የተጠሪዎች ነው 500 ካ.ሜ ደግሞ የአመልካች ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ክስ የቀረበበት 13983 ካ.ሜ መሆኑ እየታወቀ እና ተጣርቶ ከቀረበው ጋር ሲነፃፀር ደግሞ የ100 ካ.ሜ የትርፍ ቦታ ልዩነት መኖሩ እየታወቃ አለግባብ የተጠሪ ነው በማለት ክስ ባልቀረበበት እና ክርክር ያልተደረገበትን መሬት ለተጠሪዎች መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ስለሆነ እንዲታረምልኝ፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ.162536 ላይ በቀን 28/1/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክርክሩ ሁከት ይወገድልኝ የሚል ሳይሆን የመፋለም ክርክር ነው በማለት ውሳኔ በሰጠበት ሁኔታ እና ይዞታውን በተመለከተ ግን በማን እጅ እንደሚገኝ ከክፍሉ ቀበሌ አረጋግጦ እንዲወስን ጭብጥ ተይዞ የተመለሰለትን ነጥብ ተጣርቶ በቀረበው የሰነድ ማስረጃ መሰረት መወሰን ሲገባው ማስረጃውን አለግባብ ውድቅ በማድረግና የተጠሪዎች ከሆነው 500 ካ.ሜ ውጪ ሌላ መሬት አለ ወይስ የለም? ካለስ ተጠሪ የፈጠረው የሁከት ተግባር አለ ወይስ የለም? የሚል ተጨማሪ ጭብጥ በመያዝ ክርክሩን ለመወሰን እንደሞከረ ውሳኔው ያስረዳል፡፡ይሁን እንጂ ተጠሪዎች ያቀረቡት ይዞታው 18838 ካ.ሜ እንደሆነ ሲሆን በጅጅጋ ከተማ አስተዳደር በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት አጣርቶ እና አረጋግጦ ያቀረበው 18938 ካ.ሜ እንደሆነ ነው፡፡ በመሆኑም በክስ ከቀረበው እና በትዕዛዝ በተረጋገጠው መሰረት የ100 ካ.ሜ የቦታ ልዩነት መኖሩን በተረጋገጠበት ሁኔታ የአመልካች ይዞታ 500 ካ.ሜ ብቻ ስለሆነ አመልካች ከ500 ካ.ሜ ውጪ በሆነው በተጠሪዎች መሬት ላይ የፈጠረውን ሁከት እንዲያቆም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1149(1) መሰረት በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሳኔና በተዋረድ በይግባኝ ሰሚው እና በሰበር ሰሚው ችሎት የፀናው ውሳኔ በሌለ ክርክር ላይ የተሰጠ እና መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ተብሎ እንዲሻርልኝ እና በሃሳብ ልዩነት ላይ ተመስርቶ በአንድ ዳኛ በተሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያየ ጊዜ በተለያዩ መዝገቦች ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር አገናዝቦ ውሳኔ እንዲሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካች ለክርክሩ መነሻ ሆነውን ይዞታ በሕጋዊ መንገድ ከመንግስት ካገኙት አቶ አራዶም ሀጎስ ከሚባሉ ግለሰብ በግዥ ያገኙት ስለመሆናቸውና ይዞታው በአመልካች ተይዞ የሚገኝ ስለመሆኑ ከሚመለከተው የጅጅጋ ከተማ ቀበሌ 05 ተጣርቶ ቀርቦ እያለ ይዞታው የከሳሾች ነው በሚል የተወሰነበት አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪዎች በሰጡት መልስም ይህ ችሎት በመጀመሪያ ዙር የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡትን ውሳኔዎች በመሻር እና በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 341 መሰረት መታየት ያለባቸውን በነጥብ አስቀምጦ ወደ ስር ፍርድ ቤት ስለመለሰው የስር ፍርድ ቤቶችም በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት አጣርተው የፋፊን ዞን ከፍተኛ

ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ.052-104/2009 ግራና ቀኞችንን አከራክሮ በ28/04/2013 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ እንደገለፀው ግራና ቀኞችን የምንከራክርባቸውን ጭብጦች በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.246 መሰረት ለይቶ እንዲሁም በማስረጃ ላይ ተመስርቶ አስፈላጊውን ሁሉ ማጣራት ካደረገ በኋላ ተገቢውን ፍርድ ሰጥቶ ይህ ውሳኔ በየደረጀው ባሉ ፍርድ ቤቶች የፀና በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡በመሰረቱ አንድ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አወሳሰን የጠራ ፍሬ ነገር የሌለ መሆኑን ከተገነዘበ ይኸው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት ሁሉ ማድረግ እንደሚችል ከፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.136፣137፣272 እና 345 ድንጋጌዎች ለመረዳት የሚቻል ሲሆን ለጉዳዩ አወሳሰን መሰረት የሚሆንን ፍሬ ነገር በማስረጃ ሳያጣሩ መወሰን አግባብ ባለመሆኑ በክርክሩ የቀረቡት ማስረጃዎች በቂ ባልሆኑበት ጊዜ እና እነዚህን ማስረጃዎች ብቻ መሰረት አድርጎ መወሰን ፍትህን የሚያዛባ ከሆነ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ምስክር እንዲቀርብ መታዘዝ ያለበት ስለመሆኑ በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 72980፣22603 እና በሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

በመሰረቱ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.162536 ሊጣሩ ይገባቸዋል በሚል ከዘረዘራቸው ጭብጦች መሃል አመልካች ከአቶ አራዶም ሀጎስ የገዙት ቤት ያረፈበት 500 ካሜ እንደሆነ በአግባቡ የተጣራ ቢሆንም በአመልካች ከዚህ 500 ካሜ በማለፍ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትን ይዞታ መያዝ አለመያዘቸው እንዲጣራ በታዘዘው አግባብ የስር ፍርድ ቤት የደረሰበትን መደምደሚያ ስንመረምረው የፋፊን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አብላጫው ድምፅ በአመልካች እጅ የሚገኘው 500 ካሜ ብቻ መሆኑን በስፍራው በመገኘት ማረጋገጡን ሲገልፅ፣የልዩነት ሀሳቡ አመልካች አከራካሪውን ይዞታ መያዛቸውን ፍርድ ቤቱ ማረጋገጡን መግለፁ፣አብላጫው ድምፅ ከከተማ አስተዳደሩ የመሬት አገልግሎት ፅ/ቤት በ14/04/2013 ዓም የተሰጠው ምላሽ አከራካሪው ይዞታ 13938 ካሜ መሆኑን ብቻ እንደገለፀ ሲያመለክት፣የልዩነት ሀሳቡ ከአስተዳደር አካለ በ16/04/2013 ዓም የመጣው ምላሽ በአመልካች እጅ 13983 ካሜ የሚገኝ መሆኑን ማረጋገጡን የሚጠቅስ መሆኑን ማሳየቱ፣ከክፍለ ቀበሌ የመጣው ምላሽ ለአመልካች በአቶ አራዶም ሀጎስ ስለተሸጠው ይዞታና በይዞታው ላይ ስለሰፈሩት ቤቶች ብቻ የሚያመለክት መሆኑን አብላጫው ድምፅ በውሳኔው ላይ ሲያመለክት፣የልዩነት ሀሳቡ የቀበሌው ምላሽ አከራካሪው ይዞታ በአመልካች እጅ የሚገኝ መሆኑን ጭምር ያረጋገጠ መሆኑን በልዩነት ሀሳቡ ላይ ማመልከቱ አከራካሪው ይዞታ በማን እጅ ይገኛል?የሚለውን መሰረታዊ ጭብጥ አስመልክቶ ፍርድ ቤቱ የጠራ ነጥብ ላይ ሳይደርስ ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት መስጠቱን ያሳያል፡፡

ይህ ነጥብ በአግባቡ ከተጣራ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ባደረገው ማጣራት አከራካሪው ክስ የቀረበበት 13838 ካሜ ቦታ በአመልካች እጅ የማይገኝ ከሆነ ውጤቱ ምን ሊሆን ይገባል?አከራካሪው ይዞታ በአመልካች እጅ የሚገኝ ከሆነ ፤ይህ ይዞታ በአመልካች እጅ በምን አግባብ ገባ? እንደ አመልካች ክርክር በተገቢው የአስተዳደር አካል ለአመልካች ተሰጥቷቸዋል?ወይስ አልተሰጣቸውም? ተሰጥቷቸዋል ከተባለ ምን ያህል እና መቼ ተሰጣቸው? ለይዞታው የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አላቸው? ወይስ የላቸውም? አመልካች ይዞታውን በአስተዳደር አካሉ ተሰጥቷቸው ለይዞታውም የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ከሆነ ተጠሪዎች በዚህ ይዞታ በህጉ አግባብ የተረጋገጠ መብት ነበራቸው? ወይስ አልነበራቸውም? ካልነበራቸው ውጤቱ ምን ሊሆን ይገባል? በአከራካሪው ይዞታ ላይ በህጉ አግባብ የተረጋገጠ መብት እያላቸው የአስተዳደር አካሉ ይዞታውን ለአመልካች ካስተላለፈስ ውጤቱ ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉትን ነጥቦች በማጣራት ለግራ ቀኙ ክርክር የማያዳግም እልባት ሊሰጥ ሲገባ ተገቢውን ማጣራት ሳያደርግ፤ ከአስተዳደር አካለት የቀረቡት ምላሾችም የተለያዩ ከሆነ በተጨማሪ ማጣራት አድርጎ ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት ሊሰጥ ሲገባ ይህንን ሳያደርግ ተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ ካቀረቡበት 13838 ካሜ በላይ አመልካች ለተጠሪ እንዲያስረክቡ መወሰኑና ይህ ውሳኔ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች መፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 052-104/2009 ቀን 28/04/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአብላጫው ድምፅ የሠጠው ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.05-1-195/13 በቀን 30/07/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.05-1-328/13 በቀን 16/10/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ከላይ ከተመለከቱት ዝርዝር ጭብጦች አንፃር እና ከሌሎች ተያያዥ ነጥቦች አንፃር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የአስተዳደር አካላት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ፤በተገቢው ባለሙያ የተደገፈ ምልከታ በማድረግ፤አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም የይዞታውን ማህደር በማስቀረብና ባለሙያዎችን በችሎቱ አስቀርቦ በመስማት በህጉ አግባብ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ሰላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

አ/መ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ.መ.ቁ.214136

ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካቾች፡.....1. አቶ ደለሳ ጅማ -- ቀረቡ

2. አቶ ጌቱ አበበ ቱጂ -- ቀረቡ

3. አቶ አዳነ ነጊያ ደንቦባ

4. አቶ ጌቱ ይመር ዋኬኔ } አልቀረቡም

5. አቶ ሸምሱ ሲፋ ሁሴን

6. አቶ በድሩ ሃምዛ ቡሽራ -- ቀረቡ

7. አቶ ሃይሉ ቤኛ ጉደታ -- አልቀረቡም

8. አቶ ተሾመ ደምሴ ምህረቱ -- ቀረቡ

9. አቶ ከማል ሸፋ እንቁ

10. አቶ ዘይኑ አሊ አማን } አልቀረቡም

11. አቶ ተሻለ ፍቃዱ ናዶም -- ቀረቡ

12. አቶ ጸጋዬ ጉደታ አለጋ

13. ወ/ሮ ቦጋለች ደሴ አርጌ } አልቀረቡም

ተጠሪ፡...ኮልፌ ቅዱስ ራጉኤል አዲስ ሕይወት አክስዮን ማህበር-- ጠበቃ ሲሳይ መኮንን ቀረቡ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

ይህ የማህበር አባልነት ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ተከሳሾች፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ፣ በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት እነ አቶ አምሳሉ ባህሩ የሥር ጣልቃ ገቦች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ

ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.269920 ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ ተከሳሾች የከሳሽ ማህበር አባላት ሁኖ የሚጠበቅባቸዉን ክፍያዎችን ባለመፈጸማቸዉ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሰኔ 19 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ከማህበሩ እንዲሰናበቱ የወሰነ ሲሆን፣ ተከሳሾች ይህን ዉሳኔ ለማሰረዝ ክስ አቅርበዉ ዉድቅ የሆነባቸዉ ሲሆን፣ በዚህ ዉሳኔ መሰረት ለማስፈጸም ሰኔ 10 ቀን 2010 ዓ.ም በተደረገዉ ጠቅላላ ጉባኤ ክፍያ ያልከፈሉ አባላት ክፍያዉንና ቅጣቱን በሁለት ወራት ዉስጥ እንዲከፍሉ፣ ይህ ካልሆነ ሱቆቻቸዉ ወደ ማህበሩ በማስገባት ክፍያዉ ተሳስቦ እንዲከፈላቸዉ የተወሰነ በመሆኑ፣ ተከሳሾች ዉሳኔዉን ለማሰረዝ ክስ አቅርበዉ ዉድቅ የሆነቸዉ ስለሆነ፣ ተከሳሾች አልከፈሏቸዉም ያለዉን ክፍያዎች በመዘርዘር፣ በጠቅላላ ጉባኤዉ ዉሳኔ መሰረት ከማህበሩ አባልነት እንዲወጡ ወይም እንዲሰረዙ እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል።

ተከሳሾች በዚህ ክስ ላይ ባቀረቡት መልስ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሰኔ 19 ቀን 2008 ዓ.ም ተከሳሾች ከማህበሩ አባልነት እንዲሰረዙ በማለት የወሰነዉ ሥራ አልዋለም፤ ሰኔ 10 ቀን 2010 ዓ.ም የተወሰነዉ ዉሳኔ የቀደመዉን ዉሳኔ የሚሽር ነዉ፤ ተከሳሽ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔ እንጂ በማስታወቂያ ከማህብሩ ሊወጡ እንደማይገባ፤ ከሳሽ የጠቀሳቸዉ ክፍያዎች የተከፈሉትን ክፍያዎችንና የተዋጡ መዋጮዎችን ታሳቢ ያላደረገ ነዉ፤ ከማህበሩ ጋር በነበረዉ ዉይይት የማህበሩ ሂሳብ በባለሙያ ተጣርቶ እዳ ያለባቸዉ እንዲከፍሉ፣ ክፍያዎችን መክፈል ያልቻሉትን ደግሞ ማህበሩ ትብብር አድርጎላቸዉ ከአበዳሪ ተቋማት ብድር ወስደዉ እንዲከፍሉ ስለተባለ በዚህ አግባብ ትብብር እንዲደረግልን፤ ተከሳሾች ከማህበሩ ሊወጡ ይገባል የሚባል ከሆነ እንኳን የማህበሩ ሂሳብ አዲት ተደርጎ ድርሻችን ተከፍሎን ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር ባሳለፈዉ ዉሳኔ የከሳሽ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩ አባላት የሆኑት ተከሳሾች የግንባታና የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ በወሰነዉ መሰረት መክፈል ያለመቻላቸዉን ተከሳሾችም ያመኑ ጉዳይ ሲሆን፣ ተከሳሾች በዚህ አግባብ መክፈል ባለመቻላቸዉ ሰኔ 19 ቀን 2008 ዓ.ም በተደረገዉ ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነ ቢሆንም በዚህ መሰረትም መክፈል ስላልቻሉ፣ ሰኔ 10 ቀን 2010 ዓ.ም በተደረገዉ ጠቅላላ ጉባኤ በሁለት ወራት ጊዜ ዉስጥ እንዲከፍሉ ካልሆነ ሱቆቻቸዉ ወደ ማህበሩ ገቢ ተደርገዉ ያላቸዉ ሂሳብ ተሰልቶ እንዲከፈላቸዉ የተወሰነ ሲሆን፣ ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ መሰረትም ግዴታቸዉን አልተወጡም። ተከሳሾች እነዚህን የጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔዎችን ለማሻር ክስ አቅርበዉ ዉድቅ የተደረገባቸዉ መሆኑን በግራ ቀኙ የታመነ እና በማስረጃም የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፤ ተከሳሾች አሁን የጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔ ዉድቅ ነዉ በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለዉም፤ የጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔ ለማሻር የሚያስችል የሕግ መሰረት የለም፤ ተከሳሾች የሚጠበቅባቸዉን ግዴታቸዉን ሙሉ በሙሉ ያልተወጡ በመሆናቸዉ ከማህበሩ ሲወጡ ሊከፈላቸዉ ስለሚገባዉ ክፍያ ማጣራት

ስለሚኖር በዚህ አግባብ መብታቸዉ የሚጠበቅ በመሆኑ በዚህ ደረጃ ሂሳብ ማጣራቱ ተገቢ አይደለም፡፡ በዚህ መሰረት ተከሳሾች በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔዎች መሰረት ግዴታቸዉን ሊወጡ ባለመቻላቸዉ ከማህበሩ አባልነት እንዲወጡ የተወሰኑ በመሆኑና ዉሳኔዉን የሚያሽር በቂ ምክንያት ባለመገኘቱ በዉሳኔዉ መሰረት ተከሳሾች ከማህበር አባልነታቸዉ እንዲወጡ በማለት ወስኗል፡፡

ተከሳሾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን በትዕዛዝ በመሰረዝ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካቾች በ10/1/2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የተጠሪ ማህበር አመልካቾች ክፍያ ስላልከፈሉ ከማህበሩ አባልነታቸዉ እንዲወጡ በማለት ሰኔ 19 ቀን 2008 ዓ.ም ባደረገዉ ጠቅላላ ጉባኤ የወሰነ ቢሆንም ይህን ለመወሰን ስልጣን የለዉም፤ ስልጣን አለዉ ቢባል እንኳን አሁን ለፍ/ቤት አመልካቾች ከአባልነት ይሰረዙ በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ ዳግመኛ የቀረበ ጉዳይና የክርክር አመራር ጉድለት ያለበት ነዉ፤ አመልካቾች የተለያዩ ክፍያዎችን ስንከፍል የቆየን ቢሆንም ይህን የተከፈለዉን ክፍያ በሂሳብ ባለሙያ እንዲጣራ ሳያደርግ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 3 (ለ) በመጣስ ከማህበር አባልነት እንዲንሰናበት የሰጠዉ ዉሳኔን ፍ/ቤቱም በመቀበል ዳግመኛ ከማህበር አባልነት ተሰናብታቸዋል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ከማህበሩ አባልነት የሚያስወጣን ምንም የህግ ምክንያት የለም ተብሎ እንዲወሰንልን፤ አመልካቾች ከማህበሩ ሊወጡ ይገባል የሚባል ከሆነ ለአመልካቾች ሊከፈለን የሚገባዉ የገንዘብ መጠን የማህበሩ ሀብት ተሰልቶ በከፈልነዉ የገንዘብ መጠን ሊከፈለን ይገባል በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የአሁን አመልካቾች ከማህበሩ አባልነት እንዲሰናበቱ የሥር ፍ/ቤት የወሰነበትን አግባብ ከመተዳደሪያ ደንብና አግባብነት ካላቸዉ የንግድ ህግ ድንጋጌዎች አንጻር ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት መጋቢት 7 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካቾች የሚጠበቅባቸዉን ክፍያዎችን ባለመክፈላቸዉ የተጠሪ ማህበር ከአባልነት እንዲሰናበቱ የወሰነዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ በማለት አመልካቾች ከማህበሩ አባልነት እንዲወጡ ያሳለፉት ዉሳኔ ከሕግ የሚቃረን ስላልሆነ፣ የአመልካቾች ቅሬታ ዉድቅ እንዲደረግልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች በ23/7/2014 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካቾች የተጠሪ ማህበር አባላት መሆናቸዉ፣ አመልካቾች የግንባታ እና የተለያዩ ክፍያዎችን መክፈል ባለመቻላቸዉ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሰኔ 19

ቀን 2008 ዓ.ም ባሳለፈዉ ዉሳኔ ከማህበሩ አባልነት እንዲሰናበቱ መወሰኑን፣ ይህን ዉሳኔ ለማስፈጸም ሲባል የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሰኔ 10 ቀን 2010 ዓ.ም ባሳለፈዉ ዉሳኔ አመልካቾች የሚጠበቅባቸዉን ክፍያዎች በሁለት ወራት ጊዜ ዉስጥ እንዲከፍሉ፣ ይህ ካልሆነ ሱቆቻቸዉ ወደ ማህበሩ ገቢ ተደርጎ ያላቸዉ ሂሳብ ታስቦ እንዲከፈላቸዉ በማለት መወሰኑን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ አመልካቾች በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔ መሰረት ግዴታቸዉን መወጣት ያለመቻላቸዉን በሥር ፍ/ቤት በማስረጃ ከመረጋገጡም በላይ አመልካቾችም ያመኑት ጉዳይ መሆኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች እነዚህ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔዎች ከሕግ ዉጭ የተወሰኑ መሆናቸዉን በመጥቀስ ዉሳኔዎቹ እንዲሰረዙላቸዉ ለፍ/ቤት ክስ አቅርበዉ ክሳቸዉም ዉድቅ የሆነባቸዉ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች የሚጠበቅባቸዉን ክፍያዎች ሳይከፍሉ መቅረታቸዉን መነሻ በማድረግ ከማህበር አባልነታቸዉ እንዲወጡ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የወሰነዉ ዉሳኔ እንዲሰረዝላቸዉ ክስ አቅርበዉ ተቀባይነት ያጠ ሆኖ ሳለ፣ አሁን ጠቅላላ ጉባኤ ያሳለፈዉ ዉሳኔ ከመተዳደሪያ ደንብና ከሕግ ዉጭ ነዉ በማለት ያቀረቡት ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 (1) መሰረት ተቀባይነት የለዉም፡፡ አመልካቾች ግዴታቸዉን ባለመወጣታቸዉ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከማህበር አባልነት እንዲሰናበቱ ያሳለፈዉን ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤቶች በመቀበል አመልካቾች ከማህበር አባልነት እንዲወጡ ወይም እንዲሰረዙ የወሰነዉ የሚነቀፍበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3፣ ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1) መሰረት ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር አመልካቾች ከማህበር አባልነት እንዲንሰናበቱ የተወሰነዉን ዉሳኔ በተመለከተ ያቀረቡት ቅሬታ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የሚያመለክት ባለመሆኑ ቅሬታቸዉ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ነገር ግን አመልካቾች ከማህበር አባልነት እንዲወጡ እስከተወሰነ ድረስ፣ ሊከፈላቸዉ የሚገባዉ የገንዘብ መጠን ምን ያህል ነዉ? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ የተጠሪ ማህበር ሰኔ 10 ቀን 2010 ዓ.ም ባደረገዉ ጠቅላላ ጉባኤ አመልካቾች መክፈል ያለባቸዉን ክፍያዎች በሁለት ወራት ጊዜ ዉስጥ ሊከፍሉ እንደሚገባ ይህ ካልሆነ ሱቆቻቸዉ ወደ ማህበሩ ገቢ ተደርገዉ ያላቸዉ ሂሳብ ተሰልቶ ሊመለስላቸዉ እንደሚገባዉ መወሰኑን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለዉ አመልካቾች ከማህበሩ ሲወጡ ያላቸዉ ሂሳብ ተጣርቶ ሊከፈላቸዉ የሚገባቸዉ ገንዘብ መኖሩ ከተረጋገጠ እንደሚመለስላቸዉ ነዉ፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካቾች ከማህበሩ አባልነት እንዲወጡ ወስኖ ሲያበቃ ሊከፈላቸዉ የሚገባዉን ክፍያ በተመለከተ ከማህበሩ ሲወጡ ሂሳብ ማጣራቱ ስለማይቀር መብታቸዉ በዛ አግባብ የሚጠበቅ ይሆናል በማለት ያሳለፈዉ ዉሳኔ ከማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔ የሚቃረን ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ይህንን ደግሞ የፍትህብሔር ሥነሥርዓት ሕጉ በዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት አጣርቶ መወሰን ይገባል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ያሳለፈዉ ዉሳኔ የሚሻርበት በቂ

ምክንያት የለዉም ያለዉ ተገቢ ቢሆንም፣ ዉሳኔዉን በከፍል በመቀበል ከፍሉን ደግሞ ባለመቀበል ለአመልካቾች የሚከፈለዉ ክፍያ ካለ አሁን ተሰልቶ ሊከፈላቸዉ እንደሚገባ መወሰን ሲገባዉ አጥጋቢ ያልሆነ ምክንያት በመጥቀስ የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካቾች የሚጠበቅባቸዉን ግዴታቸዉን ባለመወጣታቸዉ ከማህበር አባልነት ሊወጡ ወይም ሊሰረዙ ይገባል በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ ተገቢ ቢሆንም ከማህበሩ አባልነት ሲወጡ ግን የሚከፈላቸዉ ክፍያ ካለ ተጣርቶ መወሰን ሲገባዉ ሳይወሰን መታለፉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.276498 ታህሳስ 27 ቀን 2013 ዓ.ም ያሳለፈዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.269920 ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ አመልካቾች ከማህበሩ አባልነታቸዉ እንዲወጡ ወይም እንዲሰረዙ የተወሰነዉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለአመልካቾች ሊከፈላቸዉ የሚገባቸዉ የገንዘብ መጠን በሂሳብ ባለሙያ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ፣ ግራ ቀኙ ሪፖርቱ ላይ አስተያየታቸዉን እንዲሰጡ በማድረግ፣ እንዲሁም ጉዳዩን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ሁሉ በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤቶች አመልካቾች ከተጠሪ ማህበር አባልነት እንዲወጡ ወይም እንዲሰረዙ በማለት ያሳለፉት የዉሳኔ ክፍል አልተነካም ጸንቷል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

አ/መ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ 214108

ቀን፡- 15/4 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ/ዶ/ር

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሣ ወርቁ

ደጀኜ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡- እነ ወ/ሮ ገነት ቶላ /2 ሰዎች/ አልቀረቡም

ተጠሪ/ዎች፡- እነ አቶ ብርሃኑ ቶላ /2 ሰዎች/ 2ኛ ተጠሪ ቀረቡ

መዝገቡ ለችሎት የቀረው 2ኛ ተጠሪ ወ/ሮ ኤልሳቤት አንበርብር ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በዚህ ሰበር ችሎት በክርክር ላይ የምንገኘው በጋራዥ ቤቱ ላይ ሆኖ እያለ በመኖሪያ ቤት ላይ ጨምሮ እግድ የተሰጠበት በመሆኑ ከመኖሪያ ቤቱ ላይ እግድ እንዲነሳልት ስትል አመልክታለች፡፡ የአሁን አመልካቾችም መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ታህሳስ 6 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የአፈፃፀም እግድ የተሰጠው በሚያከራክረን ንብረት ላይ በመሆኑ እግዱ ሊነሳ አይገባም ብለዋል በዚሁ መሰረት ተከታዩ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ትዕዛዝ

በዚህ መዝገብ መስከረም 10 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 162907 ላይ እግድ ተሰጥቷል፡፡ እግዱ የተሰጠው አሁን ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ አዋሳኙ በስሜን አቶ መሀመድ፣ አቶ ገመቹ፣ አቶ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መለስ፣ በምዕራብና በምስራቅ መንገድ፣በደቡብ ከድር ሁሰኔን የሚያዋስኑት ጋራዥ ቤት ላይ ብቻ ሳይሆን የአፈፃፀም መዝገቡ ላይ በመሆኑ በሌሎች ንብረቶች ላይ እየተደረገ ያለ አፈፃፀም ካለ አፈፃፀሙን የሚከለክል መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 162907 በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ አዋሳኙ በሰሜን አቶ መሀመድ፣ አቶ ገመቹ፣ አቶ መለስ፣ በምዕራብና በምስራቅ መንገድ፣ በደቡብ ከድር ሁሰኔ የሚያዋስኑት ጋራዥ ቤት ላይ የተሰጠው የአፈፃፀም እግድ እንዲቀጥል ብለናል፡፡ በሌሎች ንብረቶች ላይ እየተደረገ ያለ አፈፃፀም ካለ በዚህ ችሎት መስከረም 10 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰጠው እግድ ተሻሽሎ ከሌሎቹ ንብረቶች ላይ የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይግፍ መደበኛ ቀጠሮ አልተለወጠም፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁጥር 206083

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ፀሀይ ተፈራ ከጠበቃ ግሩም አየለ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1ኛ. ወ/ሮ ወይንሸት ከበደ
2ኛ. አቶ ሚካኤል ገ/መስቀል } ጠበቃ ሙሉቀን ልመነህ

3ኛ. አቶ ቢኒያም ገ/መስቀል አልቀረቡም

4ኛ. ወ/ሮ እፀገነት ገ/መስቀል - ጠበቃ ሙሉቀን ልመነህ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ክርክሩ የቤት ሽያጭ ውልን መነሻ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽና የከሳሽ ተከሳሽ፤ 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንደየቅደም ተከተላቸው ተከሳሾች፣ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የተከሳሽ ከሳሽ እንዲሁም 4ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ሰኔ 1 ቀን 2010 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ክስ የስር ተከሳሾች በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 154 የካርታ ቁጥሩ 20913 የሆነን ቤት ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል በብር 125,000 ሸጠውልኝ ብር 92,000 ተቀብለው ስመ ሀብቱን ለማዘወውር ተዋውለው ቤቱን ተረክቤያለው፡፡ ነገር ግን ስመ ሀብቱን ሊያዛውሩልኝ ፍቃደኛ ስላልሆኑ ቤቱ የእኔ መሆኑ ተረጋግጦ ስመ ሀብቱን እንዲያዛውሩልኝ እንዲሁም ወጪ እና ኪሳራ እንዲተኩልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

3ኛ ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው መልስ የማቅረብ መብታቸው የታለፈ ሲሆን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ሰኔ 27 ቀን 2010 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበው መቃወሚያው በብይን ታልፏል፡፡ በፍሬ ጉዳይ ላይ በሰጡት መልስ ውሉ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ስለሆነ ረቂቅ ነው፡፡ ቤቱ ቢገመት የሽያጭ ውሉ ሲደረግ ከነበረው ዋጋ በላይ ስለሚሆን በፍ/ሕ/ቁጥር 1710(2) መሰረት የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ የሀሳብ ጉድለት ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡ የሽያጭ ውሉ በተደረገበት ጊዜ የቤቱ ስመ ሀብት በ1ኛ ተጠሪ ባለቤት እና በ2ኛ ተጠሪ አውራሽ አቶ ገብረመስቀል እንዳለ ስም ስለነበር ተጠሪዎች ቤቱን በራሳቸው መሸጥ በማይችሉበት ሁኔታ የተደረገ ውል ነው፡፡ እንዲሁም ቤቱ ሲሸጥ 2ኛ ተጠሪ 18 አመት ሳይሞላኝ እና 1ኛ ተጠሪ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለመሸጥ የሚያስችል የሞግዚትነት ስልጣን ሳይኖራቸው የሽያጭ ውሉ የተደረገ በመሆኑ፤ በፍ/ሕ/ቁጥር 1013(3) መሰረት የውርስ ሀብትን ያለ ጋራ ስምምነት ማስተላለፍ ስለማይቻል እና ሌሎች የሚመለከታቸው ወራሾች ስላሉ ስመ ሀብቱ እንዲዞር የቀረበው ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

4ኛ ተጠሪ ሰኔ 27 ቀን 2010 ዓ.ም ባቀረቡት የጣልቃ ገብነት አቤቱታ የሚች አቶ ገብረመስቀል እንዳለ ወራሽ መሆኔ ሐምሌ 25 ቀን 1992 ዓ.ም በፍርድ ተረጋግጧል፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ሽያጭ እኔ ሳላውቅ እና ፍቃዴን ሳልሰጥ የተከናወነ እንዲሁም መሸጡን ላውቅ የምችልብት ሁኔታ ስላልነበረ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንድገባ ይፈቀድልኝ በማለት ጠይቀው ተፈቅዶላቸው ቤቱ 1ኛ ተጠሪ እና ሚች ከመጋባታቸው ከ1971 ዓ.ም በፊት የተፈራ የሚች የግል ሀብት ስለሆነ እና በሽያጩም ስላልተስማማው የሚች ልጆች ከሆኑት የስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጋር እኩል እንድንካፈል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

በሌላ በኩል 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ሰኔ 27 ቀን 2010 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውሉ ሲደረግ 2ኛ ተጠሪ ለአካለ መጠን ያልደረሰ፤ የተጣለበትን የሕግ ክልከላ በመተላለፍ የሽያጭ ውሉ የተደረገ እና 1ኛ ተጠሪ ስለ 2ኛ ተጠሪ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለመሸጥ ስልጣን ሳይኖራቸው እንዲሁም ሌሎች ወራሾች ሳይስማሙ የተፈፀመ የሽያጭ ውል ነው፡፡ ቤቱም ሊያወጣ ከሚችለው አምስት ሚሊዮን ብር በታች በብር 125,000 መሸጡ ለሕግ እና ሞራል ተቃራኒ ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 1710(2) መሰረት የፈቃድ ጉድለት

አለበት፡፡ በመሆኑም ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውል እንዲፈርስ እና አመልካች ቤቱን ለ12 ዓመታት ይዘው ሲገለገሉበት ስለቆዩ ያለፉት 2 ዓመታት የኪራይ ገንዘብ በወር ብር 10,000 ታስቦ በድምሩ ብር 120,000 እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በጣልቃ ገብ አቤቱታ ላይ በሰጡት መልስ ጣልቃ ገብ የቤቱ መሸጥ ላይ በ1ኛ ተጠሪ በኩል ፍቃዳቸውን የገለፁልኝ ስለሆነ ፍርድ ቤት ቀርበው በቃለ መኃላ ያረጋግጡልኝ፤ ቤቱ በሀራጅ ከተሸጠ ዋጋው ዝቅተኛ ይሆናል በሚል ስጋት በጊዜው ያወጣል በተባለው ዋጋ ሸጠውልኛል፤ ድርሻቸውን ከመጠየቅ በዘለለ ሽያጩን ሊቃወሙ አይችሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በተጨማሪም በቀረበባቸው የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ ላይ በሰጡት መልስም 2ኛ ተጠሪ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ቢሆንም ሞግዚቱ 1ኛ ተጠሪ ንብረት ለመሸጥ ባላቸው ስልጣን አማካኝነት ውሉ ተፈርሞ ፀድቋል፡፡ የሀራጅ ሽያጩን አስቀርተው በድርድር መሸጣቸውም የንግድ ችሎታቸውን የሚሳይ እንጂ የገበያ ዋጋውን በማያውቁበት ሁኔታ የተደረገ ሽያጭ ነው አያስብልም፤ የፍ/ሕ/ቁጥር 1013(3) ም ለክርክሩ ተገቢነት የለውም፤ ውሉን ከተፈራረምን በኋላም የስር ተከሳሾች ወኪል ደረሰኝ እና የቤቱን ሰነዶች ሰጥተውኝ ቤቱን የተረከብኩ ስለሆነ ክሱ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ በአመልካች እና በስር ተከሳሾች መካከል ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም ውል መደረጉ አልተካደም፡፡ የቀረበው ካርታ በስተጀርባው ወደ ተከሳሾች ዞሯል፤ በመሆኑም ውሉ በሕግ ተቀባይነት ያለው እንጂ ረቂቅ ነው ሊባል አይችልም፡፡ ቤቱም በሀራጅ ሊሸጥ ሲል በድርድር መሸጣቸው የተከሳሾችን የገበያ እውቀት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ እንጂ የገበያ ዋጋ አለማወቃቸውን አያሳይም ነገር ግን አመልካች ቤቱን የገዙት የቤቱ ስመ ሀብት በካርታው ጀርባ ላይ ለተጠሪዎች ሳይዞርላቸው እና በፍ/ሕ/ቁጥር 1195 መሰረት ካርታ ሳይሰራላቸው መሆኑን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ 4ኛ ተጠሪ ሽያጩ ላይ ፍቃዳቸውን ያልሰጡ ስለሆነና ወራሾች ተስማምተው የተፈጸመ ሽያጭ ስላልሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 1809(1)(2) መሰረት ውሉ ፈራሽ ነው፡፡ አመልካች ቤቱን በኪራይ ያልያዙ በመሆኑ የኪራይ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ መወሰኑን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው የሽያጭ ውሉ ሲፈርስ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ አለመወሰኑን፤ የካሳ ጥያቄያቸው ውድቅ መደረጉንና ቤቱን እንዲረከቡ እንዲወሰንላቸው ያቀረቡት ዳኝነት መታለፉን በመቃወም ይግባኛቸው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተለያየ መዝገብ አቅርበው መዝገቦቹ ተጣምረው ከተመረመሩ በኋላ ቤቱ የወራሾች የጋራ ንብረት መሆኑ አላከራከረም፤ ቤቱ ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት ስለሆነ ቤቱን በሽያጭ ወይም በማናቸውም መንገድ ለማስተላለፍ የሁሉም ወራሾች ፍቃድ ያስፈልጋል፡፡ ሽያጩን 1ኛ ተጠሪ እና ሞግዚት በሆኑላቸው 2ኛ ተጠሪ ስም ጭምር ያከናወኑ ከመሆኑ ውጪ ሌሎች ወራሾች ፍቃዳቸውን የሰጡ ስለመሆኑ በውሉ ላይ አልተመለከተም፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሞግዚት ለመሸጥ የፍርድ ቤትን ፍቃድ ሊኖር የሚገባ ስለመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 54827 ላይ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ አመልካች ቤቱን ሲገዙ የቤቱ ስመ ሀብት በሻጭ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ስም ያለ ስለመሆኑ ያላረጋገጡ እና ውሉን ለመዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ስላላደረጉ የቅን ልቦና ገዢ ናቸው ሊባል አይችልም፡፡ ስለሆነም የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ የሽያጭ ውሉ ለፈርስ ይገባል ከተባለ ስመ ሀብቱ ወደ አመልካች ሊዞር የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ገዢ በስር ፍርድ ቤት በቤቱ ላይ የተለያዩ እድሳቶችን ስለማድረጋቸው ጠቅሰው የተከራከሩ ቢሆንም ግንባታው የቤቱን ይዘት የለወጠ ስለመሆኑ ገልጸው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ የግንባታ ወጪው እንዲተካላቸውም የጠየቁት ዳኝነት ስለሌለ የግምባታ ወጪን ከውል መፍረስ ጋር ተያይዞ ለቀረበው መከራከሪያ ፍርድ ቤቱ ሊመረምር የሚገባ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ነገር ግን ውሉ እንዲፈርስ ሲወሰን ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት ሊመለሱ አይችልም በሚል ክርክር ባልቀረበበት የስር ፍርድ ቤት ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ አለመወሰኑ ተገቢ አይደለም በሚል በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ቤቱን የያዙት በሽያጭ ውሉ አማካኝነት ስለሆነ ውሉ እስኪፈርስ ድረስ ቤቱን ይዘው የመጠቀም መብት ስላላቸው ተጠሪዎች ቤቱ ላይ ያጡትን ጥቅም በካሳ መልክ እንዲወስንላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው፡፡ ተጠሪዎች በይግባኝ ክርክሩ የደረሰባቸውን የወጪ እና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት አላቸው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ሚያዝያ 11 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት ይህን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ እንዲሁም በጣልቃ ገብነት አቤቱታው ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገው ውል እንዲፈርስ የቀረበው ዳኝነት በፍ/ሕ/ቁጥር 1808 መሰረት በ2 ዓመት ወይም አመልካች ቤቱን ከያዝኩት 15 ዓመት የሞላው ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 1845 መሰረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ክርክሬን አቅርቤያለው፡፡ 2ኛ ተጠሪ ውሉ በተደረገበት ጊዜ የ13 ዓመት ልጅ ሁኖ ክሱ በቀረበበት ጊዜ 25 ዓመት ስለሞላው በፍ/ሕ/ቁጥር 1810(1) መሰረት ለአካለ መጠን ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በ2 ዓመት ውስጥ ሊቃወም ይገባ ነበር፡፡ 4ኛ ተጠሪም የውል ይሰረዝልኝ ክሱን በፍ/ሕ/ቁጥር 1810 እና 1845 መሰረት በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ስላላቀረቡ በይርጋ ይታገዳል በማለት ያነሳውት መቃወሚያ መታለፉ አግባብ አይደለም፡፡ 4ኛ ተጠሪ በአካል ተገኝተው በውሉ ላይ ባይፈርሙም በሽያጭ ውሉ ላይ ለፈረሙት 3ኛ ተጠሪ በቁጥር 9894/1/96 መስከረም 5 ቀን 1996 ዓ.ም ውክልና የሰጡ ስለሆነ እንዲሁም 3ኛ ተጠሪ ከተሰጠው ውክልና ስልጣን ውጪ ሰርቷል ቢባል እንኳ አመልካች ቤቱን የገዛውት አባታቸው ባለባቸው እዳ ምክንያት ተፈርዶባቸው ቤቱ በሀራጅ እንዲሸጥ ማስታወቂያ ከወጣ በኋላ የተሻለ ዋጋ እንዲያወጣላቸው በድርድር ለመሸጥ ተስማምተው ስለሆነ እና 4ኛ ተጠሪ የቤቱን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ልታስቀረው የምትችል ባለመሆኑ እኔ ሳላውቅ የተፈጸመ ሽያጭ ነው የሚለውን ክርክር የምታነሳበት ሁኔታ ስለሌለ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የፍ/ሕ/ቁ. 2207(1) (2) ድንጋጌን ይቃረናል፡፡ አመልካች ቤቱን ከገዛው በኋላ የነበረውን ቤት እና የቆርቆሮ አጥር ሙሉ ለሙሉ አፍርሼ 8 ክፍል ቤት እና የግንብ አጥር ስለሰራውበት ውሉ እንዲፈርስ ቢወሰን እንኳ ወደ ነበርንበት ልንመለስ ስለማንችል በፍ/ሕ/ቁጥር 1817 መሰረት የተዋዋዮች መብት እንዲስተካከል አለመደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚል ነው፡፡

አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት እና ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች አባት ሞት ምክንያት በነበራቸው እዳ ፍርድ ቤት በሐራጅ ሊሸጥ ሲል በወቅቱ የገበያ ዋጋ እንዲሸጥ ተስማምተው 4ኛ ተጠሪም ለ3ኛ ተጠሪ ውክልና ሰጥታ ሽያጩ ከተፈፀመ ከ10 ዓመት በላይ ቆይቶ የአሁኑ ክርክር በሻጮች እና ገዢ መካከል ሁኖ ባለበት ውሉ አልተመዘገበም ወራሾችም ፈቃድ አልሰጡም ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1808፣1810፤1845፣ 1815፣1817፣2207 እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 39336፣ 43226፣ 48094 ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንፃር ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ታዟል፡፡

1ኛ፤ 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ጥቅምት 4 ቀን 2014 ዓ.ም የተፃፈ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ስላልቀረቡ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡ የተጠሪዎች መልስ ይዘት ባጭሩ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ እና በ4ኛ ተጠሪ የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ላይ ላይ አመልካች በሰጡት መልስ በፍ/ሕ/ቁጥር 1845 መሰረት ያቀረቡት 10 ዓመት ይርጋ መቃወሚያ የለም፤ 4ኛ ተጠሪም ለ3ኛ ተጠሪ ውክልና መስጠታቸውን እና በቤቱ ላይ የማሻሻያ ስራ ስለመስራታቸው መጠኑ ታውቅ እና ተገምቶ ያቀረቡት መከራከሪያ ስለሌለ በበዚህ ረገድ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ የቀረበው ቅሬታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) መሰረት ተቀባይነት የለውም፡፡ ውሉ በተደረገበት ጊዜ የቤቱ ስመ ሀብት በአቶ ገብረመስቀል እንዳለ ስም ያለ፤ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ባሉት ተጠሪዎች ስም ያልዞረና የባለቤትነት ሰነድ ያልተዘጋጀለት በስማችን ልንሸጠው የማንችል በመሆኑ እንዲሁም በውሉ ላይ በተጠቀሰው የወራሽነት ማስረጃም 4ኛ ተጠሪን በስም የሚጠቅስ ስለሆነ አመልካች 4ኛተጠሪ መብት እንዳለት ተገንዝበው ተገቢውን ማጣራት ሊያደርጉ ይገባ ነበር፡፡ ስሙ በወራሾች ነበር ቢባል እንኳ ቤቱን ለመሸጥ የሁሉም ወራሾች ስምምነት ያስፈልጋል፡፡ 4ኛተጠሪ በውሉ ላይ አልፈረሙም፤ ውሉ ስለመደረጉም የሚያውቁት ነገር አልነበረም፤ ውሉም በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 1723 መሰረት ተቀባይት የለውም፤ የሽያጭ ውሉ ሰደረግም 2ኛ ተጠሪ ለአቅመ አዳም ያልደረሰ በመሆኑ በሞግዚትንት የተዋዋሉት 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ቤትን ፍቃድ ሊያገኙ ይገባ ነበር፤ አመልካች 2ኛ ተጠሪን በሚመለከት የፍ/ሕ/ቁጥር 1810ን ጠቅሰው 2 ዓመት የይርጋ መቃወሚያ አንስተው የነበረ ቢሆንም የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ የባለቤትነት መፋለምን የሚመለከት በመሆኑ በይርጋ አይታገድም፤ በአመልካች ክስ መነሻነት ቀረበ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ስለሆነም ይርጋ መቃወሚያ ሊነሳበት አይገባም፤ ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል የተጠቀሱት ሰበር ውሳኔዎች ለጉዳዩ ተገቢነት የላቸውም፤ አመልካች በ4ኛ ተጠሪ ለ3ኛ ተጠሪ ተሰጥቷል የሚሉትን ውክልና በስር ፍርድ ቤት በማስረጃነት አልቆጠሩም፤ በውሉ ላይም 4ኛ ተጠሪ በውክልና አልተሰየሙም፤ አመልካች በቤቱ ላይ እድሳት ስለማድረጋቸው ጠቅሰው የሚያቀርቡት መከራከሪያ በስር ፍርድ ቤት ግንባታው ስለመደረጉ እና ስለ ግንባታ ወጪው ያቀረቡት ማስረጃ ስለሌለ ወደ ነበርንበት እንዳንመለስ የሚያደርግ አንድም ነገር ስለሌለ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡

አመልካች በበኩላቸው ጥቅምት 18 ቀን 2014 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሳችውን ያቀረቡ ሲሆን የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሐሳብ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በዋናነት የሚከራከሩት 2ኛ ተጠሪ ለአካለ መጠን ከደረሰ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሉ እንዲፈርስ ክስ ስላላቀረበ እና 4ኛ ተጠሪም ውሉ በተደረገ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሉ እንዲፈርስ ስላልጠየቁ በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረብኩት መቃወሚያ መታለፉ፤ ሽያጩ የተከናወነው 4ኛ ተጠሪ ለ3ኛ ተጠሪ በሰጡት ውክልና መሰረት ሁኖ እያለ ውሉን አልፈረሙም መባሉ፤ ውክልና አልሰጡም ቢባል እንኳ አመልካች ቤቱን በስምምነት ባልገዛው በሀራጅ የሚሸጥብትን ሁኔታ 4ኛ ተጠሪ ልታስቀረው ስለማትችል የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ መወሰኑ እንዲሁም የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ቢባል እንኳ ቀድሞ የነበረውን ግንባታ አፍርሼ አዲስ ግንባታ ያካሔድኩ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1817 የተዋዋዮች መብት እንዲጠበቅ በሚያስችል ሁኔታ አለመወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው አመልካች በፍ/ሕ/ቁጥር 1845 መሰረት የ10 ዓመት ይርጋን፤ 4ኛ ተጠሪ ለ3ኛ ተጠሪ ውክልና መስጠታቸውን እንዲሁም ያደረጉት ማሻሻያ መጠኑን ጠቅሰው በስር ፍርድ ቤት ስላልተከራከሩ የቀረበው አዲስ ክርክር ተቀባይት የለውም፤ ከ2ኛ ተጠሪ አንጻር ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ክርክሩ የመፋለም ስለሆነ በይርጋ አይታገድም፤ ሽያጩ የተደረገው የቤቱ ስመ ሀብት በተጠሪዎች ሳይዞር ስለሆነ፤ ንብረቱ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመሆኑም በሞግዚቱ የተወከለው 1ኛ ተጠሪን በሚመለከት በፍርድ ቤት የተሰጠ ፍቃድ ስለሌለ፤ 4ኛ ተጠሪም በውሉ ላይ ስላልፈረሙ እና ውሉ በአዋዋይ ፊት ስላልተደረገ ውሉ ፈርሶ ወደ ነበርንበት እንድንመለስ መወሰኑ አግባብ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

የውርስ ሀብት ክፍፍል እስኪደረግ ድረስ በወራሾች መካከል ሳይነጣጠል የሚቆይ፤ ክፍፍሉ እስኪፈጸምም ወራሾች በውርስ ንብረቱ ላይ የሚኖራቸው መብት በፍትሐብሔር ሕጉ ስለ የጋራ ባለሀብትነት በተነገሩት ድንጋጌዎች የሚገዛ ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1060(1) እና (2) የተመላከተ ሲሆን ሞግዚት መሾጥ የሚችለው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት የሆኑ የሚንቀሳቀሱ ግዙፍነት ያላቸው ንብረቶችን፤አክሲዮኖችንና የገንዘብ ሰነዶችን ብቻ ስለመሆኑ በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 277(1) ላይ ተመላክቷል፡፡

በመጀመሪያ አመልካች በስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ለአቅመ አዳም ከደረሰ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዲሁም 4ኛ ተጠሪ ውሉ በተደረገ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ የውል ይፍረስልኝ ክስ ስላላቀረቡ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሳቸው እንዲሁም የጣልቃ ገብነት አቤቱታው በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረብኩት መቃወሚያ መታለፉ አግባብ አይደለም በማለት የሚያነሱትን መከራከሪያ መመልከቱ አስፈላጊ ሁኖ አግኝነተነዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ በተመለከተው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም ተደረገ የተባለውን ውል መነሻ በማድረግ 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የቤቱን ስመ ሀብት እንዲያዞሩላቸው ለማስወሰን ክስ መስርተዋል፡፡ በዚህ መነሻነት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ውሉ ሊፈርስ ይገባል የሚሉበትን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ምክንያት ጠቅሰው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ያቀረቡ ሲሆን 4ኛ ተጠሪም በጣልቃ ገብነት አቤቱታቸው ውሉ እንዲፈርስ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በ2ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረቡትን የይርጋ መቃወሚያ ለማብራራት ውሉ በተደረገበት ጊዜ የ13 አመት ልጅ የነበረ እና ክሱ በተመሰረተበት ጊዜ እድሜው የ25 ዓመት ልጅ የነበረ መሆኑን ጠቅሰው የሚያቀርቡትን መከራከሪያ ተጠሪዎች አላስተባበሉም፡፡ ይህም 2ኛ ተጠሪ በሞግዚቱ አማካኝነት የተደረገውን የቤት ሽያጭ ውል የተቃወመው ለአቅመ አዳም ከደረሰ ከ2 ዓመት በኋላ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በፍ/ሕ/ቁጥር 1808(1) ከተዋዋዮቹ አንዱ ፍቃዱን በመሳሳት፣ በተፈፀመበት የተንኮል ወይም የማስገደድ ተግባር ወይም ችሎታ ሳይኖረው የሰጠ እንደሆነ ይህን ምክንያት በመጥቀስ እና በማስረጃ በማረጋገጥ ውሉ ፈራሽ እንዲደረግለት ዳኝነት የሚጠይቅበትን አግባብ የሚያመላክት ነው፡፡ በአንፃሩ በንዑስ አንቀፅ 2 ስር የተገለፀው የውል ጉዳዩ ህገ ወጥ ወይም ኢሞራላዊ የሆነ ወይም በሕጉ የተገለፀውን የአቀራረፅ ስርዓት ባለመከተሉ ከመጀመሪያውም ሕግ እውቅና የማይሰጠው እንዳልነበረ የሚቆጠር ቢሆንም ይመለከተኛል ባይ 3ኛ ወገን ወይም ተዋዋዮች ውሉ ዋጋ አልባ እንዲባል ዳኝነት የሚጠይቁበትን ሁኔታ የሚያመላክት ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ አግባብ ውሉ ፈራሽ ወይም ዋጋ አልባ ነው በማለት እንዲወሰን ቀድሞ ዳኝነት ያልጠየቀበት ተዋዋይ በሌላኛው ተዋዋይ እንደ ውሉ እንዲፈፀምለት የጠየቀው እንደሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 1809 መሰረት ውሉ የማይረጋበትን ምክንያት በመጥቀስ በማንኛውም ጊዜ መቃወሚያ ሊያደረገው ይችላል፡፡ ይህ ድንጋጌ ዋጋ አልባ ወይም ፈራሽ ውሎችን በማለት ለይቶ መመዘኛ የማያስቀምጥ በመሆኑ ለሁለቱም ሁኔታዎች ተግባራዊ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ውሉ የማይረጋበትን ምክንያት በመጥቀስ መቃወሚያ አድረጎ ማንሳት የሚችለው በውሉ መሰረት መፈጸም ያልተጀመረ ከሆነ ብቻ ነው? ወይስ በሙሉ ወይም በከፊል ውሉ ከተፈጸመ ውሉ የማይረጋበትን ምክንያት መቃወሚያ አድረጎ ማንሳት ይችላል ወይስ አይችልም? የሚሉት ነጥቦች በትኩረት ሊመረመሩ ይገባል፡፡ በፍ/ህ/ቁጥር 1809 አገላለጽ ውሉ የማይረጋበት ምክንያት እያለ በውሉ መሰረት በሙሉ ወይም በከፊል ከተፈጸመ በተግባር ውሉ ተቀባይነት እንዳገኘ አመላካች ነው፡፡ አንድ ተዋዋይ በተግባር ተቀብሎ በውሉ መሰረት ተፈጽሞ እያለ ክስ ስለቀረበበት ብቻ ውሉ የማይረጋበትን ምክንያት በመጥቀስ የሚያቀርበው መቃወሚያ በተግባር የተቀበለውን የውል ውጤት የሚቃረን በመሆኑ መቃወሚያው ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም፡፡ ይህ ማለት ግን ውሉ አይረጋም የሚል ወገን ክስ አቅርቦ ውሉን ማስፈረስ አይችልም ማለት ባለመሆኑ በውሉ መሰረት በከፊል ወይም በሙሉ እንደውሉ ከተፈጸመ በህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክስ አቅርቦ ውሉን እስካላስፈረሰ ድረስ በውሉ መሰረት ሊፈጸም አይገባም በማለት የሚያነሳው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1809 ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው እንደውሉ ከመፈጸሙ በፊት ነው፡፡ በከፊል ወይም በሙሉ በውሉ መሰረት ከተፈጸመ በኋላ ውሉ የማይረጋበትን ምክንያት በመጥቀስ መቃወሚያ አድረጎ ማቅረብ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል በሰበር መዝገብ ቁጥር2 12820 እና ሌሎች መዝገቦች የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክስ ያቀረቡት በውል መሰረት እንዲፈጸም ወይም ቤቱ ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት የእርሳቸው ነው ተብሎ ስመ ሀብቱ እንዲዛወርላቸው ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከ1ኛ-3ኛ ባሉ ተጠሪዎች

በውሉ መሰረት የስመሀብት ዝውውር መፈጸም ያልጀመረ መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለዚህ 2ኛ ተጠሪ በፍ/ሕ/ቁጥር 1809 መሰረት ውሉ የማይረጋበትን በፍ/ሕ/ቁጥር 1808 ላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች አንዱ የሆነውን ችሎታ ማጣት ውሉ እንዲፈጸም ክስ ሲቀርብባቸው በማኛውም ጊዜ ማንሳት የሚችሉ በመሆኑ አመልካች በ2ኛ ተጠሪ ላይ የፍ/ሕ/ቁጥር 1810(1)ን ጠቅሰው ያቀረቡት የ2 ዓመት የይርጋ መቃዊሚያ መታለፉ ተገቢ ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የ4ኛ ተጠሪ የጣልቃ ገብነት አቤቱታ በ10 ዓመት የሚታገድ መሆኑን ጠቅሰው በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት መከራከሪያ የለም፡፡ በጣልቃ ገብነት አቤቱታው ላይ በሰጡት መልስ የተከራከሩት ውሉ የተደረገው ከ15 ዓመት በፊት በነበረው የገበያ ዋጋ መሆኑን በመጥቀስ እንጂ ይርጋ መቃወሚያ በማንሳት አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ያቀረቡት አዲስ ክርክር በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) መሰረት ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

በመቀጠል አመልካች ስመ ሀብቱ እንዲዞርላቸው ያቀረቡት ክስ ውድቅ ተደርጎ በአንዛሩ ውሉ እንዲፈርስ የመወሰኑ አግባብነት ተመለክተነዋል፡፡ ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም የቤት ሽያጭ ውል መደረጉ፤ ውሉ በፍ/ሕ/ቁጥር 1723 መሰረት ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት አለመፈፀሙ፤ የሽያጭ ውል የተደረገበት ቤትም ከ2ኛ እስከ 4ኛ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪዎች አባት በሆኑት ገብረመስቀል እንዳለ ስም ተመዘግቦ የሚገኝ በወራሾች መካከል ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት መሆኑ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ የማይንቀሣቀስ ንብረትን የባለቤትነት መብት ለማስተላለፍ የሚደረግ ውል በሙሉ በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሠጠው አካል ፊት መደረግ ያለበት መሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1723(1) ላይ ተመላክቷል፡፡ ይህን የአፃፃፍ ሥርዓትን መከተል ውሉ በህግ ፊት የፀና እንዲሆን ከሚያስፈልጉ መመዘኛዎች አንዱ ነው፡፡ ነገር ግን ከ1ኛ-3ኛ ባሉት ተጠሪዎች ውሉ በሚመለከተው አካል ፊት ያልተደረገ ቢሆንም ውሉ የታመነ ስለሆነ ለውል ማፍረሻ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡

በሌላ በኩል 2ኛ ተጠሪ ውሉ በተደረገበት ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ/ም ለአቅመ አዳም ያልደረሰ እና በ1ኛ ተጠሪ የሞግዚት አስተዳደር ስር የነበረ በመሆኑ በ1ኛ ተጠሪ ተወክሎ ውሉን 1ኛ ተጠሪ መፈረማቸው አላከራከረም፡፡ አመልካች ይህን ሲያከናውኑ ንብረቱ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንደመሆኑ የፍርድ ቤት ፍቃድ ሊያገኙ ይገባ የነበረ ሲሆን አመልካች ማንኛውንም አይነት ውል 1ኛ ተጠሪ በሞግዚትነት ስልጣናቸው ሊፈጽሙ ይችላሉ ብለው ከሚከራከሩ በቀር በፍርድ ቤት ፍቃድ ያገኙ ስለመሆኑ ጠቅሰው የሚያቀርቡት መከራከሪያ የለም፡፡ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ስር ፍርድ ቤቶችም በሕጉ አግባብ ፍርድ ቤት ፍቃድ ያልሰጣቸው መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ እንደዚሁም 2ኛ ተጠሪ ውሉ በተደረገበት ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ/ም ለአቅመ አዳም ያልደረሰ እና በ1ኛ ተጠሪ የሞግዚት አስተዳደር ስር የነበረ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ በውሉ ላይ መፈረማቸው አላከራከረም፡፡ ሞግዚት መሸጥ የሚችለው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት የሆኑ የሚንቀሳቀሱ ግዙፍነት ያላቸው ንብረቶችን፤ አክሲዮኖችንና የገንዘብ ሰነዶችን ስለመሆኑ በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 277(1) ላይ ተመላክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን የማይንቀሳቀስ ንበረት ሞግዚቱ ከሚመለከተው አካል ተጨማሪ ፍቃድ እስካላገኘ ድረስ

በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የማይችል መሆኑን ነው። ከዚህ በተቃራኒ 2ኛ ተጠሪ በማይንቀሳቀስ ውርስ ሀብቱ ላይ ያለውን መብት 1ኛ ተጠሪ በሽያጭ ለማስተላለፍ ያደረጉት ስምምነት የችሎታ(capacity) ጉድለት ያለበት መሆኑን ያስገነዝባል።

ከዚህም ሌላ የውርስ ሀብት በወራሾች መካከል ክፍፍል እስኪደረግበት ሳይነጣጠል የሚቆይና በዚህ ንብረት ላይ ወራሾች የሚኖራቸው መብትም በፍትሐ ብሔር ሕጉ ስለ የጋራ ባለሀብትነት መብቶች በተነገሩት ድንጋጌዎች የሚገዛ መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1060(1) እና (2) ላይ ተመልክቷል። በዚህ አግባብ የጋራ ባለሀብትነትን የሚመለከተው የፍ/ሕ/ቁጥር 1266 የጋራ የሆነውን ንብረት ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ የጋራ ባለንብረቶቹ የሁለም ስምምነት የሚያስፈልግ መሆኑ ተመልክቷል። 4ኛ ተጠሪ የሚች አቶ ገብረ መስቀል እንዳለ ወራሽ እና የውርስ ሀብቱ ተከፋይ መሆናቸውን አመልካች ክደው የሚያቀርቡት መከራከሪያ ካለመኖሩም በላይ ወራሽ መሆናቸውም በማስረጃ ተረጋግጧል። አመልካች 4ኛ ተጠሪ ለወኪሏ 3ኛ ተጠሪ በሰጠችው ውክልና አማካኝነት ፈርማለች በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ይህን ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) መሰረት ተቀባይነት የለውም። በተጨማሪም አመልካች በስር ፍርድ ቤት የተከራከሩት 4ኛ ተጠሪ ሽያጩን የማትቃወም መሆኑን በእናቷ አማካኝነት ገልጻልኛለች ይህንንም በፍርድ ቤት ቀርበው በቃለ መጎላ ያረጋግጡልኝ በሚል መሆኑን ከፍርዱ መገንዘብ ይቻላል። ይህም 4ኛ ተጠሪ ከላይ በተገለፁት የፍትሐ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች መሰረት ህጋዊ በሆነ መልኩ ተወክለው የውል ስምምነቱ ላይ እንዳልፈረሙ የሚያስገነዝብ ሲሆን ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶችም 4ኛ ተጠሪ አለመፈረሟን አረጋግጠዋል። በመሆኑም በእነዚህ ዝርዝር ምክንያቶች አመልካች ስመ ሀብቱ እንዲዛወርላቸው ያቀረቡት ዳኝነት ውድቅ ተደርጎ ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አላገኘነውም።

በመጨረሻም አመልካች ውሉ እንዲፈርስ ቢወሰን እንኳ ወደ ነበርንበት መመለስ ስለማንችል የተዋዋዮች መብት ባስከበረ መልኩ ሊወሰን ይገባል በማለት የሚያነሱት መከራከሪያ የመረመርን ሲሆን አመልካች ለዚህ ክርክራቸው በምክንያትነት የሚጠቅሱት በይዞታው ላይ ቀድሞ የነበረውን የቆርቆሮ አጥር አፍርሼ 8 ክፍል ቤት በመገንባት የግንብ አጥር አሰርቻለው በሚል ነው። ውለታውን ለመፈጸም የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ሲሆን ወይም አስቸጋሪ ሁኖ ሲገኝ ወይም ከፍ ያለ መሰናክል የሚያመጣ ሲሆን ተገቢ የሆነው ኪሳራ እንዲከፈል በማድረግ እነዚህ የተሰሩ ስራዎች እንደረጉ እንዲቀሩ የሚደረግ ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1817 ላይ ተመልክቷል። ነገር ግን አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች በይዞታው ላይ ተጨማሪ ግንባታ ያከናወኑ መሆኑን ጠቅሰው የተከራከሩ ከመሆኑ ውጪ ግንባታው በቀድሞው ግንባታ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ያደረገ መሆኑን፣ የወጪ መጠኑን እና ዝርዝሩን በመግለፅ ወደ ነበርንበት ልንመለስ አንችልም በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ የለም። ውሉ እንዲፈርስ ሲደረግም ተዋዋዮች ቀድሞ ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ የሚደረግ መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1815 ላይ በተገለፀው አግባብ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ መወሰኑ ህጉን እና የግራ ቀኙን ክርክር ያገናዘበ ነው። በመሆኑም አመልካች በይዞታው ላይ ያደረጉትን ተጨማሪ ግንባታ ወጪ

በሚመለከት በግልጽ ክስ አቅርበው ዳኝነት ከሚጠይቁ በቀር በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ያልተከፋፈለ የጋራ የውርስ ሀብት በሆነ ቤት ላይ ከ1ኛ-3ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል የ2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች የችሎታ ጉድለት ያለበት በመሆኑ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ተወስኖ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ማለትም አመልካች ለተጠሪዎች ቤቱን እንዲያስረክቡ ተጠሪዎች ደግሞ ከአመልካች የተቀበሉትን የሽያጭ ገንዘብ ብር 92,000(ዘጠና ሁለት ሺ) እንዲመለሱ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሌለ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 66070 ጥቅምት 21 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 247152 ጥር 18 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት አሻሽሎ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የስ/መ/ቁጥር 216415

ቀን 24/9/2014 ዓ/ም

ስሜ በተራ ቁጥር 3ኛ ላይ የምገኘው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን እንደምከተለው አስቀምጫለሁ

ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ምክንያት የሆነው ጉዳይ በስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ባቀረበው ክስ ከሰው በቅን ልቦና የገዛሁት መኪና ካለአግባብ ስለያዘብኝ ይልቀቅልኝ ሲል የጠየቀ ሲሆን የአሁን ተጠሪም ተከሳሽ ካለአግባብ ተያዘብኝ የሚለው መኪና በቱሪስት መልክ ወደ ሀገር ውስጥ የገባና ጊዜውን ሲጨርስ የሚወጣ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት በመሆኑ እና ከህግ ውጭ በከሳሽ በአሁን አመልካች እጅ የተገኘ በመሆኑ ተይዞ በህጉ መሰረት ቀረጥና ታክስ እንዲከፍል የተወሰነ በመሆኑ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 859/2006 መሰረት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም፡፡ መኪናውም በህገ ወጥ መንገድ በከሳሽ ተይዞ የተገኘ በመሆኑ መያዙ ተገቢ በመሆኑ ክሱ ወድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥቷል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አከራክረው ጉዳዩ የፍ/ቤት ሥልጣን አይደለም ሲሉ የአሁን አመልካችን ክስ መዝገብ ዘግተውታል፡፡

የግብር ይግባኝ ጉባኤ ሥልጣን በተመለከተ ጉምሩክ የአሁን ተጠሪ ግብርና ታክስ ከማስከፈል በተጨማሪ በህገ ወጥ መንገድ ሀገር ውስጥ የገቡ እቃዎችን ተከታትሎ መያዝና ቀረጥና ታክስ ከፍለው ህጋዊ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ለአሁን ተጠሪ የተሰጠው ሥልጣን ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ የአሁን አመልካች ጉዳይ የፍ/ቤት ሥልጣን ነው ሲል የሚያቀርበው ክርክር መኪናውን ከሰው በቅን ልቦና ከመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ተረጋግጦ የገዛሁት በመሆኑ የጉምሩክ አስተዳደራው ውሳኔ እና የግብር ይግባኝ ጉባኤ ሥልጣን አይደለም በሚል ሲሆን መኪናው በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ የአሁን አመልካች በቅን ልቦና ገዛሁት ስላለ የጉምሩክ አስተዳደራዊ ውሳኔ የማያስፈልገው የግብር ይግባኝ ጉባኤ ሥልጣን መሆኑን ያስቀረዋል ብሎ ማለት ተገቢ የሆነ ምክንያትና አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 153 እና 155 ድንጋጌን መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡

የጉምሩክ ኮሚሽን በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ እቃዎች ሲያገኝ መያዝ እና ቀረጥና ታክስ ማስከፈል እንደሚችል የማያከራክር ጉዳይ ከሆነ አሁን ያከራከረውን መኪና የአሁን ተጠሪ ከህገ ውጪ በአሁን አመልካች ተይዞ ተገኝቷል ብሎ ታክስ እንዲከፍል ወስኖበታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁን አመልካች በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 153 እና 155 ድንጋጌ መሰረት ለአሁን ተጠሪ አስተዳደራው ውሳኔ ካቀረበ በኋላ የግብር ይግባኝ ጉባኤ የይግባኝ ቅሬታ ያቀርባል፡፡ የግብር ይግባኝ ጉባኤው በሚሰጠው ውሳኔ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በህግ ጉዳይ የይግባኝ ቅሬታ ማቅረብ የሚችል ነው፡፡ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽኑ ግራ ቀኙን አከራክሮ ያከራከረው መኪና የአሁን ተጠሪ እንደሚከራከረው በህገ ወጥ መንገድ በአሁን አመልካች እጅ የተገኘ አይደለም በቅን ልቦና የገዛው በመሆኑ ሊያዝበት አይገባም ብሎ ሊወስን ይችላል፣ ወይ የአሁን ተጠሪ እንደሚከራከረው መኪናው በቱሪዝም መልክ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ እና የአሁን አመልካች ግዥውን ፈጽሞ ከሆነ ግዥውን ሲፈጽም ሊያደርግ የሚገባውን

ግዴታ ሳይወጣ የፈጸመ በመሆኑ የቅን ልቦና ገዥ አይደለም ሊል ይችላል ወይ የቅን ልቦና ገዥም ቢሆን በአሁን ተጠሪ መያዙ ተገቢ ነው ሊል ይችላል፡፡ የግብር ይግባኝ ጉባኤው ግራ ቀኙን አከራክሮ በህጉ መሰረት ሊሆን ይገባል ያለውን ውሳኔ መስጠት በአዋጅ የተሰጠው ሥልጣን ነው፡፡ የግብር ይግባኝ ጉባኤው የግራ ቀኙን ክርክር ሲያጣራ ከሚመለከተው አካል ሁሉ ማስረጃ አስቀርቦ የመመርመር ሥልጣኑ ያለው ሲሆን የአሁን አመልካች ያከራከረውን መኪና ከሌላ ሰው የገዛሁት ነው የሚለው ክርክር 3ኛው ወገን በክርክሩ መግባት አለመግባቱ ለግብር ይግባኝ ጉባኤው በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን የሚያስቀር በቂ ምክንያት አይደለም፡፡ ይህ ጉዳይ በቱሪዝም መልክ ሀገር ውስጥ ገብቶ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት በህገ ወጥ መንገድ ሀገር ውስጥ የሚንቀሳቀስ፣ ቀረጥና ታክስ መክፈል ያለበት መኪና ስለመሆን አለመሆኑ ጉዳይ እንጂ የንብረት መፋለም ክርክር ጉዳይ አይደለም፡፡ ያከራከረው መኪና ህገ ወጥነቱ ከተረጋገጠና ለአሁን አመልካች ካለአግባብ ተሸጦለት ከሆነ ለሚደርስበት ጉዳት ህጉ በሰጠው መብት መሰረት መጠየቅ ህጋዊ መብቱ እንጂ በፍ/ቤት የሚሰጠው መብት አይደለም፡፡ በመሆኑም በቂ ባልሆነ ምክንያት ጉዳዩ የግብር ይግባኝ ጉባኤው ሥልጣን እንዳልሆነና የፍ/ቤት ሥልጣን ነው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው ብዬ ስለማላምን የልዩነት ሀሳቤን አስቀምጫለሁ፡፡

የሰ.መ.ቁ 213758

ቀን ግንቦት 23 2014ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡ 1ኛ. ወ/ት ሰንሰለት ወንድይራድ ጠበቃ አገኘሁ መኮንን ቀረቡ

2ኛ. አቶ ምርጥዘር ወንድይራድ -- ቀረቡ

3ኛ. አቶ ሰውነት ወንድይራድ - ወኪል 2ኛ አመልካች ቀረቡ

4ኛ. አቶ በተለይ ወንድይራድ -- ጠበቃ አለማየሁ ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡ 1ኛ. አቶ አዳነ ተ/ሃይማኖት
2ኛ. ወ/ሮ አልማዝ ተ/ሃይማኖት
-ጠበቃ ሄየለ ጫላ ከ1ኛ አመልካች ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ በኮ.መ.ቁ 116047 በ21/9/12ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 257494 በ10/10/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ1/13/13ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የጉዳዩ አመጣጥ 1ኛ አመልካች በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪዎች እና በ4ኛ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ሚች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ አያቴ ሲሆኑ በአዲስ አበባ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 6 የቤ.ቁ 008፤ 008/09 እና 029 ቤት የነበረ ሲሆን አያቴ ከሞቱ በኋላ የውርስ ሀብት በሆኑት ቤቶች ውስጥ እስከ 21/4/06ዓ.ም ድረስ የቆየሁ ሲሆን ከዚህ ግዜ በኋላ ተጠሪዎች እና 4ኛ አመልካች(ስር ተከሳሾች) ለብቻቸው በመያዝ ክስ እስከቀረበበት ግዜ ድረስ ብር 258,000.00 የውርስ ገንዘብ ሰብስበዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ የ1ኛ አመልካች ድርሻ ብር 12,900.00 እና ወደፊት በቤቱ ላይ ድርሻዬን እስከማገኝ ድረስ የሚኖረው ክፍያ ታስቦ እንዲከፈለኝ፤ ሚች አያታችን የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ የሆኑ አራት ልጆች ያሏቸው ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የ1ኛ አመልካች አባት አቶ ወንድይራድ አለማየሁ አምስት ልጆች ያላቸው በመሆኑ የአባቴን ድርሻ 1/5ኛ ከቤ.ቁ 008፤ 008/09 እና 029 ድርሻ እንዲያካፍሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው በብይን ውድቅ የተደረገ ሲሆን በአማራጭ ባቀረቡት መልስ 1ኛ አመልካች ክስ ባቀረቡበት የቤ.ቁ 008/09 እና 029 ውስጥ ሚች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ ከመሞታቸው በፊትም ሆነ በኋላ ቤቱ ውስጥ ኖረው አያውቁም፡፡ የሚኖሩት በመንግስት በተወረሰ የቤ.ቁ 007 በሆነ የቀበሌ ቤት ውስጥ ከእናታቸው ጋር ነው፡፡ የቤ.ቁ 029 ከ1968ዓ.ም ጀምሮ የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት ሲሆን የቤ.ቁ 008/09 ደግሞ የኑዛዜ ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ከ1997ዓ.ም ጀምሮ በውርስ ያገኙት የግላቸው ነው በማለት ተከራክረው ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርበዋል፡፡

4ኛ አመልካች(ስር 3ኛ ተከሳሽ) ባቀረቡት መልስ 1ኛ አመልካች የሚች የደረጃ ወራሽ ናቸው፤ 4ኛ አመልካችም ከአውራሽ ጋር በአንድ ቤት ውስጥ እኖር ስለነበር በሰሩት አንድ ክፍል ቤትና የውርስ ሀብት በሆነው ይዞታ ላይ በራሴ ወጪ ጨምሬ በሰራሁት አንድ ክፍል ቤት በድምሩ 2 ክፍል ቤት ይገቹ እያከራየሁ እየተጠቀምኩ ነው፡፡ ስለሆነም 1ኛ አመልካች የጠየቁት በአግባቡ በመሆኑ የውርስ ሀብቱን እንደድርሻችን እንካፈል ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የሚች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ የደረጃ ወራሾች ስለሆንን የምንኖረው አረብ አገር ስለነበር ስንመጣ 1ኛ አመልካች እና 4ኛ አመልካች እንዲሁም ተጠሪዎች ክርክር ላይ መሆናቸውን ስላረጋገጥን የአባታችንን ድርሻ ልናገኝ ስለሚገባ ወደ ክርክሩ ጣልቃገብተን እንድንከራከር በማለት በጠየቁት መሰረት ወደ ክርክሩ ገብተዋል፡፡

ፍርድቤቱም ክሱን ከሰማ እና የቤ.ቁ 029 የሆነው ቤት የውርስ ሀብት ነው ወይንስ የ1ኛ ተጠሪ የግሉ? ተጠሪዎች እና 4ኛ አመልካች(የስር ተከሳሾች) የያዙት የውርስ ሀብት የቱ ነው? ምን ያህል የኪራይ ብር ሰብስበዋል? ሊከፍሉ ይገባል? የሚሉትን ጭብጦች ከያዘ፤ የ1ኛ አመልካች እና የተጠሪዎችን ምስክሮች ከሰማ፤ ማስረጃ ተጣርቶ እንዲላክ ለየካ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት እና ለየካ ክ/ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ምላሽ

ከቀረበለት በኋላ ከሰነድ ማስረጃዎች ጋር ጭምር ጉዳዩን መርምሮ የቤ.ቁ 029 የሆነው ቤት ሟች በህይወት እያሉ ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ በሰጧቸው ይዞታ ላይ ቤት በራሳቸው ወጪ ሰርተው እንደሚኖሩ የ1ኛ እና የተጠሪዎች(ስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች) ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ በ2/2/93ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ላይም የቤ.ቁ 029ን ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ ሰጥተውት የነበረና በራሱ ወጪም ቤቶችን ሰርቶ እንደሚኖር ገልጸዋል፡፡ ይህ ኑዛዜም በስጦታ ተሰጥቶ ቤቶች ሰርቶ መኖሩን እውቅና የሰጠበት እንጂ እንደአዲስ በኑዛዜው ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠው መብት የለም፡፡

1ኛ ተጠሪ በቤ.ቁ 029 ላይ ከ1968ዓ.ም ጀምሮ የከተማ ቦታ ኪራይና የቤት ግብር የሚከፍሉበት በስማቸው እንደሆነ ከቀረቡት የተለያዩ የግብር ደረሰኞች ተረጋግጧል፡፡ ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ከመሞታቸው በፊት በ1992ዓ.ም የወረዳ 15 ቀበሌ 19 አስተዳደር ጽ/ቤት የቤ.ቁ 029 1ኛ ተጠሪ በራሳቸው ከአ/ቁ 47/67 በፊት የሰሩ መሆኑን በምስክር ማረጋገጣቸውን የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑም ሟች በኑዛዜያቸው ይህን እውቅና የሰጡ ከመሆኑ ውጪ እንደ አዲስ መብት የሚሰጥ ስላልሆነ የኑዛዜው መሻሻልና የሟች ወራሾች እኩል እንዲካፈሉ ውሳኔ መሰጠቱ 1ኛ ተጠሪ ሟች በህይወት እያሉ ተፈቅዶለት የሰሯቸው እና ባለመብት የሆነባቸውን ቤቶች ወደ ውርስ ሀብት በማስገባት እንዲያካፍል የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ በመሆኑ የቤ.ቁ 029 ሟች በህይወት እያሉ ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ ተሰጥተው የሰሯቸው ቤቶች መሆናቸው ከሟች ኑዛዜ ቃል፤ ከቀረቡት ምስክሮች እንዲሁም ከየካ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ከተሰጠው ማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ቤቱ የውርስ ሀብት ሳይሆን የ1ኛ ተጠሪ የግል ሀብት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ተጠሪዎች እና 4ኛ አመልካች(ስር ተከሳሾች) የያዙት የውርስ ሀብት የቱ ነው የሚለውን በተመለከተ የቤ.ቁ 029 የ1ኛ ተጠሪ የግሉ ቤት ነው የተባለ በመሆኑ የያዘው የውርስ ሀብት የለም፡፡ 2ኛ ተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) የቤ.ቁ 008 እና 008/009 የሚባለው በውል የሚጠቀሙበት 008 በሚል መሆኑ የተረጋገጠውን ቤት በኑዛዜ የያዙ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ሲሆን ይህ ኑዛዜም በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በይግባኝ ኑዛዜው ተስተካክሎ 1ኛ አመልካችም አባታቸውን በመወከል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የወሰነ ስለሆነ 2ኛ ተጠሪ የያዙት የቤ.ቁ 008 የውርስ ሀብት ነው፡፡ 4ኛ አመልካች(ስር 3ኛ ተከሳሽ) የቤ.ቁ 008 ጋር የተያያዘ ሁለት ክፍል ቤት የያዙ መሆኑን፤ የውርስ ሀብት ተደርጎ መከፋፈል እንዳለባቸው በመልሳቸው አምነው የገለጹ ስለሆነ የውርስ ሀብት ነው፡፡

ምን ያህል የኪራይ ገንዘብ ሰብስበዋል የሚለውን በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ የሰበሰቡት የኪራይ ገንዘብ የግል ንብረታቸው/ይዞታቸው በሆነው ቤት ላይ ስለሆነ የኪራይ ገንዘቡ የውርስ ሀብት አይደለም፡፡ 2ኛ ተጠሪ ከቤ.ቁ 008 ላይ ሁለት ቤት አከራይተው ገንዘብ የሰበሰቡ መሆኑን የተረጋገጠ ሲሆን የኪራይ መጠኑን በተመለከተ ፍ/ቤቱ ከግቢዎች በተረጋገጠው መረጃ መሰረት የወሰደ ሲሆን ይህም በወር ብር 1500.00 የሚሰበስቡ ሲሆን ከ2006ዓ.ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ግዜ የ2 አመት ከ6 ወር ብር 45,000.00 መሰብሰባቸው በሰው እና በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡ 4ኛ አመልካች(ስር 3ኛ ተከሳሽ) ከቤ.ቁ 008 ላይ ብር 1500.00 በወር

ያከራዩ መሆኑን ከገቢዎች በተገኘው መሰረጃ መሰረት ተወስዶ የሚያከራየውም ከ2008ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን ምስክሮች ስላረጋገጡ ከመስከረም 2008ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 2000ዓ.ም ድረስ የ10 ወር ብር 15,000.00 የውርስ ሀብት መሰብሰባቸው በማስረጃ በመረጋገጡ ይህን የሰበሰቡትን የውርስ ሀብት የኪራይ ገንዘብ ለወራሾች እንደድርሻቸው የሚያከፋፍሉ ይሆናል።

የውርስ ሀብት ክፍፍሉን በተመለከተ የሟች የውርስ ሀብት በ2ኛ ተጠሪ እና በ4ኛ አመልካች(ስር 3ኛ ተከሳሽ) የተያዙት የቤ.ቁ 008 መሆኑ ተረጋግጧል። የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች አራት መሆናቸው አልተካደም። ሟች በኑዛዜያቸው ላይ ለወንድሜ ልጅ ሸዋረግ ወርቁ በማለት ኑዛዜ ያደረጉ በመሆኑ፤ ይህም ኑዛዜ በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የኑዛዜው ተጠቃሚዎች በኑዛዜው የተነቀለው የ1ኛ አመልካች አባት እኩል ተካፋይ እንደሚሆኑ ስለገለጸ የውርስ ሀብቱ እኩል ተካፋይ የምትሆን ይሆናል። ስለሆነም የውርስ ሀብት ተካፋዮች አምስት ናቸው። ሆኖም 1ኛ ተጠሪ የያዘው የቤ.ቁ 029 ከ11 ክፍል በላይ ስለሆነ ይህም በውርስ ከሚደርሰው ድርሻ በላይ ስለሆነ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1062(2) እና 1063(1) ከደነገጉት አንጻር የያዘውን ለመመለስ የማይገደድና ከውርስ ሀብቱ ላይም ድርሻውን እንደወሰደ የሚቆጠር በመሆኑ የውርስ ሀብት ተብሎ የተጠቀሰውን ንብረት ወይም ቤት የቀሩት የሟች ሶስት ልጆችና የኑዛዜ ወራሽ የሆኑት ግለሰብ እኩል የሚከፋፈሉ ይሆናል። በመሆኑም የቤ.ቁ 008 ላይ ያሉ ቤቶችን 2ኛ ተጠሪ 1/4ኛ፤ የኑዛዜ ወራሽ የሆኑት ሸዋረጋ ወርቁ 1/4ኛ፤ አቶ ሰለሞን አለማየሁ 1/4ኛ፤ ቀሪ የሟች ወንድይራድ አለማየሁ ድርሻ የሆነውን 1/4ኛ ድርሻ ተተኪ ወራሾች የሆኑት 1ኛ አመልካች፤ 4ኛ አመልካች(ስር 3ኛ ተከሳሽ)፤ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች(ስር ጣልቃገቦች) እያንዳንዳቸው የ1/4ኛውን ድርሻ 1/5ኛ የሚደርሳቸው ይሆናል። ስለዚህ የሟች የውርስ ሀብት የሆነውን የቤ.ቁ 008 ከላይ የተጠቀሱት ወራሾች ከተቻለ በአይነት፤ ካልሆነም በስምምነት፤ ስምምነት ከሌለም በሐራጅ ተሸጦ ሊከፋፈሉ ይገባል።

ከውርስ ሀብት የተሰበሰበውን የቤት ኪራይ በተመለከተ 2ኛ ተጠሪ ከሰበሰቡት ብር 45,000.00 ውስጥ 1ኛ አመልካች፤ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የአባታቸውን ድርሻ 1/5ኛ ብር 2250.00 ለእያንዳንዳቸው 2ኛ ተጠሪ ልትከፍል ይገባል። 4ኛ አመልካችም ከሰበሰበው ብር 15,000.00 ላይ ለ1ኛ አመልካች፤ ለ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የአባታቸውን ድርሻ 1/5ኛውን ብር 750.00 ለእያንዳንዳቸው ሊከፍል እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ እና 4ኛ አመልካች ክስ ከቀረበበት ግዜ በኋላ የድርሻቸውን እስከሚከፋፈሉ ድርስ ያለውን የኪራይ ገቢ የድርሻቸውን እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል።

አመልካቾች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም የቤ.ቁ 029 በሆነው ቤት ላይ የስር ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ አመልካቾች ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ በመሰረዝ ትእዛዝ ሰጥቶ፤ ይግባኙ ያስቀርባል በማለት ጭብጥ በያዘባቸው ጉዳዮች ላይ የተጠሪዎችን መልስ ከተቀበለ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል።

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ውሳኔዎች በመቃወም ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ የሚች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ የውርስ ሀብት መብት ይገባናል ብለን የተከራከርነው አመልካቾች እና ተጠሪዎች

ብቻ ነን። ምንም አይነት የመብት ጥያቄ ባልተነሳበትና የክርክርም ጭብጥ በሌለበት በተሰረዘ ኑዛዜ ለአውራሻችን የወንድም ልጅ ለወ/ሮ ሸዋረጋ ወርቁ ከህግ አግባብ ውጪ የተሰጠው የውርስ መብት ተሰርዞ ወራሾቹ አመልካቾች አባታችንን ተክተን በአንድ ዘንግና ተጠሪዎች በጠቅላላ 3 የሚሿ አውራሻችን ወራሾች ብቻ ናቸው። መብት ላልጠየቀና ግራቀኛችን ስንከራከር በአንድ ቀበሌ ውስጥ አብረው እየኖሩና ክርክሩን እያወቁ ቀርበው መብት አለኝ ላላሉ ወገኖች ባልተጠየቀ ዳኝነት የሚሰጥ ውሳኔ የለም እንዲባል።

በአማራጭ አቶ ሰለሞን አለማየሁም ሆነ ልጆቹ እነ ወይንሸት ሰለሞን በዚሁ ክ/ከተማ እና ወረዳ አመልካቾች እና ተጠሪዎች ከምንከራከርበት ሀብት ያላነሱ የመኖሪያ እና የንግድ ቤቶችን ከላይ በተጠቀሱት መዝገቦች ወራሾች ሆነው የውርስ ድርሻ ያገኙ ስለሆነ ሌላ ተጨማሪ የውርስ ድርሻ ሳይጠይቁ ሊሰጣቸው አይገባም። ከዚህ አንጻር የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባል።

የሚች አውራሻችን የውርስ ሀብቶች ይጎውም በአንድ ግቢ ውስጥ የሚገኙት የቤት ቁጥራቸው 008፤ 008/009 እና 029 የአመልካቾች እና የተጠሪዎች የጋራ የውርስ ሀብቶች ናቸው። የስጦታ ማስረጃ ባልቀረበበት እና በተሻረ የኑዛዜ መብት መነሻነት የቤ.ቁ 029 የሆነው ቤት የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት በሚል የተሰጠው ውሳኔ እና የከፍተኛው ፍ/ቤት ቅሬታው አያስቀርብም ሲል የሰጠው ትእዛዝ እንዲሻር እና ቤቱ የውርስ ሀብት ነው ተብሎ እንዲወሰን።

የቤት ኪራይ ገቢውም በሰው እና በሰነድ ማስረጃዎች በተረጋገጠው መሰረት ከቤ.ቁ 008፤ 008/009 የሚገኘው ወርሃዊ የኪራይ ገቢ በ2ኛ ተጠሪ የሚሰበሰበው የኪራይ መጠን በወር ብር 3,500.00 መሆኑ እና ከቤ.ቁ 029 በ1ኛ ተጠሪ የሚሰበሰበው ወርሃዊ የኪራይ ገቢም ብር 16,000.00 መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ በክሱ የውርስ ድርሻ ከተጠየቀበት ግዜ እና የውርስ ሀብቱን ድርሻ አመልካቾች እስከምናገኝበት ግዜ ድረስ ያለው የገንዘብ መጠን ተሰልቶ እንዲከፈለን ውሳኔ እንዲሰጥልን የሚል ነው።

ይህ አቤቱታቸው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የስር ፍ/ቤቶች ሸዋረጋ ወርቁ እና ሰለሞን አለማየሁ ለተባሉ በመዝገቡ ውስጥ ተከራካሪ ላልሆኑ ወገኖች የውርስ ሀብት ባለቤት እንዲሆኑ ያሳለፉት ውሳኔ እና የቤ.ቁ 029 የሆነው ቤትም የ1ኛ ተጠሪ የግሉ ነው ሲሉ የሰጡት ውሳኔ ህጋዊ መስፈርቱን ያሟላ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ2/5/14ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ ተጠሪዎች በ25/5/14ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ አግባብ ነው የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸና፤ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው እንዲወሰን ጠይቀዋል።

አመልካቾች በ17/6/14ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ፤ አቤቱታው ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ተብሎ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ከተያዘው ጭብጥ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል።

አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 6 የቤ.ቁ 029 የሆነውን ቤት በተመለከተ ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ የቤ.ቁ 029 ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ በህይወት ሳሉ ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ ሰጥተውት በራሱ ወጪ የሰራቸው ቤቶች ስለመሆናቸው ፍሬነገርን የማጣራት በህግ ስልጣን የተሰጠው የስር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረቡትን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች እንዲሁም ከየካ ክ/ከተማ ወረዳ 6 የቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት የቀረበለትን ምላሽ መርምሮ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ እንዲሁም ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ በ2/2/93ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተሻሻለ እንጂ ያልተሻረ መሆኑንም ጭምር የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍሬነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የቤ.ቁ 029 የሆነው ቤት የሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ የውርስ ሀብት ሳይሆን የ1ኛ ተጠሪ የግል ሀብት ነው፤ ከዚሁ ቤት 1ኛ ተጠሪ የሰበሰበው የኪራይ ገንዘብም የውርስ ሀብት አይደለም በማለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም በዚሁ ውሳኔ ላይ የቀረበውን ይግባኝ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሰረዝ የሰጠውን ትእዛዝ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘውም፡፡

አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ሸዋረጋ ወርቁ እና ሰለሞን አለማየሁ የተባሉትን ሰዎች በተመለከተ ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ሸዋረጋ ወርቁ እና ሰለሞን አለማየሁ የሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ ወራሾች (ሌሎች ወራሾችም ያሉ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ) መሆናቸው እና ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ በ2/2/93ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተሻሻለ እንጂ ያልተሻረ ስለመሆኑ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ ባየው የፌ/ከ/ፍ/ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ከሆነ ደግሞ የሟች ወራሾች የሆኑት ሸዋረጋ ወርቁ እና ሰለሞን አለማየሁ በጉዳዩ ላይ አለመከራከራቸው ከሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ የውርስ ሀብት ድርሻቸውን እንዳያገኙ እንዲሁም አመልካቾች ከውርስ ሀብት ከሚደርሳቸው ድርሻቸው በላይ እንዲያገኙ የማያደርጋቸው በመሆኑ ከዚህ አንጻር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሸዋረጋ ወርቁ እና ሰለሞን አለማየሁን በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ በኮ.መ.ቁ 116047 በ21/9/12ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 257494 በ10/10/13ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. በዚህ የሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

4. በዚህ መዝገብ በ24/6/14ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 6 ክልል ውስጥ የሚገኙ የቤት ቁጥራቸው 008፤ 008/009፤ 029 የሆኑ ቤቶች እንዳይሸጡ፤ እንዳይለወጡ በማንኛውም ሁኔታ ለሶስተኛ ወገን ሳይተላለፉ ባሉበት ሁኔታ ተከብረው እንዲቆዩ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለየካ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር እንዲሁም ለየካ ክ/ከተማ ወረዳ 6 አስተዳደር ጽ/ቤት ይጻፍ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ. 213747
ቀን ፡- ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ኤምቲጂዲ ኤሌክትሮ ሜካኒካል ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር --ጠበቃ ዳንኤል ግርማ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ኮንሳልት ኮንሶራቪኦ አልታቴንሲዮኔ ኢትዮጵያ ብራንች

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ፤ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ያቀረበው ክስ ውልን መሠረት በማድረግ ተጠሪ ብር 10,386,376.43 እንዲከፍለው ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ተጠሪ ባቀረበው መከራከሪያ በውላችን መሠረት አለመግባባት ቢከሰት በግልግል ጉባዔ እንዲታይ የተስማማን በመሆኑ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት ክሱ እንዲሰረዝ ጠይቋል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ በውላቸው አንቀጽ 17 መሠረት አለመግባባት ሲኖር በዓለምአቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም እንዲታይ የተስማሙ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት ወስኗል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ ተቀብሎ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በማከራከር በውሉ አንቀጽ 17 ላይ አለመግባባት ቢከሰት ተዋዋይ ወገኖች በመጀመሪያ ደረጃ ለመወያየትና ጉዳዩን በአይሲሲ የአማራጭ ሙግት መፍቻ ዘዴዎች ሕጎች መሠረት መፍትሔ ለመስጠት መስማማታቸውንና፤ ክርክሮች በመጨረሻም በዓለምቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም ድንጋጌዎች መሠረት በአንድ ወይም ከአንድ በላይ ገላጋይ ዳኛ አማካኝነት እልባት የሚያገኝ ስለመሆኑ ተመልክቷል። በሥምምነት ለመጨረስ አመልካች ጠይቆ ያልተሳካ በመሆኑ ጉዳዩ በግልግል ጉባዔ የሚታይ ነው። ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት ውሳኔውን አጽንቷል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የውሉ አንቀጽ 17 ፡- ከዚህ ሥምምነት ጋር በተያያዘ አለመግባባት ከተከሰተ ተዋዋይ ወገኖች በመጀመሪያ ውይይት ለማድረግ ጉዳዩ በአይሲሲ ኤዲአር ሕግጋት መሠረት ለግልግል ሂደት ማቅረብን እንደ አማራጭ ለመውሰድ ተስማምተዋል ይላል። ይሕም ተዋዋዮች ከፈለጉ እንደአማራጭ የሚጠቀሙት፤ ካልፈለጉ ደግሞ የሚተውት ሆኖ ሥምምነቱ መደረጉን ያሳያል። መተርጎም ያለበት የአንቀጽ 17 የመጀመሪያ ዓረፍተ ነገር ነው፤ ዓረፍተ-ነገሩ ግልጽ ነው፤ ግልጽ አይደለም ከተባለም መተርጎም ያለበት መብቱን የሚያጣው ወይም የሚገደደው ተዋዋይ ወገንን በሚደግፍ መልኩ ነው። ተጠሪ የትኛውን አማራጭ እንደሚደግፍ ደብዳቤ ተጽፎለት ምላሽ ያልሰጠ በመሆኑ ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊታይ ይገባል የሚል ነው። የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ፍርድ ቤቱ ክሱን ለማየት ሥልጣን የለኝም ማለቱ ከውሉ አንቀጽ 17 አኳያ ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ በማዘዙ ተጠሪ ያቀረበው መልስ በውሉ አንቀጽ 17 አማራጭ ሆኖ የተቀመጠ አይሲሲ ኤዲአር (ICC ADR) ሕግጋት ግጭት መፍቻ መንገዶች ተብለው የተቀመጡት እርቅና ሥምምነት ናቸው። ወደግልግል መሄድ አለመሄድ አማራጭ ሆኖ በውሉ አልተመለከተም። ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በሏል። አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካች ያቀረበው ክስ በግልግል ጉባዔ የሚታይ ነው ተብሎ መወሰኑ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል።

እንደመረመርነው አመልካች በውል መሠረት ያልተከፈለ ገንዘብና የደረሰ ኪሣራ ተጠሪ እንዲከፍለው ክስ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የውል አለመግባባት ሲኖር በግልግል ጉባዔ ለመዳኘት ስለተስማማን ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊታይ አይገባም በማለት ተከራክሯል። የዳኝነት ሥልጣን በመርሕ ደረጃ የሚወሰነው በሕግ ቢሆንም ተዋዋዮች በሕግ በተፈቀደው አግባብ አለመግባባት የሚታይበትን የዳኝነት አካል የመምረጥ መብት አላቸው። ሰዎች በመካከላቸዉ ከፈጠሩት ሕጋዊ ተግባራት በመነጨ ወይም ከዚህ ጋር በተያያዘ ለወደፊት በመካከላቸዉ የሚፈጠረዉን አለመግባባት ወይም ተፈጥሮ ያለዉን አለመግባባት ከመደበኛ ፍርድ ቤት ዉጭ በግልግል ዳኝነት በኩል ለመፍታት የመዋዋል ነጻነታቸዉን በመጠቀም መስማማት እንደሚችሉ የፍ/ሕ/ቁ. 3328 እና የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315(1) ያስረዳሉ። የግልግል ዳኝነት ሥምምነት በጽሁፍ በተዋዋሉት በዋናዉ ዉላቸዉ በሚያደርጉት የግልግል ዳኝነት ስምምነት ቃል (Arbitration Clause) ወይም አስቀድሞ

በመካከላቸዉ ተከስቶ ያለዉን አለመግባባት በግልግል ዳኝነት ለመፍታት ራሱን በቻለ የጽሁፍ የግልግል ዳኝነት ስምምነት (Arbitral Submission) ሊመለከት ይቻላል፡፡

ተዋዋዮች በውል አለመግባባቱ የሚታይበትን ሥርዓት ከወሰኑ ውል በፍ/ሕ/ቁ. 1731(1) እንደተመለከተው በተዋዋዮች መካከል እንደ ሕግ አስገዳጅ በመሆኑ በወሰኑት የዳኝነት አካል የመዳኘት ግዴታ ይጥልባቸዋል፡፡ በግልግል ዳኝነት ሊታይ የሚገባው ክስ ፍርድ ቤት ከቀረበ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለሌው ስለመሆኑ ውላቸውን መሠረት በማድረግ ተከራካሪዎች ወይም ፍርድ ቤቱም በግልግል እንዲታይ ሥምምነት መኖሩን ካወቀ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9(2) መሠረት በማናቸውም የክርክሩ ደረጃ ሊያነሳው ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የማይኖረው በሕግ መሠረት ይሁን በተዋዋዮች የግልግል ዳኝነት ጉባዔን መምረጥ ውጤቱ ተመሳሳይ ነው፡፡ ጉዳዮች ከፍርድ ቤት ውጭ እንዲታዩ ካስፈለገበት ዓላማ አንዱ የፍርድ ሂደት ቅልጥፍና (efficiency) ለመጨመር በመሆኑ ተዋዋዮች ጉዳዩ በግልግል ጉባዔ እንዲታይ ከተስማሙ በኋላ ሊተው እንደሚችል መብት (waivable right) ተቆጥሮ ክሱን በፍርድ ቤት ካቀረቡት ለግልግል ጉባዔ የማቅረብ መብታቸውን እንደተውት የሚቆጠርና ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣን የሚሰጠው አይደለም፡፡ ሥለሆነም በውል ያላቸውን አለመግባባት በግልግል ዳኝነት እንዲታይ ያደረጉትን ሥምምምነት በተመሳሳይ የጽሁፍ ሥምምነት አድርገው እስካላሻሻሉት ድረስ የዳኝነት ሥልጣን በተከራካሪዎች የክርክር አቀራረብ ሆነ ክርክሩ በደረሰበት ደረጃ ምክንያት የሚወሰን አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት የውል ሥምምነት አንቀጽ 17 ላይ “In the event of any dispute arising out of or in connection with this agreement, the parties agree in the first instance to discuss and consider submitting the matter to settlement proceedings under ICC ADR Rules. Disputes shall be finally settled under the rules of arbitration of the international chamber of commerce by one or more arbitrators appointed in accordance with the said rules of arbitration” ተብሎ ተመልክቷል፡፡ አንቀጽ 17 አለመግባባት ቢከሰት ተዋዋይ ወገኖች በመጀመሪያ ደረጃ ለመወያየትና ጉዳዩን በዓለምአቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም የአማራጭ ሙግት መፍቻ ዘዴዎች ሕጎች መሠረት መፍትሔ ለመስጠት መስማማታቸውንና፤ ክርክሮች በመጨረሻም በዓለምቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም ድንጋጌዎች መሠረት በአንድ ወይም ከአንድ በላይ ገላጋይ ዳኛ አማካኝነት እልባት የሚያገኝ ስለመሆኑ መስማማታቸውን ያረጋግጧል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በውሉ ድንጋጌ የመጀመሪያ ዓረፍተ-ነገር መሠረት ወደ ግልግል ጉባዔ መሄድ አለመሄድ በተዋዋዮች ምርጫ የሚወሰን ስለመሆኑ ያመላክታል በማለት ነው፡፡ የውሉ አንቀጽ 17 ሁለቱም ዓረፍተ-ነገሮች በዓለምአቀፍ የንግድ ምክር ቤት አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ ሕግጋትን የሚገልጹ ናቸው፡፡ የግራቀኙ የውል ሥምምነት የመጀመሪያ ዓረፍተ-ነገር እንደሚያስገነዝበው ተዋዋዮች በመወያየትና በመነጋጋር አለመግባባታቸውን በዓለምአቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም የአማራጭ ሙግት መፍቻ ዘዴዎች ሕጎች መሠረት መፍትሔ ለመስጠት መስማማታቸውን የሚገልጽ ሲሆን ቀጥሎ

ያለው የውሉ አካል በመጨረሻም በዚሁ ተቋም ጉዳዩ በግልግል የሚያልቅ መሆኑ መመላከቱ ሲታይ የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር በዓለምአቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም ከግልግል ውጭ ያለ አለመግባባት የሚፈታበት ዘዴን የሚመለከት ስለመሆኑ ተረድተናል፡፡ የዓለምአቀፍ የግልግል ተቋም አለመግባባትን በግልግል የመፍታት ዘዴ ደንቦች (arbitration rules) እና አለመግባባትን በእርቅና በሥምምነት የመፍታት ዘዴ ደንቦች (mediation rules) ያካተተ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ጉዳያቸውን በዓለምቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም በእርቅና በሥምምነት ለመጨረስ መወያየት የሚችሉ ስለመሆኑ የተመለከተ ሲሆን በሥር ፍርድ ቤት እንደተረጋገጠው በዚህ አግባብ ለመፍታት ስላልተስማሙ ጉዳዩ በግልግል የሚታይና የመጨረሻ እልባት በዓለምቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም አማካኝነት የሚሰጠው እንጂ ክሱ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ሥልጣን የለንም በማለት የአመልካችን ክስ መሰረዛቸው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 196236 ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 252488 ሐምሌ 28 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ. 213738
ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ዐሐይ መንክር

ኑረዲን አድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. አቶ ንጉሴ ወ/ማሪያም
2. አቶ ጌታቸው ወ/ማሪያም } *ጠበቃ ገ/ክርስቶስ ገ/ማርያም ቀረቡ*
3. አቶ ዐጋዬ ወ/ማሪያም

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አሰለፈች ንጋቱ

2. አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 አስተዳደር ጽ/ቤት

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ጳጉሜ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 188603 ታህሳስ 7 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠውን ብይን በማጽናት፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 270002 ሰኔ 3 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የቤት እና ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪዎች ተከሳሾች፤ በዚህ የሰበር ክርክር የሌለው የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ቤቶች አስተዳደር ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተከራክረዋል። የአሁን አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 የቤት ቁጥር 511 ቤት ግቢ በስተደርባ ከደቡብ በኩል የተወረሰ እና 1ኛ ተጠሪ የምትኖበርበት የቤ.ቁ 510 የሆነ ቤት አለ፤ አመልካቾች እና 1ኛ ተጠሪ በጋራ የምንጠቀምበትን መጸዳጃ ቤት 1ኛ ተጠሪ ያለአመልካቾች ፈቃድ በማፍረስ ሰርቪስ ቤት በመስራት እንዳንጠቀምበት አድርጋለች፤ 1ኛ ተጠሪ ማንም ሳይፈቅድላት ከምንኖርበት ቤት በስተሰሜን በኩል ከአመልካቾች ቤት ግድግዳ በማስጠጋት በግምት 100 ካ.ሜ አስፋፍታ ያጠረችውን አጥር እንድታፈርስ በተደጋጋሚ ተጠይቃ ፍቃደኛ አልሆነችም፤ 2ኛ ተጠሪም ከፕላን ውጪ ያለፈቃድ የተሰራውን እንዲያፈርስልን እንዲሁም የ1ኛ ተጠሪን ሕገወጥ ግንባታ አስቁሞ በሸንት ቤት የምናገኘውን አገልግሎት ወደ ነበረበት እንዲያስመልስን፣ 1ኛ ተጠሪ ወደ ይዞታችን ገብታ ያላግባብ ያጠረችውን አጥር እንድታፈርስ ጠይቀነው ለማስፈጸም ፍቃደኛ አይደለም፤ ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ የተገነባውን ሰርቪስ ቤት እንድታፈርስ እና መጸዳጃ ቤቱን ወደ ነበረበት እንድትመልስ አስፋፍታ ያጠረችውን አጥር በተሰጠው የፕሮፖርሽን ካርታ መሰረት እንድታፈርስ፤ 2ኛ ተጠሪም የተሰራውን ግንባታ አስፈርሶ የጋራ መጸዳጃ ቤት በ1ኛ ተጠሪ ወጪ ተሰርቶ አገልግሎት ላይ እንዲውል እንዲያደረግ አጥሩንም እንዲያስፈርስ ይወሰንልን ሲሉ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

የአሁን 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ 1ኛ ተጠሪ ለክርክር መነሻ የሆነውን ቤት በኪራይ የያዝኩት የመንግስት ቤት ላይ አመልካቾች ከሕግም ሆነ ከውል የመነጨ መብት የላቸውም፤ አመልካቾች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 33 ድንጋጌ አግባብ መብት እና ጥቅም እንዳላቸው የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረቡም፤ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ነው፤ ስለሆነም የአመልካቾች ክስ በብይን ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ከሰማ በኋላ አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መጸዳጃ ቤት በጋራ የመጠቀም መብት እንዳላቸው የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፤ 1ኛ ተጠሪ የሚኖሩበት የቀበሌ ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 ሲወረስ አከራካሪው መጸዳጃ ቤት የጋራ ተብሎ ስለመጠቀሱ አልተረጋገጠም፤ ስለሆነም አመልካቾች ለክርክር መነሻ በሆነው ቤት እና ይዞታው ላይ መብት እና ጥቅም እንዳላቸው ያልተረጋገጠ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 33 ተቀባይነት የለውም፤ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ቀሪ የተደረገ በመሆኑ በ2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ ቀሪ ሆኗል፤ አመልካቾች በክሳቸው ውስጥ በአንድ ቦታ 1ኛ ተጠሪ አጥሩን በአመልካቾች ግድግዳ በማስጠጋት አስፋፍታ ሰራች ሲሉ በሌላ ቦታ ደግሞ ወደ ይዞታችን ገብታ አላግባብ አጥራለች የሚል እርስ በእርሱ የሚጋጭ እና ግልጽነት የጎደለው ክርክር ያቀረቡ በመሆኑ ክሱ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 231 መሰረት የክስ ምክንያት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎ 1ኛ ተጠሪ ያጠሩት አጥር የአመልካቾችን የይዞታ መብት በሚጋፋ መልኩ የታጠረ እንደሆነ ክስ ማቅረብ ይችላሉ፤ የአመልካቾች ክስ ከፕላኑ ጋር የሚያያዝ ባለመሆኑ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን አለው በማለት በዚህ ረገድ ጣልቃ ገብ ያቀረበውን መቃወሚያ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም በማለት ብይን ሰጥቷል።

አመልካቾች ይህንኑ ብይን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙ ተሰርዟል።

አመልካቾች ይህን ውሳኔ በመቃወም ጳጉሜ 1 ቀን 2013 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ አመልካቾች ክሱን ስናቀርብ ቤቱ የተወረሰበት ቅጽ በአራዳ ክፍለ ከተማ ይዞታ አስተዳደር ስለሚገኝ ፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 145 መሰረት አስቀርቦ ሳይመለከት እንዲሁም የቆጠርናቸው ምሰክሮች ሳይሰሙ ያቀረብነው ማስረጃ ሳይመረመር በፍሬ ነገሩ ላይ ሳያከራክር የባለሙያ አስተያየት ባልተጠየቀበት የመከላከል እና ክስ የማስረዳት መብታችንን ተነፍገናል፤ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰር ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የለኝም የሚል ብይን ባልሰጠበት የሰር ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን የለኝም ብሎ መዝገቡ የዘጋው የሚነቀፍበት ምክንያት የለም ሲል የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ ማድረጉ ተገቢነት የለውም፤ በመሆኑም በሰር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይን እና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በዚህ ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት ክሱ ግልጽ አይደለም ካለ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 91 መሰረት እንዲያሻሽል ማዘዝ እየቻለ ክሱ እርስ እርሱ ይጋጫል ብሎ ውድቅ ማድረጉ እና በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 145 መሰረት እንዲቀርብ በአመልካች የተጠየቀውን ማስረጃ ሳይቀርብ ውሳኔ መስጠቱን አግባብነት ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

1ኛ ተጠሪ የካቲት 21 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፦ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ነው፤ አመልካቾች መጻዳጃ ቤቱ የግል ይዞታዬ ነው የሚል ክርክር አላቀረቡም፤1ኛ ተጠሪ የግንባታ ፍቃድ ከሚመለከተው አካል አግኝቼ ስለመሰራቱ ተረጋግጧል፤ ቤቱ በተወረሰበት ቅጽ ላይ መጻዳጃ ቤት የመጠቀም መብት ለአመልካቾች አልተሰጠም እንጂ ተሰጥቶ ቢሆን እንኳን መንግስት የራሱ በሆነው ይዞታ ላይ የማዘዝ ስልጣን ስላለው 1ኛ ተጠሪ ብቻ ብትጠቀም ቢወስን የህግ ድጋፍ አለው፤ አመልካቾች ክስ እንዲያሻሽሉ ተደርጎ እንደ አዲስ ክርክሩ እንዲቀጥል ከማድረግ ይልቅ አዲስ ክስ አቅርበው እንዲከራከሩ በማድረግ የታለፈባቸው መብት ካላቸው መጠየቅ ስለሚችሉ ክሱ ሊሻሻል ይገባል በማለት የሰጠው ብይን ተገቢነት ያለው እና አመልካቾችም በሰር ፍርድ ቤት ያላነሱት አዲስ ክርክር ነው፤ በመሆኑም በሰር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይን እና ትዕዛዝ ሊጸና ይገባል የሚል ነው።

2ኛ ተጠሪ መጋቢት 16 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፦ የሰር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በአግባቡ አድምጦ የሰጠው ብይን ተገቢ ነው፤ አመልካቾች መጻዳጃ ቤት የጋራ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረቡም፤ አመልካቾች ክሳቸውን በማስረጃ አስደግፈው አላቀረቡም፤ በመሆኑም በሰር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይን እና ትዕዛዝ ሊጸና ይገባል የሚል ነው።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገብ ተያይዞ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚህ ተጠናቋል። የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ በሰር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል ከተደረገው አጠቃላይ ክርክር እና ከተሰጠ ብይን እንዲሁም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል።

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው አመልካቾች በሰር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ 1ኛ ተጠሪ በጋራ የሚጠቀሙበትን መጸዳጃ ቤት 1ኛ ተጠሪ ያለአመልካቾች ፈቃድ በማፍረስ ሰርቪስ ቤት በመስራት እንዳይጠቀሙበት ያደረጓቸው እና ማንም ሳይፈቅድላቸው ከመኖሪያ ቤታቸው በስተሰሜን በኩል የአመልካቾችን ቤት ግድግዳ በማስጠጋት አጥር ያጠሩ መሆኑን፤ 2ኛ ተጠሪም ከፕላን ውጪ ያለፈቃድ የተሰራውን ግንባታ እንዲያፈርስ እና በመጸዳጃ ቤቱ የመጠቀም መብታቸውን እንዲያስመልስ ተጠይቆ ፈቃደኛ አለመሆኑን በመግለጽ 1ኛ ተጠሪ የተገነባውን ሰርቪስ ቤት አፍርሰው መጸዳጃ ቤቱን ወደ ነበረበት እንዲመልሱ እና አስፋፍተው ያጠሩትን አጥር በተሰጠው የፓሮፖርሽን ካርታ መሰረት እንዲያፈርስ፤ 2ኛ ተጠሪም የተሰራውን ግንባታ አስፈርሶ የጋራ መጸዳጃ ቤት በ1ኛ ተጠሪ ወጪ ተሰርቶ አገልግሎት ላይ እንዲውል እንዲያደረግ እና አጥሩንም እንዲያስፈርስ እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት የጠየቁ መሆኑን፤ ይህንኑ ክሳቸውን ለማስረዳትም ከክሱ ጋር አያዝየው ባቀረቡት የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን ያቀረቡ መሆኑን በማስረጃው ዝርዝር ተ.ቁ 1፤ 2 እና 10 ላይ የገለጿቸውን ማስረጃዎች ደግሞ ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሠረት በትዕዛዝ አስቀርቦ እንዲመለከትላቸው የጠየቁ መሆኑን ነው።

በመሠረቱ የአንድ መብትና ግዴታ ምንጭ ሕግ ወይም ውል ሲሆን አንድ ከሳሽ ሌላውን ወገን በተከሳሽነት ፍርድ ቤት መክሰስ የሚያስችለው ምክንያት (cause of action) እንዲኖረው የግድ የሚል መሆኑንና ለመክሰስ የሚያስችል ጥቅም ወይም መብት በማረጋገጥ አቤቱታ ካላቀረበ በቀር በማናቸውም ሰው ላይ ክስ ሊያቀርብ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33(2) ድንጋጌ ያስገነዝባል። ሆኖም በአንድ ወገን ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም መኖሩ ብቻውን ውጤት የሚያመጣ ሳይሆን ከሳሹ ተጣሰብኝ ወይም ተደፈረብኝ ወይም አልተፈፀመልኝም የሚለውን ግዴታ በሌላው ወገን ላይ በሕግ ወይም በውል የተጣሰበት መሆኑን፣ ተከሳሹ መብቱ የተደፈረበት ወይም ግዴታ ያልተፈፀመለት መሆኑን፣ መብቱ በመደፈሩ ወይም ሊፈፀምለት ይገባው የነበረው ግዴታ ባለመፈፀሙ ጥቅም የቀረበት ወይም ጉዳት የደረሰበት መሆኑን፣ እንዲሰጥለት የሚጠይቀው ዳኝነት (relief) በሕግ የተፈቀደ መሆኑን ካለሳዩ በቀር ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ ስለመሆኑም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2) እና 231 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መዘንዘብ ይቻላል። በመሆኑም አንድን ክስ የሚያቀርብ ተከራካሪ ወገን ይህንን ሊያስረዳ የሚችል ጠቋሚ ማስረጃ (Prima facie evidence) ሊያቀርብ ይገባል። ከሳሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን ከጅምሩ እንዲያስረዳ የሚጠበቀዉም ክስ ባቀረበበት ጉዳይ ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለዉ ስለመሆኑ የሚያሳይ ጠቋሚ ማስረጃ በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብት ወይም ጥቅም ማስረዳት መቻል እና እንደክሱ አቀራረብ ወይም እንደተጠየቀዉ ዳኝነት ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የማስረጃ ምዘና ደረጃ ልዩነት አላቸው። ተከራካሪ የሆኑ

ወገኖች የሚያቀርቧቸውን ክርክሮች ለመወሰን በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ፍ/ቤቶች ደግሞ ተከሳሽ ወገን ክሱን ለማስተባበል የሚያቀርበውን መከራከሪያ እና ማስረጃ መሠረት በማድረግ ፍሬነገርን አጣርተው እና ማስረጃ መዝነው ዉሳኔ መስጠት የሚጠበቅባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ ቁ 33/2 እና 231፤ 182 እና 273 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝቡናል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በዚህ ረገድ በተለይም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33 እና 231 አተገባበርን አስመልክቶ በሰ.መ.ቁ 82234፤ 135639፤ 144052 እና በሌሎችም መዝገቦች ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል።

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች ክስ ባቀረቡበት መጸዳጃ ቤት የጋራ የተጠቃሚነት መብት ያላቸው እና የአመልካቾችን መኖሪያ ቤት ግድግዳ በማስደገፍ በ1ኛ ተጠሪ ተሰርቷል የተባለው አጥር ከለምንም ፈቃድ የተሰራ መሆኑን በመግለጽ ክስ ያቀረቡ ሲሆን ክሱን ለማስረዳት የሚያስችላቸውን የተለያየ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርበዋል፤ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሠረትም ፍርድ ቤቱ የተለያዩ ማስረጃዎችን በትዕዛዝ አስቀርቦ እንዲመለከትላቸው ጠይቀዋል። በመሆኑም አመልካቾች ክሱን ለማስረዳት ያቀረቧቸው ማስረጃዎች በሌላ ማስረጃ እስካልተስተባበሉ ጊዜ ድረስ አመልካቾች ክስ ባቀረቡበት መጸዳጃ ቤት እና አላግባብ ታጥሯል በሚሉት አጥር ላይ መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ አስረጂ ወይም ጠቋሚ ማስረጃዎች እንደሆኑ ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው። ስለሆነም አመልካቾች ክሱን ለማስረዳት የሚያስችላቸውን የተለያዩ ማስረጃዎችን አስካቀረቡ እና በፍርድ ቤቱም ትዕዛዝ እንዲቀርብላቸው አስከጠየቁ ድረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሠረት ተገቢውን ትዕዛዝ በመስጠት ማስረጃዎቹ ከተጠየቁበት አካል እንዲቀርቡ በማድረግ፤ ተጠሪዎች በጉዳዩ ላይ የሰጡትን መልስ መሠረት በማድረግ አከራካሪ የሆነው የፍሬነገር ጭብጥ ከተለየ በኋላ አመልካቾች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች መሆን አለመሆናቸው በአግባቡ ተለይተው፤ ተመዝነው እና ከተገቢው ሕግ ጋር ተገናዝበው አመልካቾች በጠየቁት ዳኝነት መሠረት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ መሆን አለመሆናቸው በመግለጽ ዉሳኔ የሚሰጥበት እንጂ ከወዲሁ አመልካቾች ከመነሻውም ቢሆን ክሱን ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል አይደለም።

በሌላ በኩል አመልካቾች አላግባብ በ1ኛ ተጠሪ ታጥሯል ያሉት አጥር ራሱን የቻለ ጥያቄ እንጂ ከጸዳኛ ቤቱ በጋራ የመጠቀም መብት ጋር እርሱ በእርሱ የሚጋጭ በመሆኑ የክስ ምክንያት የለውም የሚያስብል አይደለም፤ በ2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበው ክስም 1ኛ ተጠሪ አላግባብ ፈጽመውታል በሚል የተጠቀሰውን ተግባር ለማስቆም አስተዳደራዊ ግዴታውን አልተወጣም ከሚል መነሻነት የቀረበ በመሆኑ አብሮ ተጠቃሎ የሚታይ ነው።

በመሆኑም የሰር ፍ/ቤቶች ከግራ ቀኙ ክርክር እና ክርክራቸውን ለማስረዳት ካቀረቡት ማስረጃ አንፃር አመልካቾች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች እንደክስ አቀራረባቸው ለማስረዳት የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች መሆን አለመሆናቸው በአግባቡ ከተለዩ በኋላ በእያንዳንዱ ማስረጃ ላይ ተገቢ የሆነ ሕጋዊ ትንታኔ በመስጠት አመልካቾች በጠየቁት ዳኝነት መሠረት ለማስወሰን የሚያስችል መብት ያላቸው መሆኑን አለመሆኑን ለይተው ውሳኔ መስጠት ሲገባቸው ይህንኑ ሳያደርጉ አመልካቾች ክስ ባቀረቡበት ንብረት ላይ

መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2፤ 33/3 እና 231/1/ሀ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ እና ኢ-ሥነ-ሥርዓታዊ ሆኖ አግኝተነዋል።

ውሣኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 188603 ታሕሳስ 07 ቀን 2013 ዓ.ም. የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 270002 ሰኔ 03 ቀን 2013 ዓ.ም. የሰጠው ብይን እና በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሸሯል።
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በብይን የዘጋውን መዝገብ እንደገና በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው መንገድ አመልካቾች ከተለያዩ አካላት እንዲቀርቡላቸው የጠየቋቸውን ማስረጃዎች በማስቀረብ እና ከክሱ ጋር አያይዘው ያቀረቧቸውን ማስረጃዎች እንደክስ አቀራረባቸው ለማስረዳት የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች መሆን አለመሆናቸው በአግባቡ ከለየ በኋላ በእያንዳንዱ ማስረጃ ላይ ተገቢ የሆነ ሕጋዊ ትንታኔ በመስጠት አመልካቾች ዳኝነት በጠየቁበት ጉዳይ ላይ መብትና ጥቅም ያላቸው ስለመሆኑ ተጠሪዎች በጉዳዩ ላይ ከሰጡት መልስ እና ካቀረቡት ማስረጃ ጋር ከፍሬነገር ክርክሩ ጋር አብሮ በማጣራት መርምሮ ተገቢ የሆነውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል።
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

ትዕዛዝ

- የዚህ ውሣኔ ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
- መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

አ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ 213553

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ ተስፋዬ አማረ -- ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኮልፌ ቅዱስ ራጉኤል አዲስ ህይወት አክስዬን ማህበር -- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ከማህበሩ አባልነት እንዲሰናበቱ የተወሰነበትን አግባብነት ከመተዳደሪያ ደንባቸውና አግባብነት ካላቸው የንግድ ህጉ ድንጋጌዎች አንፃር ለመመርመር ሲባል ነው።

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ክርክሩ የጀመረው የአሁን አመልካች ከሌሎች 16 ሰዎች ጋር በመሆን በተጠሪ ላይ በፌዴራሉ የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው። ከሳሾች በቀን 29/12/2011 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ተከሳሽ በ1991 ዓ.ም በተፈረመ እና ሙሉ

በሙሉ በተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ብር 55,200.00 (ሀምሳ አምስት ሺህ ሁለት መቶ) በሆነ እንዳንዳቸው ብር 50.00 በሚያወጡ 1104 አክስዬኖች የተመሰረተ ሲሆን ከሳሾች እያንዳንዳችን የተለያዩ ብዛት ያላቸው አክስዮኖች የገዛን እና ሙሉ ክፍያ የፈጸምን የማህበሩ ባለድርሻዎች ነን፡፡ ማህበሩ ከተመሰረተ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜ ያለምንም ድንገተኛ ጉባኤ ውሳኔ ገንዘብ ገቢ እንድናደርግ ተጠይቀን ከሳሾች እያንዳንዳችን ለማህበሩ የተለያየ መጠን ያለው ገንዘብ ገቢ ያደረግን ቢሆንም ገቢ ባደረግነው ገንዘብ ልክ አዲስ የአክስዬን ድርሻ አልተሰጠንም ወይም ባወጣነው ገንዘብ መጠን ልክ ያሉን የአክስዩን ድርሻዎችን ዋጋ እንዲጨመር አልተደረገልንም፡፡ ተከሳሽ በቀን 30/10/2010 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ባወጣው ማስታወቂያ ከሳሾች እያንዳንዳችን ከብር 50,000.00 (ሀምሳ ሺህ) በላይ ያልከፈልነው ውዝፍ እዳ ያለብን መሆኑን ገልጾልናል፡፡ ከሳሾች እንዳንሳተፍ በተከለከልንበት እና ተከሳሽ በቀን 10/10/2010 ዓ.ም ባካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ ባሳለፈው ውሳኔም ከሳሾች አለባቹ የተባልነውን የሊዝ ክፍያ፣ ውዝፍ የቦታ ኪራይ፣ የግንባታ እና የተለያዩ ውዝፍ ክፍያዎች ከነመቀጫው የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ (እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2010 ዓ.ም ድረስ) ክፍያውን የማናጠናቅቅ ቢሆን በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት የከሳሾችን ስም በመሰረዝ አክስዬን ማህበሩ ባስገነባነው የገበያ አዳራሽ ህንጻ ውስጥ በከሳሾች ስም የተመዘገቡ ሱቆችን ወደ አክስዬን ማህበሩ የሚጠቃለሉ መሆኑን ገልጿል፡፡ ተከሳሽ በቀን 10/10/2010 ዓ.ም ባደረገው ጉባኤ ያሳለፈው ውሳኔም በራሱ ህገወጥ በመሆኑ ፈራሽ ከመሆኑም በላይ የጠቅላላ ጉባኤው ጥሪ የተደረገው የአገልግሎት ግዜያቸውን በጨረሱ የስራ አመራር ቦርድ አባላት በመሆኑ ውሳኔው ፈራሽ ሊደረግ የሚገባ ነው፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ ማህበር በቀን 10/10/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ህገወጥ በመሆኑ እንዲሰረዝ፤ ተከሳሽ በሚያደርጋቸው እና በሚጠራቸው ጠቅላላ ጉባኤዎች ላይ ከሳሾች እንድንሳተፍ የሚያደርገው ክልከላ ህገ ወጥ ነው ተብሎ እንዲወሰን፤ እንዲሁም የተከሳሽ ስራ አመራር ቦርድ የአገልግሎት ዘመኑ አልቋል ተብሎ እንዲወሰንልንና የጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ተደርጎ አዲስ የስራ አመራር ቦርድ እንዲመረጥ እንዲወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ባቀረበው መልስ ከ1ኛ-12ኛ ከሳሾች (2ኛ ከሳሽ የነበሩትን የአሁን አመልካች ጨምሮ) ከማህበሩ እንዲሰረዙ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰኔ 19/2008 ዓ.ም

እንጂ ሰኔ 10/2010 ዓ.ም አይደለም፡፡ ሰኔ 10/2010 ዓ.ም የተላለፈው ውሳኔ ለፎርማሊቲ ከሌሎች ጋር ስማቸው በመጠቀሱ እንጂ ከሳሾች ቀደም ሲል ተሰርዘዋል፡፡ የተሰረዙበትን ሰኔ 19/2008 ዓ.ም የተደረገውን የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ለማስፈረስ ከሳሾች በተከሳሽ አክስዬን ማህበር ላይ በፈ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክስ መስርተው ተወስኖባቸው በይግባኝም እስከ ከፍተኛው ፍ/ቤት በመሄድ ክሳቸው ውድቅ የተደረገባቸው በመሆኑ በድጋሚ ክስ ማቅረባቸው አግባብ አይደለም፡፡ ማህበሩ በተመሰረተ ግዜ በወቅቱ ህጋዊ እውቅና ለማግኘት ባስመዘገበው ካፒታል ብቻ ለአባላት ጥቅም የሚያስገኝ ግዙፍ ተግባር እሰራለሁ ብሎ ሳይሆን ሰፊ ራዕይ ሰንቆ በመነሳት በግዜያዊነት የያዘውን መሬት በሊዝ በመግዛት ህንጻ ለመገንባት ስለነበር በዚው መሰረት አባላት በየግዜው የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ለሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ተገዥ በመሆን በነፍስ ወከፍ ከብር 280,000.00 በላይ መዋጮ እያዋጡ ዛሬ ከብር 360,000,000.00 (ሶስት መቶ ስልሳ ሚሊየን) በላይ የሚያወጣ ዘመናዊ የገበያ ማዕከል ህንጻ ተገንብቶ ግዴታቸውን የተወጡት አባላት ተጠቃሚ እየሆኑ ናቸው፡፡ በዚህም ከሳሾች እንደ ሌሎቹ አባላት ግዴታቸውን ሳይወጡና ተሳትፎ ሳያደርጉ በሌላው ድካምና ገንዘብ የተገነባው ህንጻ ባለቤት ለመሆን ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ከሳሾች እንዲከፍሉ የተጠየቁት ልዩ ልዩ ክፍያዎች በየጊዜው በሚደረገው የአክስዬን ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች መሰረት ሲሆን ሌሎች የማህበሩ አባላት ያወጡትን የግንባታ መዋጮም ሆነ ሌሎች ልዩ ልዩ ክፍያዎች ላለመክፈል ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡ የተከሳሽ ማህበር ቦርድ የምርጫ ጊዜን በተመለከተ የተከሳሽ አክስዬን ማህበር ቦርድ ምርጫ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ጸድቆ የወጣው ጥር 2008 ዓ.ም በመሆኑ እና የ3 አመቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርጫ ግዜው የሚያበቃው ጥር 2011 ዓ.ም ስለሆነ የከሳሾች ክርክር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ከ1-12ኛ ያሉ ከሳሾች የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በሰኔ 19/2008 ዓ.ም ክፍያ ያልከፈሉ አባላት ከማህበሩ እንዲሰናበቱ ያስተላለፈው ውሳኔ ላይ እንዲሰረዝላቸው በመ/ቁ 246539 ክስ አቅርበው ክሱ በይርጋ ውድቅ የተደረገ እና በይግባኝም በመ/ቁ 193641 የጸና ሲሆን ይህ ውሳኔ ባልተሻረበት ሁኔታና ከሳሾች ከፍለው የቀረቡ በመሆኑ በማህበር አባልነታቸው እንዲቀጥሉ የተባለበት አግባብ በሌለበት ሁኔታ እንዲሁም ይህ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ

ውሳኔ መሰረት በአባላት እንዲከፈል ውሳኔ የተሰጠበትን ክፍያ ሌሎች የማህበሩ አባላት ያልከፈሉ መሆኑን በመግለጽ ያቀረቡት መከራከሪያ የሌለ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ከሳሾች በጠቅላላ ጉባኤው በሰኔ 19/2008 ዓ.ም ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ክፍያ የፈጸሙ ስለመሆኑ ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ የለም፡፡ ከሳሾች ቀሪ የማህበሩ አባላት ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም የማህበሩ የስራ እንቅስቃሴ እንዲቀጥል ባደረጉበት አግባብ እንዲሁ በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት መከፈል ያለበትን ክፍያ መክፈል ይገባቸው የነበረ ሲሆን ሆኖም እንደ ማህበር አባልነታቸው ይህን ግዴታቸውን እንደ ሌሎች የማህበሩ አባላት ያልተወጡ ሲሆን ሰኔ 30/2010 ዓ.ም በወጣው የጋዜጣ ማስታወቂያም ከ2ኛ ከሳሽ በስተቀር የቀሪ ከሳሾች ስም ተጠቅሶ ቀሪ ክፍያ እንዲፈጽሙ መጠየቁ በጠቅላላ ጉባኤው ያልከፈሉ አባላት እንዲሰናበቱ በማለት የሰጠውን ውሳኔ ለማስፈጸም የተከናወነ መሆኑን ከሚያመላክት በስተቀር ከሳሾች በተጠቀሰው ግዜ ውስጥ ክስ በቀረበበት ግዜ እንኳን መክፈል ያለባቸውን ክፍያ ያልከፈሉ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ይህ በሆነበት አግባብ ተከሳሽ በቀን 10/10/2010 ዓ.ም ባደረገው የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ግዴታቸውን ያልተወጡ አባላት እንዲሰናበቱ ውሳኔ መስጠቱ በህግ አግባብ ነው ከሚባል በስተቀር የሚሰረዝበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ከሳሾች አዲስ የስራ አመራር ቦርድ ምርጫ ሊደረግ ይገባል በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄም የአባልነት መብታቸው ቀሪ በሆነበት ሁኔታ ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ የሌለ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት 2ኛ ከሳሽ (የአሁን አመልካች) ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ውሳኔው ጸንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች በቀን 27/12/2013 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተፈጸመ የሚሉትን ስህተት ዘርዝረው የስር ፍ/ቤት በማስረጃ ሳያጣራ ቀድሞ በመ/ቁ 246539 እና በመ/ቁ 193641 ተከራክረውበታል በማለት ብቻ የቀድሞው ክርክር አመልካች ቢያንስ የጋዜጣ ጥሪ መደረጉን ባወቅሁ 3 ወር ባልሞላ ጊዜ (በ26 ቀን ውስጥ) ብር 10000.00 ወደ ማህበሩ ገቢ ያደረኩበትን ማስረጃ እንኳ መመርመር ሲገባው አስቀድሞ በይርጋ በብይን የተዘጋውን መዝገብ ተንተርሶ ውሳኔው አልተለወጠም ሲል መወሰኑ ፤ እንዲሁም ከፍተኛው ፍ/ቤትም ብር 10,000.00 የገባበትን አግባብ አጣራለሁ በማለት ያስቀርባል ካለ በኋላ ውሳኔውን

ማጽናቱ ስህተት ነው፤ የስር ፍ/ቤቶች አመልካች በትዕዛዝ እንዲቀርቡልኝ የጠየኳቸውን ማስረጃዎች አስቀርበው አልመረመሩም፤ የቀረቡትንም አላጣራም፤ ተጠሪ የማህበሩ አባል አይደሉም ሲል በግልጽ ክዶ አልተከራከረም፤ ተጠሪ ባመነው መሰረትና በማስረጃነት የጠቀስኳቸውን ምስክሮች ተጣርቶ አለመወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ጉዳዩ ወደ ስር ፍ/ቤት እንዲመለስና እንዲቀርቡ የተጠየቁ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ተሰምተው እንዲወሰንልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በአጣሪ ችሎት ተመርምሮ ከፍሲል በመግቢያችን የገለጽነው ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪ የስር ክርክሩን በማጠናከር በቀን 30/07/2014 ዓ.ም የተፃፈ መለስ ያቀረበ ሲሆን አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረውም በዚህ ሁኔታ ነው፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀው የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ መተዳደሪያ ደንቡንና ህጉን መሰረት በማድረግ ውሳኔ ከሰጠ ውሳኔው ሁሉም አባላት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡ እንዲህ አይነቱ ውሳኔ በጉባኤው ያልነበሩም ሆኑ ተገኝተው በሃሳብ የሚለዩትን ሁሉ ያስገድዳል፡፡ (የንግድ ህጉን አንቀጽ 388(1) እና 416(1) ይመለከቷል)፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በአባልነት ከመመዝገባቸው ባለፈ እንደሌሎች አባላት ለረዥም ዘመን መዋጮ በማዋጣት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ሰኔ 19/2008 ዓ.ም በተደረገ ቃለ ጉባኤ ከአባልነት እንዲሰረዙ መወሰኑና አመልካችም ይህን የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ በመቃወም ለማሰረዝ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 246539 ክስ አቅርበው ውድቅ መደረጉ፤ እንዲሁም ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 193641 ይግባኝ አቅርበው ተቀባይት ሳያገኝ መቅረቱ ግራቀኙን አላከራከረም፡፡ ይህ ውሳኔ ባልተለወጠበት እና ፀንቶ ባለበት ሁኔታ አመልካች ማህበሩ በቀን 10/10/2010 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ ለማሰረዝ፤ በጠቅላላ ጉባኤዎች ለመሳተፍ፤ እንዲሁም የተጠሪ ስራ አመራር ቦርድ የአገልግሎት ዘመኑ አልቋል ተብሎ

እንዲወሰንልንና የጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ተደርጎ አዲስ የስራ አመራር ቦርድ እንዲመረጥ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኝበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡ ይሁንና ከዚህ ታልፎ በተያዘው ጉዳይ በተደረገው ክርክር እንደሌሎች አባላት የሚፈለጉባቸውን ክፍያ አለመፈፀማቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ በማህበሩ የሚቀጥሉበት ምክንያት የለም ተብሎ ተወስኗል፡፡ በዚህ መልኩ ታይቶ ተሰጠው ውሳኔ ደግሞ የሚነቀፍበት ምክንያት አይኖርም፡፡

በአጠቃላይ የአመልካች ያዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በመደረጉ የተፈፀመ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 266589 በቀን 05/11/2011 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 243224 በቀን 09/11/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 213492
ግንቦት 26 ቀን 2014ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ
ፀሐይ መንክር
ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የሶረታ መካነሔዋን መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- መሐመድ ሁሴን ቀርበዋል።

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 375788 ጥቅምት 2ቀን 2013ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲታረምላት አመልካች ቤተክርስቲያን በመጠየቋ ነው።

ክርክሩ በተጀመረው በነቀምቴ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ። አመልካች ጥር 4ቀን 2013 ዓ/ም በተፃፈ ክሷ በነቀምቴ ከተማ 25 ሄክታር ስፋት ያለው መሬትን ከ1972ዓ/ም ጀምሮ ይዛ እየተጠቀመች መሆኑን ተጠሪው በምስራቅ ስለሚዋሰንት በ2010ዓ/ም ከይዞታዋ ላይ 1600 ካሬ ሜትሩን በመውሰድ ስለያዘባት ክስ አቅርባ ክሣችሁን አላረጋጣችሁም ተብሎ መዝገቡ መዘጋቱ ለራሱ እንደተወሰነለት በማስመሰል እንደገና ህዳር 20 ቀን 2013ዓ/ም 500 ካሬ ሜትር ጨምሮ በጥቅሉ 2100 ካሬ ሜትር መሬት በመያዝ በመሬቱ ላይ የነበረውን 200 ባርዛፍ ቆርጦ የወሰደባት መሆኑን በመዘርዘር ያጠረውን አጥር አፍርሶ ይዞታውን እንዲለቅላት የንብረት ግምት እንድታቀርብ መብቷ እንዲጠበቅላት ጠይቃለች።

ተጠሪ አሻሽሎ ባቀረበው መልሱ በይዞታው ለ36ዓመት የተጠቀመበት በመሆኑ የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ መሆኑን፤ የአሁን አመልካች በ2010ዓ/ም ክስ አቅርበውበት ውሣኔ ባገኘ ጉዳይ በድጋሚ መክሰሱን በመዘርዘር የመጀመሪያ መቃወሚያና ከአባቱ ጀምሮ ለ56 ዓመታት ይዞ የሚጠቀምትን መሬትና ባሕር ዛፍ እንጅ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የአመልካችን ይዞታ ይዞ ባሕር ዛፍ አለመቁረጡን፣ የአመልካችም ይዞታ 25 ሄክታር ሣይሆን 9 ሄክታር ብቻ ነው ሲል ክሱ ወድቅ እንዲደረግለት ተከራክሯል።

የስር ነቀምቴ ወረዳ ፍርድ ቤት የተጠሪን መቃወሚያ ውድቅ አድርጎ ጭብጥ ይዞ በግራ ቀኙን ማስረጃና አስተዳደደሩን ጠይቆ እንዲሁም በአካባቢው ሰዎች ተጣርቶ እንዲቀርብለት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የቀረበለትን ማስረጃ መርምሮ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ከመረመረ በኋላ ተጠሪው እስከ 2013 ዓ/ም ድረስ በየጊዜው በያዘባት 2000 ካሬ ሜትር መሬት ላይ ያጠረውን አጥር በማንሣት እንዲለቅ የንብረት ግምትን በሚመለከት አመልካች ትጠይቅ ሲል ወስኗል።

በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘው ተጠሪ የይግባኝ አቤቱታውን ለምስራቅ ወለጋ ፍርድ ቤት አቅርቧል። ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የተጠሪን መቃወሚያ የመታለፉን አግባብነት በጭብጥነት ይዞ ከመረመረ በኋላ በ2010ዓ/ም ተጠሪው ባህር ዛፍ በመቁረጥ 1600 ካሬ ሜትር ያዘብኝ የሚል ክስ አመልካች አቅርባ ባለመረጋገጡ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 33(3) በሚደነግገው መሰረት ውድቅ ቢደረግም እንደገና ቀደም ሲል ባቀረበችው ክስ የጠቀሰችውን አዋሣኝ በመጥቀስ ስፋቱን በመጨመር 500 ካሬ ሜትር ይዞብኛል ስትል ክስ ማቅረቧ በድጋሚ የቀረበ አይደለም ተብሎ መታለፉ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 5 ድንጋጌን የጣሰ ነው ሲል የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሯል። በውሣኔው ቅር የተሰኘችው አመልካች የይግባኝና የሰበር አቤቱታዋን በየደረጃው ለሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብታቀርብም ስለተሰዘረባት ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርባለች።

አመልካች ነሐሴ 18ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታዋ ቀደም ሲል የነበረው ክርክር የተዘጋው ይዞታውን ለማስለካት ፈቃድ በመታጣቱ ምክንያት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 199 ትዕዛዙን በማንሣት አመልካች ክሷን አላረጋገጠችም ተብሎ እንጅ የመጨረሻ ውሣኔ ባልተሰጠበት ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው መባሉ፤ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪው የአመልካችን መሬት በየጊዜው እየገፋ መያዙ ባረጋገጠበት የይዞታው አቅጣጫ አንድ በመሆኑ ብቻ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው ሲል መወሰኑ፤ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ቀደም ሲል ያልተሰጠውን ውሳኔ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 33(2) በሚደነግገው መሰረት በይዞታው ላይ መብት እንደሌላት ተረጋግጦ የመጨረሻ ውሣኔ እንደተሰጠበት መገንዘቡ፤ የስር ፍርድ ቤቱ መቃወሚያውን ማለፉ ተገቢ አይደለም ሲል ተጠሪው በመዝገብ ቁጥር 56561 ያቀረበው ይግባኝ ውድቅ የካቲት 17ቀን 2013ዓ/ም ውድቅ ከተደረገ በኋላ በድጋሚ ይግባኙን ተቀብሎ አሰተናግዶ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምላት ጠይቃለች።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአሁን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ በ2010ዓ/ም ተጠሪ ይዞታዬን ድንበር አልፎ ይዞብኛል በሚል እንዲለቅ ይወሰንልኝ በሚል ያቀረበችው ክስ ውድቅ የተደረገ ቢሆንም እንደገና ሕዳር 20ቀን 2013ዓ/ም 500 ካሬ ሜትር ጨምሮ ይዞብኛል ስትል ያቀረበችው ክስ አስቀድሞ ታይቷል በማለት ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ መሻሩና በበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘበትን አግባብነት እንደመረምር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

ተጠሪ መጋቢት 17ቀን 2014ዓ/ም በተፃፈ መልሱ በጥቅሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በአግባቡ መርምሮ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው ሲል የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በመሻሩ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ሲል ተከራክሯል። አመልካችም የሰበር አቤቱታዋን የሚደጠናክር የመልስ መልስ አቅርባ የግራ ቀኙ ክርክር

ተጠናቋል።

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥና በዚህ ችሎት የቀረበውን ክርክር ነበር። አጣሪ ችሎቱ የያዘውን ማስቀረቢያ ነጥብ መነሻ በማድረግ ይግባኝ ሰሚ የሆነው የምስራቅ ወለጋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካች ክስ በድጋሚ የቀረበ ነው ሲል የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ የመሻሩን ተገቢነት ለጉዳዩ አግባብት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል።

እንደመረመርነው የአመልካች ክርክር በነቀምቴ ከተማ 25 ሄክታር ስፋት ካለው መሬት ላይ ተጠሪው ከይዞታዋ ላይ 1600 ካሬ ሜትሩን 2010ዓ/ም በመውሰዱ ክስ አቅርባበት ክሱ አልተረጋገጠም ተብሎ መዝገቡ መዘጋቱን አጋጣሚ ለራሱ እንደተወሰነለት በማስመሰል እንደገና ህዳር 20 ቀን 2013 ዓ/ም 500 ካሬ ሜትር ጨምሮ በጥቅሉ 2100 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው መሬት ላይ የነበረውን 200 ባርዛፍ ቆርጦ ስለወሰደባት አጥሩን አፍርሶ ይዞታውን እንዲለቅላት የንብረት ግምት እንድታቀርብ መብቷ እንዲጠበቅላት ጠይቃለች። ይህ የአመልካች የክስ አቀራረብ ቀደም ሲል አመልካችና ተጠሪ በ1600ካሬ ሜትር መሬት ሲከራከሩ እንደነበርና አመልካች ክሷን አላረጋገጠችም ተብሎ ውድቅ ከተደረገባት በኋላ እንደገና 500 ካሬ ሜትር በተጠሪ ተወስዶብኛል በሚል ሁሉንም ለማስለቅ የቀረበ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው።

ተጠሪ አሻሽሎ ባቀረበው መልሱ ይዞታውን ለ36ዓመታት እየተጠቀመበት በመሆኑ የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆን መሆኑን እንዲሁም አመልካች በ2010ዓ/ም ክስ አቅርባበት ውሣኔ ባገኘ ጉዳይ ድጋሚ መክሰሱን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ እንዲደረግለት መቃወሚያ አቅርቧል። የስር ፍርድ የአመልካችን መቃወሚያ ክርክር ውድቅ በማደረግ የፍሬ ነገር ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን ካጣራ በኋላ ተጠሪው ከ2010ዓ/ም ጀምሮ የአመልካችን ይዞታ መያዙ ተረጋጧል ሲል 2000 ካሬሜትር እንዲለቅ ወስኗል። ይህ ውሳኔም 1600 ካሬ ሜትሩን የሚጨምር መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ከፍተኛው ፍርድ ቤት በበኩሉ አመልካች በቀድሞው ክሷ ላይ መጠን በመጨመርና ቀኑን በማለያየት አዲስ ክስ አቀረበች እንጅ ለክሱ ምክንያት የሆነው ይዞታ አዋሣኝ አንድ ዓይነት መሆኑን ጠቅሶ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው ተብሎ ውድቅ መደረግ ሲገባው መታለፉ ተገቢነት የለውም ሲል በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 5 መሰረት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሯል።

እንደሚታወቀው በሕግ ስልጣን በተሰጠው ማናቸውም ፍርድ ቤት ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ቀድሞ በተወሰነው ክርክር ስረ ነገርና ከተያዘው ጭብጥ ጋር አንድ አይነት በሆነ ጉዳይ ሁለተኛ ክስ ማቅረብ እንደማይቻል የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ ቁጥር 5(1) ይደነግጋል። የዚህ ድንጋጌ ዋና ዋና ዓላማዎች መካከል ማቆሚያ በሌለው ክስ የሰዎች ኑሮ እንዳይናጋ ለመከላከል፣ ፍርድ ቤቶችም ውሣኔ የሰጡበት ጉዳይ እንዲገና ቀርቦላቸው የሚደርስባቸውን ጫና ለማስቀረት እና ክርክሮችም መቋጫ እንዲኖራቸው የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው። በመሆኑም ፍርድ ቤቶች ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው የሚል መቃወሚያ ሲቀርብ ጉዳዩን ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 5 አንፃር በጥንቃቄ መመርምር ይጠበቅባቸዋል።

በየዝነው ጉዳይ የአሁን አመልካች ተጠሪው 1600 ካሬ ሜትር መሬት ወሰደብኝ ስትል ክስ አቅርባ ክሱን አላስረዳችም መቧላ፤እንደገና አሁን ለያዝነው ጉዳይ መነሻ በሆነው ክስ ደግሞ ቀደም ሲል ክስ ያቀረበች የነበረውን 1600 ካሬ ሜትርና በአዲስ መልክ ወስዶብኛል የምትለውን 500 ካሬ ሜትር ጨምራ በድምሩ 2100 ካሬ ሜትር መሬት ለማስመለስ ክስ ማቅረቧን የጉዳዩ አመጣጥ ያስገነዝባል። በመሆኑም 1600 ካሬ ሜትር በድጋሚ ክስ የቀረበበት ሲሆን 500 ካሬ ሜትር መሬት ግን ቀድሞ ያቀረበችውን ክስ አላረጋገጠችም የሚል ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ተወሰደ የምትለው መሆኑን ተገንዝበናል።

በመሆኑም ወረዳ ፍርድ ቤቱ የአመልካች የክስ ምክንያት የሆነው 2100 ካሬ ሜትር በሙሉ ቀደም ሲል በነበረው ክርክር የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት አይደለም ሲል የተጠሪን መቃወሚያ ውድቅ ማድረጉም ሆነ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ በአመልካች የተጠቀሰው 2100 ካሬ ሜትር በሙሉ ቀድሞ በነበረው ክርክር የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት ነው በሚል የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ መሻሩ ሊታረም የሚገባው ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ውሣኔ

1) የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 375788 ሰኔ 2ቀን 2013ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 348452 ሚያዚ 20ቀን 2013ዓ/ም የተሰጡት ትዕዛዞች እና እንዲሁም የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 56817 ሚያዚያ 12ቀን 2013ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሸረዋል። የነቀምቴ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09038 መጋቢት 13ቀን 2013 ዓ/ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል።
2) አመልካች በ1600 ካሬ ሜትር መሬት ተጠሪው ይዞብኛል በሚል እንዲለቅላት ያቀረበችው ክስ ቀደም ሲል ክርክር ተደርጎበት ክሷን ባለማረጋገጧ ውድቅ በተደረገ ጉዳይ ላይ ያቀረበች በመሆኑ ከ1600 ካሬ ሜትር አንፃር የጠየቀችው ዳኝነት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 5 መሰረት በድጋሚ የቀረበ ነው ብለናል።
3) ተጠሪው ህዳር 20 ቀን 2013ዓ/ም የአመልካችን 500 ካሬ ሜትር ይዞ 200 ባሕር ዛፍ ቆርጦ መውሰዱን በመዘርዘር መሬቱን እንዲለቅ የንብረት ግምት የማቅረብ መብቷ እንዲጠበቅላት ያቀረበችውን ክስ በሚመለከለት የሰር ወረዳ ፍርድ ቤቱ አጣርቶ ውሣኔ የሰጠበት በመሆኑ ይግባኝ ሰሚ የሆነው የከተፍኛው ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 56817 እንደገና አንቀሣቀሶ የሰር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ረገድ የሰጠውን ውሣኔ መርምሮ ተገቢውን የክርክር ጭብጥ ይዞ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰንለታል።
4) ይህ ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የዬራሣቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

አ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ 213479
ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1ኛ. አቶ ነብየልዑል ካሳሁን እምሩ

2ኛ. ወ/ሮ አበሻ ካሳሁን እምሩ

3ኛ. አቶ ልዑልሰገድ ካሳሁን እምሩ

4ኛ. ወ/ሪት ቤተልሔም ካሳሁን እምሩ

} አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ፈቃደ ገ/ህይወት፡- አልቀረቡም

2ኛ. አቶ አንዷለም ደሳለኝ፡- ጠበቃ ግርማ አያሌው ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው። በመሆኑም ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የአፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ነው። አመልካች ነሐሴ 25 ቀን 2013 ዓ.ም ጸፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 26425 ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጉዳዩ አፈጻጸምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተመጀመው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች የፍርድ ባለመብቶች፣ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለዕዳ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ የመቃወም አመልካች ነበሩ፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካቾች ሐምሌ 15 ቀን 2010 ዓ.ም በተጻፈ የአፈጻጸም ክስ አቤቱታ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ልዩ ቦታውን በመጥቀስ የካርታ ቁጥር 441 እና 442 ቤቶች ከአያታቸው ከወ/ሮ ትርሲት ቀፀላ በውርስ ያገኟቸው ቤቶች ስለመሆናቸው ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተከራክረው በመ/ቁ 181985 ያስወሰኑ መሆኑን በመጥቀስ በውሳኔው መሰረት እንዲፈጸምላቸው የአፈጻጸም ክስ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ ክፍፍሉ እንዲፈጸምላቸው ትዕዛዝ አስተላልፏል፡፡

ይህን ተከትሎ 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የመቃወም ማመልከቻ ውሳኔ ያረፈበትን ቤት ጥር 28 ቀን 2011 በተደረገ የሽያጭ ውል ከአቶ ሙሉ አብርሃ ላይ የገዙት መሆኑን፣ በወቅቱም በሻጩ ስም የተመዘገበ ካርታ መኖሩንና ከእዳና እገዳ ነጻ መሆኑን ከሚመለከተው አካል ያረጋገጡ መሆኑን፣ ከሽያጩ በኋላም ተገቢውን የሊዝ ክፍያ ከፍለው የሊዝ ውል የፈጸሙ መሆኑን፣ ስመ-ሀብቱም በስማቸው የዞረና ይህ የአፈጻጸም ትዕዛዝ መውጣቱን ያወቁት ካርታ እንዲሰራላቸው በሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ባቀረቡበት ወቅት መሆኑን ገልጸው አመልካቾች አለን የሚሉትን መብት ከ1ኛ ተጠሪ ከሚጠይቁ በስተቀር ቤቱን በሀራጅ ሊያሸጡ የሚያስችላቸው መብት ስለሌላቸው በቤቱ ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ቀሪ እንዲደረግላቸው አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የመቃወም ማመልከቻው ለግራቀኙ እንዲደረስ ተደርጎ 1ኛ ተጠሪ ተጠርተው ስላልቀረቡ አስተያየት የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

አመልካቾች ደግሞ ጥቅምት 13 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አስተያየት 2ኛ ተጠሪ ገዝቻለሁ እያሉ ያሉት ክስ የቀረበበትን ግማሽ ይዞታውን 466 ካ.ሜ ነው፣ ይህ ቦታ 1ኛ ተጠሪ ራሳቸውን የወ/ሮ ትርሲት ቀጸላ ብቸኛ ወራሽ አድርገው ከወ/ሮ ትርሲት ቀጸላ ባለቤት ከሆኑት አቶ ካሳሁን እምሩ ወራሾች ጋር በሌላ መዝገብ በነበራቸው ክርክር ቦታው ለሁለት ተከፍሎ በተሰጠ ውሳኔ መነሻነት ያገኙት ነው፣ ነገርግን ይህ ቦታ የ1ኛ ተጠሪ ብቻ ሳይሆን አመልካቾችም የወ/ሮ ትርሲት ቀጸላ ወራሾች መሆናቸን ተረጋግጦ በቤቱ ላይ ድርሻ እንዳለን ተወስኖ በአፈጻጸም ላይ ይገኛል፣ 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡት የሽያጭ ውል እውነተኛ የሽያጭ ውል አይደለም፣ የካርታ አሰጣጡም በህጉ አግባብ የተሰጠ አይደለም፣ ሻጭ የተባሉት አቶ ሙሉ አብርሃ የፍ/ቤቱን መጥሪያ ጥር 22 ቀን 2011 ዓ.ም ፊርመው የተቀበሉ በመሆኑ ቤቱ ክርክር እንደነበረበት ያውቁ ነበር፣ 2ኛ ተጠሪ ከአቶ ሙሉ አብርሃ ጋር የጋብቻ ዝምድና ስላላቸው እውነተኛ ሽያጭ ሳያደርጉ አፈጻጸሙን ለማሰናከል ብቻ የታሰበ ማመልከቻ መሆኑን፣ ይህ የሽያጭ ውል መጋቢት 03/2006 ዓ.ም ተደረገ በተባለበት ወቅት 1ኛ ተጠሪ በመ/ቁ 181985 ውሳኔ ላይ ይግባኝ አቅርበው እስከ 2007 ዓ.ም ይግባኙን ሲከታተሉ መቆየታቸው ሽያጩ የአመልካቾችን መብት ለመጣስ የተደረገ ህገ-ወጥ ውል መሆኑን ያሳያል፣ አቶ ሙሉ አብርሃ ቤቱ ክርክር እንዳለበትና እግድ እያለበት ሳያጣሩ የፈጸሙት ውል በመሆኑ ከቅን ልቦና ውጭ

የተፈጸመ ነው፣ የአስተዳር ክፍሉም ቢሆን ቤቱ እግድ እያለበት እያወቀ ቤቱን ወደ 2ኛ ተጠሪ ማዞሩ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ የአመልካቾች ምስክሮች ቤቱ የተሸጠው እግድ ከተሰጠ በኋላ መሆኑን፣ 2ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ የሀራጅ ሽያጭ ከወጣ በኋላ በፍ/ቤቱ የአስተዳደር ሰራተኞች በተገኙበት ቀርቦ ያዩት መሆኑንና 1ኛ ተጠሪን ወክሎ ይሁን አይሁን እንደማያውቁ አስረድተዋል። የ2ኛ ተጠሪ ምስክሮች ደግሞ ቤቱን ከ1ኛ ተጠሪ በመግዛት ለ2ኛ ተጠሪ የሸጡት አቶ ሙሉ አብርሃ መሆናቸውን፣ አቶ ሙሉ አብርሀ ቤቱን እዳና እገዳ እንደሌለበት አረጋግጠው በ2006 ዓ.ም የገዙት ስለመሆኑና በ2008 ዓ.ም የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጣቸው መሆኑን፣ ለ2ኛ ተጠሪ ሲሸጡም እግድና እዳ እንደሌለበት ተረጋግጦ የተሸጠ መሆኑን፣ ቤቱን 2ኛ ተጠሪ ከመግዛቱ በፊት ፍ/ቤት ቀርቦ የማያውቅ መሆኑን አስረድተዋል። ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ማስረጃ መርምሮ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን የገዙት አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ አሟልተው እና መሟላቱንም አረጋግጠው እንዲሁም በተገቢው አካል ፊት ቀርበው ስለመሆኑ የሚያስረዱ ሲሆን ይህም አንድ መልካም ገዥ ሊያጣራቸው የሚገቡና መሟላታቸው ሊረጋገጡ የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት ግዥውን መፈጸማቸው የተረጋገጠ መሆኑን፣ አመልካቾች 2ኛ ተጠሪ ያውቁ ነበር የሚሉት ሽያጭ ውሉ ከተፈጸመ በኋላ በመሆኑ አስቀድመው ክርክሩን ያውቃሉ የሚያስብል አለመሆኑን በመግለጽ 2ኛ ተጠሪ እግዱን በመጣስ የገዛ ቢሆንም የእግድ ትዕዛዝ በተሰጣቸው አካላት የወንጀልም ሆነ የፍትሐብሔር ኃላፊነት ከሚያስከትል በቀር ምንም ግንኙነት በሌለው 3ኛ ወገን መብት የሚነካ ስላለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ህቁ 155 ድንጋጌ መረዳት ይቻለል በሚል እንደፍረዱ ሊፈጸም አይችልም በማለት የፍርድ አፈጻጸሙን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል። ይህ ውሳኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ፀንቷል።

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው። አመልካቾች ነሐሴ 25 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል። ፍሬ ቃሉም በተጠሪዎች መሃል ቀዳሚ ገዥ የተባሉት አቶ ሙሉ አብርሃ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር እና ከክፍለ ከተማው በቤቱ መዝገብ ውስጥ ገቢ የተደረጉትን የፅግድ ትዕዛዞች በማስወገድ ስመ-ሀባቱን ከአውራሽ ወደ 1ኛ ተጠሪ ሳይዛወር አየር ባየር በመንደር ውል የተፈጸመ ነው፣ ቤቱም ሰነድ አልባ መሆኑ በክፍለ ከተማው በተረጋገጠብት ሁኔታ ለመጀመሪያው ገዥ ለአቶ ሙሉ አብርሃ በህገ-ወጥ መንገድ ግዥ ፈጽመው ሕጋዊ በማስመሰል ለ2ኛ ተጠሪ የተሸጠበት አግባብ 2ኛ ተጠሪ ከቅን ልቦና ውጭ ገዛሁት ያሉትን ቤት የሥር ፍ/ቤቶች ህጋዊ በማድረግ የሰጡት ትዕዛዝ ህገ-መንግስታዊ የመውረስ መብታቸውን የሚጋፋ ነው፣ ቤቱ ዋናው ፍርድ ያረፈበት እንጂ ለፍርድ ማስፈጸሚያ ተብሎ የተያዘ ባለመሆኑ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት የመቃወም አቤቱታ ሊያቀርቡ አይችሉም፤ ስለሆነም እነኚህ ሁኔታዎች ታልፈው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾች ተጠሪ አከራካሪው ቤት በክርክር ላይ መሆኑን የሚያውቅ መሆኑን በተለያየ ማስረጃ አስረድተው ባለበት ሁኔታ ተጠሪ ግዥር የፈጸሙት በቅን ልቦና ነው በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ ተይዞ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸውን ችሎቱ ታልፏል፡፡

2ኛ ተጠሪ በቀን የካቲት 24/2014 ዓ.ም በጻፈው መልስ ቤቱን የገዙት ከ3ኛ ወገን ላይ በሚመለከተው አካል ቤቱ እግድና እዳ የሌለበትና አስፈላጊውን ትጋት በማድረግ በውል አዋዋይ ፊት በመንግስት አካል የጀርባ ማህተም ተደርጎበት ግዥን የፈጸሙ መሆኑን፣ ግዥውን ከፈጸሙ በኋላ የአስተዳደር ሰራተኞች ከፈለጉ ፍ/ቤት ቀርበው ጉዳዩን ማየት ይችላሉ ስለተባሉ ቀርበው የነበር መሆኑን፣ አመልካቾች እግዱን ጥሶ በውረስ ሀብታቸው እንዳይጠቀሙ ያደረጋቸውን አካል መክሰስ እንደሚችሉ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠ መሆኑን በመግለጽ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀናላቸው ተከራክወረዋል፡፡

አመልካች በበኩላቸው ከተጠሪ ለቀረበላቸው መልስ መጋቢት 13/2014 ዓ.ም በጻፉት የመልስ መልስ 2ኛ ተጠሪ ከአቶ ሙሉ አብርሃ ጋር ውልና ማስረጃ ሄደው የፈጸሙት ውል ጥር 28 ቀን 2011 ዓ.ም ሲሆን የፍ/ቤቱ መጥሪያ ከጥር 22 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የደረሳቸው በመሆኑ ቤቱ የአመልካቾች የውርስ ንብረት ስለመሆኑ እያወቁ የገዙት ነው፣ የሊዝ ውል የፈጸሙት ደግሞ መጋቢት 4 ቀን 2011 ዓ.ም ስለመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ባቀረበው የሊዝ ውል ማረጋገጥ ይቻላል፤ ርስበርስ በጥቅም በመተሳሰር በፍ/ቤት የወጡ እግዶችን ከመዝገቡ በማስወጣት በመንደር ውል በ1ኛ ተጠሪ ስም ያልነበረን ቤት ወደ አቶ ሙሉ ገ/ህይወት እንደተዘዋወረ ተደርጎ አቶ ሙሉ አብርሃን ከተጠያቂነት ለማዳን ተብሎ የተሰራ የሀሰት ሰነድ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ከሰበር ቅሬታው አኳያ እና ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ይዘት አንፃር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል፡፡

በመሠረቱ አንድ ሰዉ የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን የተሠጠዉ ዉሳኔ መብቴን ነክቷል የሚል ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ በማቅረብ የሚተናገድበት ሥርዓት ያለ መሆኑን፤ በሌላ በኩል በፍርድ አፈጻጸም ክርክር ላይ ለፍርድ ማስፈጸሚያ የተያዘ ወይም የተከበረ ንብረት የፍርድ ባለእዳ ሳይሆን የእኔ ነዉ ባይ ሶስተኛ ወገን ንብረቱ ለፍርድ ማስፈጸሚያ ሊዉል አይገባም የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የሚስተናገድ ሥርዓት አለ፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት፣ ዓላማና አተገባበር አድማስ አስመልክቶ የፈዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 29653፣ 53067፣55842፤ 141600 የክርክሩ ተካፋይ ያልነበረ ሶስተኛ ወገን በዋናዉ

ክርክር ላይ የተሰጠዉ ፍርድ መብቱን የሚነካ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ፍርዱን በመቃወም ሊቀርብ የሚገባዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መሆን እንዳለበት እና በሌላ በኩል ፍርድ ያላረፈበት ንብረት በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት በፍርድ ባለመብት ጥያቄ መሠረት እንዲከበር ወይም እንዲያዝ ሲደረግ ንብረቱ ላይ ሊፈጸም አይገባም የሚል ሶስተኛ ወገን መቃወሚያዉን ማቅረብ ያለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት እንደሆነ፤ የሁለቱም ድንጋጌዎች መሠረታዊ ልዩነቱም የፍ/ብ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ 358 ተቃዋሚ ወገን የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን ጥቅሙን የሚነካ ፍርድ የተሰጠ እንደሆነ ፍርዱ እንዲሰረዝ አቤቱታ የሚያቀርብበት ስርዓት የሚመለከት መሆኑን፤ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 ደግሞ ለፍርድ ማስፈጸሚያ በሚል በአፈጻጸም ክርክር የተያዘ ንብረት ለማስለቀቅ የመቃወም አቤቱታ የሚቀርብበት መሆኑን፤ በዚሁ ድንጋጌ መሰረት በአፈጻጸም ክርክር ላይ በሚቀርብ መቃወሚያ ዋናዉ ፍርድ ሊሻር እንደማይችል በመግለጽ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው በሐራጅ እንዲሸጥ የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተላለፈበት ቤት አመልካቾች ከአያታቸው ከወ/ሮ ትርሲት ቀፀላ በውርስ ያገኙት ቤት መሆኑ ተረጋግጦ ፍርድ ያረፈበት ሲሆን ይህንኑ ፍርድ ለማስፈጸም በተከፈተ የአፈጻጸም መዝገብ ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ ክፍፍሉ እንዲፈጸም የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተላልፏል፡፡ ይህም 2ኛ ተጠሪ የኔ ነው በሚሉት ቤት ላይ ዋናው ፍርድ መሰጠቱን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ቤቱን አስመልክቶ የአመልካቾች የውርስ ሐብት ነው ተብሎ የተሰጠዉ ፍርድ ሳይሻር በአፈጻጸም መዝገብ ላይ ቤቱ ላይ አፈጻጸም ሊቀጥል አይገባም በሚል የሚቀርበው አቤቱታ ከመነሻውም ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም፡፡ ስለሆነም 2ኛ ተጠሪ በአከራካሪዉ ቤት ላይ ከተጠሪዎች የተሻለ መብት አለኝ የሚሉ ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት ዋናው ፍርድ እንዲሰረዝ መጠየቅ ይገባቸዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶችም ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት 2ኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው አቤቱታውን ተቀብለው በቤቱ ላይ የተጀመረው አፈጻጸም እንዲቆም የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የሥነሥርዓት ሕጉን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 257876 ሕዳር 17 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 261425 ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት 2ኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙን የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

4. ይህ ውሳኔ 2ኛ ተጠሪ ዋናውን ፍርድ በመቃወም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት የሚያቀርቡትን አቤቱታ አያግድም ብለናል።

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበርመ.ቁ.-213330

ቀን፡- ታህሳስ 13/2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሽምሱ ሲርጋጋ

አለማየሁ ሹናራ

ደረጀ አያና

አመልካች/ቾች/ ፡- እነ ወ/ሮ ማርታ በቀለ /2 ሰዎች/ ጠበቆች በሻዳ ገመቹ - አብርሃ አሸ / ቀረቡ

ተጠሪ/ዎች/፡- እነ አቶ ሚልኪያስ መንገሻ /2 ሰዎች/

መዝገቡ ተከፍቶ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካች /ቾች/ ነሐሴ 21 ቀን /2013 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ በ ፌደራል ጠቅላይ /ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.199317 በ ግንቦት 25 ቀን 2013 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በመግለፅ በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው በሚል የቀረበ ነው፡፡ በመሆኑም መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ት እ ዛ ዝ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡትን የወራሽነት ማስረጃ ውጫዊ ዜጋ ስለሆኑ በአ/ቁ 922/2008 አንቀፅ 6/1/ መሰረት ስልጣን ባለው የኢትዮጲያ ቆንስላ ፅ/ቤት ተረጋግጦ ያልቀረበ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ተጠሪዎች ወራሽ ስለመሆናቸውን አመልካቾች አልካዱም በማለት ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም አላቸው ሲል የወሰነበት አግባብነት ከአ/ቁ 922/2008 አንቀፅ 6/1/ እና ከፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር መ/ቁ 32282 አንፃር መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩስ ሰበር ሰሚ ችሎት ይቅረብ ብለናል፡፡
2. የትዕዛዝ ግልባጭ ከመጥሪያ ጋር ለተጠሪዎች ደርሷቸው መልስ እና የመልስ መልስ በሬጅስትራር ፅ/ቤት በኩል ይቀባበሉ

መልስ ስመቀበል ስ 05/05/2014 ተቀጠረ። 9:00

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ.መ.ቁ 213041

ቀን ሚያዝያ 26 2014ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡ ወ/ሮ ወይንሸት ወርቁ ጅማ --ወኪል ወርቅነህ ነገሎ ቀረቡ

ተጠሪ፡ አቶ ፈይሳ ኃይሌ ሮቢ --ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 31939 በ9/7/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ፤ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 32664 በ20/8/13ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 375407 በ25/9/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ17/12/13ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች በስር የሲናና ወረዳ ፍ/ቤት 2ኛ ከሳሽ ሆነው፤ አሁን ሰበር ክርክሩ ላይ የሌሉት ፈቃዱ ስሜ(የስር 1ኛ ከሳሽ)፤ ብርሃኑ ኃይሌ(ስር 3ኛ ከሳሽ) ሆነው በተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) እና አሁን ሰበር ክርክሩ ላይ በሌሉት ወ/ሮ ደሚቱ ሮቢ(ስር 1ኛ ተከሳሽ) ላይ ባቀረቡት ክስ ለስር 1ኛ ተከሳሽ አያታችን ወ/ሮ ኡርጎ ጂማ አክስቷ ሲሆኑ፤ ተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) ደግሞ የአያታችን የልጅ ልጅ ሲሆን አያታችን ወ/ሮ ኡርጎ ጂማ በ24/1/10ዓ.ም ሞታለች፡፡ ሟች አያታችን ያላት ልጆች 4 ይኸውም የስር 1ኛ ተከሳሽ አባት፤ ኃይሌ ሮቢ፤ የስር 1ኛ ከሳሽ አባት ስሜ መርጋ፤ የአመልካች(ስር 2ኛ ከሳሽ) እናት ሙሉ ሮቢ እና የስር 3ኛ ከሳሽ እናት ዘውዲቱ ሮቢ ናቸው፡፡ የአያታችን ልጆች አራቱም በህይወት ስለሌሉ የአያታችን ወራሾች መሆናችን ተረጋግጦ አከራካሪውን በተጠሪ(ስር 2ኛተከሳሽ) እጅ የሚገኝ በሮቤ ከተማ በአዳ ሮቤ ቀበሌ የሚገኝ የመኖሪያ ቤት እንዲሁም በክሱ ከተራ

ቁጥር 2ኛ-6ኛ ስፋቱና አዋሳኙ የተገለጸው የእርሻ መሬት እንዲሁም በተጠሪ እና በስር 1ኛ ተከሳሽ እጅ የሚገኝ ኦንሾ በሚባል አካባቢ የሚገኝ ስፋቱ 16 ጥማድ የሚሆን እና አንድ ሺህ እግር ባህርዛፍ የሚገኝበትን በማለት እንዲሁም ሌሎች የእርሻ መሬት እና መኖሪያ ቤት በመዘርዘር አያታችን ከተከሳሾች ጋር ስትጠቀምበት ቆይታ ለወራሾቹ የሚገባውን እና ስር ከሳሾች በቤተሰባችን ምትክ አያታችንን መውረስ እንድንችል እንዲረጋገጥልን እና ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ሀብትና ይዞታ ከመሰረቱ የአያታችን መሆኑ እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ስር 1ኛ ተከሳሽ ባቀረቡት መልስ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪም ባቀረቡት መቃወሚያ በክሱ ተ.ቁ B የተገለጸው ይዞታ ላይ ሟች የከሳሾች አያት ወ/ሮ ኡርጎ ጂማ በህይወት እያለች ምንም መብት አልነበራትም፡፡ ሟች በህይወት እያለች ይዞታውን ተጠሪ ለ20 አመት በግሌ ይገፎ በእጄ ያለ ነው፡፡ ሟች መብት ያላት ቢሆንም እንኳ በህይወት ካለችበት ግዜ አንስቶ ይዞታው ከ15 አመት በላይ በእጄ ስለቆየ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፡፡ ስለሆነም ከሳሾች ሟች የሌላትን መብት ሊያነሱ አይችሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በፍሬጉዳዩ ላይ ባቀረቡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ መሰረቱ የአባቴ ሲሆን ሟች በህይወት እያለች ተላልፎልኝ ለሀያ አመት በእጄ አስገብቼ በስሜ ተመዝግቦ የባለቤትነት መታወቂያ ወረቀት ያለኝ በመሆኑ፤ የመንግስትም ግብር እየከፈልኩበት በመሆኑ ሟች በዚህ ይዞታ ላይ መብት ስለሌላት ከሳሾችም ሟች የሌላትን መብት ለመውረስ መብት ስለሌላቸው ይህ ይዞታ የተጠሪ የግል ነው ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በሮቤ ከተማ የሚገኘው መኖሪያ ቤት መሰረቱ የኡርጎ ጂማ መሆኑ እውነት ነው፤ ሆኖም ቤቱን ሟች በህይወት እያለች በ13/4/04ዓ.ም በተደረገ የሽያጭና ግዢ ውል ሸጣልኝ ማስረጃ ተሰጥቶኝ በእጄ ያለ እና አሮጌውን ቤት አፍርሼ ዘመናዊ በሆነ መልኩ በራሴ ወጪ ያለማንም ተቃውሞ በላዩ ላይ የሰራሁበትና ከ2004ዓ.ም ጀምሮ በእጄ ያለ በመሆኑ ይህ የመኖሪያ ቤት አመልካችን ጨምሮ ለስር ከሳሾች በውርስ የሚተላለፍ ንብረት አይደለም ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አሁን የሰበር ክርክሩ ላይ የሌሉ የስር ጣልቃገብም የራሳቸውን ክርክር አቅርበዋል፡፡

ፍርድቤቱም ግራቀኙን በቃል ካከራከረ፤ ለጉዳዩ ተገቢ ናቸው ያላቸውን ሰነዶች ከያዘ እና የስር ከሳሾችን፤ ተከሳሾችን እና ጣልቃገብ ምስክሮችን ከሰማ በኋላ በተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ፍሬጉዳዩን በተመለከተ ጉዳዩን መርምሮ የተሰሙት ምስክሮች ቃል ሲመዘን ተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) ያቀረባቸው ምስክሮች በክርክሩ ውስጥ የተገለጹት ይዞታዎች የተጠሪ መሆናቸውን እና አመልካችን ጨምሮ የስር ከሳሾች አያት በዚህ ይዞታ ላይ መብት የሌላት መሆኑን፤ ይዞታው ለአስራ አምስት አመት በተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) እጅ መቆየቱን አላረጋገጡም፡፡ አመልካችን ጨምሮ ስር ከሳሾች እና የጣልቃገብ ምስክሮች ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ ከመሰረቱ የስር ከሳሾች አያት የወ/ሮ ኡርጎ ጂማ ይዞታ መሆኑን እና እሳቸው ከሞቱ በሃላ ይዞታው ተጠሪን ጨምሮ በስር ተከሳሾች እጅ መግባቱን የመሰከሩ በመሆኑ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የሟች የወ/ሮ ኡርጎ ጂማ ይዞታ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በሮቤ ከተማ የሚገኘው መኖሪያ ቤትን በተመለከተ ተጠሪ በ13/4/04ዓ.ም በተደረገ የግዢና ሽያጭ ውል ያገኘ ስለመሆኑ ላቀረበው ክርክር በ13/4/04ዓ.ም በተጻፈ የሽያጭና ግዢ ውል መግዛቱን የሚገልጽ የጽሁፍ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) በ13/4/04ዓ.ም በተጻፈ የግዢና ሽያጭ ውል ቀደም ብሎ በ27/3/04ዓ.ም የስም መቀየሪያ ብሎ ክፍያ መፈጸሙን የሚገልጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የግዢና ሽያጭ ውሉ ሳይፈጸም በቅድሚያ የስም ቅያሪ ክፍያ የሚፈጸምበት አግባብ የለም፡፡ በሌላ በኩል ወ/ሮ ኡርጎ ጂማ በ9/2/04ዓ.ም በፈጸሙት የውክልና ውል ይህን ንብረት እንዲሸጥ፤ ስም

እንዲቀይር፤ ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ እንዲችል ሃይሌ ሮቢ ለሚባል ሰው ውክልና የሰጠች መሆኑን የቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ ያስረዳል፡፡ ሆኖም ይህን የመኖሪያ ቤት ሌላ አካል እያስተዳደረው ባለበት ቦታ ሚጅ ለዚህ አካል የሰጠችውን ውክልና ሳታነሳ ንብረቱን የምትቆጣጠርበት መንገድ የለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ሚች ኡርጎ ጂማ ከተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) ጋር ያደረገችው የመኖሪያ ቤቱ የሽያጭና ግዢ ውል ተቀባይነት ያለው ስላልሆነ ተጠሪ የመኖሪያ ቤቱን በሽያጭና ግዢ ውል አፍርቼዋለሁ በማለት ያቀረበው ክርክር ውድቅ ሆኗል፡፡ ስለሆነም በክሱ ውስጥ የተገለጸው የእርሻ መሬት ይዞታ የሚች ኡርጎ ጂማ ይዞታ መሆኑን እና ለክርክሩ መነሻ በሆነው መኖሪያ ቤት የተደረገው የሽያጭና ግዢ ውል ውድቅ ተደርጎ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ እና በክሱ ውስጥ የተጠቀሰው የመኖሪያ ቤት የአመልካች እና ሌሎች ስር ተከሳሾች አያት ሀብትና ንብረት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት በውሳኔው ላይ በተገለጸው መልኩ ክፍፍል እንዲፈጸም ወስኗል፡፡

ተጠሪ ከላይ በተገለጸው በተጠሪ እጅ ይገኛል በተባለው የእርሻ መሬት ይዞታን በተመለከተ እንዲሁም በሮቤ ከተማ በአዳ ሮቤ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት በተመለከተ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም የስር ከሳሾችን እና ስር ጣልቃገብን መልስ ከተቀበለ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) እጅ ይገኛል የተባለው በክሱ ውስጥ አዋሳኙ እና ስፋቱ ተገልጾ የቀረበውን ይዞታ በተመለከተ ተጠሪ ሚች በህይወት እያለች በእጁ በማስገባት ሁለት ዙር በስሙ አስመዝግቦ በሱ ስም ተፈጽሞ ሲጠቀምበት የነበረ ስለመሆኑ ከሰው እና ከጽሁፍ ማስረጃ ላይ የምንገነዘበው በመሆኑ በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማሻሻል በተጠሪ እጅ ይገኛል የተባለው አዋሳኞቹ እና ስፋቱ በክሱ የተገለጸው የመሬት ይዞታ መሰረቱ የሚችድ ቢሆንም ሚች በህይወት እያለች ተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) ሲጠቀምበት የቆየ ስለሆነ የግል ይዞታው በመሆኑ ከውርስ ውስጥ እንዲወጣ በማለት ወስኗል፡፡

በሮቤ ከተማ የሚገኘው አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሱትን ስፋቱ 620ካ.ሜ የሆነ ባለ 150 ቆርቆሮ ቤት ያለበት ቦታ በ13/4/04ዓ.ም በሚች እና በተጠሪ መካከል በተደረገ የሽያጭ ውል ለተጠሪ ተላልፎ ስልጣን ባለው አካል ተረጋግጦ በተጠሪ ስም ተቀይሮ እሱም የባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ ወረቀት ተሰጥቶት ያለው መሆኑ ስለተረጋገጠ የተጠሪ የግል ንብረቱ ነው በማለት ወስኗል፡፡

የስር ከሳሾች እና ስር ጣልቃገብ ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ በዚሁ ላይ የስር ከሳሾች እና ስር ጣልቃገብ የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም በሰጠው ውሳኔ አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት አይቀርብም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

አመልካች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ከስር የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጀምሮ በየደረጃው ያሉት ፍ/ቤቶች በተጠሪ እጅ የሚገኘው የመሬት ይዞታ እና በሮቤ ከተማ የሚገኘው በክሱ የተጠቀሰው መኖሪያ ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ነው ሲሉ የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲሻር እና የስር የሲናና ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዲጸና፤ ወጪና ኪሳራም እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነው በተጠሪ እጅ የሚገኘው የእርሻ መሬት የአመልካች አውራሽ ወ/ሮ ኡርጎ ጂማ ይዞታ መሆኑ በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ በተመለከተበት ሁኔታ ለተጠሪ እንዲሆን የተወሰነበትን እና በሮቤ ከተማ አዳ ሮቤ ቀበሌ ውስጥ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሚገኘውን 620ካ.ሜ ይዞታ ለተጠሪ ተሸጧል የተጠሪ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ24/12/13ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ በ15/2/14ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ ከስር የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጀምሮ በየደረጃው ያሉት የበላይ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸና፣ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል።

አመልካች በ6/3/14ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች የሰጡት ትእዛዝ እና ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል።

የስር የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በህግ በተሰጠው ማስረጃዎችን የመመርመር እና የመመዘን ስልጣኑ በስር የሲናና ወረዳ ፍ/ቤት የተሰሙትን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ እና መዝኖ በተጠሪ እጅ ይገኛል ተብሎ በክሱ አዋሳኙ እና ስፋቱ የተገለጸው የእርሻ መሬት ይዞታ የተጠሪ የግል ይዞታ ነው ስለሆነም ከውርሱ እንዲወጣ በማለት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም በሮቤ ከተማ በአዳ ሮቤ ቀበሌ የሚገኘው አዋሳኞቹ በክሱ የተገለጹትን ስፋቱ 620ካ.ሜ የሆነ ባለ 150 ቆርቆሮ የመኖሪያ ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ፣ በዚሁ ውሳኔ ላይ የቀረበውን ይግባኝ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመሰረዝ የሰጠውን ትእዛዝ እንዲሁም በዚሁ ላይ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለሰበር ሰሚ ችሎት አይቀርብም በማለት የሰጠውን ውሳኔ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1) እና የኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) ከደነገጉት አንጻር የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘውም። ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

1. የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 31939 በ9/7/13ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 32664 በ20/8/13ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 375407 በ25/9/13ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል።

2. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።

3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ።

4. በዚህ መዝገብ በሰበር አጣሪ ችሎቱ በ24/12/13ዓ.ም ለክርክር ምክንያት የሆነው በሮቤ ከተማ አዳ ሮቤ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው 620ካ.ሜ የከተማ ይዞታ እና ንብረት እንዳይሸጥ ለሌላ 3ኛ ወገን በማናቸውም ሁኔታ እንዳይተላለፍ ታግዶ እንዲቆይ የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል። ለሮቤ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት እና ማኔጅመንት ኤጀንሲ ይጻፍ።

5. ውሳኔው በ2/9/14ዓ.ም ተነቧል።

6. መዝገቡ ተዘግቷል። ይመለስ።

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የመ/ቁ/212950
ህዳር 30/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ ሰለሞን አረዳ

እትመት አሰፋ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ ቶቼኖ ቶማ

ተጠሪ፡ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጠቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የውንብድና ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ የወንጀል ህግ አንቀፅ 670 ድንጋጌን ጠቅሶ በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት አመልካች የተጠቀሰውን የወንጀል ህግ ድንጋጌን በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ አልያም ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስቦ በክሱ ዝርዝር ውስጥ በተገለፀው ቀን፣ ቦታ እና ሰዓት የግል ተበዳይ ወደሆኑት ወ/ሮ አበበች ባደቦ የንግድ ቤት በመሄድ የተበዳይን ጉረሮ አንቆ በመያዝ አንገታቸው ላይ የነበረ የዋጋ ግምቱ ብር 50,000(ሃምሳ ሽህ) የሚያወጣ 20 ግራም የወርቅ ሀብል፣ እንዲሁም ባንኮኒ ውስጥ የነበረውን ብር 20,000(ሃያ ሺህ) ወስዶ በጓሮ በኩል ያመለጠ በመሆኑ የውንብድና ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነው፡፡

አመልካች ለዚሁ ክስ በሰጠው መልስ ድርጊቱን እና ጥፋተኝነቱን ክዶ በመከራከሩ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙ ከተደረገ በኋላ እንደክሱ አቀራረብ አስረድተዋል በሚል አመልካች ክሱን እንዲከላከል ታዟል፡፡ አመካችም አራት መከላከያ ምስክሮችን አሰምቷል፡፡ የመከላከያ ምስክሮቹም አመልካች እና የግል ተበዳይ ባል አና ሚስት የነበሩ መሆኑን፣ ክስ የቀረበበት ድርጊት ተፈፀመ ከተባለ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በጓላ በዚያው ጉዳይ ሁለቱን ለማሸማገል ሽምግልና ተቀምጠው የነበረ መሆኑን፤ በዚሁ ጊዜ የግል ተበዳይን ስለድርጊቱ ሲጠይቋቸው አመልካች ንብረት ዘርፎኛል በሚል የከሰሷቸው ዘወትር ሰክሮ እየሄደ ስለሚረብሻቸው እንጂ የተወሰደባቸው ንብረት እንደሌላ የነገሯቸው መሆኑን ተናግረዋል። ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤትም ለጉዳዩ አወሳሳን ይረዳኛል በማለት የሸማግሌዎቹ ሰብሳቢ የነበሩትን ፓስተር ታደሰ ታንቱ የተባሉትን ግለሰብ አስቀርቦ ሰምቷል። ተጨማሪ ምስክሩም አመልካች እና የግል ተበዳይ ባልና ሚስት መሆኑቻውን፤ ክስ የቀረበበት ጉዳይ ተፈፀመ ከተባለ በጓላ የሁለቱን ጉዳይ በሽምግልና የተመለከቱ መሆኑን፤ በሽምግልናው ላይም የግል ተበዳይ በእርግጥም ዝርፊያ ተፈፅሞባቸው እንደሆን በሚል የጠየቋቸው መሆኑን፤ ተበዳይም አመልካች ዘወትር ሰክሮ ንግድ ቦታቸው እየሄደ ስለሚረብሻቸው ለመከላከል በሚል የከሰሷቸው እንጂ የተፈፀመባቸው ውንብድና እንደሌለ የነገሯቸው መሆኑን ገልፀዋል።

ከዚህ በጓላ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙ ክርክር መርምሮ እና የቀረቡትን ማስረጃዎች መዝኖ የዐቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃ ተስተባብሏል በሚል አመልካችን ከቀረበባቸው ክስ በነፃ አሰናብቷል። ይህንኑ ውሳኔ በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በመከላከያ ማስረጃው ያስመሰከረውን ፍሬ ነገር አስምልክቶ በዋናው ክርክር ወቅት በመስቀልኛ ጥያቄ ያስተባበለው ነገር የለም፤ ከተበዳይ ጋር ተደርጓል የተባለውን የእርቅ ስምምነት አስምልክቶም በጽሑፍ የቀረበ የእርቅ ስምምነት የለም፤ የድርጊቱ አፈፃፀምም አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር የነበረው ጋብቻ ከተቋረጠ በጓላ ጉልበቱን በመጠቀም ለማስቀጠል ፍላጎት ያለው መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ድርጊቱ ከውንብድና ወንጀል ይልቅ በማስገደድ መጠቀም ወንጀልን የሚያቋቁም ነው በማለት ክስ የቀረበበትን አንቀፅ ወደ አንቀፅ 713 በመቀየር አመልካችን ጥፋተኛ ብሎት በ1 ዓመት ከ2 ወር ቀላል እስራት እና በብር 2,000(ሁለት ሺህ) የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጣ ወስኗል። አመልካች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም።

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው። አመልካች ነሓሴ 14/2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራሩ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም አመልካች የዐቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃን አላስተባበለም በሚል በወንጀል ህግ አንቀፅ 713 ስር ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት በወንጀል ጉዳት ተከሳሽ የሆነ ሰው በመከላከያ ማስረጃው ማስረዳት ከሚጠበቅበት የማስረዳት ደረጃ አኳያ መርምሯል።

በወንጀል ጉዳይ ዐቃቤ ህግ ያቀረበውን ክስ አስረድቷል የሚባለው ባቀረባቸው ማስረጃዎች ክሱን በቂ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ ሲያስረዳ እንደሆነ የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 141 ይደነግጋል። በወንጀል ክሱ ተከሳሽ የሆነው ሰውም የቀረበበትን ክስ አስምልክቶ ማስተባበያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚታዘዘው ይኸው ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 141 እና 142 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ሊነሳ እና መልስ ሊሰጠው የሚገባው ነጥብ "በወንጀል የተከሰሰ ሰው በመከላከያ ማስረጃው ማስረዳት/ማረጋገጥ/ የሚጠበቅበት የማስረዳት ደረጃ ምን ያክል ነው?" የሚለው ነው። በሌላ አገላለፅ በወንጀል ተከስሶ ክሱን እንድከላከል ከተነገረው ተከሳሽ የሚጠበቀው ዐቃቤ ህግ ባስረዳው ልክ በመከላከያ ማስረጃው በቂ እና አሳማኝ በሆነ መልሉ መረጋገጥ ነው ወይስ የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ላይ ጥርጣሬ እንዲፈጠር ማድረግ ነው እንደማለት ነው።

እንግዲህ ከላይ እንደተመለከተው በወንጀል የተከሰሰ ሰው መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚታዘዘው በዐቃቤ ህግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን ክስ እና ማስረጃን እንዲያስተባብል ነው፡፡ ማስተባበል ማለት ደግሞ የተከሳሹን የወንጀል ድርጊት እና ጥፋተኝነት አረጋግጠዋል በተባሉት ማስረጃዎች ላይ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ጥርጣሬ እንዲፈጠር በማድረግ በማስረጃዎቹ የማስረዳት አቅም ላይ መተማመን እንዳይኖር ማድረግ ስለመሆኑ ከማስረጃ ህግ መሰረተ ሀሳብ እና በዚሁ ዙሪያ ከተደረጉ የምርምር ፅሁፎች የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከተከሰሰው ሰው የሚጠበቀው በመከላከያ ማስረጃው በቂ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ ማስረዳት ሳይሆን የዐቃቤ ህግ ማስረጃን አስመልክቶ ቀድሞ በተያዘው አቋም ላይ ጥርጣሬን መፍጠር ብቻ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ዐቃቤ ህግ ክሱን ለማረጋገጥ ያቀረበው የሰው ምስክር ብቻ ነው፡፡ ቀርበው የተሰሙት የዐቃቤ ህግ ምስክሮችም እንደ ክሱ አቀራረብ አመልካች በግል ተበዳይ ላይ የውንብድና ወንጀል ሲፈጽም መመልከታቸውን ተናገረዋል፡፡ ሆኖም አመልካች ከተከሰሰበት የወንጅል ድርጊት ጋር በተያያዘ በአመልክች እን የግል ተበዳይ መካከል ሽምግልና ተቀምጠው የነበሩት የአመልካች መከላከያ ምስክሮች እና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማጣሪያ ምስክርነት የተሰሙት ሽማግሌዎቹ ሰብሳቢ የግል ተበዳይዋ በሽምግልናው ላይ አመልካችን በወንጀል የከሰሷቸው ዘወትር ሰክሮ በመሄድ ስለሚረብሻቸው እንጂ የፈፀመባቸው የወንብድና ድርጊት እንደሌለ የነገሯቸው ስለመሆኑ ተናግረዋል፡፡ በእንዚህ አሸማጋይ ሽማግሌዎች ይህ ሁኔታ መረጋገጡ ቀድሞ በተሰሙት የዐቃቤ ህግ ምስክሮች የምስክርነት ቃል ላይ ጥርጣሬ እንዲኖር የሚያደርግ ነው፡፡

ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአመልካች እና የግል ተበዳይ መካከል ተደርጓል የተባለው የእርቅ ስምምነት በፅሁፍ አልቀረበም፣ እንዲሁም አመልካች በመከላከያ ማስረጃው ያረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመስቀልኛ ጥያቄ አልጠየቀም በሚል ምክንያት የአመልካችን መከላከያ ማስረጃ ውድቅ ማድረጉ የቀረበው ጉዳዩ የወንጀል ክርክር መሆኑን እና በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ የሚጠበቅበትን የማስረዳት ደረጃ ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1. የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/34748 ላይ ግንቦት 04/2013 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔን በማፅናት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/36060 ላይ ነሐሴ 04/2013 የሰጠው ትዕዛዝ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁር 195(2(ለ(2))) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/46898 ላይ ታህሳስ 19/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካችን ከተከሰሰበት ወንጀል ነፃ በመልቀቅ የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ለ(2))) ፀንቷል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. አመልካች በዚህ መዝገብ ላይ ከተከሰሰበት ወንጀል በነፃ የተሰናበተ በመሆኑ በሌላ ወንጀል የማይፈለግ መሆኑን አረጋግጦ በአስቸኳይ ከእስር እንዲለቀው ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡

2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ